የነርስ ልዑክ

ለነርስ ረዳቶች እና ለቤት ውስጥ እንክብካቤ ሰጪዎች

የስልጠና ትምህርት

ዋሽንግተን ውስጥ ለሚገኙ የነርስ ረዳቶች እና የቤት ውስጥ እንክብካቤ ሰጪዎች

ጁላይ 2019

Washington State Department of Social & Health Services

Transforming lives

DSHS 22-1736 AM (Rev. 7/19) Amharic

ይህ መጽሀፍ እና የቪድዮ ፕሮጀክት የዋሽንግተን የማህበራዊ እና ጤና አገልግሎቶች መምሪያ (DSHS) የአረጋውያን እና የረዥም ጊዜ አገልገሎት አስተዳደር እና የእድገት ውስንነት አስተዳደር የጋራ ጥረት ነው፡፡

የሚከተሉትን ሰዎች እና ኤጀንሲዎች ላደረጉልን እርዳታ ማመስገን እንወዳለን፡

Jo Lynn Abernathy, Madeline Alexander, Elaine Blum R.N.D., Bonnie Brian- Caldwell, Nancy Carter M.D., Colleen Erskine, Karen Fogarty R.N., Terry Gammage R.N., Saif Hakim, Joe Honda, Agnes Hubble R.N., Jacquie Luck, Paula Meyer R.N., Leann Riley, Catherine Rucker, Alice Santolla R.N.

የዋሽንግተን ግዛት የአዋቂ ቤተሰብ ቤቶች

Medicine Shoppe መድሀኒት ቤት

Rochester መጦሪያ ቤት

የእድገት ውስንነት መምሪያ፣ DSHS

NOR ALFA

West Woods እገዛ የሚደረግለት መኖሪያ

South Puget Sound የማህበረሰብ ኮሌጅ

ዋሽንግተን የአረጋውያ ቤቶች እና አገልግሎቶች ማህበር

የዋሽንግተን ግዛት የጤና መምሪያ

የዋሽንግተን ግዛት የነርስ እንክብካቤ ጥራት ማረጋገጫ ኮሚሽን

የዋሽንግተን ግዛት የመድሀኒት ቤት ቦርድ

የዋሽንግተን ግዛት የነዋሪዎች እንክብካቤ ኮሚቴ

ለዚህ መጽሀፍ እና ቪድዮ ፕሮጀክት ስራ አስተዋጽኦ ያደረጉ በርካታ ሌሎች ገምጋሚዎች፡፡

የርዕስ ማውጫ

ስለመጀመር

መግቢያ 1

መግቢያ እና የትምህርት ግቦች 1

የማጠናቀቂያ መስፈርቶች 2

የትምህርት ማውጫ & ቅድመ-እይታ 3

የትምህርት ሂደት 4

የትምህርት ምልክቶች ወይም ምስሎች፡፡ 5

የስኬት ምክሮች 6

ትምህርት 1

የነርስ ተልዕኮህግ & በተልዕኮ ያለዎት ሚና 7

አጠቃላይ መግለጫ እና የትምህርት አላማዎች 7

የነርስ ልኡክ ምንድን ነው 8

በነርስ ልዑክ ውስጥ አምስት ሁኔታዎች 8

ሚና እና ሀላፊነቶች: ባለጉዳዩ 15

ሚና እና ሀላፊነቶች: RN አስተላላፊው 15

ሚና እና ሀላፊነቶች: የነርስ ረዳት / የቤት ውስጥ እንክብካቤ ሰጪ 17

ሚና እና ሀላፊነቶች: የጉዳዩ ሀላፊ 18

ሚና እና ሀላፊነቶች: የኤጀንሲ ተቆጣጣሪ 19

ሚና እና ሀላፊነቶች: ቀጣሪው/አስተዳደር 19

የነርስ ተልዕኮ ተግባቦች ዝርዝር 20

የትምህርት ማጠቃለያ 21

የተግባር ልምምድ 24

የተግባር ልምምድ መልስ ቁልፍ 26

ትምህርት 2

የባለጉዳይ እንክብካቤ እና ሰውነት ስርአት 29

አጠቃላይ መግለጫ እና የትምህርት አላማዎች 29

የባለጉዳይ ግለታሪክ 30

ዋና ዋና ሰውነት ስርአቶች 32

የልብ ስርአት 33

የአተነፋፈስ ስርአት 35

የላይኛው ቆዳ ስርአት 36

የቆዳ እንክብካቤ 37

ከክብደት የሚመጡ አደጋዎች 39

የቆዳ መሰነጣጠቅ 40

የብልት-ሽንት መሸኛ ስርአት 41

የጨጓራ አንጀት ስርአት 43

ዝግ እጢ ስርአት 45

የስኳር በሽታ ተጨማሪ መረጃ 46

የነርቭ ስርአት 48

የጅማትአጥንት ስርአት 50

የስሜት ህዋሳት ስርአት 52

የትምህርት ቅድመ-እይታ 53

የተግባር ልምምድ 56

የተግባር ልምምድ የመልስ ቁልፍ 58

ትምህርት 3

መድሀኒት አሰጣጥ 63
አጠቃላይ መግለጫ እና የትምህርት አላማዎች 63
የመድሀኒት መሰረታዊ ነገሮች 64
የመድሀኒት አሰጣጥ መንገዶች 68
የመድሀኒት ማሸጊያ እና ስም መስጠት 70
የመድሀኒት እገዛ & የመድሀኒት አሰጣጥ 71
የመድሀኒት አሰጣጥ አምስት ትክክለኛ ሁኔታዎች 72
የመድሀኒት አሰጣጥ ሂደት 73
የተለዩ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ ምን እንደሚደረግ 76
የመድሀኒት አቀማመጥ እና አወጋገድ 77
የትምህርት ማጠቃለያ 78
የተግባር ልምምድ 82
የተግባር ልምምድ ቁልፍ 84

ትምህርት 4

ህክምናዎች 87
አጠቃላይ መግለጫ እና የትምህርት አላማዎች 87
የጆሮ ጠብታ 88
የአይን ጠብታ ወይም ቅባት 89
የአፍንጫ ጠብታ ወይም የሚረጭ 91
በአፍ ወደ ውስጥ የሚተነፈስ ህክምና 92
በፊንጢጣ የሚወሰድ መድሀኒት ወይም ቅባት 93
በማህጸን የሚወሰድ መድሀኒት ወይም ቅባት 94
ከጀርም ነጻ ያልሆነ የቁስል ማሸጊያ መለወጥ 96
የግሉኮሜትር መመርመሪያ 98
የጋስትሮስቶሚ አመጋገብ 99
የኦስቶሚ እንክብካቤ 102
ቀጥያለ ንጹህ በትቦ ሽንት መሽናት 104

የተግባር ፈተና

የተግባር የትምህርት ፈተና መግለጫ 106
የተግባር የትምህርት ፈተና 107
የተግባር የትምህርት ፈተና የመልስ ቁልፍ 112

የቃላት መፍቻ 119

የስራ አጋዥ 127

የነርስ ተልዕኮ መግባቢያ
የህክምና ምህጻረ-ቃላት ዝርዝር
የጆሮ ጠብታ መስጠት
የአይን ጠብታ ወይም ቅባት መስጠት
የአፍንጫ ጠብታ ወይም የሚረጭ መስጠት
በአፍ ወደውስጥ የሚተነፈስ ህክምና
በፊንጢጣ የሚወሰድ መድሀኒት ወይም ቅባት መስጠት
በማህጸን የሚወሰድ መድሀኒት ወይም ቅባት መስጠት
ከጀርም ነጻ ያልሆነ የቁስል ማሸጊያ መለወጥ
የግሉኮሜትር መመርመሪያ
የጋስትሮስቶሚ አመጋገብ
የኦስቶሚ እንክብካቤ
ቀጥያለ ንጹህ በትቦ ሽንት መሽናት

መግቢያ

መግቢያ
እና ትምህርት
ግቦች

ወደ ***ለነርስ ረዳት ሁ የቤት ውስጥ እንክብካቤ እርዳታ የነርስ ተልእኮ*** እንኳን በደህና መጡ። ትምህርቱ የተቀረጸው እርስዎ የነርስ ተልዕኮ ስራዎችን እንዲሰሩ ለማዘጋጀት ለመርዳት ነው።

ስልጠናው በሁለት ደረጃ ይደረጋል። የሚከተለውን ያደርጋሉ፡

- የተልእኮውን መሰረታዊ ነገሮች፣ የመድሀኒት አሰጣጥ እና አንዳድ የተለዩ የጤና እንክብካቤ አሰራሮችን ለመስራት በዚህ ትምህርት መማር።
- ለግለሰብ ባለጉዳይ እንዴት እንክብካቤ እንደሚደረግ አስመልክቶ በቦታው የሚደረግ ባለጉዳይ-ተኮር የሆነ ስልጠና ሀላፊነቱን ከሚያስተላለፉት የተመዘገቡ ነርስ (RN) ማግኘት።

የስልጠና ግቦች

ይህ ትምህርት የሚከተሉትን ያስተምራል፡

- ለነርስ ተልዕኮ እንዲሟላ ህግ የሚያስገድደው።
- ስራ በማስተላለፍ ሂደቱ ውስጥ እንደ የነርስ ረዳት እና የቤት ውስጥ እክብካቤ ረዳት የሚጫወቱት ሚና።
- ስራ ከምታስተላልፈው RN ጋር ሽሪክ በመሆን የባለጉዳይ እንክብካቤን በተመለከተ እርስዎ የሚጫወቱት ሚና አስፈላጊነት።
- የመድሀኒት አሰጣጥ መሰረታዊ ነገሮች።
- የተለዩ አሰራሮችን ወይም ህክምናዎችን ለመስራት የሚያስፈልግዎት የህክምና እውቀት።
- ብቃት ያለው የባለጉዳይ እንክብካቤ ለመስጠት የሚያስፈልግዎት ባህሪይ።

ሀላፊነት ከሚያስተላልፉት RN የማቀላጠፊያ ስልጠና

ለእያንዳንዱ ግለሰብ ባለጉዳይ ለተልዕኮው የተለየ መመሪያ ሀላፊነት ከሚያስተላልፉት RN ያገኛሉ። ሀላፊነት የሚያስተላልፉት RN ስለእያንዳንዱ ባለጉዳይ ጠቃሚ መረጃ፣ የሚሰሩ የተለዩ ስራዎች እና እያንዳንዱን ስራ በትክክለኛ እንዴት እንደሚሰራ ያስተምራሉ።

ሀላፊነት ከሚያስተላልፉት RN የሚያገኙት ስልጠና በዚህ ሂደት በጣም ጠቃሚው ክፍል ነው። ሀላፊነት ከሚያስተላልፉት RN የተልዕኮ ስራ ባገኙ ቁጥር ይህ መመሪያ ይመጣል። እንዲሁም ሀላፊነት የሚያስተላልፉት RN የተልዕኮውን ስራ የመስራት ብቃትዎን ይገመግማሉ።

ይህን ትምህርት
የሚማረው ማን ነው?

ይህ ***ለነርስ ረዳት ሁ የቤት ውስጥ እንክብካቤ ረዳት የነርስ ተልዕኮ፡ የስልጠና ትምህርት*** ለሚከተሉት የዋሽንግተን ግዛት እንክብካቤ ሰጪዎች ነው፡

- ገጽ 14 ላይ በተገለጸው መሰረት ማህበረሰብ-ተኮር የረዥም ጊዜ እንክብካቤ መስጫ ቦታ ውስጥ የሚሰራ ወይም ወደፊት የሚሰራ።
- በአሁን ሰአት የተረጋገጠ የቤት ውስጥ እርዳታ (HCAs) ወይም የነርስ ረዳት ማረጋገጫ ያለው (NA-Cs) ወይም የነርስ ረዳት የተመዘገበ (NA-Rs) ወይም ከእነዚህ ማረጋገጫዎች አንዱን የሚተላለፍ ስራን ከመቀበል በፊት የሚያገኝ።
- ሀላፊነት በሚያስተላልፉት RN የሚሰጡ ስራዎችን የሚቀበል እና የሚሰራ።

ለእርስዎ የሚሰጡ መጽሀፍት/እቃዎች

ስልጠናውን ከመጀመርዎት በፊት እባክዎ የሚከተሉት ነገሮች እንዳለዎት ያረጋግጡ። ለትምህርቱ ሲመዘገቡ የስልጠና ቪድዮዎች መገናኛ ያለበት መጽሀፍ ይሰጥዎታል።

የተማሪ መጽሀፍ

የተማሪውን መጽሀፍ ይወስዱታል። የሚከተሉትን ይይዛል፡

- የስልጠና ትምህርቶች ከ 1 እስከ 4
- የተግባር ፈተናዎች (ትምህርት 5)
- የቃላት ፍቺ
- የስራ አጋዥ እና ዝርዝር

የስልጠና ቪድዮዎች

የስልጠና ቪድዮዎች ከመጽሀፉ ጋር አብረው ናቸው። ሲታዘዙ፤ እነዚህን የትምህርት ቪድዮዎች ለማየት መገናኛውን ይከተላሉ።

እርስዎ ማቅረብ ያለብዎት መጽሀፍት እና የግብአት/መረጃ ምንጮች

በተጨማሪ የሚከተሉት ያስፈልግዎታል፡

- ሳይረበሹ የሚሰሩበት ጸጥታ ያለው ቦታ
- ኢንተርኔት
- እስራስ ወይም እስኪርብቶ እና ማድመቂያ
- ባዶ ወረቀት (ማስታወሻ ለመያዝ እና ጥዬቄዎች ለመጻፍ)

ይህን የስልጠና ትምህርት በስኬታማነት ማጠናቀቅ

ይህን ትምህርት ማጠናቀቅ መማሪያ ክፍል ውስጥ ከአስተማሪ ጋር ከመሆን ይለያል። ይህ ክፍል ትምህርቱን በስኬታማ ለማጠናቀቅ እንዲዘጋጁ ይረዳዎታል። ትምህርቱን ከመጀመርዎት በፊት እባክዎን ይህን ክፍል በሙሉ ያንቡት።

ይህን ትምህርት በስኬታማነት ለመጨረስ፤ ይህን ትምህርተ ከጨረሱ በኋላ የሚከተሉትን ማድረግ አለብዎት፡

- ፈተናውን 80% ወይም ከዛ በላይ በማግኘት ማለፍ።
- የተማሪ ግምገማዎትን ለስልጠና አስተባባሪው መስጠት።
- መጽሀፉ ላይ ያለው የተግባር ልምምድ ተሰርቶ ለግምገማ ለስልጠና አስተባባሪው ማቅረብ።

ትምህርቶቹ የተቀረጹት እርስዎ ፈተናውን እንዲያልፉ ሙሉ-በሙሉ እንዲያዘጋጅዎት ተደርጎ ነው። እያንዳንዱን ትምህርተ ከሰሩ፣ የተግባር ጥያቄዎቹን ከመለሱ እና በትምህርት 5 ላይ የሚገኘውን የተግባር ፈተና ከሰሩ ለትምህርቱ ፈተና ዝግጁ ይሆናሉ።

የትምህርት አደረጃጀት

የትምህርት ማውጫ

ይህ የስልጠና ትምህርተ በአምስት ክፍሎች ተከፍሏል፡

ትምህርተ 1 - የነርስ ተልዕኮ ህግ እና በተልዕኮው እርስዎ ያለዎት ሚና

ትምህርት 2 - ባለጉዳይ እንክበካቤ እና የሰውነት ስርአት

ትምህርት 3 - መድሀኒት አሰጣጥ

ትምህርት 4 - ህክመናዎች

ትምህርት 5 - የትምህርት ማጠቃላያ እና የተግባር ፈተና

የነርስ ተልዕኮ ህግ እና በተልዕኮው እርስዎ ያለዎት ሚና

ትምህርት 1
ቅድሙ-እይታ

ይህ ትምህርት የነርስ ተልዕኮን ሁሉንም መሰረታዊ ነገሮች ይዘረዝራል እንዲሁም ዋና ዋናውን የ"ማን፣ ምን፣ የት፣ መቼ፣ ለምን እና እንዴት" ጥያቄዎች ይመልሳል። የሚከተሉትን ይማራሉ፡

- የነርስ ተልዕኮ ምነድን ነው እና የሚሳተፈው ማን ነው?
- የነርስ ተልዕኮ ሚያገለግለው ለምንድን ነው?
- ተልዕኮ የሚከናወነው የት ነው?
- ስራ የሚሰጠኝ ማን ነው እና ማይሰጠኝስ ማን ነው?
- የተሰጠን ስራ የምቀበለው መቼ ነው?
- ለእኔ ሚሰጡኝ ስራዎች ምን አይነት ናቸው?
- ነእኔ የማይሰጠኝ ስራ ምንድን ነው?
- የእኔ ሚና እና ሀላፊነት ምንድን ነው?
- የተልዕኮ ሂደቱ ሚከናወነው እንዴት ነው?

የባለጉዳይ እንክብካቤ እና የሰውነት ስርአት

ትምህርት 2
ቅድሙ-እይታ

በዚህ ትምህርት ከባለጉዳይዎት ጋር የሚኖርዎትን ግነኙነት እናያለን። ሊያጋጥምዎት ስለሚችል አንዳንድ ሁኔታዎች ለመዘጋጀት እንዲረዳዎት ስለባለጉዳይ የኋላ ታሪክ እንወያያለን።

በሰውነት ውስጥ ስላለው ዋና ዋና የሰውነት ስርአቶች፣ እርጅና ስለሚያመጣው ጫና እና አንዳድ የተለመዱ በሽታዎች ይማራሉ። ይህ መረጃ በትምህርት 3 ላይ ስለመድሀኒት አሰጣጥ እና በትምህርት 4 ላይ ስለህክመና ስንወያይ መሰረት የምናደርገው መረጃ ይሆናል።

ይህ የኋላ ታሪክ እውቀት የተልዕኮ ስራን በራስ መተማመን ለመስራት እና ለባለጉዳይዎት ከፍተኛ ደረጃ ያለው አጠቃላይ እንክብካቤ እንዲሰጡ ይረዳል።

የመድሀኒት አሰጣጥ

ትምህርት 3
ቅድሙ-እይታ

ለባለጉዳይ መድሀኒት ሲሰጡ በጣም አስፈላጊ ሚና ይጫወታሉ። የጎንዮሽ ችግሮችን የሚያዩ እና ችግሮቹም ከተፈጠሩ በፍጥነት እርምጃ ሚወስዱ ቁልፍ ሰው እርስዎ ነዎት። እንዲሁም ባለጉዳይዎት መድሀኒት አልወስድም ካለ ወይም ስህተት ካገኙ ምነ ማድረግ እንዳለበዎት ማወቅ አለብዎት።

ትምህርት 4
ቅድመ-እይታ

ህክምናዎች

በዚህ ትምህርት ለእርስዎ ሚሰጥዎት የተለመዱ ህክመና ለምሳሌ ከጀርም ነጻ ያልሆነ ቁስል መሸፈኛ መለወጥ፣ የግሉኮሜትር ምርመራ እና የጋስትሮስቶሚ አመጋገብ ለመስራት የሚመከሩ መንገዶችን ይማራሉ፡፡

ከተለያዩ በሽታዎች ሊመጣ የሚችል ውስብስብነትን በመለየት እና የባለጉዳይዎትን ሁኔታ ሀላፊነት ለሚያስተላልፉት RN በማሳወቅ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ፡፡

ትምህርት 5
ቅድመ-እይታ

የተግባር ፈተና

በመጨረሻው ትምህርተ ላይ፤ ትምህርቱን በሙሉ ይገመግሙ እና ለመጨረሻ የትምህርተ ፈተናዎት ይዘጋጃሉ፡፡ ስለፈተናው አይነት እና ርዕስ ለማወቅ የተግባር ፈተና ይወስዳሉ፡፡

የተግባር ፈተናውን ከጨረሱ በኋላ የመጨረሻ የትምህርተ ፈተናውን በስኬታማነት ለመጨረስ በደንብ ዝግጁ ይሆናሉ፡፡

የትምህርተ ሂደት

ለእያንዳንዱ ትምህርት የትምህርተ ቪድዮውን መገናኛ እና መጽሀፍ ይጠቀማሉ፡፡ ለእያንዳንዱ ትምህርት የሚከተሉትን ያደርጋሉ፡

ያንቡ በመጽሀፉ ውስጥ ያለውን ትምህርት፡፡ መጽሀፉ የሚከተሉትን ያደርጋል:

- የትምህርቱን ግብ ይገልጻል፡፡
- ርዕሱን ይገልጻል፣ ጽንሰ-ሀሳቡን ያብራራል እና ምሳሌ ይሰጣል፡፡
- የተማሩትን ያጠቃልላል፡፡
- አንዳንድ በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎችን ይመልሳል፡፡

ይገምግሙ በመጨረሻ ፈተናው ላይ ሊመጡ የሚችሉ የፈተና ጥያቄዎች እና ምሳሌዎችን፡፡

ይመልከቱ ቪድዮ ውስጥ ያለውን ትምህርት፡፡ ቪድዮው ሚከተሉትን ያደርጋል:

- በመጽሀፉ የተማሩትን ይገመግማል፡፡
- አሰራሮችን ያሳያል፡፡
- የተማሩትን ስራ ላይ ሲተገብሩ የሚያጋጥሙ ጉዳዮች ላይ ውይይት ያደርጋል እንዲሁም ምን መጠንቀቅ እዳለብዎት ያሳያል፡፡
- ስራ ላይ የሚፈጠሩ ሁኔታዎችን ያሳያል እንዲሁም መደረግ ያለበትን የተሻለ መንገድ ያወያያል፡፡

ይገመግማል መጽሀፉ ውስጥ ያለውን ትምህርት፡፡

- ቪድዮውን ካዩ በኋላ ጥያቄ ካለዎት መጽሀፉ ውስጥ ያለውን የሚመለከተው ክፍል ጋር በመመለስ መገምገም ይችላሉ፡፡ እንዲሁም ለጥያቄዎቹ ማስታወሻ በመያዝ አስተማሪውን መጠየቅ ይችላሉ፡፡

ተራኪዎች

የቪድዮው ክፍሎች የዚህ ስልጠና በጣም አስፈላጊ አካል ናቸው፡፡ የነርስ ረዳት እና ሀላፊነት የሚያስተላልፉት RN ስራ ላይ ስለሚያጋጥምዎት የተለመዱ ጉዳዮች አብረው ሲያወሩ ያያሉ፡፡ እነዚህ ንግግሮች የእርስዎን ሀላፊነት ከሚያስተላልፉት RN መጠየቅ የሚፈልጓቸውን ጥቄዎች እንዲያስቡ ያግዝዎታል፡፡

የትምህርት ምልክቶች ወይም ምስሎች

ስልጠናውን በቀላሉ እንዲወስዱ እንዲያግዝዎት መጽሀፉ ምልክቶች ወይም ምስሎች ይጠቀማል። መጽሀፉ የተጠቀማቸው የምልክቶቹ ዝርዝር።

ምልክት/ምስል	ትርጉም
	ቁም እዚህ ጋር መጽሀፉን ማንበብ ወይም ቪድዮውን ማየት አቁሙ።
	መጽሀፍ የመጽሀፉን ቀጣዩን ክፍል ያንቡ።
	ቪድዮ የቪድዮውን ቀጣይ ክፍል ይመልከቱ።
	በህግ የሚጠየቅ ይህ ጽሁፍ የተወሰደው የነርስ ልዑክን ከሚመለከት ደንብ ወይም ህግ በቀጥታ ነው።
	አሰራር የተወሰነ ስራን ለማጠናቀቅ የሚከተሉት ደረጃውን የጠበቀ ሂደት። ስራ ላይ እንዲያግዝዎት በርካታ አሰራሮች የስራ ዝርዝሮች ላይ ይካተታሉ።
	ለስኬት ምክር ሂደትን ለማቅለል ወይም ለባለጉዳይ የተሻለ እንክብካቤ ለመስጠት የሚሰጥ ምክር።
	እርዳታ መጠየቅ ሀላፊነት ከሚያስተላልፉት RN ጋር መወያየት ያለብዎት ርእስ ወይም ጉዳይ ነው።
	ቁልፍ ቃል ማስታወስ ያለብዎት አዲስ ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ ሲገባ ይተረጎምልዎታል። ቁልፍ ቃላት በማውጫው ላይም ይገኛል።
	ሪፖርት ሀላፊነት ለሚያስተላልፉት RN፣ ተቆጣጠሪዎት፣ የጉዳይ ሀላፊዎት ወይም የባለጉዳዩ ሀኪም የሆነ ነገር ማሳወቅ ሲኖርብዎት።

የስኬት ምክር

- መጀመሪያ መጽሀፉን ያንቡ እና ያንኑ ክፍል ቪድዮውን ይመልቱ። ቪድዮውን ካዩ በኋላ አሁንም ጥያቄ ካለዎት ወደ መጽሀፉ ይመለሱ እና እስኪገባዎት ድረስ ያንን ክፍል ይገምግሙ።
- ያልገባዎት ቃል ካገጠምዎት በመጽሀፉ ጀርባ **ማውጫውን** ይመልከቱ።
- በደንብ ለመረዳት ቪድዮውን አቁመው መገምገም ይችላሉ።
- አነስተኛ መረበሽ በሚኖርበት ጊዜ እያንዳንዱን ትምህርት ለማጠናቀቅ ጊዜ ይመድቡ።
- እያንዳንዱን ትምህርት ሲማሩ መጽሀፉ ላይ ማስታወሻ ይወሰዱ እና ቁልፍ ጽንሰ-ሀሳቦችን ያድምቁ። መረጃውን የበለጠ እንዲያስታውሱት ይረዳወታል።
- ከእየንዳዱ ትምህርት በኋላ ያለዎትን ጥያቀ ይጻፉ።
- ጥያቄዎት በመጽሀፉ ወይም ቪድዮ ላይ ካልተመለሰ የስልጠና አስተባበሪውን ይጠይቁ።

እዚህ ጋር መጽሀፉን ማንበብ ያቁሙ ።

የቪድዮውን ክፍል ይመልከቱ ለመጀመር።
ለ DSHS ድህረ-ገጽ ይህን መገናኛ ይከተሉ። በትምህርት መደዳ ስር የነርስ ተልዕኮ ወደሚለው ያውርዱ። በመረጡት ቋንቋ ላይ ይጫኑ። ማየት የሚፈልጉትን ቪድዮ ይምረጡ።
www.dshs.wa.gov/altsa/training/dshs-curriculum-available**።**

የነርስ ተልዕኮ ህግ እና እርስዎ በተልዕኮ ያለዎት ሚና

አጭር መግለጫ እና ቅድመ-እይታ

ይህ ትምህርት ዋና ዋና የሆኑትን ማን፣ ምን፣ የት፣ መቼ፣ ለምን እና እንዴት ጥያቄዎችን በመመለስ የነርስ ተልዕኮ ሁሉንም መሰረታዊ ነገሮች ይዘረዝራል። የሚከተሉትን ይማራሉ፡

- የነርስ ተልዕኮ **ምንድን** ነው እና ሚሳተፈው ማን ነው?
- ተልዕኮ የሚከናወነው **የት** ነው?
- ስራ የሚሰጠኝ **ማን** ነው እና ስራ ለእኔ መስጠት የማይችለው ማን ነው?
- የተሰጠ ስራ የምቀበለው **መቼ** ነው?
- ማረጋገጫ ላላቸው የቤት ውስጥ እንክብካቤ ረዳቶች፣ የነርስ ረዳት ማረጋገጫ ያለው እና በነርስ ረዳትነት በመመዝገብ የሚሰጡ ስራዎች **ምን** አይነት ናቸው?
- ለእኔ የማይሰጠኝ ስራ **ምንድን** ነው?
- ሚናዬ እና ሀላፊነቴ **ምንድን** ነው?
- የነርስ ልዑክ የሚጠቅመው **ለምንድን** ነው?
- የተልዕኮው ሂደት የሚከናወነው **እንዴት** ነው?

የትምህርት አላማዎች

ይህን ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ፡

- የነርስ ልዑክን ማብራራት።
- በህጉ መሰረት የነርስ ተልዕኮ ስራን መቀበል እና መስራት የሚችሉበትን ቦታዎች መዘርዘር።
- በህጉ መሰረት ለእርስዎ ማይሰጥዎትን ስራ መዘርዘር።
- የተልዕኮ ስራ ለመቀበል ብቁ ለመሆን ማድረግ ያለብዎትን መግለጽ።
- በነርስ ተልዕኮ ውስጥ ተሳታፊ ማን እንደሆነ እና በሂደቱ ውስጥ እያንዳንዱ ሰው ሚና ምን እንደሆነ መግለጽ።
- በተልዕኮ ውስጥ እርስዎ ያለዎትን መብት እና ሀላፊነት መግለጽ።
- በሚሰሩበት ቦታ የሚጠቀሙትን የመግባቢያውን ሂደት ማወቅ።

ተልዕኮ ማለት ለሰው ሀላፊነት ወይም ስራ ማስተላለፍ ማለት ነው።

ተልዕኮን ማብራራት:
ለነርስ ተልዕኮ አምስት ሁኔታዎች

የነርስ ተልዕኮ ምንድን ነው?

የነርስ ተልዕኮ ማለት ፈቃድ ያለው **የተመዘገ ነርስ** (RN) ለ ባለጉዳይ መሰራት ያለበትን የተወሰነ ስራ **በ** ማህበረሰብ ውስጥ እና/ወይም ቤት **ውስጥ ለሚሰራ ብቁ ለሆነ የነርስ ረዳት ወይም** የቤት ውስጥ እንክብካቤ **ረዳት ማስተላለፍ ነው**::.

ስራውን ሚሰጠው ፈቃድ ያለው RN ለባለጉዳዩ የነርስ እንክበካቤ ሀላፊነት ይወስዳል እነዲሁም ተጠያቂ ይሆናል::

የተሰጠ ስራ መቀበል ማለት:

- በ RN ምትክ ለባለጉዳዩ እንክብካቤ ለመስጠት የተወሰነ ስራ ለመስራት ፈቃደኛ ይሆናሉ::
- ሀላፊነት ከሚሰጠው RN ምን ማድረግ እንዳለብዎት እና መቼ እንደሚያደርጉት ግልጽ እና የተወሰነ መመሪያ ተሰጥቶዎታል::
- ስራውን በትክክል እና ደህነቱን ጠብቀው እንደሚሰሩ ይመኑ::

የተሻሻለው ዋሽንግተን ህግ (RCW) 18.88A.210፣ RCW 18.88A.230 እና RCW 18.79.260 (the law)::

የዋሽንግተን የአስተዳደር ህግ ከ(WAC) 246-840-910 እስከ 246-840-970፣ WAC 246-841-405 (the rules)::

አምስቱ ሁኔታዎች

ለነርስ ተልዕኮ አምስት ሁኔታዎች አሉ:

1. ፈቃድ ያለው **የተመዘገበ ነርስ** ስራው እንዲሰራ ያስተላልፋል::
2. ስራው መተላለፍ ይችላል:: መተላለፍ **የማይችሉ** አራት **ስራዎች** አሉ::
3. ስራ የሚተላለፈው **ለአንድ ባለጉዳይ የተወሰነ ስራ ለመስራት ነው**::
4. **ብቁ የነርስ ረዳት ምስክር ወረቀት ያለው፣ የነርስ ረዳት-የተመዘገበ እና ምስክር ወረቀት ያለው የቤት ውስጥ እንክብካቤ ረዳት** ብቻ ስራ መቀበል ይችላሉ::
5. ስራ የሚተላለፈው በአራት የማህበረሰብ ሁኔታ ውስጥ ነው::

ሀላፊነት ማስተላለፉ በህጉ መሰረት እንዲሆን እያንዳንዱ የሀላፊነቱ አካላት በአግባቡ መደረግ አለበት::

የቤት ውስጥ እንክብካቤ ረዳት ማለት ምነ ማለት ነው?

ማሳሰቢያ፣ "የቤት ውስጥ እክብካቤ ረዳት" ማለት ከጤና መምሪያ የቤት ውስጥ እንክብካቤ ረዳትነት የምስክር ወረቀት ያለው የረዥም ጊዜ የእንክብካቤ ሰራተኛ ነው::[RCW 74.39A.009(14) እና RCW 18.88B.010(3).] እንክብካቤ ሰጪዎች ከጤና መምሪያ የምስክር ወረቀት ካላገኙ በስተቀርእራሳቸው "የቤት ውስጥ እክብካቤ ረዳት" ነን ላይሉ እንደሚችሉ እባክዎ ያስታውሱ:: በዚህ መመመሪያ ላይ የተጠቀሱት "የቤት ውስጥ እክብካቤ ረዳት" ትርጉም እንክብካቤ ሰጪው የምስክር ወረቀት አለው ማት ነው::

ሁኔታ 1 - ፈቃድ ያለው የተመዘገበ ነርስ(RN)

ሁኔታ 1
ሀላፊነት መስጠት
የሚችለው ማን ነው?

ለእርስዎ ስራ መስጠት የሚችለው RN ዋሽንግተን ውስጥ ፈቃድ ያገኘ እና እርስዎ ለሚሰሩለት ባለጉዳይ ሀላፊነት ያለበት RN ነው፡፡

ስለዚህ ለእርስዎ ስራ ማስተላለፍ የማይችለው ማን ነው?

- የስራ ማስኬድ አስተዳደሩ፤ ሀላፊነት የሚሰጠው RN ካልሆነ
- ተቆጣጠሪዎት ወይም መሪዎት፤ ሀላፊነት የሚሰጠው RN ካልሆነ
- ፈቃድ ያለው የተግባር ነርስ (LPN)
- የቤት ውስጥ የጤና እንክብካቤ ነርስ፤ ሀላፊነት የሚሰጠው RN ካልሆነ
- ለባለጉዳዩ መደበኛ ሀላፊነት የሌለበት ሌላ RN

ሁኔታ 2 - የተወሰነ ስራ

ሁኔታ 2
የሚሰጠው ስራ
ምንድን ነው?

የሚከተሉት ሊሰጥዎት ሚችሉ የስራ አይነቶች ምሳሌዎች ናቸው:

- **የመድሀኒት** አሰጣጥ::
- **ከጀርም ነጻ ያልሆነ የቁስል መሸፈኛ መለወጥ፡፡**
- ንጹህ ስልት በመጠቀም **የሽንት ቱቦ ማስገባት**፡፡
- በተደራጀ እና በዳነ ሁኔታ ላይ **የኦስቶሚ እንክበካቤ** ፡፡
- **የደም ስኳር ቁጥጥር፡፡**
- **በተደራጀ እና በዳነ ሁኔታ ላይ**የጋስትሮስቶሚ አመጋገብ፡፡

እያንዳንዱን ስራዎች ወደበኋላ በዝርዝር እንመለስበታለን፡፡
ለቃላት ትርጉም እባክዎ ማውጫውን ይመልከቱ፡፡

የሚከተሉት ስራዎች ለእርስዎ **አይሰጡም**:

ለእኔ ሊሰጠኝ
የማይችለው ስራ
ምንድን ነው?

- ከኢንሱሊን በስተቀር መርፌ መውጋት
- ከጀርም ነጻ የሆነ አሰራር
- ማዕከላዊ መስመሮችን መያዝ
- የነርስ ውሳኔ የሚያስፈልገው ማንኛውም ነገር

ሁኔታ 3 - የተልዕኮ ገደብ ምንድን ነው?

ሁኔታ 3 - ለአንድ ባለጉዳይ የተወሰነ ስራ

ተልዕኮ ለአንድ ባለጉዳይ የተወሰነ ስራ በመስራት የተገደበ ነው። ይህ በምሳሌ ይብራራል። እርስዎ ለ Mary Jones የጆሮ ጠብታ እንዲሰጡ RN ሃላፊነት ሰጥቷል እንበል። ይህ ስራ የሚሸፍነው ለአንድ ባለጉዳይ Mary Jones የጆር ጠብታ ለመስጠት ብቻ ነው።

የተወሰነ ስራ - በተጨማሪ Mary እግሯ ላይ ያለው ከክብደት የመጣ ህመም የተጠቀለለው መለወጥ አለበት። እርስዎ ሀላፊነት ያለብዎት የ Maryን የጆር ጠብታ ለመስጠት ቢሆኑም ሀላፊነት የሚሰጠው RN በሌላ ተልዕኮ፣ ለ Mary የተጠቀለለውን ለመቀየር የተሟላ መመሪያ ካልሰጠ በስተቀር የተጠቀለለውን መቀየር አይችሉም።

አንድ ባለጉዳይ – Arthur Rodriguez ሌላ ባለጉዳይዎት ነው። ለ Mary Jones የሚሰጧት የጆር ጠብታ አይነት ያስፈልገዋል። የ Maryን የጆር ጠብታ የመስጠት ሀላፊነት ቢኖርብዎትም የ Arthurን የጆር ጠብታ መስጠት ግን አይችሉም። የ Arthurን የጆር ጠብታ መስጠት የሚችሉት RN ስራውን ከ Arthur የእንክብካቤ ሙሉ መመሪያ ጋር ከሰጠዎት ብቻ ነው።

ሁኔታ 4 - የተሰጠ ስራ የምቀበለው መቼ ነው?

ሁኔታ 4 - ብቁ የነረስ ረዳት ወይም የቤት ውስጥ እንክብካቤ ረዳት

ሚሰጥዎትን ስራ **መቼ** መቀበል እንዳለብዎት መረዳት በጣም አስፈላጊ ነው። የሚሰጥዎትን ስራ ከመቀበልዎት በፊት ማሟላት ያለብዎት አራት መስፈርቶች አሉ። የሚከተለውን ማድረግ አለብዎት፥

1. በሚከተሉት የምስክር ወረቀት መኖር:
   i. **የቤት ውስጥ እንክበካቤ ረዳት** (HCA)፤ ወይም
   ii. **የነርስ ረዳት የምስክር ወረቀት ያለው** (NA-C)፤ወይም
   iii. በ WAC 246-980-070 ስር የቤት ውስጥ እንክበካቤ ረዳት የምስክር ወረቀት ከማቅረብ ከተተወ፣ **የተመዘገበ የነርስ ረዳት(NA-R) ሆነው መሰረታዊ የስልጠና ዋና ብቃቶችን ካሟሉ**፣ የሀያ ስምንት ሰአታት **የእንክብካቤ መሰረታዊ ነገሮች መሻሻል ካልተሟላ** በስተቀር ወይም
   iv. የነርስ ተልዕኮ የቤት ውስጥ እንክብካቤ ረዳት የምስክር ወረቀት ከመገኘቱ በፊት እንክብካቤ እቅድ መተግበር ካስፈለገ፣ **የተመዘገበ የነርስ ረዳት(NA-R) ሆነው መሰረታዊ የስልጠና ማና ብቃቶችን ካሟሉ**።

2. ለተለየ ባለጉዳይ የተለየ ስራን ለመስራት ለነርስ ረዳት እና የቤት ውስጥ እንክብካቤ ሰጪ ረዳት የነርስ ተልዕኮ ትምህርት እና ስልጠና ማጠናቀቅ።

3. የሚሰጠውን ስራ ለመስራት ፈቃደኛ መሆን።

4. ሀላፊነት ለሚሰጠው RN የተለየ ስራ ያለቀጥታ ቁጥጥር በቀጥታ በትክክል ለመስራት ያለዎትን ብቃት ማሳየት።

የምስክር ወረቀት ያለው የቤት ውስጥ እንክብካቤ ሰጪ (HCA) ለመሆን ለማመልከት በዋሽንግተን ግዛት የማህበራዊ እና ጤና አገልግሎት መምሪያ የጸደቀ የስልጠና መርሀግብር መጨረስ፣ ማረጋገጫ ለሚሰጥ የጤና መምሪያ ማመልከት እና የፕሮሜትሪክ ፈተናውን በስኬት ማለፍ አለብዎት። ማስረጃዎች በየአመቱ መታደስ አለባቸው።

ሁኔታ 4
ክፍል 1፤ ፈቃድ
HCA

ከስልጠና መርሀግብሩ የ75 ሰአት የማጠናቀቅ የምስክር ወረቀት፣ የስልጠና መርሀግብር የምስክር ወረቀት፣ ለቤት ውስጥ እንክብካቤ ሰጪ ረዳትነት (DOH 675-002 [የተሻሻለ. 7/16]) ለምስክር ወረቀት ማመልከቻ፣ የማመልከቻ ክፍያ እና የፕሮሜትሪክ ፈተና ክፍያ ኮፒ ለሚከተለው ይላኩ፡

Department of Health
Home Care Aide Credentialing
P. O. Box 1099
Olympia, WA 98507-1099

ስለማመልከቻው እና የምስክር ወረቀት ሂደቱ መረጃ ለማግኘት DOH በሚከተለው ያነጋግሩ፡

የጤና መምሪያ ድረ-ገፅ

http://www.doh.wa.gov/LicensesPermitsandCertificates/ProfessionsNewReneworUpdate/HomeCareAide

የቤት ውስጥ እንክብካቤ ሰጪ መረጃ (360) 236-2700

የምስክር ወረቀት ያለው የነርስ ረዳት (NA-C) ለመሆን ለማመልከት በዋሽንግተን ግዛት የነርስ እንክብካቤ ጥራት ማረጋገጫ ኮሚቴ የጸደቀ የስልጠና መርሀግብር መጨረስ እና የፕሮሜትሪክ ፈተናውን በስኬት ማለፍ አለብዎት። ማስረጃዎች በየአመቱ መታደስ አለባቸው።

ሁኔታ 4
ክፍል 1፤ ፈቃድ
NA-C

የስልጠና መርሀግብር የምስክር ወረቀት፣ ለነርስ ረዳት (DOH 667-029 [የተሻሻለ. 9/16]) ለምስክር ወረቀት ማመልከቻ፣ የማመልከቻ ክፍያ ለሚከተለው ይላኩ፡

Washington State Nursing Commission
P.O. Box 1099
Olympia, WA 98507-1099

ስለማመልከቻው እና የምስክር ወረቀት ሂደቱ መረጃ ለማግኘት DOH በሚከተለው ያነጋግሩ፡

የጤና መምሪያ ድረ-ገፅ

http://www.doh.wa.gov/LicensesPermitsandCertificates/ProfessionsNewReneworUpdate/NursingAssistant

DOH የተጠቃሚ አገልግሎት (360) 236-4700

ሁኔታ 4 ክፍል 1፤ ፈቃድ NA-R

ለ **ተመዘገበ የነርስ ረዳት (NA-R)** ለመመዝገብ የጤና መምሪያውን የ HIV/AIDS ስልጠና* ማጠናቀቅ አለብዎት:: የ HIV/AIDS ስልጠናውን ከወሰዱ በኋላ **ለነርስ ረዳትነት ምዝገባ ማመልከቻ** (DOH 667-025[Rev. 9/16]) ይሙሉ እና ከማመልከቻው ክፍያ እና የዋሽንግተን ግዛት የነርስ ኮሚቴ (አድራሻው ከላይ የሚገኘው) የ HIV/AIDS የምስክር ወረቀትዎ ጋር ይላኩት:: ማስረጃዎች በየአመቱ መታደስ አለባቸው::

የ HCA መሰረታዊ ስልጠና ትምህርት የማጠናቀቅ ማስረጃ ለ HIV/AIDS የምስክር ወረቀት መስፈርቱን ያሟላል::

ሁኔታ 4 ክፍል 1፤ ከግዛት ውጪ የተገኘ ፈቃድ

ስምዎት በሌላ ግዛት መዝገብ ላይ ካለ ለነርስ ረዳትነት ምስክር ወረቀት ከግዛት-ግዛት ፈቃድ ብቁ ነዎት:: የተሞላ **ለነርስ ረዳትነት ምስክር ወረቀት ከግዛት-ግዛት ፈቃድ ማመልከቻ** (DOH 667-039 [Rev. 9/16]) እና ከላይ ባው አድራሻ የሌላ ግዛት መዝገብ ላይ እንዳሉ ማረጋገጫ ይላኩ::

ሁኔታ 4 ክፍል 2፤ የትምህርት መስፈርቶች

.....ከሆኑ	.....በስኬታማነት ማተናቀቅ አለብዎት
HCA	ለነርስ ረዳት እና የቤት ውስጥ እንክበካቤ ረዳት የነርስ ተልዕኮ*
NA-C	ለነርስ ረዳት እና የቤት ውስጥ እንክበካቤ ረዳት የነርስ ተልዕኮ*
NA-R	መሰረታዊ ስልጠና (በDSHS የጸደቀ መሰረታዊ ስልጠና) **እና** ለነርስ ረዳት እና የቤት ውስጥ እንክበካቤ ረዳት የነርስ ተልዕኮ*
NA- R ድጋፍ ለሚደረግለት የመኖሪያ ኤጀንሲ የሚሰራ	የ መሰረታዊ ስልጠና (የ40 ሰአታት ስልጠና) **እና** ለነርስ ረዳት እና የቤት ውስጥ እንክበካቤ ረዳት የነርስ ተልዕኮ*
NA-R አሁን የነርስ ተልዕኮ አገልገሎት ለሚገኝ ባለጉዳይ የቀድሞ የማደጎ ወላጅ	የ PRIDE ስልጠና (የ43 ሰአታት) ለሌላ የተልዕኮ ባለጉዳይ የማይተላለፍ:: **የልጅ የማደጎ ቤት የሚሰሩ ከሆነ እንክብካቤ ሰጪው ዋና ስልጠና(CCT) እና የ3 ሰአታት ቃል-መግለጫ እና የመጀመሪያ ደረጃ እርዳታ ስልጠና ያሟሉ::** **እና** ለነርስ ረዳት እና የቤት ውስጥ እንክበካቤ ረዳት የነርስ ተልዕኮ*

*የኢንሱሊን መርፌ የመውጋት ስራ ከተሰጠዎት የነርስ ተልዕኮ ለነርስ ረዳትን በስኬት ማጠናቀቅ አለብዎት: ልዩ ትኩረት የስኳር በሽታ ስልጠና ላይ::

የ DDA የምስክር ወረቀት መርሀግብሮች ውስጥ የሚሰሩ አገልግሎት ሰጪዎች የነርስ ተልዕኮ የሚሰጠው የ DDA ዋና ስልጠናው እና አስፈላጊ የአገልግሎት-ላይ ስልጠና ከተጠናቀቀ በኋላ ብቻ ነው:: በ DDA የምስክር ወረቀት ድጋፍ የሚደረግለት የመኖሪያ አገልግሎት ውስጥ የሚሰራ ሰራተኛ የ DDA መሰረታዊ ስልጠና ይወስዳል::

ከላይ የተሰጡትን መስፈርቶች ማሟላትዎን ሀላፊነት ለሚሰጠው RN ለማሳየት መዘጋጀት አለብዎት፡፡ ሀላፊነት ለሚሰጠው RN የሚከተሉትን ለማቅረብ ዝግጁ መሆን አለብዎት፡

ሰነዶች

- የጤና መምሪያ ፈቃድ (HCA የምስክር ወረቀት፣ NA-C የምስክር ወረቀት ወይም NA-R ምዝገባ) ሰነድዎትን፡፡
- NA-R ብቻ: የ HCA መሰረታዊ ስልጠና የምስክር ወረቀትዎን ወይም የ DDA ዋና ብቃት መሰረታዊ ስልጠና የምስክር ወረቀትዎን ማቅረብ አለብዎት፡፡
- የነርስ ተልዕኮ ለነርስ ረዳት እና የቤት ውስት እንክብካቤ ሰጪ ረዳት ምስክር ወረቀትዎን፡፡ (የነርስ ተልዕኮ የስልጠና የምስክር ወረቀትዎን የሚያገኙት ፈተናውን ካለፉ በኋላ ነው)፡፡

ለመስራት ፈቃደኝነት

ሁኔታ 4 ክፍል 3፤ ለመስራት ፈቃደኝነት

የሁኔታ 4 ሶስተኛው መስፈርት የተልዕኮ ስራውን ለመስራት ፈቃደኛ መሆንዎት ነው፡፡

ስራውን መስራት የማይችሉ ከመሰልዎት ወይም የባለጉዳዩ ደህነት አደጋ ላይ የወደቀ ከመሰለዎት ስራውን እንዳይሰሩት፡፡ ሀላፊነት ለሰጠው RN፣ ለጉዳዩ ሀላፊ እና/ወይም ለቀጣሪዎት ወይም ለተቆጣጣሪዎት ስጋትዎን ይንገሩ፡፡ መስራት የማይችሉትን ስራ እንዲሰሩ ማንም አያስገድድዎትም፡፡

በህዝብ አገልግሎት መስጫ ውስጥ የሚሰሩ ከሆነ የነርስ ተልዕኮ ሂደቱን እና በቅጥርዎት ወቅት ከስራዎት ጋር የሚገናኘውን መስፈርት መፈጸምዎትን ያረጋግጡ፡፡ በአጠቃላይ የነርስ ረዳት/የቤት ውስጥ እንክብካቤ ሰጪ ረዳት ስራ ሲቀበሉ እንደስራዎት ለመስራት ፈቃደኛ መሆንዎን ገልጸዋል ማለት ነው፡፡

ለመስራት ችሎታ

ሁኔታ 4 ክፍል 4፤ ለመስራት ችሎታ

የሁኔታ 4 የመጨረሻው ክፍል **ስራውን ለመስራት ችሎታው** ሊኖርዎት ይገባል ነው፡፡ ስራ ለእርስዎ ከመሰጠቱ በፊት ስራውን ያለእርዳታ መስራት እንደሚችሉ RN ማረጋገጥ አለበት፡፡

ለእያንዳንዱ የተልዕኮ ስራ RN የተለየ፣ የጽሁፍ መመሪያ ይሰጥዎታል፡፡ በመቀጠል RN ስራውን ያስለማምድዎታል፣ ስራው እንዴት እንደሚሰራ ያሳይዎታል እንዲሁም መስራት እንደሚችሉ ያረጋግጣል፡፡

RN ስራ የሚሰጥዎት በትክክል እና ደህንነቱን ጠብቀው እንደሚሰሩ ሲያረጋግጥ ብቻ ነው፡፡

ሁኔታ 5 በማህበረሰብ ውስጥ

ሁኔታ 5 - የማህበረሰብ ሁኔታዎች

የነርስ ተልዕኮ በአራት የማህበረሰብ ሁኔታዎች ውስጥ ሊደረግ ይችላል፡፡

1. የአዕምሮ ውስንነት ላለባቸው የምስክር ወረቀት ያለው የማህበረሰብ መኖሪያ መርሀግብር፡፡
2. ፈቃድ ያለው የአዋቂ የቤተሰብ ቤት፡፡
3. ፈቃድ ያለው እገዛ የሚደረግለት የመኖሪያ ቦታ፡፡
4. በባለጉዳዩ ቤት ውስጥ፡፡

ተጨማሪ ማስታወሻዎች

የሚረዳዎት ስለነርስ ተልዕኮ ተጨማሪ ማስታወሻ፡፡

- ያስታውሱ፤ ተልዕኮ የሚተገበረው ለተለየ ስራ ለአንድ ባለጉዳይ ብቻ ነው፡፡ ለአንድ ባለጉዳይ Mary Jones ስራ ከተሰጠዎት ከ RN ተጨማሪ ተልዕኮ ሳይሰጥዎት ተጨማሪ ስራዎችን ለ Mary መስራት አይችሉም፡፡ በተመሳሳይ ለ Mary እንዲሰሩ የተሰጠዎትን ስራ ለሌላ ባለጉዳይ መስራት አይችሉም፡፡
- ሀላፊነት የሚሰጠው RN በየ90 ቀናቱ ባለጉዳዩን በድጋሚ መገምገም እና ተልዕኮውን መቆጣጠር አለበት፡፡
- ባለጉዳዩ ወይም ህጋዊ ተወካዩ ስራው ለእርስዎ እንደተሰጠ ማወቅ፣ መስማማት እና የጽሁፍ ስምምነት መስጠት አለበት፡፡
- ተልዕኮው በጽሁፍ መሆን አለበት፡፡
- ተልዕኮው ሀላፊነት በሚሰጠው RN ፣ በባለጉዳዩ እና በእርስዎ መካከል የሚደረግ ባለሶስትዮሽ ስምምነት ነው፡፡

ሚና እና ሀላፊነት

ሚና

በተልዕኮ ሂደት ውስጥ መረዳት ያለብዎት አምስት ቁልፍ ሚናዎች አሉ። የሚከተሉትን ካትታል፤

1. ደንበኛ ወይም ደንበኛ ተወካይ።
2. ሀላፊነት የሚሰጥ RN።
3. የነርስ ረዳት/የቤት ውስጥ እንክካቤ ረዳት።
4. የጉዳይ ሀላፊ።
5. የቤት ውስጥ እንክብካቤ ሰጪ ኤጀንሲ ተቆጣጠሪ ወይም የቦታ ቀጣሪ/አስተዳዳሪ።

የሚከተሉት መረጃዎች በነርስ ተልዕኮ ውስጥ ያለውን ሚና ለመረዳት ይጠቅማሉ።

ሚና እና ሀላፊነት - ባለጉዳዩ ወይም ተወካይ

ደንበኛ ወይም ተወካይ

ባለጉዳዩ የነርስ ተልዕኮ ማግኘት መፈለጉን/አለመፈለጉን ይወስናል። ባለጉዳዩ ስለእንክበካቤ አማራጮች ሊነግረው እና ስለነርስ ተልዕኮው በጽሁፍ ስምመነት ሊሰጥ ይገባል።

ለቤት ውስጥ አገልግሎት እንክብካቤ ሰጪው ሲቀር ወይም የተሰጠውን ስራ ካልሰራ ባለጉዳዩ ወይም ተወካዩ ሀላፊነት ለሰጠው RN፣ የጉዳይ ሀላፊ ወይም እንክበካቤ ሰጪው ለቤት ውስጥ እንክበካቤ ሰጪ ኤጀንሲ ሚሰራ ከሆነ ለተቆጣጣሪው የማሳወቅ ሀላፊነት አለበት።

ሚና እና ሀላፊነት - ሀላፊነት የሚሰጠው RN

ሀላፊነት የሚሰተው RN

በተልዕኮ ውስጥ RN አምስት ዋና-ዋና የሀላፊነት ቦታዎች አሉት። እነዚህ የሚያካትቱት፤

1. ባለጉዳዩን መገምገም እና የተልዕኮውን ተገቢነት መገምገም።
2. ለነርስ ተልዕኮው ከባለጉዳዩ ወይም ፈቃድ ያለው ተወካይ በእውቀት ላይ ተመሰረተ የጽሁፍ ስምምነት ማግኘት።
3. ስራውን መስጠት።
4. ባለጉዳዩን በድጋሚ መገምገም እና ተልዕኮውን መቆጣጠር።
5. ተልዕኮውን ማስቀረት (መሰረዝ)።

በተልዕኮ ሂደት ውስጥ ሀላፊነት ከሚሰጠው RN ምን መጠበቅ እነዳለብዎት እንዲያውቁ የ RN መስፈርትን መረዳት ጠቃሚ ነው።

ባለጉዳዩን መገምገም እና ስምምነት ማግኘት

የባለጉዳዩ ሁኔታ የተረጋጋ እና ተገማች መሆኑን ለማወቅ ሀላፊነት የሚሰጠው RN የባለጉዳዩን ስርአት በሙሉ ይገመግማል፡፡ ተልዕኮ የሚደረገው የባለጉዳዩ ሁኔታ የተረጋጋ እና ተገማች ሲሆን ነው፡፡

ሀላፊነት የሚሰጠው RN ስለተልዕኮው ከባለጉዳዩ ወይም ከህጋዊ ወኪሉ ጋር መወያየት እና ስምመነቱን በጽሁፍ መቀበል አለበት፡፡

ስራውን ማስተላለፍ

RN ስራ ለእርስዎ ከመስጠቱ በፊት ሚከተሉትን ማድረግ አለበት፤

- ባለጉዳዩን ወይም ፈቃድ ያለው ወኪሉን ማነጋገር እና ለተልዕኮው ስምመነቱን በጽሁፍ መቀበል፡፡
- የሚመለከታቸው ሶስቱም ሰዎች ስለተልዕኮው መስማማታቸውን ማረጋገጥ፤
  - RN፡፡
  - ደንበኛ ወይም ፈቃድ ያለው ተወካይ፡፡
  - እርስዎ እንደ NA ወይም HCA፡፡
- የስልጠና መስፈርቱን ማሟላትዎን ማረጋገጥ፡፡
- ስራው እንዴት እደሚሰራ ማስተማር፡፡
- ስራው በትክክለኛ እና ደህንነቱ ተጠብቆ መሰራቱን ለማረጋገጥ ስራውን ለመስራት ያለዎትን ብቃትዎን ማረጋገጥ፡፡
- የጽሁፍ የተልዕኮ መመሪያ መስጠት፡፡

ተልዕኮውን መቆጣጠር

ተልዕኮው አንዴ ከተጀመረ በኋላም RN ለባለጉዳዩ እንክብካቤ ሀላፊነት ይወስደል እዲሁም ተጠያቂ ሆናል፡፡ RN የሚከተሉትን ያደርጋል፤

- ስለባለጉዳዩ ሁኔታ ወይም ስለተሰጠው ስራ ያለዎትን ማንኛውንም ጥያቄ መመለስ፡፡
- የባለጉዳዩን ሀኔታ የሚሰሩትን ስራ ውጤት እና ማንኛውም የተፈጠረ ችግርን በድጋሚ መገምገም፡፡
- ደህንነቱ የተጠበቀ እና ውጤታማ አገልግሎት መሰተጡን ለማረጋገጥ ተልዕኮውን በምን ያህል ጊዜ መቆጣጠር እንዳለበት መወሰን፡፡
- የባለጉዳዩ ሁኔታዎች ላይ ያሉ ለውጦችን ለእንክበካቤ ሰጪው እና/ወይም ለጉዳይ ሀላፊው ማሳወቅ፡፡

አንዳንዴ ለተልዕኮው ሀላፊ የሆነው RN ይለወጣል፡፡ አዲስ RN ፣ የሚከተሉትን የሚያውቅ ከሆነ ሀላፊነት ለሰጠው RN ሀላፊነት መውሰድ ይችላል፤

- በራሱ ግምገማ የባለጉዳዩን ሁኔታ ካወቀ፡፡
- የችሎታ ደረጃዎችን፣ እንደ ተልዕኮውን የሚሰራው NA ወይም HCA፡፡
- የባለጉዳዩን የእንክብካቤ እቅድ፡፡

ሀላፊነት የተሰጠው RN መለወጥ በባለጉዳዩ መሀደር ውስጥ መጠቀስ አለበት፡፡ ስለ ለውጡ እርስዎ፣ ባለጉዳዩ እና የጉዳይ ሀላፊው ማወቅ አለባችሁ፡፡

የሚከተለው ከሆነ RN የነርስ ስራ ተልዕኮውን መተው (መሰረዝ) ይችላል፤

ተልዕኮውን መተው

- የባለጉዳዩ ደህንነት አደጋ ላይ ነው ብሎ ነርሱ ካመነ፡፡
- የባለጉዳዩ ሁኔታ የተረጋጋ እና ተገማች ካልሆነ፡፡
- የሰራተኛ ገቢ ተልዕኮውን ባለበት ሁኔታ ለመቀጠል አስቸጋሪ ካደረገው፡፡
- ስራውን ደህነነቱ ተጠብቆ መስራት ካልቻሉ፡፡
- ምዝገባዎትን ወይም የምስክር ወረቀትዎን በወቅቱ ካላደሱ፡፡
- ስራው በትክክለኛ መንገድ እየተሰራ ካልሆነ፡፡
- ባለጉዳዩ ወይም ፈቃድ ያለው ተወካይ ተልዕኮው እዲሰረዝ ከጠየቀ፡፡
- ባለጉዳዩ ወደእንክበካቤ መስጫ ቤት ከገባ (ባለጉዳዩ ሲመለስ RN ተልዕኮው ሊያስቀጥል ይችላል)፡፡
- በተለያዩ በርካታ አጋጣሚዎች የባለጉዳይ የህክምና ትዕዛዞች ወይም ሁኔታዎች ሲለወጡ RN ካልተነገረው፡፡
- ፈቃድ ላላቸው የእንክብካቤ ሁኔታዎች እንክበካቤ መስጫ ቦታው ወይም የቤት ውስጥ እንክብካቤ ኤጀንሲው (እንደሚመለከተው) ጊዜው ያለፈበት ፈቃድ ካለው ወይም ፈቃ የተነጠቀ ከሆነ (የታደሰ ፈቃ ሲመጣ RN ተልዕኮው ሊያስቀጥል ይችላል)፡፡

RN ተልዕኮውን ከተወ ወይም ከሰረዘ የባለጉዳዩ የእንክብካቤ ፍላጎቶች ማሟላታዎን ለማረጋገጥ RN ሌላ እቅድ ማዘጋጀት አለበት፡፡

ሀላፊነት የሚሰጠው RN ተልዕኮው የተተወበትን ምክንያት እና ለቀጣይ እንክብካቤ የታቀደውን መሀደሩ ላይ ማያያዝ አለበት፡፡

ሚና እና ሀላፊነት - የነርስ ረዳት ወይም የቤት ውስጥ እንክብካ ረዳት

የነርስ ረዳት/ቤት ውስጥ እንክብካቤ ሰጪ ረዳት

በእርስዎ ባለጉዳይ እንክብካቤ እና ደህንነት ላይ ጠቃሚ ሚና ይጫወታሉ፡፡ የተልዕኮ ስራ አንዴ ከተቀበሉ በኋላ ለአምስት ዋና-ዋና ስራዎች ሀላፊነት ይወስዳሉ፤

1. RN በሰጠው የተለየ መመሪያ መሰረት የተሰጠውን ስራ **መስራት**፡፡ ሀላፊነት የሰተው RN በሰጠው መመሪያ መሰረት ስራዎችን መሀደሩ ላይ ማያያዝ፡፡
2. ባለጉዳዩ ላይ የሚከተሉትን፡ አይነት ለውጦች እንዳሉ/እንደሌሉ **ማስተዋል**፤
   - የመድሀኒቶች የጎንዮሽ ጉዳዮች፡፡
   - ለአሰራሮች አሉታዊ ምላሽ ማሳየት፡፡
   - ከባለጉዳዩ በሽታ የሚመጣ ውስብስብነት፡፡
3. ባለጉዳዩ ላይ የሚታዩ ለውጦችን በፍጥነት **ማሳወቅ** ፡፡
   - እንክብካቤ መስጫ ቦታ ወይም የቤት ውስጥ እንክንካቤ መስጫ ኤጀንሲ ውስጥ የሚሰሩ ከሆነ በቀጣሪዎት ፖሊሲ መሰረት ሀላፊነት ለሚሰጠው RN እና ተቆጣጣሪዎት ያሳውቁ፡፡
   - የግል አገልግሎት ሰጪ ከሆኑ ሀላፊነት ለሚሰጠው RN እና ለጉዳይ ሀላፊው ያሳውቁ፡፡
4. ማንኛውም አዲስ ወይም የተለወጠ መድሀኒት ወይም ህክምና ካለ ሀላፊነት ለሚሰጠው RN **መሳወቅ** ፡፡
5. የተልዕኮ ስራ በህጋዊ መንገድ መስራት እንዲችሉ ምዝገባዎትን ወይም የምስክር ወረቀትዎን **ማደስ** ፡፡

አስተዋይ በመሆን እና ቶሎ በማሳወቅ የባለጉዳይዎትን የጤና እና ህይወት ጥራት ላይ ለውጥ ማምጠት ይችላሉ፡፡

- ከሀኪም ወይም ሀኪሙ ቢሮ ካለ ሰራተኛ በስልክ ትዕዛዝ አይቀበሉም፡፡ ትዕዛዝ በስልክ ከተቀበሉ ሀላፊነት የሚሰጠውን RN እና/ወይም ተቆጣሪዎትን ያነጋግሩ፡፡
- በሀኪሙ የተፈረመ በፋክስ የተላከ ትዕዛዝ ለማረጋገጫነት መጠቀም ይቻላል፡፡ ይህ ቢሆን ምንም አይነት ለውጥ ከማካሄድዎት በፊት ሀላፊነት የሚሰጠውን RN ማነጋገር አለብዎት፡፡

የነርስ ልዑክ ስራን ለመቀበል ወይም ላለመቀበል ምርጫ አለዎት፡፡

ተልዕኮ አንዴ ከተቀበሉ በኋላ እርስዎ ሊሰሩት የማይችሉት ሁኔታዎች ሊፈጠሩ ይችላሉ፡፡ በሚከተሉት ሁኔታዎች የተልዕኮ ስራ አልሰራም ቢሉ በቀጣሪዎት አይቀጡም ወይም የስነ-ምግባር እርምጃ አይወሰድብዎትም፡

- የባለጉዳዩ ደህንነት አደጋ ላይ ከሆነ፡፡
- ስራውን ለመስራት በቂ ስልጠና ካላገኙ፡፡
- ባለጉዳዩ ተባባሪ ካልሆነ፡፡
- ባለጉዳዩ ለስራው አሉታዊ ምላሽ ካሳየ፡፡
- አስፈላጊው አቅርቦት ከሌለ (ጓንት፣ የቁስል ማሸጊያዎች ወዘተ)፡፡
- በባለጉዳዩ የመድሀኒት ወይም ህክምና ለውጥ ምክነያት ተጨማሪ ስልጠና ካስፈለገዎት፡፡

እነዚህ ሁኔታዎች ከተፈጠሩ ሀላፊነት ለሚሰጠውን RN፣ የባለጉዳዩ የጉዳይ ሀላፊ እና ለቀጣሪዎት በፍጥነት ማሳወቅ፡፡ **ለባለጉዳይ የሚሰጥ እንክበካቤ አለመጓደሉን እና አለመቋረጡን ማረጋገጥ የእርስዎ ሀላፊነት ነው፡፡**

ኬዝ ማናጀር

ሚና እና ሀላፊነት - የጉዳይ ሀላፊ

የጉዳይ ሀላፊ የባለጉዳዩን ፍላጎቶች የሚዘረዝር የእንክብካቤውን ግምገማ ያደርጋል፡፡ የጉዳይ ሀላፊው ሀላፊነቶች

- በባለጉዳዩ የእንክብካቤ እቅድ ላይ የነርስ ተልዕኮ እንደሚያስፈልግ መለየት፡፡
- ብቁ የሆነ የነርስ ተልዕኮ ሰጪ ለማግኘት ባለጉዳይን ማገዝ፡፡
- በውል የሚሰራ ሀላፊነት ለሚሰጥ RN ወይም የነርስ ተልዕኮ ለሚሰጥ አካል ጥቆማ ማድረግ፡፡
- ሀላፊነት ለሚሰጠው RN ክፍያ መፍቀድ፡፡
- የባለጉዳዩ ሁኔታ ላይ የሚታዩ ለውጦችን ሀላፊነት ለሚሰጠው RN እና/ወይም እንክብካቤ ሰጪ ማሳወቅ፡፡

ለቤትውስጥ ሁኔታ የጉዳይ ሀላፊው ሀላፊነት፡

- እንክብካቤ ሰጪ የነርስ ተልዕኮ ስልጠና እንዲያገኝ ወደስልጠና ሽርክና መላክ፡፡
- እንክብካ ሰጪው የነርስ ተልዕኮ ለነርስ ረዳት እና የቤት ውስጥ እንክብካቤ ሰጪ ረዳ ስልጠናውን ሲቸርስ ክፍያ መፍቀድ፡፡
- ደረሰኝ መስጠት እና የግል አገልግሎት ሰጪ NA-R ሆኖ እንዲመዘገብ ማመቻቸት፤ አስፈላጊ ከሆነ፡፡
- የነርስ ረዳት/የቤት ውስጥ እንክብካቤ ረዳት እስኪሰለጥን እና የሚሰጡ ስራዎችን ለመስራት መስፈርት እስኪያሟላ ድረስ በነርስ ሚሰሩ ስራዎች እነዲሰሩ ማድረግ፡፡

ሚና እና ሀላፊነት - የቤት ውስጥ እንክብካቤ ሰጪ ኤጀንሲ

ኤጀንሲ ተቆጣጣሪ

ለቤት ውስጥ ባለጉዳዮች፤ የቤት ውስጥ እንክብካቤ ሰጪ ኤጀንሲው ሀላፊነት፤

- ኤጀንሲው የነርስ ተልዕኮ እንደሚሰጥ መወሰን፡፡
- ብቃት ያላቸው እንክበካቤ ሰጪዎች የባጉዳዩን ፍላጎት እንዲያሟሉ ማዘጋጀት፡፡
- እንክበካቤ ሰጪው ሚያስፈልገውን ስልጠና እንዲያገኝ ማገዝ፡፡
- እንክበካቤ ሰጪው እንደ NA-R እንዲመዘገብ ማገዝ፤ አስፈላጊ ከሆነ፡፡
- የባለጉዳዩ ሁኔታ ላይ የሚታዩ ለውጦችን ሀላፊነት ለሚሰጠው RN እና/ወይም እንክብካቤ ሰጪ ማሳወቅ፡፡
- የግል እንክብካቤ ሀላፊነቶችን መቆጠጠር፡፡
- ለባለጉዳይ እንክብካቤ ተጠባበቂ ሰራኛ ማዘጋጀት፡፡

ሚና እና ሀላፊነት - ቀጣሪ/አስተዳደር

የቀጣሪ አስተዳደር

በእንክብካቤ ሰጪ ቦታ የሚደረግ ማንኛውም የነርስ ተልዕኮ በነርስ ተልዕኮ ደንቦች መሰረት መደረጉን ቀጣሪው/አስተዳደሩ የማረጋገጥ ሀላፊነት አለበት፡፡ ይህ የሚከተሉትን ያካትታል፤

- የሚሰራው ስራ በህግ የተከለከለ አለመሆኑን ማረጋገጥ፡፡
- ስራ ከመቀበሉ በፊት የነርስ ረዳት/የቤት ውስጥ እንክብካቤ ሰጪ ረዳት ሁሉንም ስልጠና እና የምዝገባ መስፈርቶች ማሟላቱን ማረጋገጥ፡፡
- የተልዕኮ ሂደቱ በትክክል መሰራቱን ማረጋገጥ፡፡
- ስራው በትእዛዙ መሰረት መሰራቱን ማረጋገጥ፡፡

እገዛ በሚደረግለት እንክብካቤ መስጫ ቦታ ወይም የአዋቂ ቤተሰብ ቤት ውስጥ ለሚደረጉ ነገሮች ቀጣሪው/አስተዳደሩ ሀላፊነት አለበት፡፡ ተልዕኮው በትክክል ካልተሰራ በደንብ አስከባሪዎች ይጠራሉ፡፡

የቦታው ፖሊሲ ማዘጋጀት

በቦታው መተግበር ያለባቸው አሰራሮችን የማዘጋጀት እና የማሳወቅ/መንገር ተጨማሪ ሀላፊነት ቀጣሪው/አስተዳደሩ አለበት፡፡ የቦታውን መጠን እና ሰራተኞችን ደረጃ ከግንዛቤ በማስገባት ምርጥ የባለጉዳይ እንክብካቤ የሚሰጥበት ፖሊሲ የመዘጋጀት ሀላፊነት አስተዳደሩ አለበት፡፡

አስተዳደሩ ለባለጉዳዩ እንክብካቤ አጠቃላይ ሀላፊነት ስላለበት አስተዳደሩ፣ ሀላፊነት የሚሰጠው RN እና የነርስ ረዳቱ/የቤት ውስጥ እንክብካቤ ሰጪ ረዳቱ የተልዕኮውን ደንቦች እና የቦታውን ወይም የቤቱን ፖሊሲዎች በግልጽ ማወቃቸው በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

ይህን ትምህርት ከጨረሱ በኋላ ስለቦታው ፖሊሲዎች ከአስተዳደሩ ጋር ይወያዩ፡፡ የሚደረጉትን መግባቢያ ሂደቶች መረዳትወዎን ያረጋግጡ፡፡ ለምሳሌ የነርስ ረዳቱ/የቤት ውስጥ እንክብካቤ ሰጪ ረዳቱ ሀላፊነት የሚሰጠው RN ሲያነጋግር ሁልጊዜ አስተዳደሩን ማነጋገር አለበት የሚል ፖሊሲ ቦታው ሊኖረው ይችላል፡፡

እርዳታ መጠየቅ

የትም ቢሰሩ የሆነ ነገር ሲፈጠር ማን ጋር መደወል እነዳለብዎት ማወቅ አለብዎት፡፡ የተለዩ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ ማን ጋር መደወል እንዳለብዎት ለማወቅ እንዲረዳዎት በዚህ መጽሀፍ "የስራ አጋዥ" ክፍል ላይ የነርስ ተልዕኮ መግባቢያ ዝርዝር ያገኛሉ፡፡

የሆነ ነገር ሲፈጠር ማን ጋር መደወል እንዳለብዎት ሀላፊነት ከሚሰጠው RN፣ ተቆጣጠሪዎት/ቦታው አስተዳደር እና/ወይም የጉዳይ ሀላፊ ጋር ለመወያየት ይህን መሳሪያ ይጠቀሙ:: የቅጹ ምሳሌ በሚቀጥለው ገጽ አለ፡፡

የነርስ ተልዕኮ መግባቢያ ዝርዝር

ዝርዝር

ይህ ቅጽ በተለየ ሁኔታ ላይ ማነጋገር ያለብዎትን ሰው በተመለከተ ስለፖሊሲዎች እና የሚጠበቁ ነገሮች እነዲወያዩ እና እንዲያስቀምጡ ይረዳዎታል፡፡

ይህን ትምህርተ ከጨረሱ በኋላ ከስር ስላሉት ነገሮች ለመዋየት ሀላፊነት ከሚሰተው RN፣ ተቆጣጠሪዎት፣ የቦታው አስተዳደር ወይም በአንዳንድ ሁኔታዎች ላይ ከጉዳይ ሀላፊ ጋር ይገናኙ፡፡ ፖሊሲዎቹን ያዙ እና በተሰጠው ቦታ ላይ መገኛ አድራሻ፡፡

የሚከተለው ሲሆን የምደውለው ማን ጋር ነው፤

አደጋ

_____

_____

የእቃ አቅርቦት ካስፈለገ

_____

_____

የሀኪም ትዕዛዝ ላይ ለውጥ ካለ

_____

_____

የነርስ ተልዕኮ ስራ በሚሰራበት ቀን ወደስራ መሄድ ባልችል

_____

_____

ባለጉዳዩ የሚከተሉትን ከሆነ የማነጋግረው ማንን ነው፤

መታመም ከጀመረ

_____

_____

በሁኔታው ላይ ለውጥ ካሳየ

_____

_____

መድሀኒት ወይም ህክምና መውሰድ ካልፈለገ

_____

_____

አጠቃላይ መረጃ

_____

_____

ለነርስ ተልዕኮ አምስት ሁኔታዎች

ለነርስ ተልዕኮ አምስት ሁኔታዎች አሉ፤

1. ፈቃድ ያለው**የተመዘገበ ነርስ** ስራው እንዲሰራ ያስተላልፋል፡፡
2. መተላለፍ **የማይችሉ አራት የተለዩ ስራዎች**አሉ፡፡
3. አንድ ተልዕኮ**የአንድን ባለጉዳይ የተወሰነ ስራ ብቻ ይሸፍናል፡፡**
4. ብቁ የነርስ ረዳት ምስክር ወረቀት ያለው፣ የነርስ ረዳ-የተመዘገበ እና ምስክር ወረቀት ያለው የቤት ውስጥ እንክብካቤ ረዳት ብቻ ስራ መቀበል ይችላሉ፡፡
5. ስራ የሚተላለፈው **በአራት የማህበረሰብ ሁኔታ ውስጥ ነው፡፡**

የማይሰጡ ስራዎች

ሚከተሉት አራት ስራዎች ለእርስዎ አይተላለፉም፡፡

1. ከኢንሱሊን ሌላ መርፌ መውጋት፡፡
2. ከጀርም ነጻ የሆነ አሰራሮች፡፡
3. የማዕከላዊ መስመር መያዝ፡፡
4. የነርስን ውሳኔ የሚተይቅ ስራ፡፡

ብቁ NA

ተልዕኮ ለመቀበል ብቁ ለመሆን አምስት መስፈርቶች አሉ፡፡ የሚከተለውን ማድረግ አለብዎት፥

1. ዋሽንግተን ግዛት ውስጥ የአሁን እና የቆየ HCA፣ NA-R ወይም NA-C መሆን፡፡
2. ለተልዕኮ የሚሆን የትምህርት መስፈርቶችን መጨረስ፡፡
3. የሚሰጠውን ስራ ለመስራት ፈቃደኛ መሆን፡፡
4. የሚሰጠውን ስራ በትክክል እና ሀላፊነት ከሚሰተው RN ቀጥተኛ ቁጥጥር ሳይኖር ለመስራት ብቃትዎን ያሳዩ፡፡

በማህበረሰብ ውስጥ

ተልዕኮ የሚደረግበት አራ ሁኔታዎች አሉ፤

1. የእድገት ውስንነት ላለባቸው የምስክር ወረቀት ያላቸው ማህበረሰብ መኖሪያ መርሀግብሮች፡፡
2. ፈቃድ ያላቸው የአዋቂ ቤተሰብ ቤቶች፡፡
3. ፈቃድ ያላቸው እገዛ የሚደረግላቸው መኖሪያ ቤቶች፡፡
4. ባለጉዳዮች ቤት፡፡

የትምህርት ማጠቃለያ

ሚና

በተልዕኮ ሂደት ውስጥ መረዳት ያለብዎት አምስት ቁልፍ ሚናዎች አሉ። የሚከተሉት አካላት ሚናዎች፤

1. ደንበኛ፡
2. ሀላፊነት የሚሰተው RN
3. የነርስ ረዳት/የቤት ውስጥ እንክበካቤ ሰጪ ረዳት
4. የጉዳይ ሀላፊ
5. የቤት ውስጥ እንክብካቤ ሰጪ ኤጀንሲ ተቆጣጠሪ ወይም የቦታ አስተዳደር

ደንበኛ ወይም ተወካይ

ባለጉዳዩ ወይም ተወካዩ ስለነርስ ተልዕኮው ስምመነት መስጠት አለበት።

ሀላፊነት የሚሰተው RN

በተልዕኮው ላይ RN አምስት ዋና-ዋና የሀላፊነት ቦታዎች አሉ፤

1. ባለጉዳዩን መገምገም እና የተልዕኮውን ተገቢነት መገምገም።
2. ከባለጉዳዩ ወይም ፈቃድ ካለው ከተወካዩ በግንዛቤ ላይ የተመሰረተ የጽሁፍ ስምመነት ማግኘት።
3. ስራውን መስጠት።
4. ተልዕኮውን መቆጣጠር።
5. ተልዕኮውን ማስቀረት (መሰረዝ)።

የነርስ ረዳት የቤት ውስጥ እንክብካቤ ሰጪ ረዳት

ተልዕኮው ላይ የእርስዎ ሀላፊነት የሆኑ አራት ዋና እርምጃች አሉ፤

1. RN በሰጠው የተለየ መመሪያ መሰረት የተሰጠውን ስራ **መስራት**።
2. ባለጉዳዩ ላይ የሚከተሉትን እንዳሉ/እንደሌሉ **ማስተዋል**፡
   - የመድሀኒቶች የጎንዮሽ ጉዳዮች።
   - ለአሰራሮች አሉታዊ ምላሽ ማሳየት።
   - ከባለጉዳዩ በሽታ የሚመጣ ውስብስብነት።
3. ባለጉዳዩ ላይ የሚታዩ ለውጦችን በፍጥነት ሀላፊነት ለሚሰጠው RN **ማሳወቅ**።
4. አዲስ ወይም የተለወጠ መድሀኒት ወይም ህክምናን ሀላፊነት ለሚሰጠው RN **መሳወቅ**።
5. የተልዕኮ ስራ በህጋዊ መንገድ መስራት እንዲችሉ ምዝገባዎትን ወይም የምስክር ወረቀትዎን **ማደስ**።

ኬዝ ማናጀር

የጉዳይ ሀላፊው ሀላፊነቶች

- በባለጉዳዩ የእንክብካቤ እቅድ ላይ የነርስ ተልዕኮ እንደሚያስፈልግ መለየት፡፡
- ብቁ የሆነ የነርስ ተልዕኮ ሰጪ ለማግኘት ባለጉዳይን ማገዝ፡፡
- በውል የሚሰራ ሀላፊነት ለሚሰጥ RN ወይም የነርስ ተልዕኮ ለሚሰጥ አካል ጥቆማ ማድረግ፡፡
- ሀላፊነት ለሚሰጠው RN ክፍያ መፍቀድ፡፡

ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ

የቤት ውስጥ እንክብካቤ ሰጪ ኤጀንሲ ሀላፊነት፤

- ኤጀንሲው የነርስ ተልዕኮ እንደሚሰጥ መወሰን፡፡
- ብቃት ያላቸው እንክበካቤ ሰጪዎች የባጉዳዩን ፍላጎት እንዲያሟሉ ማዘጋጀት፡፡
- የግል እንክብካቤ ሀላፊነቶችን መቆጠጠር፡፡
- ለባለጉዳይ እንክብካቤ ተጠባበቂ ሰራተኛ ማዘጋጀት፡፡

የቀጣሪ አስተዳደር

የቀጣሪው/አስተዳዳሪው ሀላፊነት፤

- ሁሉም የህግ መስፈርቶች መሟላታቸውን ማረጋገጥ፡፡
- ለቦታው ፖሊሲ እና አሰራር ማዘጋት፡፡

ቁልፍ ነጥቦች

- የተሰጠ ስራ ለመቀበል ግዴታ የለብዎትም፡፡ የባለጉዳዩ ደህንነት አደጋ ላይ የሚወድቅ ከመሰለዎት ወይም ስራውን ለመስራት እርስዎ ብቁ የሆኑ ካልመሰልዎት አልሰራም ማለት ይችላሉ፡፡
- በተልዕኮው ውስጥ የሚሳተፉ ሶስት ሰዎች መስማማት አለባቸው፡ RN ፣ ባለጉዳዩ ወይም ፈቃ ያው ተወካይ እና እርስዎ፡፡
- ከኢንሱሊን በስተቀር መርፌ መውጋት፣ ከጀርም ነጻ አሰራሮች እና የማዕከላዊ መስመር መያዝ ለእርስዎ የሚሰጡ ስራዎች አይደሉም፡፡
- RN ተልዕኮውን በየወቅቱ መገምገም አለበት፡፡
- የነርስ ተልዕኮ ስራ ለአንድ ባለጉዳይ ብቻ ነው፡፡ ለሌላ ባለጉዳይ የተወሰነ ስራ እንዲሰሩ ካልተላኩ በስተቀር ለዛ ባለጉዳይ ተልዕኮ ስራ መስራት አይችሉም፡፡

የተግባር ልምምድ

መመሪያዎች፤ በማስታወስ የቻሉትን ያህል ጥያቄ ይመልሱ። በመቀጠል ለቀሪዎቹ ጥያቄዎች በመጽሀፉ ላይ ያሉትን መልሶች ይመልከቱ።

ጥያቄዎቹን ከጨረሱ በኋላ ከዚህ የተግባር ልምመድ ቀጥሎ የሚገኘው የተግባር ልምምድ የመልስ ቁልፍ ላይ በመሄድ የሰጡትን መልስ ያረጋግጡ።

ለነርስ ተልዕኮ መሞላት ያለበት አምስት ሁኔታዎች ምንድን ናቸው?

1. _____

2. _____

3. _____

4. _____

5. _____

ተልእኮ የሚደረግበት አራቱ ሁኔታዎች አሉ። ምንድን ናቸው?

1. _____

2. _____

3. _____

4. _____

ለእርስዎ የማይሰጥዎት አራት የተለዩ ስራዎችን ይዘርዝሩ።

1. _____

2. _____

3. _____

4. _____

የኢንሱሊን መርፌ መውጋት የሚሰጥ ስራ ነው።

☐ እውነት ☐ ሀሰት

በተልዕኮ ውስጥ የነርስ ረዳት/የቤት ውስጥ እንክብካቤ ሰጪ ረዳት የመስራት ሀላፊነት ካለበት አምስት ዋና ድርጊቶች ሁለቱን ዘርዝሩ፡፡

1. _____

2. _____

ለ Barbara Jones የቁስል መሸፈኛ የመለወጥ ስራ ተሰጥቶዎታል፡፡ ይህን ስራ ለ30 ቀናት እየሰሩት ነው እንዲሁም በጣም ለምደውታል፡፡ Michael Delgado የሚባል ሌላ ባለጉዳይ ከክብደት የመጣ ህመም አለው እና አሁን እሱም የቁስል መሸፈኛ የመለወጥ ስራ ይፈልጋል፡፡ Barbara ጋር ተመሳሳይ ጥሩ ስራ እየሰሩ ስለሆነ ተቆጣጠሪዎት (ሀላፊነት የሚሰጠው RN ያልሆነ) ለ Michael የቁስል መሸፈኛ የመለወጥ ስራ እንዲሰሩለት ጠየቀዎት፡፡ ምነ ማድረግ አለብዎት?

_____

_____

_____

_____

_____

የተግባር ልምምድ የመልስ ቁልፍ

ከስር የሚገኙትን ምላሾች ይገምግሙ፡፡ ከጥያቄው ቀጥሎ የሚያገኙት የገጽ ቁጥር በመጽሀፉ ላይ ስለዚህ ጥያቄ መረጃ የሚያገኙበት ገጽ ነው፡፡

ለነርስ ተልዕኮ መሟላት ያለባቸው አምስት ሁኔታዎች ምንድን ናቸው? (**ገጽ 9**)

1. ፈቃድ ያለው **የተመዘገበ ነርስ** ስራ ይሰጣል፡፡
2. የማይተላለፉ **አራት** የተለዩ **ስራዎች**አሉ፡፡
3. ተልዕኮ**ማለት ለአንድ ባለጉዳይ የተወሰነ ስራን**የሚሸፍን ነው፡፡
4. ተልዕኮን መቀበል የሚችሉት**ብቁ የነርስ ረዳት/የቤት ውስጥ እንክብከቤ ሰጪ ረዳት** ብቻ ናቸው፡፡
5. ተልዕኮ የሚደረገው በአራት**የማህበረሰብ ሁኔታዎች** ብቻ ነው፡፡

ተልእኮ የሚደረግበት አራቱ ሁኔታዎች አሉ፡፡ ምንድን ናቸው? (**ገጽ 14**)

1. **የእድገት ውስንነት ላለባቸው የምስክር ወረቀት ያለው የመኖሪያ መርሀግብር፡፡**
2. **ፈቃድ ያላቸው አዋቂ የቤተሰብ ቤት፡፡**
3. **ፈቃድ ያለው እገዛ ሚደረግለት መኖሪያ ቦታ፡፡**
4. **በባለጉዳዩ ቤት፡፡**

ለእርስዎ **ማይሰጥዎትን** አራት የተወሰኑ ስራዎች ይዘርዝሩ፡፡(**ገጽ 9**)

1. **ከኢንሱሊን ሌላ መርፌ መውጋት**
2. **ከጀርም ነጻ የሆነ አሰራር**
3. **ማእከላዊ መስመር መያዝ**
4. **የነርስ ውሳኔን የሚፈልጉ ስራወች**

የኢንሱሊን መርፌ መውጋት የሚተላፍ ስራ ነው፡፡(**ገጽ 9**)

እውነት፡፡የኢንሱሊን መርፌ መውጋት ብቸኛው ሚተላለፍ መርፌ የመውጋት ስራ ነው፡፡

በተልዕኮ ውስጥ የነርስ ረዳት/የቤት ውስጥ እንክብካቤ ሰጪ ረዳት መስራት ካለበት አምስቱ ዋና ተግባሮች ሁለቱን ዘርዝሩ፡፡(**ገጽ 17**)

1. _____
2. _____

ከአምስቱ ማንኛውም ሁለቱ ትክክል ናቸው፡፡

1. RN በሰጠው የተለየ መመሪያ መሰረት የተሰጠውን ስራ መስራት፡፡
2. ባለጉዳዩ ላይ የሚከተሉትን ለውጦች እንዳሉ/እንደሌሉ ማስተዋል፤
   - የመድሀኒቶች የጎንዮሽ ጉዳቶች፡፡
   - ለአሰራሮች አሉታዊ ምላሽ ማሳየት፡፡
   - ከባለጉዳዩ በሽታ የሚመጣ ውስብስብነት፡፡
3. ባለጉዳዩ ላይ የሚታዩ ለውጦችን በፍጥነት ሀላፊነት ለሚሰጠው RN እና ለተቆጣጠሪዎት ወይም ለጉዳዩ ሀላፊ ማሳወቅ ፡፡
4. አዲስ ወይም የተለወጠ መድሀኒት ወይም ህክምናን ሀላፊነት ለሚሰጠው RN መሳወቅ፡፡
5. ምዝገባዎትን ወይም የምስክር ወረቀትዎን በወቅቱ ያሳድሱ፡፡

ለ Barbara Jones የቁስል መሸፈኛ የመለወጥ ስራ ተሰጥቶዎታል፡፡ ይህን ስራ ለ30 ቀናት እየሰሩት ነው እንዲሁም በጣም ለምደውታል፡፡ Michael Delgado የሚባል ሌላ ባለጉዳይ ከክብደት የመጣ ህመም አለው እና አሁን እሱም የቁስል መሸፈኛ የመለወጥ ስራ ይፈልጋል፡፡ Barbara ጋር ተመሳሳይ ጥሩ ስራ እየሰሩ ስለሆነ ተቆጣጠሪዎት (ሀላፊነት የሚሰጠው RN ያልሆነ) ለ Michael የቁስል መሸፈኛ የመለወጥ ስራ እንዲሰሩለት ጠየቀዎት፡፡ ምነ ማድረግ አለብዎት? (**ገጽ 11**)

መልስ፤ ለ Michael የቁስል መሸፈኛ የመለወጥ ስራን ከተቆጣጣሪዎት መቀበል አይችሉም ምክነያቱም ሀላፊነት የሚሰጠው RN ስላልሆነ፡፡

ስራውን መስራት እንደሚችሉ የሚወስነው እና በህግ መስፈርቶች መሰረት ሂደቱን የሚጨርሰው ሀላፊነት የሚሰጠው RN ጋር ተቆጣጣሪዎት እንዲደውል ይጠይቁ፡፡

መጽሀፉን መንበብ እዚህ ጋር ያቁሙ፡፡

ስለነርስ ተልዕኮ ህግ እና እርስዎ ያለዎትን ሚና የሚያሳየውን የቪድዮ ክፍል ይመልከቱ፡፡

ወደ ድህረ-ገጽ የሚወስደውን መገናኛ ይከተሉ፡፡ በትምህርት መደዳ ስር የነርስ ተልዕኮ ወደሚለው ያውርዱ፡፡ በመረጡት ቋንቋ ላይ ይጫኑ፡፡ ማየት የሚፈልጉትን ቪድዮ ይምረጡ፡፡
www.dshs.wa.gov/altsa/training/dshs-curriculum-available**፡፡**

የባለጉዳይ እንክብካቤ እና የሰውነት ስርአት

አጭር መግለጫ እና ቅድመ-እይታ

በዚህ ትምህርት ላይ ከባለጉዳይዎት ጋ ስለሚኖርዎት ግነኙነት ትኩረት እናደርጋለን፡፡ ሊያጋጥምዎት ስለሚችሉ ሁኔታዎች ለማስረዳት አንዳንድ የባጉዳይ አይነቶችን እንገልጻለን፡፡

የሰውነት ዋና-ዋና ስርአቶችን፣ በእርጅና ምክንያት የሚፈጠሩ ሁኔታዎችን እና የእነዛ ስርአቶች አንዳንድ የተለመዱ በሽታዎችን ይማራሉ፡፡ ይህ የኋላ ታሪክ እውቀት የተሻለ የነርስ ረዳት/የቤት ውስጥ እንክብካቤ ሰጪ ረዳት እንዲሆኑ ይረዳዎታል፡፡

የትምህርት አላማዎች

ይህን ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ፡

1. ዘጠኝ ዋና-ዋና የሰውነት ስርአቶችን ማብራራት እና በእያንዳንዱ ስርአት ያለውን ዋና የሰውነት ክፍል ስራ መለየት፤
    1. ልብ (ልብ እና የደም ስሮች)
    2. አተነፋፈስ (ሳንባ)
    3. የላይኛው ቆዳ (ቆዳ)
    4. ብልት-ሽንት መሽኛ (ኩላሊት፣ የሽንት ቧንቧ እና የመራቢያ አካላት)
    5. የጨጓራ አንጀት (ምግብ መፍጫ ስርአት እና የሰገራ እንቅስቃሴ)
    6. ዝግ እጢ (እጢ)
    7. ነርቭ (ጭንቅላት አከርካሪ አጥንት እና ነርቮች)
    8. የጅማትአጥንት (አጥንት እና ጅማት)
    9. የስሜት ህዋሳት (አይን እና ጆሮ)

2. በእያንዳንዱ የሰውት ስርአት ላይ እርጅና ሚያመጣውን ውጤት ይግለጹ፡፡

3. በእያንዳዱ ስርአት ላይ የሚፈጠር ሁለት ወይም ከዛ በላይ ችግሮች ግለጹ፡፡

መግቢያ

የባለጉዳዩ ግለ-ታሪክ

እያንዳዱ ሰው የተለየ ፍላጎት እና ነገሮችን የማድረግ መንገድ ያለው ስለሆነ "የተለመደ" የሚባል ባለጉዳይ የለም። ከስር የተገለጹት ሁለት ሰዎች እና ሁኔታዎች የተልዕኮ ስራ ሲሰሩ ሊያጋጥምዎት ከሚችሉ ሁኔታዎች ጋር ይመሳሰላሉ። ሁሉም ሁኔታ የተለየ እንደሆነ ያስታውሱ።

ምሳሌ 1፤ የአዋቂ ቤተሰብ ቤት ባለጉዳይ

Sarah Goldstein በአዋቂ የቤትሰብ ቤት ውስጥ ከሌላ አራት አረጋውያን ሰዎች ጋር ትኖራለች። 80 አመቷ ሲሆን በርካታ ስክለሮሲስ፣ ግላውኮማ ከፍተኛ ደም ግፊት እና የልብ በሽታ አለባት። ወ/ሮ Goldstein ላለባት ግላውኮማ የአይን ጠብታ ታዘላታል። ያለባት በርካታ ስክለሮሲስ እጆቿን ስላደከመው እጆቿ ትኩረት የሚፈልጉ ነገሮችን መስራት ስለማይችሉ የአይን ጠብታዋ በሌላ ሰው መደረግ አለበት። የጠብታ እቃውን ተጭና ጠብታውን አይኗ ውስጥ ማስገባት አትችልም።

ሀላፊነት የሚሰጠው RN፣ Jane የወ/ሮ Goldstein የአይን ጠብታ የመስጠት ስራ ለሌላ ሰው እንዲያስተላልፍ ከባለጉዳይዋ የጽሁፍ ፈቃድ አለው። Jane አሁን ስራውን ለሰው ለመስጠት የሚያስፈልጉትን ሌሎች ሁኔታዎች ለማሟላት ይቀጥላል። አሰራሩን በትክክል እየሰሩ እነደሆነ እና የተልዕኮው ሁሉም ሌሎቹ ሁኔታዎች በተመሳሳይ ሁኔታ መቀጠላቸውን ለማረጋገጥ በየወቅቱ ይቆጣጠርዎታል።

የእድገት ውስንነት

የእድገት ውስንነት ካለባቸው ባለጉዳዮች ጋርም ሊሰሩ ይችላሉ። ***የእድገት ውስንነት***በዙ ጊዜ የሚከተሉት ሶስት ባህሪያት አሉት፤

1. ከ18 አመት በፊት ይጀምራል።
2. ላልተወሰነ ጊዜ ይቀጥላል።
3. አካል ጉዳተኝነትን ያስከትላል።

እድገት ውስንነት ምሳሌዎች፤

- የእውቀት ውስንነት
- የሰረብራል ዝለት
- የሚጥል ህመም
- ኦቲዝም
- የአዕምሮ ዝግመት

የዘር ችግር፣ በእርግዝና ወቅት ሚያጋጥሙ የተወሰኑ ችግሮች፣ በመጀመሪያዎቹ ህይወት ዘመን ላይ የሚያጋጥም የተጓደለ አካባቢ ሁኔታ እና የአዕምሮ መጎዳትን ጨምሮ ከ200 በላይ የሚታወቁ የእድገት ውስንነትን የሚያመጡ መንስኤዎች አሉ።

ውስንነቶችን ማብራራት

የእውቀት ውስንነት — በ IQ ፈተና ውጤት (ብዙጊዜ 69 ወይም ከዛ በታች ውጤት) ይታወቃል። የእውቀት ውስንነት ያለበት ሰው የመማር ችግር አለበት። የእውቀት ውስንነት ያለበትን ሰው የሚለየው ፈቃድ ያለው የስነ-አዕምሮ ባለሙያ ነው።

የሰረብራል ዝለት— በጡንቻ መገተር፣ መዛል ወይም መንቀጥቀጥ ምክንያት የሰውን እንቅስቃሴ መቆጣጠር አለመቻል ነው። የሰረብራል ዝለት የሚከሰተው አዕምሮ ላይ በሚደርስ ጉዳት ነው። የሰረብራል ዝለት ችግርን የሚያገኘው ሀኪም ነው።

የሰረብራል ዝለት ያለበት ሰው መደበኛ ወይም ከዛ በላይ እውቀት ሊኖረው ይችላል።

የሚጥል በሽታ— አዕምሮ ውስጥ የነርቭ መልዕክቶች ያላስፈላጊ ሲላኩ እና ሲዝር ሲያስከትሉ ነው። ብዙ ጊዜ በመድሀኒት መቆጣጠር ይቻላል። የሚጥል በሽታን የሚያገኘወ ሀኪም ነው።

ኢቲዝም —የመግባባት ችግር፣ የማህበራዊ ሁኔታዎች ላይ ችግር እና በእለተ-ተእለት ኑሮ እንቅስቃሴ ላይ መገደብን ያካትታል። ኦቲዝምን የሚያገኘው የስነ-አዕምሮ ሀኪም ወይም የህክመና ስነ-አዕምሮ ባለሙያ ነው።

የአዕምሮ ዝግመት— ከክሮሞሶሞቹ መካከል አንዱ ላይ የሚያጋጥም ችግር ሲሆን ከሰው ጋር የተፈጥሮ/አብሮ የሚወለድ ሁኔታ ነው። አዕምሮ ዝግመት የተለየ የፊት መልክ፣ እውቀት ውስንነት፣ የእድገት ዝግመት እና ምናልባትም የታይሮይድ ወይም የልብ በሽታ ያመጣል

ምሳሌ፡2: የእድገት ውስንነት ያለበት ባለጉዳይ

የሚከተለው የነርስ ተልዕኮ ስራ የሚያገኝ የእድገት ውስንነት ያለበት ባለጉዳይ ግለታሪክ ነው።

Belinda Greer 38 አመቷ ሲሆን የሚጥል በሽታ፣ የእውቀት ውስንነት እና የጡት እብጠት (ፋይብሮሲስቲክ ጡት) አለባት። ለሲዝር መድሀኒት ትወስዳለች ግን አልፎአልፎ ያንቀጠቅጣታል። ከሌላ ሴት ጋር አብራ በምትኖርበት ቤት ውስጥ የ24 ሰአት የመኖሪያ ድጋፍ አገልግሎት ታገኛለች።

ወ/ሪት Greer ኪኒን በአፏ መውሰድ ትችላለች ግን ስለምትንቀጠቀጥ እና ትክክለኛውን መጠን መውሰዷን ለማረጋገጥ የጆር ጠብታ የሚያደርግላት ሰው ትፈልጋለች። የጆሮ ጠብታው የታዘዘው ለተጠራቀመ የጆሮ ቆሻሻ ነው።

ይህን ስራ ለነርስ ረዳት/የቤት ውስጥ እንክብካቤ ሰጪ ረዳት ለማስተላለፍ ወ/ሪት Greer ተስማምታለች። ቤት ውስጥ ያሉ ሰራተኞች ሰልጥነው ለወ/ሪት Greer የጆሮ ጠብታ የመስጠት ስራ ተሰጥቷቸዋል።

መግቢያ

ዋና-ዋና የሰውነት ስርአቶች

ባለጉዳይዎት በበሽታ፣ በእርጅና፣ በእድገት ውስንነት ወይም አካል ጉዳተኝነት ያስከተለ አደጋ ምክንያት በርካታ ችግሮች ሊያጋጥመው ይችላል፡፡

ይህ የሰውነት ስርአት አጭር መግለጫ እርስዎ መድሀኒት ሲሰጡ ወይም ህክመና ሲያደርጉ የሚጠቅምዎት የጓላ ታሪክ እውቀት ይሰጣል፡፡

በዚህ ትምህርት መጨረሻ ላይ ስለሁኔታው ያለዎትን እውቀት ለማደስ የሚያዩት የማጠቃላያ ሰንጠረዥ አለ፡፡

የሰውነት ስርአቶች ዝርዝር

ዘጠኝ ዋና-ዋና የሰውነት ስርአቶችን እንገልጻለን፡፡

ልብ - ልብ፣ የደም ስር እና ደም

መተንፈሻ - አፍንጫ፣ ጉሮሮ (ፋሪኔክስ)፣ የድመጽ ሳጥን (ላሪኔክስ)፣ የአየር ቧንቧ (ትራኪያ)፣ መተንፈሻ እና ሳንባ

ቆዳ - የተፈጥሮ ሰውነት መሸፈኛ - ቆዳ እና ከስሩ ያሚገኙት እጢዎች፣ ጸጉር እና ጥፍር፡፡

ብልት -ሽንት መሸኛ - ሽንትን በማምረት እና በማስወገድ ስራ ላይ ሚመለከታቸው አካሎች - ኩላሊት፣ ዩሬተር፣ የሽንት ፊኛ፣ ዩሬትራ እና መራቢያ አካላት

ጨጓራ አንጀት - የምግብ አፈጫጭ ስርአት - ጨጓራ፣ ትንሹ አንጀት፣ ትለቁ አንጀት (ሰገራ ያለበት)፣ ጉበት፣ የሀሞት ከረጢት፣ ጣፊያ

ዝግ እጢ - ወደደም ስር ሆርሞን የሚያከማች እጢ

ነርቭ - ጭንቅላት፣ አከርካሪ አጥንት እና ነርቭ

ጅማት-አጥንት - አጥንት እና ጅመት

የስሜት ህዋሳት - አይን፣ ጆር፣ አፍንጫ፣ ምላስ እና መዳሰሻ

ስርአት ማጠቃለያ

ለእያንዳንዱ የሰውነት ስርዓት የሚከተሉትን እንወያያለን፤

- የስርአቱ ዋና-ዋና አካሎች እና ምን እንደሚሰሩ
- የተለመዱ የእርጅና ለውጦች
- የተለመዱ ችግሮች

በዚህ ትምህርት መጨረሻ ላይ ይህ መረጃ በማጠቃላያ ሰንጠረዥ ላይ ተጠቃሏል፡፡

የልብ ስርአት

የልብ ሰርአት ልብ፣ ***የደም ስር***, ***እና*** ደምን***ይይዛል።*** የዚህ ስርአት ዋናው አላማ በሰውነት ውስጥ ላሉ የተለያዩ አካላት ኦክሲጂን ለመስጠት እና ካርቦንዳይ ኦክሳይድ ለማስወገድ ደም ማንቀሳቀስ ነው።

ሰውነት ውስጥ ደም ለመርጨት አብዛኛውን ሀይል የሚሰጠው ልብ ነው።

ልብ አራት ክፍሎች (ወይም መያዣዎች) እና ከ ወይም ወደ ክፍሎቹ የሚያመሩ ትላልቅ የደም ስሮች ያሉት ክፍት የሆነ ጡንቻ ነው።

የደም ስሮቹ በሁሉም ሰውነት ክፍል የሚገኙ ለስላሳ እና የተለያዩ መጠኖች ያሏቸው ተጣጣፊ ቱቦዎች ናቸው።

አርተሪ ኦክስጅን ያለበት ደም ከልብ ወደ ሰውነት ይወስዳል። ካፒላሪ አርተሪ እና ቬይን የሚያገናኝ በጣም ትንሹ ስር ነው። ቬይን ካርቦን ዳይኦክሳይድ የያዘ ደም ወደልብ ይመልሳል።

ደም ኦክሲጅን፣ ካርቦን ዳይኦክሳይድ፣ ጠቃሚ ነገሮች፣ በሽታ ተከላካይ እና መወገድ የለባቸው ነገሮችን ወደ ህዋስ ይወስዳል።

የተለመዱ የእርጅና ለውጦች

ስናረጅ የደም ስሮች ተጣጣፊነታቸውን ይቀንሳሉ። የካፒላሪ ግርግዳ ከእድሜ ጋር የተያያዘ ለውጥ ያሳያል ማለትም በደም እና በህዋስ መካከል የሚደረግ ልውውጥ መቀነስ ያመጣል። ደም በአግባቡ አይረጭም። ይህም ልብ በተኮማተረ እና በተፍታታ ቁጥር አነስተኛ ደም እንዲረጭ ያደርጋል።

ዋና-ዋና የሰውነት ስርአቶች እና ምን እነደሚሰሩ



ሊረዱት የሚገባ ስድስት ዋና-ዋና ችግሮች አሉ። ባለጉዳይዎት ከሚከተሉት ችግሮች አንዱ ካለበት ስለምልከቶቹ፣ የህክመና እቅድ እና እርስዎ በትክክል ማድረግ ያለብዎትን ከቀጣሪዎት/አስተዳደር እና ሀላፊነት ከሚሰጠው RN ጋር ይወያዩበት።

ችግር	ማብራሪያ
1. **ሀይፐርቴንሽን (ከፍተኛ የደም ግፊት)**	የአርተሪ ግርግዳ ላይ ከፍተኛ የደም ግፊት።
ሀይፐርቴንሽን (ዝቅታ የደም ግፊት)	የደም ግፊቱ ለመደበኛው የደም ፍሰት እና ለሰውነት ህዋሶች በቂ ኦክሲጂን ለመስጠት በቂ አይደለም።
2. **በመታፈን የልብ ስራ ማቆም** (CHF)	ልብ በሰውነት ሙሉ ደም ለመርጨት በቂ ጥንካሬ የለውም። ልብ የሚረጨው በጣም በቀስታ ስለሆነ ደም ወደ ቬይን እና የሰውነት አካላት ይመለሳል።
3. **ልብ ድካም** (Myocardial Infarct **ወይም** MI)	የልብ ጡንቻ ውስጥ ያለው ደም ስር ይዘጋል ወይም ይታፈናል፤ ስለዚህ የልብ ጡንቻ ራሱ በቂ ኦክሲጂን ስለማያገኝ ይጎዳል።
4. **የልብ ምት ወይም የሰረብራል ልብ አደጋ** (CVA)	ጭንቅላት ውስጥ ደም ስር ይፈነዳ ወይም ይደፈናል፣ ይህ የጭንቅላት አካላት ደም እንዳያገኙ ያግዳል።
5. **የልብ አሪትሚያ**	የልብ ምት(ፐልስ)ያልተለመደ አመታት አለው።

የአተነፋፈስ ስርአት

የአተነፋፈስ ስርአትኦክሲጂን ከአየር ወደ ደም እንዲገባ እና ካርቦን ዳይኦክሳይድ ከደም ወደ አየር እነዲወጣ የሚያደርጉ የአካላት ስብስብ ነው፡፡

የአተነፋፈስ ስርአት አፍንጫ፣ ጉሮሮ (ፋርኒክስ)፣ የድምጽ ሳጥን (ላሪኒክስ)፣ የአየር ቧቧ (ትራኪያ)፣ መተንፈሻ እና ሳንባን ያካትታል፡፡

ንጹህ አየር ወደ ሰውነት በማስገባት ወደሳንባ ይሄዳል፡፡ ከአየር የሚገኘው ኦክሲጂን በልብ ስርአት አማካኝነት ወደ ሁሉም የሰውነት አካላት ይሄዳል፡፡

ኦክሲጂን ወደ ሰውነት ህዋስ ሲገባ የማያስፈልጉ ጋዞች ተለይተው ወደ ሳንባ ይመለሳሉ፤ ከሳንባ በእስትንፋስ ይወጣሉ፡፡ በአጭሩ ኦክሲጂን በትንፋሽ ወደ ውስጥ ይገባል ካርቦን ዳይኦክሳይድ ይወጣል፡፡

ዋና-ዋና የሰውነት ስርአቶች እና ምን እነደሚሰሩ



የተለመዱ የእርጅና ለውጦች

ስናረጅ ሳንባ ተጣጣፊነቱን ቀንሳል፡፡ በዚህ ለውጥ ምክነያት የመተንፈስ ችሎታ ይቀንሳል፡፡ አረጋዊ ሰው ዋጣት ሰው በጣም እንደሚተነፍሰው አይተነፍስም፡፡

የተለመዱ ችግሮች

አራት ዋና-ዋና የአተነፋፈስ ችግርችን ማወቅ አለብዎት፡፡ ባለጉዳይዎት ከሚከተሉት ችግሮች አንዱ ካለበት ምልክቶቹን፣ የህክምና እቅድ እና ለእርስዎ ትክክለኛ ሀላፊነትን ሀላፊነት ከሚሰጠው RN ጋር ተወያዩ፡፡

ችግር	ማብራሪያ
1. **የላይኛው መተንፈሻ ህመም** (URI)	URI ጉንፋን፣ የሳይነስ ችግሮች፣ ከባድ ሳል፣ የጉሮሮ ህመም፣ የንፍጥ መብዛት፣ የሳይነስ መመረዝ እና ቶንሲልን ያካትታል፡፡ እነዚህን ባክቴሪያ ወይም ቫይረስ ያመጣቸዋል፡፡
2. **ኒሞኒያ**	በባክቴሪያ፣ ቫይረስ ወይም ፈንገስ የመጣ የሳንባ መቆጣት፡፡ ምልክቶቹ ትኩሳት፣ ብርድ-ብርድ ማለት እና ሳልን ካትታል፡፡
3. **ስር-የሰደደ ኦብስትራክሽን ፐልሞናሪ በሽታ** (COPD)	ሳንባ ወይም መተንፈሻ ላይ በሚኖር ችገር ምክንያት፣ እየባሰ የሚሄድ እና የማይድን፣ ሰው ወደ ውጪ እና ወደ ውስጥ መተንፈስ ማይችልበት ሁኔታ፡፡ ስር-የሰደደ ብሮንካይተስ እና ፐልሞናሪ ኢምፋይሴማ የ COPD ምሳሌዎች ናቸው፡፡ የተለመደው መንስኤ ማጨስ ነው፡፡
4. **አስም**	በአካባቢው ላሉ ነገሮች ለምሳሌ አቧራ፣ የአበባ ብናኝ፣ ጭስ እና አንዳንዴ ምግብ የአተነፋፈስ ስርአቱ ላይ በሚያስከትሉት ተጽዕኖ የሚመጣ ስር-የሰደደ በሽታ፡፡ አስም ብዙ ጊዜ የሚፈጠረው በ"አስም ጥቃት" ሰው መተንፈስ ሲቸገር እና አየር ሲያጥረው ነው፡፡

ዋና-ዋና የሰውነት ስርአቶች እና ምን እነደሚሰሩ



የቆዳ ስርአት

ቆዳ ሶስት የተለዩ ተደራቢዎችን ይይዛል፡ ኢፒደርሚስ፣ ደርሚስ እና ሰብኩታኒየስ ተደራቢ።

ኢፒደርሚስ የውጭኛው ተደራቢ ሲሆን የተሰራው በየጊዜው ከሚገፈፍ እና ከሚተካ ወጥ የሆነ እና ጠንካራ ህዋስ ነው። ይህ ተደራቢ ጀርም እዳይገባ እና እርጥበት እንዳይወጣ (የሰውነት ህዋሶች እንዳይደርቁ ውሀን መያዝ) ይከላከላል:: ይህ ተደራቢ ከተከፈተ ባክቴሪያ ውስጥ ያሉትን ህዋሶች ሊያጠቃ ይችላል።

ደርሚስ ከኢፒደርሚስ ተደራው ስር የሚገኝ ነው። ጥቃቅን የደም ስሮች እና የነርቭ መጨረሻዎች ካላቸው አገናኝ ህዋሶች የተሰራ ነው። ሌሎች በርካታ መዋቅሮች አሉት፤

- ሰውነታችንን ሚሸፍነው ትናንሽ ጸጉር የሚያድግበት የጸጉር ቀዳዳዎች።
- ጸጉሩን የሚያለሰልሱት የሰባሲየስ እጢዎች (የቅባት እጢ)።
- የሰውነት ሙቀትን ለመቆጠጠር ሚረዳው የላብ እጢ።
- ህመም፣ ጫና፣ ሙቀት፣ ቅዝቃዜ ወይም መነካካት ሲኖር ወደ አዕምሮ መልዕክተ ሚልኩ የስሜት ተቀባዮች።

ሰብኩታኒየስ ተደራቢ የፋይብሪየስ እና የስብ አገናኝ ህዋስ ጥምረት ነው። ፋይብሪየስ ህዋስ የላይኛውን ቆዳ ተደራቢ ከአጥንት ጡንቻ ጋር ያገናኛል። የስብ ህዋስ ሰውነት ሙቀት ይይዛል፣ ቅዝቃዜ ይከላከላል እና ትርፍ የሀይል አይነት ነው።

የተለመዱ የእርጅና ለውጦች

ስናረጅ ኢፒደርሚስ እየሳሳ፣ እየነጣ እና ብርሀን እያሳለፈ ይመጣል። ለደርሚስ እና ሰብኩታነስ ህዋስ ሚደርሰው የደም አቅርቦት ይቀንሳል።

የሰብኩታነስ ስብ መጠንም ይቀንሳል በተለይ ከንድ እና እግር ላይ፤ በመቀጠል ይሳሳል። ቆዳ ይሸበሸባል፣ መስመር ያወጣል እና ይተጣጠፋል እንዲሁም የሰውነት ሙቀት የመያዝ ችሎታው ይቀንሳል።

ጥፍር ዱልዱም፣ የሚሰባበር፣ ጠንካራ እና ወፍራም ይሆናል። አብዛኛው የጥፍር ለውጦች የሚከሰቱት ለጥፍር ስር የሚደርሰው ደም አቅርቦት ስለሚቀንስ ነው።

የቆዳ እነክብካቤ

ቆዳን ንጹ እና ደረቅ (ግን ድርቀት ያልሆነ) ማድረግ ጤናማ ያደርገዋል፡፡

የባለጉዳይዎትን ቆዳ በመደበኛነት መመርመር አለብዎት፡፡ ሰው አቀማመጥ ከቀየረ እና ጫና ከተወገደ በኋላ ቀይ ሚሆንበትን ቦታ ይመልከቱ፡፡

ቆዳ ከቆሸሸ ወዲያው መጸዳት አለበት፡፡ ሲታጠቡ የቆዳ መቆጣትን እና ከልክ በላይ የደረቀ ቆዳን ለመከላከል ተጨማሪ ጥንቃቄ ያስፈልጋል፡፡ ትኩስ ያልሆነ ግን ሞቅ ያለ ውሀ እና ጠንካራ ያልሆነ ሳሙና ይጠቀሙ፡፡ የቆዳ ድርቀት ለመከላከል ክሬም ወይም ቅባት ይጠቀሙ እነዲሁም ቀዝቃዛ እና ደረቅ አየር ያስወግዱ፡፡

ባለጉዳይዎት ሽንት ፊኛ አለመቆጣጠር ችገር ካበት ሽንቱን የሚመጥ ሞዴስ ወይም ሽንት ጨርቅ ይጠቀሙ እና እርጥበት ከቆዳው ያስወግዱ፡፡ ለቆዳ ጥበቃ ክሬም ወይም ቅባት መጠቀም ይችላሉ፡፡

ቆዳን ከጉዳት መከላከል

የባለጉዳይዎትን ቆዳ ለመጠበቅ ሌላኛው አስፈላጊው መንገድ ቶሎ ቶሎ እንዲገላበጡ እና ጎን እንዲቀያይሩ ማድረግ ነው፡፡ ባለጉዳይዎት ሰውነታቸውን ማንቀሳቀስ የሚችሉ ከሆነ በየ15 ደቂቃው መንቀሳቀስ አለባቸው፡፡

ባለጉዳዮ ጎን እንዲቃያይሩ በሚያግዙበት ወቅት ቆዳቸው ለይ መፋፋቅ እንዳይኖር **ብድግ** ያድርጓቸው፤ እንዳይጎትቷቸው፡፡

አጥንት ያለበት የሰውነት ክፍል ላይ ያለውን ቆዳ እንዳያሹት፡፡ የቀለበት ቅርጽ ያላቸው ትራሶችን አይጠቀሙ፤ ስስ ቦታዎች ላይ የበለጠ ከክብደት የሚመጣ ጉዳት ያመጣል፡፡

የአመጋገብ ምክር

ከፍተኛ የፕሮቲን፣ ካሎሪ እና ፈሳሽ ያለው የተመጣጠነ ምግብ መመገብ ለቆዳ ጤና እና ቁስል ለማዳን በጣም ጠቃሚ ነው፡፡

ባለጉዳዩ የተመጠጣነ ምግብ መመገብ ካልቻለ የምግበነት ይዘት ያላቸው ተጨማሪ ንጥረነገሮች ሊያስፈልጉ ይችላሉ፡፡ ስለባለጉዳይዎት አመጋገብ ምክር ለማግኘት ሀላፊነት ከሚሰጠው RN ጋር ይወያዩ፡፡

የተለመዱ ችግሮች

ስምንት የቆዳ ችግሮችን ማወቅ አለብዎት፡፡ ባለጉዳይዎት ከሚከተሉት ችግሮች አንዱ ካለበት ስለምልከቶቹ፣ የህክመና እቅድ እና እርስዎ በትክክል ማድረግ ያለብዎትን ከቀጣሪዎት/አስተዳደር እና ሀላፊነት ከሚሰጠው RN ጋር ይወያዩበት፡፡

ችግር	ማብራሪያ
1. **ከክብደት የሚመጡ ጉዳቶች (ዴሲቢተስ አልሰር ወይም ረጅም ጊዜ በመተኛት የቆዳ መቆጣት)**	በረዥም ጊዜ የክብደት ጫና ምክንያት የደም ፍሰት እጥረት የህዋስ ጉዳት ያስከተለበት የቆዳ ቦታ፡፡ ከክብደት የሚመጣ ጉዳቶችን መከላከል ይቻላል፡፡
2. **ስታሲስ/ቬነስ አልሰር**	ቬይን ውስጥ ያለው ደም በፍጥነት ወደ ልብ ተመልሶ ባለመገፋቱ ምክንያት ስር-የሰደደ ክፍት ማስተንፈሻ ቦታ፡፡ ጉዳቱ የደረሰበት ቦታ አካባቢ ፈዛዛ ቡኒ ይሆናል፡፡ ይህ ባብዛኛው ሚፈጠረው በእግር ታችኛው ክፍል እና ተረከዝ ነው፡፡
3. **አርተሪ አልሰር**	ወደ እግር ደም ስለማይፈስ በመርገጫ እና የእግር የታችኛው ክፍል ላይ ክብ ክፍት ቦታዎች ያገኛሉ፡፡
4. **ሽፍታ እና መመረዝ**	ሽፍታ ማለት ብዙጊዜ የሚያሳክክ ቆዳ ላይ ያለ አበጥ እና ቀላ ያለ ቦታ ነው፡፡ የቆዳ መመረዞች ሚመጡት ቆዳ ላይ በሚኖር ክፈተት ለምሳሌ በቡጭሪያው በኩል ባክቴሪያ በመግባት ነው፡፡
5. **ቃጠሎ**	በእሳት፣ በጸሀይ፣ በኬሚካል፣ በትኩስ ነገር ወይም በፈሳሽ ወይም በኤሌክትሪክ የሚመጣ የቆዳ ጉዳት፡፡ ቃጠሎ የሚመደበው ቆዳው የተጎዳበትን መጠን መሰረት በማድረግ ነው፡፡ 1ኛ ደረጃ ቃጠሎ ማለት ቆዳው ቀልቶ እና አብጦ እንዲሁም ሳስቷል፡፡ 2ኛ ደረጃ ቃጠሎ ማለት ብዙጊዜ ቁስል ያለው፣ በጣም የቀላ፣ ህመም እና እበጠት ያለው ነው፡፡ 3ኛ ደረጃ ቃጠሎ ማለት በጣም ከባድ እና ቆዳን ሁሉንም ተደራቢዎች የነካ ነው፡፡
6. **የቆዳ ካንሰር/ሌሲዮን**	የቆዳ ላይ የልተለመደ እድገት፡፡ አብዛኛዎቹ ትንሽ፣ ክብ እብጠቶች ወይም የሚደሙ ህመም ያላቸው፣ ቆዳው ላይ ያሉ ግን የማይድኑ ናቸው፡፡ ብዙጊዜ አይራቡም እንዲሁም ይድናሉ፡፡ በጣም አደገኛ የሆነ የቆዳ ካንሰር ሜላኖማ ነው፡፡ ሜላኖማ ቅርጽ አልባ "ያልተለመደ አይነት እብጠት" ወይም የሚለዋወጥ እበጠተው ነው፡፡
7. **የመረቀዘ ቁስል**	ያልዳነ እና ክፍት የሆነ የቀዶ-ጥገና ክፍተት፡፡ ይህ ቀስ-በቀስ በአጠቃላይ መዳን አለበት፡፡
8. **ፊስቱላ**	በተለምዶ የማይያያዙ የሰውነት አካላትን የሚያያይዝ ማንኛውም ያልተለመደ ኣያያዥ፡፡ አንዳንዴ ከፊስቱላ ፍሳሽ ይኖራል ለምሳሌ ሰገራ ወይም ሌላ የሰውነት ፍሳሽ፡፡

ተጨማሪ መስረጃ

የሚከተለው መረጃ ከጀርም ነጻ የሆነ ቁስል ማሸጊያ የመለወጥ ስራ የሚሰሩ ከሆነ ሊያጋጥምዎት የሚችል ከክብደት የሚመጡ ጉዳቶች (ረዥም ጊዜ በመተኛት የሚመጣ የቆዳ መቆጣት) እና ሌላ ቁስሎችን በተመለከተ ተጨማሪ የኋላ ታሪክ ይሰጥዎታል። በዚህ መረጃ ላይ ጥያቄ ካልዎት ሀላፊነት ከሚሰጠው RN ጋር ይወያዩበት።

ከክብደት የሚመጡ ጉዳቶች (ረጅም ጊዜ በመተኛት የቆዳ መቆጣት)

ከክብደት የሚመጣ ጉዳት ማለት ቆዳ ደም ባለማግኘቱ የህዋስ ጉዳት የደረሰበት የቆዳ ቦታ ነው። የሚከተሉት ሲሆን ቆዳው ይጎዳል፤

- ቆዳው ላይ ብዙ እርጥበት ሲኖር
- ድርቀት እና መሰነጣጠቅ
- በሽንት ወይም በሰገራ ምክንያት ቆዳ ሲቆጣ
- በፋትኒያ እና መሰንጠቅ (የጫና እና የፍትኒያ ጥምረት)

ባለጉዳይዎት ከክብደት የሚመጣ ጉዳት ከነበረው ድጋሚ የመመለሱ እድል ይጨምራል።

ለአደጋ ተጋላጭ ቦታዎች

ከክብደት የሚመጣ ጉዳት የሚከሰተው አጥንት ቆዳ እና ህዋስ ላይ ከባድ ግፊት ሚያደርግት እና ከውጫዊ አካል ጋር ጫና በሚኖርበት ቦታ ላይ ነው። የሰውነት አጥንት ክፍሎች ሌላ ሰውነት አካላት፣ ፍራሽ ወይም ወንበር ላይ ጫና ሲኖር ነው። አልጋ ላይ ላሉ ባለጉዳዮች አብዛኛው ከክብደት የሚመጣ ጉዳት የሚፈጠረው፤

- ከወገብ በታች ታችኛው ጀርባ (የጭራ አጥንት ያለበት ቦታ)
- የዳሌ አጥንት
- ተረከዝ

አደጋ ላይ ያሉ ባለጉዳዮች

ወንበር ወይም ተሽከርካሪ ወንበር ላይ ላሉ ባለጉዳዮች ከክብደት የመጣ ጉዳት የሚከሰትበት ቦታ እንደአቀማመጡ ይወሰናል። ከክብደት የሚመጣ ጉዳት ጉልበት፣ ቁርጭምጭሚት፣ የትከሻ መገጣጠሚያ፣ ክርን፣ የራስ ቅል ጀርባ እና አከርካሪ ላይ ይከሰታል።

መንቀሳቀስ የማይችሉ አልጋ ላይ ያሉ ባለጉዳዮች ከ 1–2 ሰአታት በኋላ ከክብደት የሚመጣ ጉዳት ያጋጥማቸዋል። መንቀሳቀስ የማይችሉ ወንበር ላይ ያሉ ባለጉዳዮች ቆዳቸው ላይ የሚያርፈው ክብደት ከባድ ስለሆነ ከዛ ባነሰ ሰአት ውስጥ ከክብደት የሚመጣ ጉዳት ያጋጥማቸዋል። ተደጋጋሚ የአቀማመጥ ለውጥ ከክብደት የሚመጣ ጉዳትን ለመከላከል ያግዛል።

ቆዳ ላይ ያሉ ነርቮች ቆዳ ላይ ያለውን ጫና ለማስታገስ መቼ መንቀሳቀስ እንዳለብን ለሰውነት "ይነግራሉ"። አንዳንድ ስር-የሰደዱ በሽታዎች ለምሳሌ ስኳር በሽታ የሰውን ጫና የመሰማት ችሎታ ይቀንሳሉ።

አልጋ ላይ ላሉ ባለጉዳዮች

ባለጉዳይዎት አልጋ ላይ የዋለ ከሆነ ስፖንጅ፣ አየር፣ ቅባት ወይም ውሀ የያዘ ልዩ ፍራሽ ከክብደት የሚመጣ ጉዳትን ለመከላከል ይረዳል።

የአልጋው ራስጌ ለአጭር ጊዜ ትንሽ ከፍ ማለት አለበት። ጉልበት ወይም ቁርጭምጭሚት እርስ በእርስ እንዳይነካካ ትራስ መደረግ አለበት።

ባለጉዳይዎ በጎን ሲተኛ በቀጥታ በዳሌ አጥንት እንዳያስተኙት። ክብደትን እና ጫናን በእኩሌታ የሚያሰራጭ አኳኋን መመረጥ አለበት:: እንዲሁም ከሰውየው ጀርባ ትራስ ማስገባት ይረዳል።

ባለጉዳዩ ምንም መንቀሳቀስ የማይችል ከሆነ ተረከዝን ከአልጋው ላይ ከፍ ለማድረግ ከእግር ስር ከባት እስከ ቁርጭምጭሚት ድረስ ትራስ መቀመጥ አለበት። በቀጥታ ከጉልበት ጀርባ ትራስ በፍጹም እዳያስቀምጡ።

ወንበር ላይ ላሉ ባለጉዳዮች

ባለጉዳይዎት ወንበር ወይም ተሽከርካሪ ወንበር ላይ ካለ ጫና ለመቀነስ የስፖንጅ፣ ቅባ ወይም አየር ትራስ መጠቀም አለብን።

ክብ ትራስ እንዳይጠቀሙ ምክንያቱም የደም ፍሰትን ይቀንሳሉ እና ህዋስ እንዲያብጥ ያደርጋሉ፤ ይህ ደግሞ ከክብደት የሚመጣ ጉዳት የመከሰት እድሉን ይጨምራል።

ባለጉዳዩ ሳይንቀሳቀስ እንዳይቀመጥ ያድርጉ። በጣንም ትንሽ እንቅስቃሴም ቢሆን ጫና ያለባቸው ቦታዎችን ለመከላከል ይረዳል።

የቆዳ መሰነጣጠቅ

የቆዳ መሰነጣጠቅ አደገኝነት በአብዛኛው የሚገለጸው በደረጃ ነው። በብሄራዊ በክብደት የሚመጣ አልሰር አማካሪ ውይይት (NPUAP) በተገለጸው መሰረት የሚከተለው ሰንጠረዥ ከክብደት የሚመጣውን ህመም በአራት ደረጃዎች ያሳያል።

ደረጃ	ዝርዝር መግለጫ
	**ዝርዝር መግለጫ** • ያልተሰነጠቀ የቆዳ መቅላት፤ ከ 15 – 30 ደቂቃ ወይም ከዛ ባይ የሚቆይ። • ጫና ባለበት ቦታ ላይ መቅላት እና ሙቀት። • በዚህ ደረጃ ላይ ጫናውን በማስወገድ ጉዳቱ ማስተካከል ይቻላል። **ህክምና** • ሰውየው አቀማመጥ እንዲቀይር በማድረግ ጫናውን ማስወገድ። የቀላውን ቆዳ አይሹት በተለይ አጥንት ላይ ከሆነ። • ጫናውን ለመቀነስ ትራስ፣ የበግ ቆዳ፣ የአልጋ ድጋፍ፣ ተረከዝ እና ቁርጭምጭሚት የሚከላከል ወይም መንሳፈፊያ ፍራሽ ይጠቀሙ።
	**ዝርዝር መግለጫ** • በከፊል የወፍራም ቆዳ መሰነጣጠቅ። • ጉዳቱ ቀላል ነው፤ የተላጠ/የተቧጨረ፣ ውሀ የቋጠረ ወይም በትንሹ የተበደሰ ይመስላል። **ህክምና** • ይህ ደረጃ ከታወቀ ጉዳቱን ለማከም እገዛ ለማግኘት የሚከተሉትን ሁሉ ወይም አንዳቸውን ያሳውቁ ቤተሰብ፣ ሀላፊነት የሰጠው RN፣ ሀኪም ወይም ተቆጣጣሪ። • ህክመናው መተላለፍ ያለበት በ RN ነው። • ቁስሉ ከመሸፈኑ በፊት መጸዳት አለበት። ቁስል ለማጽዳት ሀላፊነት የሰጠው RN በሰጠው መመሪያ መሰረት አጠቃላይ አሰራር ይከተሉ።
	**ዝርዝር መግለጫ** • በሙሉ የወፍራም ቆዳ መሰነጣጠቅ። • ሁሉም የቆዳ ተደራቢ መጎዳት። • የቁስል ቅርፊት ይኖረዋል (ወፍራም፣ ደረቅ፣ ቅርፊት የመሰለ)። **ህክምና** • ህክመናው መተላለፍ ያለበት በ RN ነው። • ደረጃ 2 ላይ የተጠቀሙትን መመሪያ ይከተሉ።
	**ዝርዝር መግለጫ** • ሙሉ ውፍረት ያለው ቆዳ በካባዱ ሲጎዳ • ህዋሱ ሞቷል ወይም ጡንቻ፣ አጥንት ወይም ደጋፊ መዋቅሮች (ለምሳሌ ጅማት ወይም መገጣጠሚያ) ተጎድቷል። **ህክምና** • ህክመናው መተላለፍ ያለበት በ RN ነው። • ደረጃ 2 ላይ የተጠቀሙትን መመሪያ ይከተሉ።

የብልት-ሽንት መሸናት ስርአት

የቁስል መዳን ሂደት

የሚድነው በሶስት ዋና-ዋና ሂደቶች ነው፤

1. **የቦታው መቆጣት**፡፡ በርካታ የደም ፍሰት (መቅላት) ካለ ሰውነት ምላሽ ይሰጣል፤ ቦታውን ለመከላከል ልዩ የህዋስ አይነት ይልካል፡፡
2. **የቁስል መዳን**፡፡ የተጎዱ ህዋሶችን ለመተካት አዳዲስ ህዋሶች ማደግ ይጀምራሉ፡፡
3. **የቆዳ መሸፈን**፡፡ ክፍት የሆነ ቁስልን ለመሸፈን ቆዳ ተመልሶ ያድጋል፡፡

ቁስል እርጥበት ሊኖረው ይገባል በቁስሉ ዙሪያ ያው ቆዳ ግን ደረቅ መሆን አለበት፡፡

ቁስል ማጽዳት

አንዳዴ የቁስል መሸፈኛ መቀየር የሞቱ ህዋሶችን ያስወግዳል፡፡ ተጨማሪ የሞቱ ህዋሶችን ማስወገድ ካስፈለገ መስራት ያለበት የጤና ባለሙያ ነው፡፡

ቁስል ማጽዳት ማለት የሞቱ ህዋሶችን እና ፍሳሽ እንዲሁም በቁስሉ ስር የሚገኙ ትርፍ ቁስል መሸፈኛዎችን ማስወገድ ማለት ነው፡፡

ማስወገድ ማለት ኔክሮቲክ (የሞቱ) ህዋሶችን እነዲሁም ከቁስሉ ስር የሚገኙ አንዳንድ ጤናማ ህዋሶችን ማስወገድ ነው፡፡ **ቁስል ማስወገድ የነርስ ረዳት ወይም የቤት ውስጥ እንክብካቤ ሰጪ ረዳት ሀላፊነት አይደለም፡፡**

ወንድ



የብልት-ሽንት መሸኛ ስርአት የሚይዘው፤

- ደምን በማጣራት ሽንት የሚሰሩ ሁለት ***ኩላሊቶች***
- ሽንት ከኩላሊት ወደ ሽንት ፊኛ ሚወስዱ ሁለት ***የሽንት ቱቦዎች (ዩሬተር)***
- እስከሚወገድ ድረስ ሽንት የሚይዝ ***የሽንት ፊኛ***
- የ ***ሽንት ቱቦ (ዩሬትራ)***፣ ሽንት ከሽንት ፊኛ ወደ ውጪ የሚያስተላልፍ
- ወንድ እና ሴት የመራቢያ አካላት፡፡

ይህ ስርአት አራት ዋና-ዋና ስራዎች አሉት፤

1. ደምን ከቆሻሻ ነገሮች ማጽዳት (በርካታ መድሀኒቶች በኩላሊት ውስጥ ያልፋሉ)
2. በሰውነት ውስጥ የሚገኘውን ውሀ መቆጣጠር
3. ሰውነት ውስጥ ያለውን የአሲድ እና ሚነራል መመጣጠን መቆጣጠር
4. መራባት

"ብልት" ማለት የመራቢያ አካላት ናቸው እና "ሽንት" ማለት ሽንትን በመስራት እና በማስወገድ ሚሳተፉ አካላትን ያካትታል፡፡

ሴት

የተለመዱ የእርጅና ለውጦች

ስናረጅ በብልት-ሽንት መሸናት ስርአት ላይ የሚከተሉት ለውጦች ይከሰታሉ፤

- የኩላሊት አወቃቀር ይለወጣል፤ የማጣራት ችሎታቸው ይቀንሳል
- ወደኩላሊት የሚፈሰው ደም ይቀንሳል
- የሽንተ ፊኛው የጡንቻ ጥንካሬ ይቀንሳል
- የሽንት ፊኛው የሚይዘው ሽንት ይቀንሳል
- አንዳንድ ሰዎች የሽንት ፊኛቸውን በሙሉ ባዶ ማድረግ ይሳናቸዋል
- የወንዶች ፕሮስቴት እጢ ሊተልቅ ይችላል፤ ይህ ደግሞ ሽንት መሸናት መጀመር ወይም ሽንት ፊኛቸውን በሙሉ ባዶ ማድረግ አስቸጋሪ ይደረግባቸዋል
- መድሀኒት በኩላሊት ውስጥ ለማለፍ ጊዜ ሊወስድበት ይችላል

እነዚህ ሁሉ ለውጦች በእያንዳንዱ ሰው ላይ ይለያያል።

የተለመዱ ችግሮች

ሶስተ የሽንት ችግሮችን ማወቅ አለብዎት። ባለጉዳይዎት ከሚከተሉት ችግሮች አንዱ ካለበት ስለምልከቶቹ፣ የህክመና እቅድ እና እርስዎ በትክክል ማድረግ ያለብዎትን ከቀጣሪዎት/አስተዳደር እና ሀላፊነት ከሚሰጠው RN ጋር ይወያዩበት።

ችግር	ማብራሪያ
1. **የሽንት ሂደት መስመር መመረዝ** (UTI)	አንድ ወይም ከዛ በላይ የሽንት ሂደት መስመር መመረዝ። ይህ ሁኔታ ሴቶች ላይ የበለጠ የተለመደ ሲሆን ምልክት ለውም።
2. **ሽንተ አለመቆጣጠር**	ሽንት መቆጣጠር አለመቻል።
2. **የተለቀ ፕሮስቴት**	በፊኛው የታችኛው ክፍል እና በብልት የላይኛው ክፍል መካከል የሚገኘው ወንዶች ፕሮስቴት እጢ ሊተልቅ ይችላል። ይህ ሲሆን የሽንት ፍሰትን ሊደፍን ይችላል። ይህ ደግሞ ወንዶች ሽንት መሸናት መጀመር እና ፊኛቸውን በሙሉ ባዶ ማድረግ ያስቸግራቸዋል።

የጨጓራ-አንጀት ስርአት

ዋና-ዋና የሰውነት ስርአቶች እና ምን እነደሚሰሩ

የጨጓራ-አንጀት ስርአት (ሌላ ስሙ የ GI መስመር)በዋናነት ***ጨጓራ*** እና ***አንጀትን*** ያጠቃልላል እንዲሁም በበርካታ ሌሎች አካሎች ይደገፋል። ይህ ስርአት ሰውነት ውስጥ የሚገኙ ህዋሶችን በሙሉ የሚጠቀሙትን ምግብ ይፈጫል። እንደ ሀይል የማያገለግሉት የምግብ ክፍሎች በቆሻሻ መልክ ይወጣሉ።

የመፍጨት ሂደት የሚጀምረው ምግብ **አፍ** ውስጥ ከገባበት ጊዜ ጀምሮ ነው። ምግብ አፍ ውስጥ **በጥርስ** ይታኘካል በቀጣይ በቀላሉ መዋጥ እንዲቻል **በምላስ** ወደ ትናንሽ ቁርጥራጭ ይቀየሩ እና ከምራቅ ጋር ይቀላቀላሉ። ***በጉሮሮ*** አድርጎ ወደ ጨጓራ ይሄዳል። ምራቅ ውስጥ የሚገኙ ኢንዛይሞች ምግብ ለሰውነት ጥቅም ላይ መዋል በሚችልበት መልኩ ማድቀቅ ይጀምራል።

ጨጓራ ምግቡን ይይዝ እና ከተጨማሪ ኢንዛይም ጋር በመቀላቀል መመጠጥ ወደ ሚችልበት ከፊል-ፈሳሽነት ያደቀዋል። በመቀጠል ምግቡ ከጨጓራ ወደ **ትንሹ አንጀትይሄዳል**።

የአንጀት እና ጉበት ኢንዛይሞች ምግቡን የበለጠ ይሰባብሩታል። ***ጉበት*** ስብን ለመፍጨት አስፈላጊ የሆነውን ሀሞት ያመርታል። ሀሞት ***በሀሞት ከረጢት***ውስጥ ይቀመጣል። ሀሞት ስብ ለመፍጨት እና ለመምጠጥ ወደ ትንሹ አንጀት ይገባል። ትንሹ አንጀት በአማካይ ከ 19–20 ጫማ ርዝመት አለው። እንዲሁም***ጣፊያ*** ምግብ የሚፈጭ ጁስ ወደ ትንሹ አንጀት ይረጫል።

የሚፈጩት ጁሶች ምግቡን የትንሹ አንጀት ግርግዳ እንዲመጠው ወደሚያስችል አልሚ ምግብነት ለመፍጨት በጋራ ይሰራሉ። መመጠጥ ያልቻለው ምግብ ትንሹ አንጀት ውስጥ ይቆይ እና በከፊል-ፈሳሽ ሆኖ ወደ **ትልቁ አንጀት** ይሄዳል።

ትልቁ አንጀት ወይም ***ኮሎን*** 5 ጫማ አካባቢ ይሆናል። ትልቁ አንጀት ውስጥ በከፊል-ፈሳሽ ሁኔታ ላይ ያሉ ነገሮች በድጋሚ ወደ ሰውነት ይመጠጣሉ። ***እንቅስቃሴ*** (ሞገድ አይነት የአንጀት እንቅስቃሴ) የቀረውን ጠጣር ነገር (ሰገራ) ወደታችኛው የኮሎን ክፍል ያንቀሳቅሳል። በቂ ሰገራ ከተጠራቀመ በኋላ በፊንጢጣ በኩል ይወጣል፤ አንጀቶች ውስጥ የተመረቱ ጋዞችም አብረው ይወጣሉ። ይህ የሰገራ እንቅስቃሴ ነው።



የተለመዱ የእርጅና ለውጦች

ስናረጅ ምግብን በመፍጨት ስርአት ላይ በርካታ ለውጦች ይኖራሉ። ለውጦቹ በሰዎች መካከል ይለያያል እንዲሁም የሚከተሉትን ያካትታል፡

- የጣዕም መለያ አካት ቁጥር መቀነስ
- የማኘክ አቅም መቀነስ (በጥርስ ቁሻሻ ወይም ጥርስ በማጣት ምክንያት)
- የሚፈጩ ኢንዛይሞች ቁጥር መቀነስ
- የሰገራ ጡንቻ እና ስፊኒክተር (የሰገራ እና ጋዝ መውጣትን የሚቆጣጠሩ፣ ፊንጢጣ ጫፍ ላይ የሚገኙ ጡንቻዎች) ጥናካሬ መቀነስ
- የምግብ እንቅስቃሴ መቀነስ (ምግብ በሚያንቀሳቅሰው አንጀት ውስጥ የጡንቻ እንቅስቃሴ)
- አልሚ ምግብ መምጠጥ መቀነስ
- የጨጓራ አሲድ መጨመር

የተለመዱ ችግሮች

የሚከተሉትን ችግሮች ማወቅ አለብዎት። ምልክቶችን፣ የህክመና እቅድ እና የእርስዎን ትክክለኛ ሀላፊነት ከቀጣሪዎ/አስተዳዳሪዎ እና ሀላፊነት ከሚሰጠው RN ጋር ይወያዩ።

ችግር	ማብራሪያ
ድርቀት	የተለመደ የሰገራ እንቅስቃሴ አለመኖር። ሰጋራ ጠንካራ እና ደረቅ ይሆናል።
የሰገራ ጫና	የሰገራ ጫና ማለት በታችኛው ኮሎን ውስጥ ሰገራ መሰብሰብ እና ለረጅም ጊዜ መያዝ ነው። የሰገራ ጫና መንስኤ፤ ያልዳነ ድርቀት ድርቀት ረዥም የአልጋ ላይ እረፍት የድርቀት የጎንዮሽ ችግር ያለባቸው መድሀኒቶች የባለጉዳዩ የአልሚ ምግብ ይዞታ ተመናምኗል።
ሄሞራይደስ	በትልቁ አንጀት ውስጥ ቫሪኮስ ቬይን ናቸው። ውስጥ ወይም ውጪ ሊሆኑ ይችላሉ ሄሞራይድስ ሚመጣው፤ ሰገራ ለማውጣት ማማጥ ድርቀት ረዥም ጊዜ መቀመጥ ልጅ መውለድ
የጨጓራ-አንጀት አልሰር	የጨጓራ-አንጀት አልሰር በ መስመሩ በየትኛውም ክፍል ላይ የህዋስ መሰንጠቅ ወይም መቆጣት ነው።
ኮሊትስ (የሚቆጠቁጥ ሰጋራ)	የሰገራ ሂደት በቀላሉ ቁጡ ይሆናል እንዲሁም በተለየ ሁኔታ ቶሎ-ቶሎ ሰገራ ይመጣል፤ ይህ ተቅማጥ ያስከትላል።
ድርቀት	ድርቀት ማለት በጣም ብዙ ውሀ ከሰውነት ህዋስ ሲወጣ ወይም ስውነት በቂ ፈሳሽ ካልወሰደ ነው።
GERD (ጋስትሮ-ኤሶፋጊያል ሪፍሌክስ)	"ቃር" የምግብ/አሲድ ቅልቅል በከፊል መፈጨት እና ወደታችኛው የጉሮሮ ክፍል መመለስ ነው።

የዝግ እጢ ስርአት



ዋና-ዋና የሰውነት ስርአቶች እና ምን እነደሚሰሩ

የዝግ እጢ ስርአት የደም ፍሰት ውስጥ ***ሆርሞን*** ከሚያከማቹ እጢዎች የተሰራ ነው፡፡ ሆርሞን የሰውነት እንቅስቃሴን ወይም እድገትን የሚያስተካክል እና የሚቆጣጠር ኬሚካል ነው፡፡ እያንዳንዱ ሆርሞን በሰውት ውስጥ የሚዟዟረው የተለየ መልዕክት ይዞ ነው፡፡ የተወሳሰበ የመልዕክት ስርአት የሆርሞን ክምችትን ይቆጣጠራል፡፡ በጤናማ ሰዎች ላይ የተወሰኑ ሆርሞኖች የሚመረቱት ሲያስፈልጉ ብቻ ነው፡፡

አንዳንድ የዝግ እጢዎች ፒቱታሪ፣ ታይሮይድ እና ፓራታይሮይድ፣ አድሬናሊን ጣፊያ፣ የሴት እንቁላል እና ቴስቴስ ናቸው፡፡

የተለመዱ የእርጅና ለውጦች

በዝግ እጢው ስርአት ላይ የሚያጋጥሙ ለውጦች ከሰው-ሰው ይለያሉ፡፡ የሆርሞን ክምችት መጠን ሊጨምር ይችላል፡፡ የእድሜ አጋማሽ ላይ የወንድ እና የሴት ሆርሞን መቀነስ የተለመደው ምሳሌ ነው (የሴቶች ማረጥ)፡፡

የተለመዱ ችግሮች

ሁለት ዋና-ዋና ችግሮችን ማወቅ አለብዎት። ባለጉዳይዎት ከሚከተሉት ችግሮች አንዱ ካለበት ስለምልከቶቹ፣ የህክመና እቅድ እና እርስዎ በትክክል ማድረግ ያለብዎትን ከቀጣሪዎት/አስተዳደር እና ሀላፊነት ከሚሰጠው RN ጋር ይወያዩበት።

ችግር	ማብራሪያ
1. **የስኳር በሽታ ሜሊተስ**	ጣፊያ ኢንሱሊን የሚባል ሆርሞን ምንም ወይም በቂ አያመርትም። የሰውነትን ህዋሶች ሀይል ለመስጠት ያለኢንሱሊን ሰውነት ስኳርን በአግባቡ መጠቀም አይችልም። በመሆኑም ስኳር (ግሉኮስ) ደም ውስጥ ይቀመጣል እንዲሁም በሽንት ይወጣል።
2. ***ሀይፖታይሮይዲዝም*** **(*አነስተኛ ታይሮይድ*)**	የታይሮይድ እጢ በቂ ታይሮይድ ሆርሞን አያመርትም። ይህ አረጋውያን ላይ የተለመደ ሁኔታ ሲሆን በሰው ሰራሽ ታይሮይድ በቀላሉ ይታከማል

የስኳር በሽታ - ተጨማሪ መረጃ

የስኳር በሽታ በጣም ከባድ የጤና ችግር ነው፤ በአግባቡ ካልታከመ ሌላ ችግሮች ሊያስከትል ይችላል። የሚከተሉት የተወሰኑት የጤና ችግሮች ናቸው፤

- ከፍተኛ የደም ግፊት
- ልብ ድካም
- ስትሮክ
- የአይን ስውርነትን የሚያስከትል የአይን ችግር
- የኩላሊት በሽታ ወይም አለመስራት
- ደካማ የሰውነት ውስጥ ዝውውር እና የመዳን ሂደት
- ህመም
- የጥርስ ችግር
- ተደጋጋሚ መመረዞች
- የህመም ስሜትን አለመስማት እና የጡንቻ ድክመት በተለይ እግር፣ መርገጫ እግር እና እጆች ላይ።

የህመም ስሜትን አለመስማት ከአነስተኛ መመረዝን መከላከል አቅም ጋር ተደምሮ ለእግር ጣት፣ ለመርገጫ እግር እና ለእግር መቆረጥ ዋና ምክንያት ነው።

ዓይነት I የስኳር በሽታ

አይነት I ብዙጊዜ በልጅነት ስለሚጀምር የወጣቶች የስኳር በሽታ ይባላል። ሰውነት ኢንሱሊን አያመርትም ወይም በበቂ መጠን አያመርትም። አይነት I ያለበት ባለጉዳይ ኢንሱሊን በመርፌ መውሰድ አለበት።

አይነት I መንስኤ በአብዛኛው አይታወቅም፤ ግን በዘር፣ ጭንቀት፣ አደጋ ወይም በህመም ሊመጣ ይችላል።

ሁለተኛው አይነት የስኳር በሽታ ሜሊተስ አይነት II በአብዛኛው የሚከሰተው ከ40 አመት በላይ በሆኑ እና የሰውነት

ዓይነት II የስኳር በሽታ

ክብደት ባላቸው ሰዎች እና ደካማ አመጋገብ ባላቸው ሰዎች ላይ ነው፡፡ ሌላው መንስኤ የዘር እና ጭንቀት ነው፡፡ አይነት II በአጠቃላይ ከአይነት I የተሻለ ነው፡፡ የስኳር በሽታ ካለባቸው ሰዎች 90 በመቶው ያለባቸው አይነት II ነው፡፡

ጣፊያ ኢንሱሊንን ያመርታል ግን በቂ ኢንሱሊን አያመርትም ወይም ሰውነት በአግባቡ አይጠቀመውም፡፡ ስለሆነው ከምግብ የሚገኘው ግሉኮስ ደም ውስጥ ይጠራቀማል፡፡

ይህን አይነት የስኳር በሽታ ያለባቸው ሰዎች ብዙ ጊዜ ምግብ በማስተካከል፣ ቶሎ-ቶሎ የደም ምርመራ በማድረግ፣ በስፖርት እና በመድሀኒት በሽታውን ለተወሰነ ጊዜ መቆጣጠር ይችላሉ፡፡ በሽታው ሲጨምር ግን ኢንሱሊን መጠቀም መጀመር አለባቸው፡፡

የደም ስኳር መጠን መለዋወጥ

የደም ስኳር በእያንዳንዳችን ውስጥ ይለያያል፡፡ የደም ስኳር ከ70 ካላነሰ (ሀይፖግሊሴሚያ) ወይም ከ200 ካልበለጠ (ሀይፐርግሊሴሚያ) በስተቀር ችግር የለውም፡፡ እነዚህ ሁለት ጽንፎችን በሚከተለው መረጃ ማወቅ ይቻላል፡፡

መደበኛ የደም ስኳር በ105 እና 110 መካከል ነው፡፡ በ110 እና 200 መካከል ያለ የደም ስኳር ከመደበኛው በላይ ቢሆንም አመጋገብ በማስተካከል እና ስፖርት በመስራት መቆጣጠር ይቻል፡፡

ሀይፖግሊሴሚያ **(ዝቅታ የደም ስኳር - ከ 70mg/dl ያነሰ)**	***ሀይፐርግሊሴሚያ*** **(ከፍተኛ የደም ስኳር - ከ 200mg/dl በላይ)**
ምልክቶች	**ምልክቶች**
መወዛገብ (ብዙግዜ በመጀመሪያ ይታወቃል)	ድካም
ዝለት፣ መንቀጥቀጥ	ብዥታ ያለው እይታ
ረሀብ	ከፍተኛ የሆነ የውሀ ጥም
ድካም	እንቅልፍ-እንቅል ማለት
ራስ-ምታት	በተደጋጋሚ መሽናት
መቆጥቆጥ	ድካም
ቀዝቃዛ እና ላብ ያለው ቆዳ	የቆዳ እና የአፍ ድርቀት
የባህሪይ ለውጥ	ራስ-ምታት
የተጓተተ ንግግር	ማቅለሽለሽ
ብዥታ ያለው እይታ	የጣፋጭ/ፍራፍሬ ሽታ
ራስን መሳት	ቶሎ-ቶሎ መተንፈስ

ማስታወሻ፡- ባለጉዳዩ ራሱን ከሳተ ወዲያው 911 ጋር ይደውሉ!

የእንክብካቤ መርሆዎች

የስኳር በሽታ ያለበት ሰው በሽታውን በቁጥጥር ስር ለማድረግ እና ሌሎች ውስብስብነቶችን ለመቀነስ በርካታ ነገሮችን ማድረግ ይችላሉ። እርስዎ እንክብካቤ ሰጪ እንደመሆንዎት መጠን እነዚህን ነገሮች በማወቅ እና በመርዳት ባለጉዳይን መደገፍ ይችላል።

- ምግብ መበላት ያለበት መካከለኛ መጠን ያለውን ምግብ ቶሎ-ቶሎ ነው። ኢንሱሊን ከተወሰደ በኋላ ምግበ መወሰድ አለበት።
- ሰው የሚወደውን እና የማይወደውን መሰረት በማድረግ ተገቢ የአመጋገብ ሁኔታ በመቅረጽ የስነ-ምግብ ባለሙያ ሊረዳ ይችላል። ባለጉዳይ ሲታመም አመጋገቡን እንዴት ማሻሻል እንዳለበት የስነ-ምግብ ባለሙያ ማማከር ይችላል።
- የባለጉዳዩን የቆዳ ሁኔታ በትኩረት መከታታል በተለይ እግር እና የእግር መርገጫን። እንደ ጠባብ ካልሲ ወይም የሚከረክር ካልሲ የመሳሰሉ የሰውነት ዝውውርን የሚገድቡ ልብሶችን አስወግዱ።
- የሰውነት እንቅስቃሴ የደም ስኳር ላይ ተጽዕኖ እንደሚያመጣ ይወቁ። ባለጉዳዩ አዲስ ወይም ያልተለመደ የአካል እንቅስቃሴ ሲያደርግ በፍጥነት የሚሰራ የስኳር አይነት እንዲይዝ ያድርጉት።
- በአደጋ ጊዜ ሰው መናገር ካልቻለ እጅ ላይ የሚታሰር ወይም አንገት ላይ የሚንጠለጠል ለስኳር በሽታ የህክመና ተቋሚ እርዳታ በፍጥነት ለማግኘት ይረዳል።
- ሀላፊነት በሰጠው RN በተላለፈልዎት መሰረት የግሉኮስ ቁጥጥር ያድርጉ። የደም የግሉኮስ መጠኑን በትክክለኛ ይመዝግቡ።
- የደም ስኳር ማነስ በጣም አደገኛ ሁኔታ ሊሆን ይችላል። ባለጉዳዩ የደም ስኳሩ ዝቅተኛ ሲሆን ምን መደረግ እንነዳለበት ሀላፊነት የሚሰጠው RN፣ እርስዎ እና ባለጉዳዩ እቅድ ሊኖራችሁ ይገባል።

ዋና-ዋና የሰውነት ስርአቶች እና ምን እነደሚሰሩ

የነርቭ ስርአት

የነርቭ ስርአት የሰውነት ስራን ያስተባብራል፣ የሰውነት እና አካባቢ ላይ የሚፈጠሩ ለውጦችን ይቆጣጠረል። ይህ ስርአት ሰውነት እንዲያይ፣
እንዲሰማ፣ እዲያሸት፣ እንዲያጣጥም እና እንዲዳስስ ያስችላል።

አዕምሮ የነርቭ ስርአት ዋነው ተቆጣጠሪ ነው።

አከርካሪ አጥንት የስሜት እና የሞተር ነርቭ ምቶችን ከ እና ወደ አዕምሮ ያስተላልፋል።

አዕምሮ እነዚህን የነርቭ ምቶች ይተረጉም እና
መወሰድ ስላለበት እርምጃ ይወስናል በመቀጠል በሰውነት ሙሉ ለሚገኙ ነርቮች መልሶ
መልዕክት ይልካል።



የተለመዱ የእርጅና ለውጦች

በእርጅና ወቅት የነርቭ ህዋሶች ይቀንሳሉ፡፡ የሚቀንሱት ህዋስ መጠን አዕምሮ ውስጥ ባለው የተለያዩ አካላት ላይ ይለያያል፡፡ አንዳድ ቦታዎች ህዋስ በቀላሉ አይቀንሱም ሌሎች ደግሞ በርካታ ህዋስ በቀላሉ ይቀንሳሉ፡፡

ነርቮች ምልክቶችን በሰውነት ሙሉ እንዲሁም አዕምሮ ውስጥ በጣም በዝግታ ያስተላልፋሉ፡፡

የተለመዱ ችግሮች

አራት የነርቭ ስርአት ችገሮችን ማወቅ አለብዎት፡፡ ባለጉዳይዎት ከሚከተሉት ችግሮች አንዱ ካለበት ስለምልክቶቹ፣ የህክመና እቅድ እና እርስዎ በትክክል ማድረግ ያለብዎትን ከቀጣሪዎት/አስተዳደር እና ሀላፊነት ከሚሰጠው RN ጋር ይወያዩበት፡፡

ችግር	ማብራሪያ
1. **ሲዝር (ማንቀጥቀጥ) እና የሚጥል በሽታ**	**ሲዝር** ማለት በአዕምሮ አንድ ክፍል ላይ የኤሌክትሪክ እንቅስቃሴ በድንገት መጨመር ነው፡፡ ሲዝሩ የተለየ እና ውስን ምልክቶች ኖሮት በአንድ ቦታ ሊከሰት ወይም በሙሉ አዕምሮ ውስጥ ሊሰራጭ ይችላል፤ ይህ ራስን ማሳት እና የሰውነት መንቀጥቀጥን ያስከትላል፡፡ ይህ ድንገተኛ የኤሌክትሪክ እንቅስቃሴ መጨመር በርካታ ምክንያቶች አሉት፤ ከሚጥል በሽታ ጀምሮ እስከ የጭንቅላት ጉዳት ድረስ፡፡ በርካታ አይነት ሲዝሮች አሉ፡፡ **የሚጥል በሽታ** ሲዝር ሊያስከትል የሚችል የማዕከላዊ የነርቭ ስርአት ችግር ነው፡፡
2. **የፓርኪንሰን በሽታ እና ሌሎች የሚያንቀጠቅጡ በሽታዎች**	በቀስታ እየባሰ የሚመጣ የማዕከላዊ የነርቭ ስርአት በሽታ፡፡ የማንቀጥቀጥ ሌላ ምክንያት የአዕምሮ ህመም እና የመድሀኒት የጎንዮሽ ችገር ነው፡፡
3. **አልዛይመር እና ሌላ የመርሳት ችግር**	የአዕምሮ ህዋሶች በመረበሽ የሚመጣ እየባሰ የሚሄድ በሽታ፡፡ የመርሳት በሽታ በርካታ ምክንያቶች አሉት፡፡ አልዛይመር የተለመደው ነው፡፡
4. **የሚረብሽ የአዕምሮ ጉዳት**	የአዕምሮ ጉዳት በሚከተሉት፡ በአደጋ፣ በድበደባ፣ በመውደቅ ወይም የደም እና ኦክሲጅን እጦት ለምሳሌ ውሀ ውስጥ ከመስመጥ ከተረፉ በኋላ ወይም ልብ ለጊዜው መስራት ሲያቆም፡፡

የጡንቻ-አጥንት ስርአት

የጡንቻ የጀርባ እይታ



የጡንቻ-አጥንት ስርአት የሚከተሉትን ይይዛል **አጥንት፣ ጡንቻ፣ ጅማት፣ ቴንዶን እና ካርቲሌጅን ይይዛል**፡፡

ይህ ስርአት ውስጣዊ አካላትን ከጉዳት ይከላከላል፣ ለሰውነት ቅርጽ ይሰጣል፣ አቋም ያስተካክላል እንዲሁም የሰውነት እንቅስቃሴን ያስተካክላል፡፡ አጥንቶች የሚገናኙት ***መገጣጠሚያ*** ላይ ነው፡፡

አንዳንድ **አጥንቶች** ለምሳሌ የክንድ እና የእግር ረዣዥም አጥንቶች ትልቅ እንቅስቃሴዎች ያከናውናሉ፡፡ እጅ፣ ክርን፣ ቁርጭምጭሚት እና የእገር ጣት ላይ ያሉ አነስተኛ አጥንቶች አነስተኛ እንቅስቃሴዎችን ያከናውናሉ፡፡ የራስ ቅል እና የዳሌ አጥንት የመሳሰሉ ጠፍጣፋ አጥንቶች ከጉዳት ይጠብቃሉ፡፡ አከርካሪ አጥንት ለመተጣጠፍ እና አከርካሪን ለመጠበቅ ይረዳል፡፡

አንዳድ ***ጡንቻዎች*** ከአጥንት ጋር የተያያዙ ሲሆኑ እንቅስቃሴው እንዲከናወን ያደርጋሉ፡፡ የልብ እና አንጀት መሳሰሉ ሌሎች ጡንቻዎች በራሳቸው ይሰራሉ፡፡

ጅማት መገጣጠሚያዎችን አገናኝቶ የሚይዝ ጠንካራ ማሰሪያ ነው፡፡ ***ቴንደንስ*** እንዲሁ ጡንቻን ከአጥንት ጋር የሚያገናኝ ጠንካራ ተሳቢ ማሰሪያ ነው፡፡ ***ካርቲሌጅ*** የተረጋጋ እንቅስቃሴ ለማድረግ የሚያስችል መጋጠሚያዎች ላይ የአጥንት መጨረሻ ላይ የሚገኝ ሌላ ጠንካራ ህዋስ ነው፡፡

የተለመዱ የእርጅና ለውጦች

ስናረጅ መገጣጠሚያዎች ይገተራሉ፤ ጡንቻዎች ይደከማሉ፡፡ አጥንት ካልሲየም ስለሚያጣ ይሳሳል እንዲሁም ለመሰበር ተጋላጭ ይሆናል፡፡

ቀስ በቀስ የአከርካሪ ቆሚው ያጥራል እንዲሁም ሰውየው ያጥራል፡፡

ማወቅ ያለብዎት ሶስት ዋና-ዋና ችግሮች አሉ። ባለጉዳይዎት ከሚከተሉት ችግሮች አንዱ ካለበት ስለምልከቶቹ፣ የህክመና እቅድ እና እርስዎ በትክክል ማድረግ ያለብዎትን ከቀጣሪዎት/አስተዳደር እና ሀላፊነት ከሚሰጠው RN ጋር ይወያዩበት።

ችግር	ማብራሪያ
1. **ኦስቴኦፖሮሲስ**	በኦስቴኦፖሮሲስ ላይ ቀስ በቀስ አጥንት በጣም እየሳሳ ይሄድ እና እንደማስነጠስ የመሳሰሉ ቀላል ነገር ሲያጋጥመው ይሰበራል። ኦስቴኦፖሮሲስ በተጨማሪ የታችኛው ጀርባ ህመም፣ የትከሻ መጉበጥ እና ፈጣን የቁመት ማጠር ያመጣል። በአብዛው የሚያጠቃው ድህረ-ማረጥ ላይ ያሚገኙ ሴቶችን ነው።
2. **አርትራይተስ**	አርትራይተስ የመገጣጠሚያዎች መቆጣት ነው፤ ከተለያዩ አይነቶቹ አንዱ ሊሆን ይችላል። የአርትራይተስ ዋና አይነቶች ኦስቲዮአርትረይተስ፣ ሪሁማቶይድ አርትራይተስ እና ጎውት ናቸው።
3. **ስብራት**	ስብራት ማለት የአጥንት ስብራት ነው። ስብራት የሚታከመው የተሰበሩትን አጥንቶች ወደ አንድ በማምጣት መደበኛ ቦታቸውን እንዲይዙ በማድረግ እንዲሁም አጥንቱ ውስጥ በብሎን፣ ማያየዝ ወይም ብረት በማስገባት በጀሶ የስብራቱን አካባቢ እንዳይንቀሳቀስ በማድረግ ነው። እጥንት ለመዳን በርካታ ሳምንታት ይወስዳል። አረጋውየን ለመዳን ረዥም ጊዜ ያስፈልጋቸዋል።

የስሜት ህዋሳት ስርአት

ዋና-ዋና የሰውነት ስርአቶች እና ምን እነደሚሰሩ

ከአምስቱ ስሜት ህዋሳት ሁለቱ አይን እና ጆሮ ናቸው። እንድናይ እና እንድንሰማ ያደርጋሉ። ሰውነት ውስጥ ሌላ የስሜት ህዋሳት አሉ ለምሳሌ አፍንጫ ለማሽተት፣ ቆዳ ለመንካት እና ምላስ ለጣዕም፤ ይህ ትምህርት ግን የሚያተኩረው አይን እና ጆሮ ላይ ነው።

የተለመዱ የእርጅና ለውጦች

ስናረጅ የአይን ብሌን ለብርሀን ምላሽ ሚሰጠው በጣም በዝግታ ነው፣ ቅንድብ ከነበረበት ቦታ ይወርዳል እንዲሁም ጸጉሩ ይሳሳል፣ አይን የእንባ ምርቱን ይቀንሳል።

ጆሯችንም እንዲሁ ድምጽ መስማት ችሎታቸው እና በጆር ቱቦ ውስጥ ያሉት ትናንሽ የጸጉር ህዋሶች ስራቸውን ይቀንሳሉ።

የተለመደ ችገር

ማወቅ ያለብዎት አምስት ዋና-ዋና የአይን ችግሮች እና ሶስት ዋና-ዋና የጆሮ ችግሮች አሉ። ባለጉዳይዎት ከሚከተሉት ችግሮች አንዱ ካለበት ስለምልከቶቹ፣ የህክመና እቅድ እና እርስዎ በትክክል ማድረግ ያለብዎትን ከቀጣሪዎት/አስተዳደር እና ሀላፊነት ከሚሰጠው RN ጋር ይወያዩበት።

ችግር - አይን	ማብራሪያ
1. **ካታራክት**	የአይን ሌንስ አያሳይም።
2. **የአይን ድርቀት**	አይን የውጪውን ክፍል ለማለስለስ በቂ እንባ አያመርትም፤ ስለዚህ ብዙ ጊዜ አይን ውስጥ የሆነ ነገር ለምሳሌ ቆሻሻ ወይም ቅንድብ የገባ አይነት ስሜት ይሰማል። ይህ አይን የውጪውን ክፍል ላይ ጭረት ይፈጥራል።
3. **ማኩላር ዲጀነሬሽን**	የዕይታ መቀነስ እና የአይን መታወር የሚያስከትል አይን ውስጥ የሚከሰት ከባድ ለውጥ። መዳን የማይችል ሂደት ነው።
4. **ግላውኮማ**	የአይን መታወርን የሚያስከትል አይን ውስጥ የተጠራቀመ ፈሳሽ ግፊት። ግላውኮማ በመድሀኒት መቆጣጠር ይቻላል።
5. **የስኳር በሽታ ሬቲኖፓቲ**	የአይን ብሌን የሚነካ ስኳር በሽታ ውስብስብነት፤ ይህ የዕይታ መቀነስ እና የአይን መታወር ያመጣል።
ችግር - ጆሮ	**ማብራሪያ**
1. **መስማት አለመቻል**	በተለያዩ ሁኔታዎች ሊከሰቱ የሚችሉ ማለትም ረዥም ጊዜ ለከፍተኛ ድምጽ መጋለጥን ጨምሮ የተወሰኑ ድምጾችን መስማት አለመቻል።
2. **ቲኒቲስ**	በተለያዩ ሁኔታዎች ሊከሰቱ የሚችሉ ማለትም ረዥም ጊዜ ለከፍተኛ ድምጽ መጋለጥ፣ መመረዝ ወይም አንዳድ መድሀኒቶች የጎንዮሽ ችግሮችን ጨምሮ የጩኸት እና "ጥዝ" የሚል ድምጽ መሰማት
3. **ራስ ማዞር ወይም መንገዳገድ**	በአንዳድ ጆሮ ውስጥ በሚፈጠሩ ውስጣዊ ለውጦች እና በርካታ ሌሎች ምክነያቶች አረጋውያን ላይ የሚታይ የተለመደ ሁኔታ።

የሰውነት ስርአት	ምን ያደርጋል	የስርአቱ አካላት	መደበኛ የእርጅና ለውጦች	ችግሮች
ልብ	ለተለያዩ የሰውነት አካላት ኦክሲጂን ለመስጠት እና ካርቦን ዳይኦክሳይድ ለማስወገድ ደም ማንቀሳቀስ	• ልብ • የደም ስር • አርተሪ፣ ቬይን እና ካፒላሪስ • ደም	• የደም ስሮች ተጣጣፊነታቸውን ይቀንሳል • ልብ በአግባቡ አይረጭም	• ሀይፐር ቴንሽን • ሀይፖቴንሽ • የታፈነ ልብ አለመስራት (CHF) • ልብ ድካም • ስትሮክ ወይም CVA • የልብ አሪትሚያ
አተነፋፈስ	ከአየር ወደደም የኦክሲጂን ዝውውርን መቆጣጠር እና ከደም ወደአየር ካርቦን ዳይኦክሳይድን ማስወገድ	• አፍንጫ • ጉሮሮ (ፋኔክስ) • የድምጽ ሳጥን (ላሪኔክስ) • የንፋስ ቱቦ (ትራኪያ) • መተንፈሻ • ሳንባ	• አነስተኛ የአተነፋፈስ ችሎታ • ዝቅታ የሳንባ የመተጣጠፍ ችሎታ • ሳንባ ውስጥ የኦክሲጂን እና የካርቦን ዳይኦክሳይድ ዝውውር መቀነስ	• የላይኛው የመተንፈሻ መመረዝ (URI) • ኒሞኒያ • ስር-የሰደደ ኦብስትራክቲቭ ፑልሞናሪ በሽታ (COPD) • አስም
ቆዳ	**ኢፒደርሚስ** – ባክቴሪያ እና እርጥበት ይከላከላል፡፡ የሰውነት ህዋሶች እንዳይደርቁ እርጥበት ይይዛል **ደርሚስ** – የጸጉር ቀዳዳ፣ የቅባት እጢ፣ የሰውነት ሙቀት የሚቆጣጠረው የላብ እጢ እና ህመም፣ ግፊት፣ ሙቀት፣ ቅዝቃዜ ወዘተ የሚለዩ የስሜት መልዕክት ተቀባዮችን ይይዛል፡፡ **ሰብኩታነስ ህዋስ** – ፋይብረስ ህዋስ የላይኛውን ቆዳ ተደራቢ ከአጥንት ጡንቻ ጋር ይገናኛል፡፡ የስብ ህዋስ ሰውነት ሙቀት ይይዛል፣ ሙቀት ያመጣጥናል እንዲሁም የሀይል ምነጭ ነው፡፡	3 የቆዳ ተደራቢዎች • ኢፒደርሚስ • ደርሚስ - የጸጉር ቀዳዳ - የቅባት እጢ - ላብ እጢ - የስሜት መልዕክት ተቀባይ • ሰብኩታነስ ህዋስ - ፋይብረስ ህዋስ - የስብ ህዋስ	• ኢፒደርሚስ የሳሳ እና የነጣ ይሆናል • ደርሚስ እና ሰብኩታነስ ህዋስ አነስተኛ ደም ያገኛሉ • ሰብኩታነስ ስብ ይቀንሳል፤ በተለይ ክንድ እና እግር ላይ • ቆዳ ይተጣጠፋል፣ መስመር ያወጣል እና ይሸበሸባል እንዲሁም የሰውነት ሙቀት መቆጣጠር ችሎታ ይቀንሳል • ጥፍር ይዶለዱማል፣ ቶሎ ይሰበራል፣ ይጠነክራል እንዲሁም ይወፍራል	• ክብደት ጉዳቶች (በመተኛት የሚመጣ የቆዳ መቆጣት) • የስታሲስ/ቬነስ አልሰር • አርተሪ አልሰር (የስኳር በሽታ) • ሽፍታ እና መመረዝ • ቃጠሎ • የቆዳ ካንሰር/ሌሲዮን • የመረቀዘ ቁስል • ፊስቱላ
ብልት-ሽንት ለመሸናት	• ቆሻሻ ነገሮችን በሽንት ያስወግዳል • ሰውነት ውስጥ ያለውን ውሀ ይቆጠጠራል • ደም ውስጥ የለውን የኬሚካል መመጣጠን ይቆጣጠራል • መራባት	• ሁለት ኩላሊት • ሁለት ዩሬተር • የሽንት ፊኛ • ዩሬትራ • ወንድ እና ሴት የመራቢያ አካላት	• ወደ ኩላሊት የሚፈሰው ደም ይቀንሳል • የሽንት ፊኛ ጡንቻ መቀነስ • ሽንተ ፊኛ አነስተኛ ሽንት መያዝ • አንዳዶች የሽንት ፊኛቸውን በሙሉ ባዶ ማድረግ አይችሉም	• የሽንት ሂደት መስመር መመረዝ (UTI) • ሽንት አለመቆጣጠር • (ማስጨነቅ፣ ጫና መፍጠር እና ከልክ በላይ መፍሰስ) • የፕሮስቴት መተለቅ

የትምህርት ግምገማ

የሰውነት ስርአት	ምን ያደርጋል	የስርአቱ አካላት	መደበኛ የእርጅና ለውጦች	ችግሮች
የጨጓራ-አንጀት	• ምግብን ሰውነት ውስጥ ያሉ ህዋሶች በሙሉ ወደሚጠቀሙት አይነት መቀየር • በሰገራ አማካይነት ቆሻሻ ነገሮችን ማስወገድ	• አፍ • ጉሮሮ • ጨጓራ • ትንሹ አንጀት • ትለቁ አንጀት (ኮሎን) • ጉበት • የሀሞት ከረጢት • ጣፊያ	• የጣዕም መለያ አካላት ቁጥር መቀነስ • የማኘክ አቅም መቀነስ (በጥርስ ቁሻሻ ወይም ጥርስ በማጣት ምክንያት) • የሚፈጩ ኢንዛይሞች ቁጥር መቀነስ • የሰገራ ጡነቻ ጥናካሬ መቀነስ • አንጀት ውስጥ የምግብ እንቅስቃሴ መቀነስ • አልሚ ምግብ መምጠጥ መቀነስ	• ድርቀት • የሰገራ ጫና • ሄሞራይደስ • የጨጓራ-አንጀት አልሰር • ኮሊትስ (የሚቆጠቁጥ ሰጋራ) • ድርቀት • GERD
ዝግ እጢ	የሰውነት እንቅስቃሴ እና እድገት የሚቆጣጠር ሆርሞን የሚባል ኬሚካል ያመርታል	• ወደ ደም ስር ሆርሞን የሚያጠራቅሙ እጢዎች፡፡ እጢዎች • ፒቱታሪ • ታይሮይድ • ፓራታይሮይድ • አድሬናል • ጣፊያ • የሴት እንቁላል • ቴስቴስ	• የሚመረተው የሆርሞን መጠን መቀነስ	• የስኳር በሽታ ሜሊተስ - አይነት I እና II • ሀይፖታይሮይድዝም
ነርቭ	የሰውነት ስራን ያስተባብራል እንዲሁም በሰውነት እና በአካባቢው ላይ ያለውን ለውጥ ይቆጣጠራል	• አዕምሮ • አከርካሪ አጥንት • ነርቭ	• የነርቭ ህዋሶች ቁጥር መቀነስ • በሰውነት በሙሉ በሚገኙ የነርቭ መጨረሻ ላይ ዝውውር መቀነስ	• ሲዝር እና የሚጥል በሽታ • የፓርኪንሰን በሽታ እና ሌሎች የሚያንቀጠቅጡ በሽታዎች • አልዛይመር እና ሌላ የመርሳት ችግር • የሚረብሽ የአዕምሮ ጉዳት (TBI)
የጡንቻ-አጥንት	ይህ ስርአት ውስጣዊ አካላትን ከጉዳት ይከላከላል፣ ለሰውነት ቅርጽ ይሰጣል፣ አቋም ያስተካክላል እንዲሁም የሰውነት እንቅስቃሴን ያስተካክላል	• አጥንት • ጡንቻ • ጅማት • ቴንደንስ • ካርቲሌጅ	• የመገጣጠሚያዎች መገተር • የጡንቻዎች መድከም • አጥንት ካልሲየም ያጣ እና ለስብራት የበለጠ ተጋላጭ ይሆናል • የአከርካሪ ቋሚ ማጠር	• ኦስቲዮፖሮሲስ • አርትራይተስ • ስብራት

የሰውነት ስርአት	ምን ያደርጋል	የስርአቱ አካላት	መደበኛ የእርጅና ለውጦች	ችግሮች
ስሜት ህዋስ	በእይታ፣ ሽታ፣ መስማት፣ በመንካት እና በመቅመስ በአካባቢው ያለውን አለም ሁኔታ ለሰውነት መረጃ ይሰጣል	• አይን • ጆሮ • አፍንጫ • ቆዳ • ምላስ	**አይን፤** • የአይን ብሌን ለብርሀን ምላሽ ሚሰጠው በጣም በዝግታ ነው • ቅንድብ ከነበረበት ቦታ ይወርዳል እንዲሁም ጸጉሩ ይሳሳል፣ • አይን የእንባ ምርቱን ይቀንሳል **ጆር፤** • ድምጽ የመስማት ችሎታው ይቀንሳል • በጆሮ ቱቦ ውስጥ ያሉት ትናንሽ የጸጉር ህዋሶች ስራቸውን ይቀንሳሉ	**አይን፤** • ካታራክት • ግላውኮማ • ማኩላር ዲጀነሬሽን • የስኳር በሽታ ሬቲኖፓቲ • የአይን ድርቀት **ጆር፤** • መስማት አለመቻል • ቲኒቲስ • ራስን ማዞር ወይም መንገዳገድ

የተግባር ልምምድ

መመሪያዎች፤ በማስታወስ የቻሉትን ያህል ጥያቄ ይመልሱ። በመቀጠል ለቀሪዎቹ ጥያቄዎች በመጽሀፉ ላይ ያሉትን መልሶች ይመልከቱ። ልምመዱን ከጨረሱ በኋላ መልስዎትን በመጽሀፉ የመልስ ቁልፍ ክፍል ላይ ከሚገኙት የመልስ ቁልፎች ጋር ያመሳስሉ።

የሰውነት ስርአት

የልብ	አተነፋፈስ	ቆዳ	ብልት-ሽንተ መሽናት	ስሜት ህዋስ
የጨጓራ-አንጀት	ዝገ እጢ	ነርቭ	ጡንቻ-አጥንት	

1. ከስር ላሉት እያንዳዱ የሰውት አካላት የየትኛው የሰውነት ስርዐቱ ውስጥ እንደሚመደቡ ይግለጹ። ከሰውነት ስርዐት በላይ የተዘረዘረው የሰውነት አካል ነው ስለዚህ ካስፈለገዎት ስርአቶቹን ከአንድ ጊዜ በላይ መጠቀም ይችላሉ።

የሰውነት አካል	የሰውነት ስርአት
አዕምሮ	
ጣፊያ	
ኮሎን	
አፍንጫ	
አፍ	
የላብ እጢ	
አጥንት	
የደም ስር	
አከርካሪ አጥንት	
ኩላሊት	

2. ከላይ ካሉት ሶስተ የሰውነት ስርአቶች ይምረጡ እና ዋና ስራቸውን ይግለጹ።

የሰውነት አካል	ምን ደርጋል?

3. አንዱን የሰውነት ስርአት ይምረጡ እና ለስርአቱ ዋና የሆነውን አካል ይግለጹ፡፡

የስርአት ስም፤ _____

ዋና-ዋና አካላት፤ _____

_____

_____

4. ለእያንዳዱ ችግር የሚከሰትበትን የሰውነት ስርአት ይግለጹ፡፡

ችግር	የሰውነት ስርአት
ኒሞኒያ	
የሽንት ሂደት መስመር መመረዝ	
በመታፈን የልብ ስራ ማቆም	
ድርቀት	
የክብደት ጉዳቶች	
የስኳር በሽታ	
ሲዝር	
ሀይፐርቴንሽን (ከፍተኛ ደም ግፊት)	
ስታሲስ አልሰር	
ሽንተ አለመቆጣጠር	
የአዕምሮ መጠቃት(ስትሮክ)	
ስር-የሰደደ ኦብስትራክቲቭ ፐልሞናሪ በሽታ (COPD)	

5. እርጅና ቆዳ ላይ የሚያመጣው አንዳንድ ተጽዕኖ ምንድን ነው፡፡

_____

_____

_____

_____

_____

_____

መልሶች የሚገኙበት የገጽ ቁጥር ተዘርዝሯል፡፡

1. ከስር ላሉት እያንዳዱ የሰውት አካላት የየትኛው የሰውነት ስርዐቱ ውስጥ እንደሚመደቡ ይግለጹ፡፡ ከሰውነት ስርዐት በላይ የተዘረዘረው የሰውነት አካል ነው ስለዚህ ካስፈለገዎት ስርአቶቹን ከአንድ ጊዜ በላይ መጠቀም ይችላሉ፡፡

የሰውነት አካል	የሰውነት ስርአት
አዕምሮ	**ነርቭ** (ገጽ 48)
ጣፊያ	**የጨጓራ-አንጀት እና ዝግ እጢ - ይህ የሰውነት አካል የሁለቱም ስርአቶች አካል ነው** (ከገጽ 43 - 45)
ኮሎን	**የጨጓራ-አንጀት** (ገጽ 43)
አፍንጫ	**አተነፋፈስ** (ገጽ 35)
አፍ	**የጨጓራ-አንጀት** (ገጽ 43)
የላብ እጢ	**ቆዳ** (ገጽ 36)
አጥንት	**የጡንቻ-አጥንት** (ገጽ 50)
የደም ስር	**ልብ** (ገጽ 33)
አከርካሪ አጥንት	**ነርቭ** (ገጽ 48)
ኩላሊት	**ብልት-ሽንት መሸናት** (ገጽ 41)

2. ከላይ ካሉት ሶስተ የሰውነት ስርአቶች ይምረጡ እና ዋና ስራቸውን ይግለጹ፡፡

የሰጡት መልስ የተሟላ እና ትክክል መሆኑን ለማወቅ ከገጽ 53-55 ላይ ያለውን ትምህርት ግምገማ ይጠቀሙ፡፡

ልብ፤ ለተለያዩ የሰውነት አካላት ኦክሲጂን ለመስጠት እና ካርቦን ዳይኦክሳይድ ለማስወገድ ደም ማንቀሳቀስ

ዝግ እጢ፤ የሰውነት እንቅስቃሴ እና እድገት የሚቆጣጠር ሆርሞን የሚባል ኬሚካል ያመርታል

አተነፋፈስ፤ ከአየር ወደ ደም ኦክስጅንን የማዘዋወር እና ከደም ወደ አየር ካርቦን ዳይኦክሳይድን የማስወጣት ስራን ይቆጣጠራል፡፡

ነርቭ፤ የሰውነት ስራን ያስተባብራል እንዲሁም በሰውነት እና በአካባቢው ላይ ያለውን ለውጥ ይቆጣጠራል

ቆዳ፤ ኢፒደርሚስ - ባክቴሪያ እና እርጥበት እንዳይገባ ይከላከላል፡፡ የሰውነት ህዋሶች እንዳይደርቁ እርጥበት ይይዛል፡፡ **ደርሚስ** - የሚከተሉትን ይይዛል የጸጉር ቀዳዳ፣ የቅባት እጢ፣ የሰውነትን ሙቀት የሚቆጣጠር የላብ እጢ እና ህመም፣ ጫና፣ ሙቀት፣ ቅዝቃዜ ወዘተን የሚለዩ የስሜት መልዕክቶች ተቀባይ፡፡ ***ሰብኩታነስ ህዋስ*** - ፋይብሮስ ህዋስ የላይኛውን ቆዳ ተደራቢን ከአጥንታዊ ጡንቻ ጋር ያያይዛል፡፡ የስብ ህዋስ የሰውነት ሙቀት ይይዛል፣ ሙቀት ያመጣጥናል እንዲሁም የሀይል ምንጭ ነው፡፡

የጡንቻ-አጥንት፤ ውስጣዊ የሰውነት አካሎችን ከጉዳት ይከላከላል፣ ለሰውነት ቅርጽ ይሰጣል፣ አቋም ያስተካክላል እንዲሁም ሰውነት እንዲንቀሳቀስ ያደርጋል፡፡

በብልት-ሽንት መሸናት፤ በሽንት ቆሻሻን ያስወግዳል፣ ሰውነት ውስጥ ያለውን የውሀ መጠን ይቆጣጠራል እንዲሁም ደም ውስጥ ያለውን የኬሚካል መመጣጠን ይቆጣጠራል። መራባት።

ስሜት ህዋሳት፤ በእይታ፣ ሽታ፣ መስማት፣ በመንካት እና በመቅመስ በአካባቢው ያለውን አለም ሁኔታ ለሰውነት መረጃ ይሰጣል።

ጨጓራ-አንጀት፤ ምግብን ሰውነት ውስጥ ያለ ህዋስ በሙሉ መጠቀም ወደሚችለው ንጥረነገር ይለውጣል እንዲሁም በሰገራ መልክ ቆሻሻ ነገሮችን ያስወግዳል።

3. አንዱን የሰውነት ስርአት ይምረጡ እና ለስርአቱ ዋና የሆነውን አካል ይግለጹ።

የሰውነት ስረዐት ስም	ዋና-ዋና አካሎች
ልብ	ልብ የደም ስር አርተሪ፣ ቬነስ እና ካፒላሪስ ደም
አተነፋፈስ	አፍንጫ ጉሮሮ (ፋሪኔክስ) የድምጽ ሳጥን (ላሪኔክስ) የንፋስ ቱቦ (ትራኪያ) መተንፈሻ ሳንባ
ቆዳ	3 የቆዳ ተደራቢ ኢፒደርሚስ ደርሚስ፤ • የጸጉር ቀዳዳ • የቅባት እጢ • የላብ እጢ • የስሜት ህዋሳት መልዕክት ተቀባይ ሰብኩታነስ ህዋስ ፋይብሮስ ህዋስ የስብ ህዋስ
በብልት-ሽንት መሸናት	ሁለት ኩላሊት ሁለት ዩሬተር የሽንት ፊኛ ዩሬትራ የወንድ እና ሴት የመራቢያ አካል
ጨጓራ-አንጀት	አፍ ጉሮሮ ጨጓራ ትንሹ አንጀት ትልቁ አንጀት (ኮሎን) ጉበት የህሞት ከረጢት ጣፊያ

(ወደሚቀጥለው ገጽ የቀጠለ)

የሰውነት ስረዐት ስም	ዋና-ዋና አካሎች
ዝግ እጢ	ፒቱታሪ ታሮይድ ፓራታይሮይድ አድሬናሊ ጣፊያ የሴት እንቁላል ቴስቴስ
ነርቭ	አዕምሮ አከርካሪ አጥንት ነርቭ
ጡንቻ-አጥንት	አጥንት ጅማት ካርቲሌጅ ጡንቻ ቴንዶን
ስሜት ህዋስ	አይን አፍነጫ ምላስ ጆሮ ቆዳ

4. ለእያንዳዱ ችግር የሚከሰትበትን የሰውነት ስርአት ይግለጹ፡፡ የገጽ ቁጥር ጥቆማዎች በቅንፍ ተቀምጠዋል፡፡

ችግር	የሰውነት ስርአት
ኒሞኒያ	አተነፋፈስ (ገጽ 35)
የሽንት ሂደት መስመር መመረዝ	በብልት-ሽንት መሸናት (ገጽ 41)
በመታፈን የልብ ስራ ማቆም	ልብ (ገጽ 33)
ድርቀት	ጨጓራ-አንጀት (ገጽ 41)
የክብደት ጉዳቶች	ቆዳ (ገጽ 36)
የስኳር በሽታ	ዝግ እጢ (ገጽ 45)
ሲዝር	ነርቭ (ገጽ 48)
ሀይፐርቴንሽን ((ከፍተኛ የደም ግፊት)	ልብ (ገጽ 33)
ስታሲስ አልሰር	ቆዳ (ገጽ 36)
ሽንተ አለመቆጣጠር	በብልት-ሽንት መሸናት (ገጽ 41)
ስትሮክ ወይም CVA	ልብ (ገጽ 41)
ስር-የሰደደ ኦብስትራክቲቭ ፐልሞናሪ በሽታ (COPD)	አተነፋፈስ (ገጽ 35)

5. እርጅና ቆዳ ላይ የሚያመጣው ተጽዕኖ ምንድን ነው? (ገጽ 36)

ስናረጅ ኢፒደርሚስ እየሳሳ፣ እየነጣ እና ብርሀን እያሳለፈ ይመጣል። ለደርሚስ እና ሰብኩታነስ ህዋስ የሚደርሰው የደም አቅርቦት ይቀንሳል።

የሰብኩታነስ ስብ መጠንም ይቀንሳል በተለይ ክንድ እና እግር ላይ፤ በመቀጠል ይሳሳል። ቆዳ ይሸበሸባል፣ መስመር ያወጣል እና ይተጣጠፋል እንዲሁም የሰውነት ሙቀት የመያዝ ችሎታው ይቀንሳልይ።

ጥፍር ዱልዱም፣ የሚሰባበር፣ ጠንካራ እና ወፍራም ይሆናል። አብኛው የጥፍር ለውጦች የሚከሰቱት ለጥፍር ስር የሚደርሰው የደም አቅርቦት ስለሚቀንስ ነው።

እዚህ ጋር መጽሀፉን ማንበብ ያቁሙ ።

የባለጉዳይ እንክብካቤ እና የሰውነት ስርአት የሚለውን የቪድዮ ክፍል ይመልከቱ።

ወደ ድህረ-ገጽ የሚወስደውን መገናኛ ይከተሉ። በትምህርት መደዳ ስር የነርስ ተልዕኮ ወደሚለው ያውርዱ። በመረጡት ቋንቋ ላይ ይጫኑ። ማየት የሚፈልጉትን ቪድዮ ይምረጡ። www.dshs.wa.gov/altsa/training/dshs-curriculum-available**።**

የመድሀኒት አሰጣጥ

አጭር መግለጫ እና ቅድመ-እይታ

ይህ ትምህርት ከተሻሻለውመሰረታዊ እንክብካቤ የመስጠት ትምህርት ውስጥ ከመድሀኒት ጋር ስለመስራት ያሉትን መሰረታዊ ነገሮች ይገመግማል። የመድሀኒት አሰጣጥ ተልዕኮን ለመቀበል የሚያስፈልጉትን መስፈርቶች በመማር ያንን ጽንሰ-ሀሳብ ያዳብሩታል።

ለባለጉዳይ መድሀኒት ሲሰጡ በጣም አስፈላጊ ሚና ይጫወታሉ። የጎንዮሽ ችግሮችን የሚያዩ እና ችግሮቹም ከተፈጠሩ በፍጥነት እርምጃ ሚወስዱ ቁልፍ ሰው እርስዎ ነዎት። እንዲሁም ባለጉዳይዎት መድሀኒት አልወስድም ካለ ወይም ስህተት ካገኙ ምነ ማድረግ እንዳለበዎት ማወቅ አለብዎት።

የትምህርት አላማዎች

ይህን ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ፡

- የሚከተሉትን ለማድረግ ከመድሀኒት ጋር ስለመስራት ያሉትን መሰረታዊ ነገሮች በአጭሩ ማጠቃለል፤
  - የ **መድሀኒት** መብራራት።
  - የመድሀኒቶችን አካሄድ መግለጽ።
  - በ **መድሀኒት ረዳት** እና **በመድሀኒት አሰጣጥ** መካከል ያለውን ልዩነት መረዳት።
  - ስድስቱን የመድሀኒት አሰጣጥ ትክክለኛ ሁኔታዎች መግለጽ።

- የመድሀኒት አሰጣጥ ሂደቱን ማብራራት፤ የሚከተሉትን ጨምሮ፤
  - በመድሀኒት አሰጣጥ ላይ የባለጉዳዩ መብት።
  - መድሀኒት ሲሰጡ መተግበር ያለብዎት ጥሩ ልምድ።
  - የጎንዮሽ ችግሮችን እነዴት እንደሚለዩ፣ የጎንዮሽ ችግሮችን መቼ እንደሚከታተሉ እና የጎንዮሽ ችግሮች ሲፈጠሩ ምን እንደሚደረግ።
  - መድሀኒት አሰጣጥ እንዴት እንደሚመዘግቡ።
  - በፍጹም የማይፈቀዱ ስራዎች።

- የሚከተሉት ሲሆኑ ምን እንደሚደረግ ያብራሩ፤
  - መድሀኒት ሲረሳ።
  - ባለጉዳዩ መድሀኒት አልወስድም ሲል።
  - ስህተት ሲሰሩ ወይም ስህተት ሲያገኙ።

- መድሀኒት እነዴት እንደሚቀመጥ እና እንደሚወገድ ይግለጹ።

የመድሀኒት መሰረታዊ ነገሮች

መድሀኒት ምንድን ነው?

መድሀኒት ማለት በሰው ሰውነት ውስጥ ያለውን የኬሚካል እንቅስቃሴ ሚለውጥ ማንኛውም ድብልቅ ነው፡፡

ይህ መለት መድኒት ሰውነት ውስጥ ወይም ሰውነት ላይ የተለያዩ ነገሮችን በማድረግ ለምሳሌ እርጥበታማ/ንፈጥ ያለበትን አፍንጫ ማሻል፣ ሽፍታ ማዳን፣ ትኩሳት መቀነስ ወይም ጀርም በመግደል ተጽዕኖ ይፈጥራል፡፡

የመድሀኒት አይነቶች

ሁለት አይነት መድሀኒቶች አሉ፡

- **የጽሁፍ መድሀኒቶች** - እነዚህ መድሀኒቶች መሸጥ የሚችሉት በማዘዣ እንደሆነ በህግ ተደንግጓል፡፡
- **የጽሁፍ ያልሆኑ መድሀኒቶች** - እነዚህ ከመሸጫ መደርደሪያ (OTC) ላይ ወይም ያለማዘዣ የሚገዙ መድሀኒቶች ናቸው፡፡ የጀርባ ህመም፣ የሚቆጠቁጥ ጉሮሮ፣ የሆድ ህመም፣ ሳል፣ ጉንፋን፣ ድርቀት እና አጠቃለይ የሆኑ ህመሞችን የመሳሰሉ ሁኔታዎችን የሚያሽሉ ናቸው፡፡

ማዘዣ

ማዘዣ ማለት የአጠቃቀም የተለየ መመሪያ ያለው ለመድሀኒት ወይም ፈቃድ ባለው የጤና እንክብካቤ ባለሙያ የሚሰጥ የህክምና ትዕዛዝ ነው፡፡ ማዘዣ መስጠት የሚችሉ የጤና እንክብካቤ ባለሙያዎች ሀኪም፣ ነርስ፣ የሀኪም ረዳት ወይም የጥርስ ሀኪም ናቸው፡፡

የጽሁፍ መድሀኒቶች አስፈላጊ ስብስብ ቁጥጥር የሚደረግባቸው ንጥረ ነገሮች ናቸው፡፡ **ቁጥጥር የሚደረግባቸው ንጥረ ነገሮች** አለአግባብ ለመጠቀም እና ለሱስ ከፍታ አቅም የላቸው መድሀኒቶች ናቸው፡፡

ቁጥጥር የሚደረግበት ንጥረ ነገር

ያለአግባብ የመጠቀም አደጋ ምክንያት ቁጥጥር የሚደረግባቸው ንጥረ ነገሮች ማዣዣ በምን ያህል ጊዜ ድጋሚ እንደሚሰጥ ቁጥጥር ይደረጋል፡፡ ምሳሌዎች፡-

- ናርኮቲክ፡፡
- የድብርት መድሀኒቶች፡፡
- አነቃቂ መድሀኒቶች፡፡
- ሳይኮትሮፒክ መድሀኒቶች፡፡

ቁጥጥር የሚደረግባቸው ንጥረ ነገሮች በአምስት ቡድን ወይም ፕሮግራም ይመደባሉ፤ እያንዳንዱ ፕሮግራም በድጋሚ ማዘዣ የመስጠት ገደቡን የሚያብራራ የራሱ ልዩ ደንብ አለው፡፡ በ1970 የወጣው አጠቃላይ የመድሀኒት አላግባብ መጠቀም መካለከል እና ቁጥጥር ህግ ቁጥጥር ለሚደረግባቸው ንጥረ ነገሮች ደንቦች አውጥቷል፡፡

ቫይታሚን፣ ማሟያ መድሀኒቶች እና መፍትሄዎች

እባክዎ ያስተውሉ፡ ቫይታሚን፣ በትንፈሽ ሚሰጡ ንጥረ ነገሮች፣ የቅጠላ-ቅጠል መፍትሄዎች፣ ምግብ-ተኮር መፍትሄዎች እና የቤት ውስጥ መፍትሄዎች ሁሉ መድሀኒቶች ናቸው፡፡

ከመሸጫ መደርደሪያ(OTC) ላይ የሚገዙ መድሀኒቶች የተወሰነ ሁኔታን ለማዳን ጥቅም ላይ የሚውል ከሆነ የመድሀኒት መስጠት ስራው መተላለፍ አለበት፡፡ ግን እንደመከላከያ ሚያገለግል ከሆነ የመድሀኒት መስጠት ስራው መተላለፍ የለበትም ለምሳሌ "ሰው ሰራሽ እንባ" አይን ድርቀትን ለመከላከል አገልግሎት ላይ ሲውል፡፡

እውቅና ባገኘ ሁኔታ ውስጥ ባለጉዳይ ማንኛውም አይነት መድሀኒት ማለትም የጽሁፍ (በማዘዣ)**ወይም** ያለጽሁፍ (ከመደርደሪያ ላይ የሚገዛ መድሀኒት) **የሚወስድ ከሆነ** እና መድሀኒቱን ወደአፍ ማስገባት ወይም ሰውነቱ ላይ ማድረግ ካልቻለ ወይም መድሀኒት እንደሚወስድ ካላወቀ**እርስዎ መድሀኒቱን የሚሰጡት ሀላፊነት ከሚሰጠው RN ስራውን እንዲሰሩ ሀላፊነት ከተሰጥዎት ብቻ ነው**፡፡

ሁሉም መድሀኒቶች ከአንድ በላይ ስም አላቸው፡፡ በአብዛኛው ***አጠቃለይ ስም*** እና ***የምርቱን ስም***ማወቅ አለብዎት፡፡

- አጠቃለይ ስም - መድሀኒቱ በምግብ እና የመድሀኒት አስተዳደር (FDA) ከመጽደቁ በፊት በአምራቹ የሚሰጥ ስም ነው፡፡ ስለመድሀኒቱ ኬሚካላዊ ውህደት የተወሰነ መረጃ ይሰጣል፡፡ አንዳንድ ምሳሌዎች፤
  1. አሴታሚኖፌን
  2. ኢቡፕሮፊን
  3. ፉሮስሚድ
- የምርት ስም - እንዲሁም የብራንድ (ምልክት) ስም ይባላል፡፡ አምራቹ ምርቱን ገበያ ላይ ሲሸጠው የሚጠቀምበት ስም ነው፡፡ የስሙ ባለቤት አምራቹ ነው፤ ስሙን ሌላ ድርጅት ሊጠቀመው አይችልም፡፡

  የሚከተሉት መድሀኒቶች ለእርስዎ እና ለአጠቃላይ ህዝቡ የተለመዱ የመድሀኒት ስሞች ናቸው፤
  1. ታይሌኖል (አሴታሚኖፌን)
  2. ሞትሪን ወይም አድቪል (ኢቡፕሮፌን)
  3. ላሲክ (ፉሮስሚድ)

የመድሀኒት ስሞች

መድሀኒቶች ብዙጊዜ በርካታ የምርት ስም (የብራንድ ስም) ሲኖራቸው አጠቃለይ ስም ግን አንድ ብቻ አላቸው፡፡

- RN የመድሀኒት አሰጣጥ ስራ ለእርስዎ ሲሰጥዎት መድሀኒቱን ሁለታችሁም ምን ብላችሁ እንደምትጠሩት (በአጠቃላይ ወይስ በብራንድ ስሙ) መስማማት አለባችሁ፡፡ ይህ መድሀኒትን ከመሳሳት ይከለከላል፡፡
- የመድሀኒት መሀደሩ ላይ ያለው የመድሀኒት ስም በመድሀኒቱ እቃ ላይ የተጻፈው ስም ቢሆን ጥሩ ነው፡፡

መድሀኒት ምን ያደርጋል?

መድሀኒት ሶስተ ዋና-ዋና ነገሮችን ደርጋሉ፤

1. ለህመም መፍትሄ መስጠት፣ ማዳን ወይም መቆጣጠር
2. የስቃይ ምልክቶችን ማስታገስ
3. በሽታ መከላከል።

መድሀኒት ሲወሰድ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ መንስኤዎች

መድሀኒት ሰውነት ውስጥ ካለው ህዋስ ጋር በመቀላቀል ህዋሱ የሚሰራበትን መንገድ ይቀይራል። መድሀኒት የተለያዩ ሰዎች ላይ የተለያየ ተጽዕኖ አለው።

ሰዎች ተመሳሳይ መድሀኒት ሲሰጣቸው አነስተኛ ልዩነት ሊያስከትሉ የሚችሉ ስድስት የሰው ባህሪያት አሉ። ባህሪያቶቹ፤

1. ዕድሜ
2. ክብደት
3. ጾታ
4. የዘር ሀረግ
5. አካላዊ ሁኔታ
6. ስሜታዊ ሁኔታ

ለመድሀኒት የሚሰጠው ምላሽ ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ሌሎች መንስኤዎች የሚከተሉት ናቸው፤

የመድሀኒት አሰጣጥ መንገድ

መድሀኒቱ የተሰጠበት ሰአት

የተሰጠው መድሀኒት ቁጥር

የመድሀኒቱ ልኬት መጠን

የውጪ ሙቀት ወይም ጨኸት የበዛበት አካባቢ (ለምሳሌ በራስ ምታት ህመም) የመሳሰሉ አካባቢያዊ ሁኔታዎች

የመድሀኒት የጎንዮሽ ችግሮች

መድሀኒት ለባለጉዳይ የሚሰጠው የታሰቡ አዎንታዊ ጥቅም እንዲሰጥ፣ ጤናን እንዲያሻሽል፣ ህመም እንዲቀንስ፣ በሽታን ወይም ችግርን እንዲቆጣጠር ወይም የህመም ምልክቶችን እንዲቀንስ ነው።

መድሀኒት የህክምናው አላማ አካል ያልሆነ ሰውነት ላይ ያልታሰበ ውጤትም ይኖረዋል። **የጎንዮሽ ችግሮች** ይባልል።

የጤና ባለሙያው መድሀኒት ሲያዝ ሊያጋጥሙ የሚችሉ የጎንዮሽ ችግሮችን ከግንዛቤ ማስገባት አለበት።

ያረጁ ወይም የተወሰነ በሽታ(ዎች) ያለባቸው ሰዎች

የበለጠ የጎንዮሽ ችግሮች ያጋጥማቸዋል።

የመድሀኒት መቀላቀልም እንዲሁ የማይፈለግ የጎንዮሽ ችግሮች ያመጣል (ገጽ 67ን ይመልከቱ)።

የሚያዘው ባለሙያ ባለጉዳዩ ሚወስዳቸውን መድሀኒቶች በሙሉ ማለትም የ OTC መድሀኒቶች፣ ቪታሚንስ እና የቅጠላ-ቅጠል ማሟያ መድሀኒቶችን ጨምሮ ማወቅ አለበት።

የተለመዱ የጎንዮሽ ችግሮች

አንዳንድ የተለመዱ የጎንዮሽ ችግሮች ዝርዝር ከስር ይገኛሉ። አንዳዶቹ የጎንዮሽ ችግሮች ከባድ ሊሆኑ ይችላሉ። የትኛውን የጎንዮሽ ችግር መከታተል እና ማሳወቅ እንዳለብዎት ሀላፊነት የሚሰጠውን RN ይጠይቁ።

የመድሀኒት የተለመዱ ጎንዮሽ ችግሮች	
ስጋት እና ጭንቀት	መቆጥቆጥ
ጥቁር (የከረመ) ሰገራ	ማሳከክ
ብዥታ ያለው እይታ	ቀላል ራስ ምታት
የጡት መጠጠር	የምግብ ፍላጎት ማጠት
የመተንፈስ ችግር	ዝቅተኛ ደም ግፊት
መበለዝ	የወር-አበባ መዛባት
የማቃጠል ስሜት	አፍንጫ መደፈን
የደረት ህመም	ማቅለሽለሽ
መወዛገብ	ጭንቀት
ድርቀት	ፈጣን የልብ ምት (ያልተለመደ/ፈጣን የልብ ምት)
የሚሸመቅቅ	ሽፍታ
ድብርት	እረፍት ማጣት
ተቅማጥ	ጆሮ ውስጥ የጩኸት ድመጽ
ራስ ማዞር	ላብ
እንቅልፍ-እንቅል ማለት	ውጋት
የአፍ፣ የአፍንጫ፣ የቆዳ ድርቀት	ቅጥቅጥ
ቆዳ ላይ ውሀ መቋጠር (እብጠት)	መንቀጥቀጥ
ድካም ወይም ያልተለመደ ድካም	የሆድ መረበሽ
ትኩሳት	በተደጋጋሚ ሽንት መሽናት
የውስጥ ሙቀት ወይም የቆዳ መቅላት እና መሞቅ	የሽንት ቀለም መለወጥ
ራስ-ምታት	ሽንት አለመሽናት
ቃር	የማህጸን ፈሳሽ
ስርቅታ	ድካም
የቆዳ መቆጣት ወይም ሽፍታ	ክብደት መጨመር
የወሲብ ድክመት	

የመድሀኒት መቀላቀል

ሁለት ወይም ከዛ ባለይ መድሀኒት ሲሰጥ የመድሀኒቶች**የመቀላቀላቸው እድል** ከፍተኛ ነው።

የመድሀኒት መቀላቀል ማለት ቀደም ብሎ፣ በተመሳሳይ ሰአት ወይም ሌላ መድሀኒት ከተሰጠ በኋላ የተሰጠ መድሀኒት የአንዱን ወይም የሁለቱንም መድሀኒት ውጤት/ተጽዕኖ ሲቀይረው ነው። የአንዱን ወይም የሁለቱንም መድሀኒት ውጤት/ተጽዕኖ ሊጨምር ወይም ሊቀንስ ይችለል። ሁለቱም መድሀኒቶች ሊቀላቀሉ እና የማይፈለግ የጎንዮሽ ችግር ሊያስከትሉ ይችላሉ።

በርካታ መድሀኒት በተወሰደ ቁጥር የመድሀኒት መቀላቀል የመፈጠሩ እድል ይጨምራል።

አለርጂ

አለርጂ የሚፈጠረው የሰውነት በሽታ የመከላከል ስርአት ማሳከክ፣ ማበጥ፣ የጡንቻ መኮማተር የሚያስከትሉ እና ጉሮሮ እና አየር መተላለፊያ የሚያጠቡ ኬሚካሎችን ሰውነት እንዲያመርት በማድረግ ለመድሀኒት ምላሽ ሲሰጥ ነው። ምላሹ ከመካከለኛ እስከ ህይወትን አደጋ ላይ እስከመጣል ይደርሳል።

የመድሀኒት አሰጣጥ መንገዶች

ሰባት መንገዶች

መድሀኒት ለባለጉዳይ በበርካታ የተለየዩ መንገዶች ወይም ዘዴዎቸ ይሰጣል፡፡ ዘዴዎቹ መንገዶች ይባላሉ፡፡ እነዚህ ሰባት የመድሀኒት አሰጣጥ መንገዶች ናቸው፡፡

1. በአፍ	በአፍ በመውሰድ መዋጥ
2. በምላስ	ከምላስ ስር በማስቀመጥ
3. ወቅታዊ	በቀጥታ ቆዳ ላይ ወይም የሙከስ ሜምብሬን ላይ መስጠት
4. በፊንጢጣ	ፊንጢጣ ውስጥ በማስገባት
5. በማህጸን	ማህጸን ውስጥ በማስገባት
6. በትንፋሽ	በአፍነጫ ወይም ጉሮሮ በትንፋሽ ወደ ውስጥ የሚወሰድ ወይም የሚረጭ
7. መርፌ	ቆዳ ስር በሚገኝ ጡንቻ ወይም በደም-ስር ውስጥ በመርፌ ማስገባት

ከስር የሚገኘው ሰንጠረዥ እያንዳንዱን የመድሀኒት አሰጣጥ መንገድ ያብራራል፡፡

ማብራሪያ

መንገድ	ማብራሪያ
በአፍ	የአፍ መድሀኒቶች በአፍ ተወስደው በውሀ ወይም ከውሀ ጋር ይዋጣሉ፡፡ አፍ መድሀኒቶች በፈሳሽ፣ ሹሮፕ፣ ዱቄት፣ ኪንን ወይም መድሀኒት በሚይዝ ከረጢት መልኩ ይሰራሉ፡፡ መድሀኒቱ በጨጓራ እና በአንጀት መስምር አድርጎ ደም ስር ውስጥ ይመጠጣል፡፡ መድሀኒት ወደ ሰውነት ህዋስ የሚደርስበት ቀስተኛ መንገድ ነው፡፡
በምላስ	በምላስ የሚወሰድ ማለት መድሀኒቱን ከምላስ ስር በማስቀመጥ በባለጉዳዩ ምራቅ ይሟሟል፡፡ መድሀኒቱ በአፍ የውስጠኛው ተደራቢ በሆነው በሙከስ ሜምብሬን ይመጠጣል፡፡ ባለጉዳዩ ኪኒኑን መዋጥ የለበትም ወይም መድሀኒቱ እስኪሟሟ ድረስ ምግብ እና መጠጥ መውሰድ የለበትም፡፡ በምላስ የሚሰጡ መድሀኒቶች በአፍ ከሚሰጡት መድሀኒቶች ይበልጥ በፍጥነት ይመጠጣሉ፡፡
ወቅታዊ	ወቅታዊ መድሀኒት አሰጣጥ መድሀኒት በቀጥታ ቆዳ ወይም ሙከስ ሜምብራን ላይ መስጠት ነው፡፡ በወቅታዊ አሰጣጥ የሚሰጡ መድሀኒቶች የተቆጡ ህዋሶችን ለማስታገስ ወይም አካባቢያዊ መመረዞችን ለመከላከል ወይም ለማዳን የተቀረጹ ናቸው፡፡ ወቅታዊ መድሀኒት በክሬም፣ ሎሽን፣ ቅባት፣ ፈሳሽ፣ ዱቄት፣ የሚለጠፍ እና በጆሮ እና የአይን ጠብታ መልክ ይገኛሉ፡፡
በፊንጢጣ	በፊንጢጣ አሰጣጥ ማለት በሰፖሲቶሪ ወይም ኢነማስ መልክ የሚገኝ መድሀኒትን በፊንጢጣ ማስገባት ነው፡፡ በፊንጢጣ መስመር ላይ መድሀኒቱ የሚመጠጠው በዝግታ እና ባልተለመደ ሁኔታ ነው፡፡ ይህ መንገድ የሚያገለግለው አንዳንዴ ባለጉዳዩ መድሀኒት በአፍ መውሰድ ካልቻለ ነው፡፡
በማህጸን	የማህጸን አሰጣጥ ማለት በክሬም፣ አረፋ፣ ኪኒን ወይም ሰፖሲቶሪ መልክ የሚገኝ መድሀኒት በማህጸን ማስገባት ነው፡፡ የማህጸን መድሀኒቶች ብዙጊዜ የሚሰጡት በዛ አካባቢ ለሚፈጥሩት ውጤት ነው፤ ለምሳሌ የማህጸን መመረዝ ህክምና፡፡
በትንፋሽ	በትንፋሽ የሚሰጥ መድሀኒት ማለት አፍነጫ፣ ጉሮሮ እና ሳንባ ላይ በመርጨት ወይም በመተንፈስ ማስገባት ነው፡፡ መድሀኒቱ የሚመጠጣው አፍንጫ እና ጉሮሮ ውስጥ ባሉ የሙከስ ሜምብሬን ወይም ሳንባን በሚሞሉ ደቃቅ የአየር ከረጢቶች በኩል ነው፡፡
በመርፌ	ቆዳን በመርፌ በመውጋት እና መድሀኒቱን ጡንቻ ውስጥ፣ ቆዳ ስር ወይም ደምስር ውስጥ በማስገባት መድሀኒት ማስገባት ይቻላል፡፡

የመድሀኒት አስተሻሸግ እና ስም አሰጣጥ

የመድሀኒት ማሸጊያ

መድሀኒት በተለያየ መንገድ ይታሸጋል። የተለመደው አይነት፡

- **ብልቃጥ ወይም ጠርሙስ** - የላስቲክ ወይም የብርጭቆ ጠርሙስ ወይም የጠብታ ጠርሙስ ሊሆን ይችላል።
- **የበብል እሽግ** - ሌላ ስሙ ቢንጎ ካርድ ሲሆን የቢንጎ ካርድ ሚመስል የካርድቦርድ ካርድ ነው እነዲሁም ለእያንዳዱ የመድሀኒት ልኬት የላስቲክ በብል ረድፍ አለው።
- **የመድሀኒት ማደራጂያ** - የመድሀኒት ማስቀመጫ ወይም የሳምንታዊ መድሀኒት ሳጥን ነው።
- **አንድ የመድሀኒት መጠን ማሸጊያ** - የመድሀኒቱ እያንዳንዱ መጠን ተለይቶ/ለብቻው ሲታሸግ።

የመድሀኒት ስም

መድሀኒቱ ምንም አይነት ማሸጊያ ቢኖረውም አንዳንድ በጣም አስፈለጊ የሆኑ መረጃዎች በመድሀኒቱ መያዣ ላይ ሁሌ መኖር አለባው። ይኸውም፡

- **የባለጉዳይ ስም** - ስም እና የአባት ስም መኖረ አለበት።
- **የመድሀኒት ስም** - አጠቃላይ ወይም የብራንድ ስም መጻፍ አለበት።
- **መጠን** - የሚወሰደው የኪኒን፣ ጠብታ ወዘተ ቁጥር መጻፍ አለበት።
- **መንገድ** - መድሀኒቱ እንዴት እንደሚሰጥ (በአፍ፣ ወቅታዊ ወዘተ) መጻፍ አለበት። መድሀኒቱ በአፍ የሚወሰድ ከሆነ ማሸጊያው ላይ ብዙጊዜ አይጻፍም። የተለያዩ መንገዶች ምህጻረ-ቃል ለማግኘት በዚህ መጽሀፍ ጀርባ ላይ የሚገኘውን የስራ-አጋዥ ይመልከቱ።
- **ፕሮግራም** - መድሀኒት በየስንት ጊዜው እንደሚሰጥ (ለምሳሌ በቀን ሁለቴ ወይም በየአራት ሰአቱ)።

  ባለጉዳይ በቀን አንዴ መድሀኒት መውሰድ ካለበት፣ የተለየ ሰአት ካለተጠቀሰ በስተቀር በማንኛውም ሰአት መወሰድ ይችላል፤ ለምሳሌ ማታ።

  በቀን አንዴ የሚወሰዱ መድሀኒቶች ሁል ቀን በተመሳሳይ ሰአት መሰጠት አለባቸው።

  ባለጉዳይ መድሀኒት መውሰድ ከልረሳ በሚቀጥለው መድሀኒት መውሰጃ ሰአት እጥፍ እንዳይሰጡት፤ በህክመና ባለሙያ ካልታዘዙ በስተቀር።

- **የመጠቀሚያ ጊዜ ማብቂያ**

የመድሀኒት እገዛ እና መድሀኒት አሰጣጥ

የመድሀኒት ረዳት እና አሰጣጥን መብራራት

በነርስ ተልዕኮ ውስጥ የመድሀኒት እገዛ እና መድሀኒት አሰጣጥ መካከል የህግ ልዩነት አለ፡፡ ልዩነቱን መረዳት አስፈላጊ ነው፡፡

የመድሀኒት ረዳት ማለት ባለጉዳዩ የራሱን መድሀኒት እራሱ እንዲወስድ ያግዙታል፡፡ ባለጉዳዩ ስራውን እራሱ መስራት አለበት፡፡ ባለጉዳዩ መድሀኒቱን እራሱ አፉ ውስጥ መቸመር ወይም ቆዳው ላይ ማድረግ እና እራሱ ሚወስደው እንደሆነ ማወቅ አለበት፡፡

የመድሀኒት ረዳት የሚያደርጋቸው አንዳንድ ነገሮች፤

- የመድሀኒት መያዣ መክፈት፡፡
- መድሀኒቱን ለባለጉዳዩ ለመስጠት መያዣውን ወይም የመድሀኒት መቀነሻ እቃ ለምሳሌ ኩባያ ወይም ጎርጓዳ ሰህን ለባለጉዳዩ ማቀበል፡፡
- ለፈሳሽ መድሀኒት መጠን ለክቶ ከመድሀኒቱ ጠርሙስ ወደ ማንኪያ፣ የመድሀኒት ኩባያ ወይም ሌላ የተለየ መለኪያ መሳሪያ መቅዳት፡፡
- ባለጉዳዩ መድሀኒት እንዲወስድ ማስታወስ፡፡
- መድሀኒት መፍጨት እና ማሟሟት፡፡

የመድሀኒት ረዳት ለመባል በህግ መሰረት መሟላት የለባቸው ሁለት ሁኔታዎች አሉ፡፡ ባለጉዳዩ፤

1. "የመጨረሻውን ቅደም-ተከተል" በራሱ መስራት አለበት እንዲሁም
2. መድሀኒት እየወሰደ እንዳለ ማወቅ አለበት፡፡

ባለጉዳዩ እነዚህ ሁለት የመድሀኒት ረዳት "ሁኔታዎችን" ካላሟላ መድሀኒቱ መሰጠት ያለበት በነርስ ተልዕኮ ነው፡፡

በነርስ ተልዕኮ ስር መድሀኒት መስጠት ማለት ሀላፊነት በሰጠው RN በታዘዙት መሰረት ለባለጉዳዩ መድሀኒት ይሰጣሉ፡፡ በእንደዚህ አይነት ሀኔታ ላይ ባለጉዳዩ ግራ ሊጋባ ወይም መድሀኒት እንደሚወስድ ላያውቅ ይችላል ወይም "የመጨረሻውን ቅደም-ተከተል" ለመስራት አይችል ይሆናል፡፡

በነርስ ተልዕኮ ስር የመድሀኒት አሰጣጥ ስራ መስራት የሚችሉበት አንዳንድ መንገድ፤

- በባለጉዳዩ አፍ ውስጥ መድሀኒት ማስገባት፡፡
- ባለጉዳዩ ቆዳ ላይ መድሀኒት ማድረግ፡፡
- በጋስትሮስቶሚ ቲዩብ መድሀኒት መስጠት፡፡
- የደም ስኳር ምርመራ ማድረግ፡፡

የሚቀጥሉት ገጾች በነርስ ተልዕኮ ስር የመድሀኒት አሰጣጥ ስራ ሲሰራ ሀላፊነት ከሚሰጠው RN እና ባለጉዳዩ ጋር ያለዎትን ሚና ያብራራሉ፡፡

የመድሀኒት አሰጣጥ አምስት ትክክል ሁኔታዎች

ለእያንዳዱ የመድሀኒት አሰጣጥ አምስት ትክክል ሁኔታዎች "አዎ" ብለው መመለስዎትን ያረጋግጡ፤

አምስቱ ትክክል ሁኔታዎች

- ትክክለኛ ደንበኛ
- ትክለኛ መድሀኒት
- ትክክለኛ መጠን
- ትክክለኛ መንገድ
- ትክክለኛ ሰአት

1 ትክክለኛ ደንበኛ

ባለጉዳዩን በሆነ መንገድ ሁሉ መለየት መቻልዎት በጣም አስፈላጊ ነው። መድሀኒት ከመስጠትዎ በፊት ባለጉዳዩን እንዳወቁት በፍጹም ማረጋገጥ የእርስዎ ሀላፊነት ነው። ለባለጉዳይ መድሀኒት መስጠት የሚችሉት ሀላፊነት ከሚሰጠው RN የተለየ ተልዕኮ ሲቀበሉ በቻ ነው።

መድሀኒቱን ትክክለኛው ባለጉዳይ መውሰዱን ለማረጋገጥ ባለጉዳዩ መድሀኒቱን እስኪወስድ ድረስ አብረውት ይቆዩ።

2 ትክክለኛ መድሀኒት

ስም ከተጻፈበት መያዥ ውስጥ ብቻ መድሀኒት መስጠትዎን ያረጋግጡ። መድሀኒቱ የሚሰጥበት ሰአት ድረስ የአንድ-መጠን ማሸጊያ ላይ የመድሀኒቱ ስም እንደተቀመጠ እንዲቆይ ማሸጊያውን አይላጡት። መድሀኒት ሊሰጡ ሲሉ ያዘጋጁት፤ ቀደም ብለው አያዘጋጁት። መድሀኒቱን እንደሚከተለው ሲያዘጋጁት ስሙን ሶስት ጊዜ ያንቡት፤

1. ከተቀመጠበት መደርደሪያ ወይም መሳቢያ ሲያወጡት።
2. መድሀኒቱን ሲቀዱ ወይም ሲለኩ።
3. መድሀኒቱን ከለኩበት ወይም ከቀዱበት እቃ ጠርሙሱን ወይም ማሸጊያውን ሲቀይሩ።

3 ትክክለኛ መጠን

ትክክለኛ የመጠን ምልክቶችን እና ምህጻረ-ቃላትን ማወቅ አስፈላጊ ነው (በዚህ መጽሀፍ ጀርባ የሚገነውን የስራ አጋዥ ክፍል ይመልከቱ)። እንዱሁም በአግባቡ ጽሁፍ የለባቸው መለኪያ እቃዎችን መጠቀምዎትን ያረጋግጡ። ባለጉዳዩ የሚወስደው መጠን የታዘዘለትን መሆኑን ያረጋግጡ። እያንዳንዱ መድሀኒቱን እስኪወስድ ድረስ አብረው ይቆዩ።

4 ትክክለኛ መንገድ

የመድሀኒት አሰጣጡን መንገድ በመድሀኒት ጠርሙሱ፣ እሽጉ ወይም የመድሀኒት መሀደሩ ላይ ሁሌ ይመልቱ እንዲሁም ምህጻረ-ቃሉን ይወቁ።

5 ትክክለኛ ሰአት

መድሀኒት በሚሰጡበት ወቅት ትክክለኛ ምህጻረ-ቃላቱን ይወቁ። መድሀኒት ሚሰጡበት ትክክለኛ ሰአት ለማወቅ ጠርሙሱን፣ ሽፋኑን ወይም መድሀኒት መሀደሩን ይመልከቱ። መድሀኒቱን በተገለጸው ሰአት/በተቻለ መጠን በሚቀርበው ሰአት ይስጡ።

የመድሀኒት አሰጣጥ ሂደት

ደረጃ በደረጃ

መድሀኒት ከመስጠትዎ በፊት፣ ሲሰጡ እና ከሰጡ በኋላ ማስታወስ ያለብዎት በርካታ ነገሮች አሉ። ሀላፊነትዎ ለባለጉዳይ መድሀኒት ከመስጠት በላይ ነው። እርስዎ፤

- መድሀኒቱ ከመሰጠቱ በፊት እና በኋላ የባለጉዳዩን ሁኔታ ለመቆጣጠር ቁልፍ ሰው ነዎት።
- የጎንዮሽ ችግሮች ለመከታተል እና ሲከሰቱ ቀደም ብለው እርምጃ ለመውሰድ ተመራጭ ሰው ነዎት።
- ባለጉዳዩ መድሀኒት አልወስድም ቢል ወይም ስህተት ካገኙ ምን መደረግ እንዳለበት ማወቅ አለብዎት።

የሚከተሉትን አምስት ቀላል ቅደም-ተከተሎች ከተከተሉ መደረግ ያለባቸው የመድሀኒት አሰጣጥ አስፈላጊ ደረጃዎችን ሁሉ ለማስታወስ ይቀልዎታል፤

ቅድመ-ተከተል 1 ባለጉዳዩን መገምገም

ቅድመ-ተከተል 2 መድሀኒቱን ማዘጋጀት

ቅድመ-ተከተል 3 መድሀኒት መስጠት

ቅድመ-ተከተል 4 የመድሀኒት አሰጣጡን መመዝገብ

ቅድመ-ተከተል 5 ባለጉዳዩ የጎንዮሽ ችግሮች እንዳሉት መከታተል

ቅደም ተከተል 1፤ መገምገም

የመጀመሪያው ደረጃ ባለጉዳዩን መድሀኒት ከመስጠት በፊት መገምገም ነው። መድሀኒት ለባለጉዳዩ ለመስጠት ካልተመቸዎት ወይም ጥርጣሬ ካልዎት RNን ማነጋገር አለብዎት።

RN ጋር ይደውሉ እና ሚከተሉት ከሆኑ መድሀኒቱን **አይስጡ**፡

- የባለጉዳዩ ጤና ላይ ትልቅ ለውጥ ካዩ።
- ስለ አምስቱ የመድሀኒት አሰጣጠት ትክክለኛ ሁኔታዎች ጥርጣሬ ካለዎት።
- መድሀኒቱ እንዴት እንደሚሰጥ ካልገባዎት።
- ለባለጉዳዩ ሀላፊ በሆነ RN መድሀኒቱ (በማዘዣ ወይም OTC) እንዲሰጥ ካልተላለፈ።

ቅደም ተከተል 2፤ ዝግጅት

መድሀኒት ማዘጋጀት ማለት በመድሀኒቱ መሀደር ላይ ያለውን መረጃ በማንበብ ትክክለኛውን የመድሀኒት መጠን ለባለጉዳዩ ማዘጋጀት ነው፡፡ የሚከተሉት መመሪያዎች መድሀኒት በትክክለኛ እንዲያዘጋጁ ያግዝዎታል፤

- **ራስዎን ያዘጋጁ፡፡**
  - ራስዎትን ከሚረብሹ ሀሳቦች በሙሉ ነጻ ያድርጉ እና ለባለጉዳዩ መድሀኒት መስጠት ላይ ትኩረት ያድርጉ፡፡ ምንም አይነት ወሬ ያቁሙ፡፡ እያወሩ ከሆነ ወይም ትኩረትዎ በሙሉ ስራዎት ላይ ካልሆነ ስህተት መስራት ቀላል ነው፡፡
  - እጅዎን በሳሙና እና ውሀ ይታጠቡ እና ሙሉውን ያድርቁት፡፡
- **መድሀኒቱን ያዘጋጁ፡፡**
  - የሚያዘጋጁበትን ቦታ ንጹህ እና ያልተዝረከረከ የድርጉ፡፡
  - አንድ መድሀኒት ማዘጋጀት ያለብዎት ለአንድ ባለጉዳይ ብቻ ነው እንዲሁም መድሀኒቱ መዘጋጀት ያለበት ለባለጉዳዩ ሊሰጡ ሲሉ ብቻ ነው፡፡
  - መድሀኒት ለመስጠት ሚያስገልግዎትን ማንኛውንም እቃ እና መሳሪያ ያቅርቡ፡፡
  - መድሀኒቱን ለማዘጋጀት አምስቱን ትክክለኛ ሁኔታዎች ይጠቀሙ፡ ትክክለኛ ባለጉዳይ፣ ትክክለኛ መድሀኒት፣ ትክክለኛ መጠን፣ ትክክለኛ መንገድ እና ትክክለኛ ሰአት፡፡
  - መድሀኒቱን እዳይነኩት፡፡
  - መድሀኒት መስጠት ያለባችሁ ስም ከተጻፈበት እቃ ውስጥ ነው፡፡
  - መድሀኒቱን እስከሚሰጡ ድረስ ለአንድ ጊዜ ሚሰጡ መጠኖችን እንደታሸጉ ያስቀምጡ፡፡
  - መድሀኒት የሚፈጩት፣ የሚቆርጡት ወይም ከምግብ ጋር የሚቀላቅሉት ሀላፊነት የሰጠው RN መመሪያ ከሰጠ ብቻ ነው፡፡
  - የመድሀኒቱ ጠርሙስ ላይ ከመድሀኒቱ ስም ቀጥሎ የሚከተሉት ፊደሎች ምልክት ያለባቸውን መድሀኒቶችን አይፍጩ ወይም አይስበሩ፡፡ ይህ የመድሀኒቱን መሸፈኛ ይሰብረዋል እንዲሁም የመድሀኒቱን ስራ ይቀይረዋል፡፡

    LA = በዝግታ የሚመጡ

    SR = በተወሰነ ሰአት ውስጥ ከደም ጋር ሚቀላቀሉ

    ER = በረዥም ሰአት ውስጥ ከደም ጋር ሚቀላቀሉ

    EC = የሚሟማ የመድሀኒት መሸፈኛ
- *መድሀኒት ከጠርሙስ ሲቀዱ በጎን በኩል ጽሁፉ ጋር ሳይደርሱ ይቅዱት፡፡ ከጠርሙስ አፍ ጠብታ ካለ ጽሁፉን እንዳያበላሽው፡፡*
- የሚያስፈልገውን መጠን ከጠርሙሱ ከቀዱ በኋላ የጠርሙሱን ክዳን አጥብቀው ይዝጉ እና ከነበረበት መልሰው ያስቀምጡ፡፡
- *መድሀኒቱ ላይ ማንኛውም ያላተለመደ ነገር ካስተዋሉ ለባለጉዳዩ አይስጡት፡፡ እንደውም ሀላፊነት ለሰጠው RN ይደውሉ፡፡*
- እንክብካቤ ሰጪ እና ሀላፊነት የሰጠው RN የመድሂኒት ማደራጃ ለምሳሌ መድሂኒት ማስቀመጫ ለመጠቀም ከወሰኑ ለተላለፈው የመድሂኒት አሰጣጥ ስራ የመድሂኒት ማስቀመጫውን የሚሞላው የመድሂኒት ባለሙያ ወይም ሀላፊነት የሰጠው RN፡፡

  ማሳሰቢያ፣ የመድሂኒት ማስቀመጫው ላይ የባለጉዳዩ ስም፣ የመድሂኒት ስም፣ መጠን፣ መንገድ እና መድሂኒቱ የሚሰጥበት ሰአት መጻፍ አለበት፡፡

ቅደም ተከተል 3፤ መስጠት

ሶስተኛው ቅደም-ተከተል መድሀኒት መስጠት ነው። ሀላፊነት የሰጠው RN የጻፈውን መመሪያ ይከተሉ። የሚከተሉት ከግንዛቤ መግባት ያለባቸው ጥቂት አጠቃላይ መመሪያዎች ናቸው፤

- በአፍ የሚሰጥ መድሀኒት ሲሰጡ ባለጉዳዩ እንዲቀመጥ ያድርጉ። ባለጉዳዩ መቀመጥ ካልቻለ እና አልጋ ላይ ከተኛ መድሀኒቱን ከመስጠትዎ በፊት በጎናቸው እነዲሆኑ ያድርጉ።
- በአፍ የሚወሰድ መድሀኒት ከ4-8 አውንስ ውሀ ጋር ቢወስዱት ብዙ ጊዜ ጥሩ ነው፤ ይህ የመሚሆነው ባለጉዳዩ ፈሳሽ መውሰድ ካልተከለከለ ነው።

ቅደም ተከተል 4፤ መመዝገብ

አራተኛው ቅደም-ተከተል የመድሀኒት አሰጣጡን መመዝገብ ነው። የባለጉዳዩን መሀደር ቅጂ እና የተለየ የጽሁፍ መመሪያ ለእርስዎ መስጠት ሀላፊነት የሚሰጠው RN ሀላፊነት ነው። መመሪያው የተሰጠዎትን ስራ እንዴት መመዝገብ እንዳለብዎት ማካተት አለበት። ሁልጊዜ ሀላፊነት የሚሰጠው RN የሚሰጠውን የተለየ መመሪያ ይከተሉ።

አንዳንድ አጠቃላይ መመሪያዎች፤

- ሁል ጊዜ መድሀኒት እንደተሰጠ ወይም ከተሰጠ በኋላ በተቻለ መጠን በቶሎ መመዝገብ።
- በመድሀኒት አሰጣጥ መሀደር ላይ መነሻዎችን መጻፍ ይችላሉ፤ ግን ሁልጊዜ በመሀደሩ የሆነ ቦታ ላይ ሙሉ ስምዎትን ይፈርሙ።
- መድሀኒት ለመውሰድ ፈቃደኛ ያልሆነባቸው አጋጠሚዎችም መመዝገብ።
- የመድሀኒት ስህተት ለምሳሌ የተሳሳተ መድሀኒት፣ የተሳሳተ ሰው ፣ የተሳሳተ መጠን፣ የተሳሳተ መንገድ፣ መጠኑ ከተቀነሰ፣ መጠኑ ከተጨመረ ይመዝግቡ።
- የመድሀኒት አሰጣጥ ስህተት ከተፈጠረ ምን መደረግ እንዳለበት ሀላፊነት ከሚሰጠው RN ጋር ይወያዩ።
- የ PRN መድሀኒት (አስፈላጊ ሲሆን የሚወሰድ) የመስጠት ምክንያትን እና እንዴት እንደሚሰራ ይመዝግቡ።

ቅደም ተከተል 5፤ መከታተል

ከመድሀኒት አሰጣጥ ሂደት የመጨረሻው ቅደም-ተከተል መድሀኒቱን ከሰጡ በኋላ ባለጉዳዩን መከታተል ነው። የጎንዮሽ ችገሮችን እና የመድሀኒት መቀላቀልን መከታተል አስፈላጊ ነው።

በጽሁፍ የተልዕኮ መመሪያው ላይ ሀላፊነት የሚሰጠው RN የትኞቹ የጎንዮሽ ችግሮች ክትትል እንደሚያስፈልጋቸው እና ከተከሰቱ ምን መደረግ እንዳለበት መለየት አለበት።

የባለጉዳይ መብት

ሰዎች መድሀኒት ወይም ህክመና **ያለመውሰድ መብት** አላቸው። ሰው ለምን መድሀኒት መውሰድ እንደማይፈልግ ወደ በኋላ ይማራሉ።

መድሀኒት ሲሰሰጥ ሰዎች **የብቻኝነት መብት** አላቸው። ብቻነታቸውን ለማክበር ጥንቃቄ ያድርጉ። ይህ የመድሀኒት መሀደር እና የጤና መረጃ ብቻነትን ያካትታልን።

ልዩ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ ምን እንደሚደረግ

መግቢያ

የመድሀኒት አሰጣጥ ስራ ሲሰጥዎት ለሁለቱ ሁኔታዎች መዘጋጀት አለብዎት። የሚከተለው ሲሆን ምን ማድረግ እንዳብዎት ማወቅ አለብዎት፤

- ባለጉዳዩ መድሀኒት አልወስድም ሲል።
- የመድሀኒት ስህተት ሲፈጽሙ ወይም መፈጸሙን ሲያውቁ።

ባለጉዳይ መድሀኒት አልወስድም ሲል

አንዳንዴ ባለጉዳይ መድሀኒት መውሰድ አይፈልግም። መጀመሪያ ማድግ ያለብዎት ለምን መድሀኒቱን እንደማይወስዱ መጠየቅ ነው።

ባለጉዳዮች በተለያዩ ምክነያቶች መድሀኒት መውሰድ አይፈልጉም፤ ከስር የሚገኘው ሰንጠረዥ ላይ የተዘረዘሩትን ጨምሮ። አንዳዴ ባለጉዳይ መድሀኒት መውሰድ እንደማይፈልግ አይነግርዎትም ግን ጉንጫቸው ውስጥ፣ ከምላስ ስር "ይደብቁታል" ወይም እርስዎ ከክፍሉ ከወጡ በኋላ ይተፉታል።

አንዳድ የተለመዱ ባለጉዳይ መድሀኒት አልውጥም የሚልባቸው ምክነያቶች እና መፍትሄያቸውን በሚከተለው ሰንጠረዥ ይመልከቱ፡

ማሳሰቢያ፡- ባለጉዳይዎት መድሀኒት አልወስድም ካለ ምን ማድረግ እንደለብዎት ሀላፊነት ከሰጠው RN ጋር እቅድ የዘጋጁ። ይህ ለአሳሳቢ መድሀኒቶች በተለየ አስፈላጊ ነው።

ምክንያት	መፍትሄ
ደስየማይል ጣዕም	• መጥፎ ጠዕምን ለመሸፈን ባለጉዳዩ መድሀኒት ከወሰዱ በኋላ ብስኩት፣ ፖም ወይም ጁስ መስጠት። • ባለጉዳዩ መድሀኒት ከመውሰዱ በፊት የምላስ ማጣጣሚያዎችን በረዶ በመጠቀም ማደንዘዝ። • ባለጉዳዩ የተለየ መድሀኒት ወይም የመድሀኒት አይነት መውሰድ እንደሚችል ለማወቅ ጉዳዩን ሀላፊነት ከሰጠው RN ጋር መወያየት።
ደስየማይል የጎንዮሽ ችግር	ደስ የማይል የጎንዮሽ ችግር ምሳሌ መደካከም ወይም የአፍ መድረቅ ሊሆን ይችላል። ሌላ መድሀኒት መስጠት ሚቻል ከሆነ ወይም መድሀኒቱ በሌላ ሰአት ላይ መወሰድ እንደሚቻል ሀላፊነት የሰጠውን RN ይጠይቁ። መድሀኒቱ መለወጥ ካልተቻለ የመድሀኒቱን የጎንዮሽ ችግሮች እንዴት ማስታገስ እነደሚቻል ይወያዩ።
ሁኔታውን አለመረዳት	"ይህ መድሀኒት ከፍተኛ የደም ግፊትዎን ይቀንሳል" የመሳሰሉ ቀላል ማስታወሻ ይስጡ።
የመድሀኒት አስፈላጊነትን መካድ	ከባለጉዳዩ ጋር ስለመድሀኒት መውሰድ አስፈላጊነት ይወያዩ ግን እንዳይከራከሩ። ሀኪም የጻፈውን ማዘዣ ማሳየት አንዳንዴ ይረዳል። ባለጉዳይ መድሀኒት አልወስድም የማለት መብት አለው።

ስህትትን ማስተካከል

መድሀኒት በተሰጠው መመሪያ መሰረት ካልተሰጠ ስህተት ነው ይባላል። ከ"አምስቱ ትክክለኛ ሁኔታዎች" ጋር የተያያዙ ማንኛውንም ስህተት ያካትታል የሚከተሉትን ጨምሮ፤

- የተሳሳተ ሰአት
- የተሳሳተ መድሀኒት
- የተሳሳተ ሰው
- የተሳሳተ መጠን
- የተሳሳተ መንገድ
- ማንኛውም ቅነሳ

ስህተት ሲያገኙ ምን ማድረግ እንዳለብዎት ማወቅ አለብዎት። ቀጣሪዎት የተወሰኑ አሰራሮች ሊኖሩት ይችላሉ እንዲሁም ሀላፊነት የሰጠው RN ለእርስዎ መመሪያ ይኖረዋል።

ያገኙትን ስህተት ወዲያው ማሳወቅ ጠቃሚ ነው።

ሁላችንም ስህተት ላለመስራት ብንሞክርም አንዳንዴ ግን ይፈጠራል። ስህተት አለማሳወቅ ስህተት ከመስራት የባሰ ነው፤ ስህተቱን ማንም ቢሰራውም።

መድሀኒት ማስቀመጥ እና ማስወገድ

አቀማመጥ

ስለመድሀኒት አቀማመጥ ማወቅ ያለብዎት በርካታ መመሪያዎች አሉ፤

- መድሀኒት መቀመጥ ያለበት በዋናው መያዣ፣ ዋነው ጽሁፉ በሚነበብበት መልኩ ነው።
- ፍሪጅ ውስጥ የማይቀመጡ መድሀኒቶች ደረቅ ቦታ መቀመት አለባቸው ከ85°ፋራናይት ያልበለጠ።
- ፍሪጅ ውስጥ የሚቀመጡ መድሀኒቶች ከ35 - 50°ፋራናይት ውስጥ መቀመጥ አለባቸው። ፍሪጅ ውስጥ የሚቀመጡ መድሀኒቶችን መዝጊያ ባለው የላስቲክ ቦርሳ ወይም ሌላ ማያፈስ መያዣ ውስጥ መቀመጥ አለባቸው።
- የመድሀኒት ማስቀመጫን ከምግብ ማስቀመጫ ጋር ይለዩ።
- የአዋቂ ቤተሰብ ቤት ወይም እገዛ የሚደረግለት መኖሪያ ቦታ የሚሰሩ ከሆነ የመድሀኒት አቀማመጥን በተመለከተ የቦታውን ፖሊሲ ይመልከቱ።

አወጋገድ

መድሀኒቱን መወሰድ ሲቆም መወገድ አለበት። ህዝብ አገልግሎት ውስጥ የሚሰሩ ከሆነ መድሀኒት ስለማስወገድ ያለብዎትን ሀላፊነት ለማወቅ የሚሰሩበትን ቦታ ፖሊሲ ይመልከቱ።

መድሀኒት ለማስወገድ ሀላፊነት ካለብዎት የሚከተሉትን ያድርጉ፤

- መድሀኒቱ እንዴት መወገድ እንዳለበት ባለጉዳዩን ወይም ተወካዩን ይጠይቁ።
- ባለጉዳዩ ወይም ተወካዩ መድሀኒቱን ካልፈለገ እርስዎ እና ባለጉዳዩ ወይም ተወካይ መድሀኒቱን ማስወገድ አለባችሁ።

  የህዝብ አገልገሎት መስጫ ውስጥ የሚሰሩ ከሆነ መድሀኒቱ መወገዱን ለመመዝገብ እርስዎ እና ምስክር የመድሀኒት ማስወገጃ ቅጽ መሙላት አለብዎት።
- ባለጉዳዩ ወይም ቤተሰቡ መድሀኒቱን ማስቀመጥ ከፈለጉ ቤተሰቡ መድሀኒቱን ስለመውሰዱ መመዝገቡ አስፈላጊ ነው።

የትምህርት ማጠቃለያ

መድሀኒቶች

- **መድሀኒት** ሰውነት ውስጥ ያለውን የኬሚካል እንቅስቃሴ የሚለውጥ ማንኛውም ውህድ ነው፡፡
- ሁለት አይነት መድሀኒቶች አሉ፤
  - የጽሁፍ መድሀኒቶች - በማዘዣ ብቻ የሚሰጥ
  - የጽሁፍ ያልሆኑ መድሀኒቶች - ያለማዘዣ መግዛት ይቻላል እንዲሁም የ OTC መድሀኒቶች በመባል ይታወቃል፡፡
- **ማዘዣ** ማለት ስለአጠቃቀም የተለየ መመሪያ ያለው እና ፈቃድ ባለው የጤና ባለሙያ የሚሰጥ የመድሀኒት ወይም የህክመና ትእዛዝ ነው፡፡ ማዘዣ መስጠት የሚችሉ የጤና እንክብካቤ ባለሙያዎች ሀኪም፣ ነርስ፣ የሀኪም ረዳት ወይም የጥርስ ሀኪም ናቸው፡፡
- መድሀኒቶች ሁለት ስም አላቸው፤
  - አጠቃላይ ስም
  - የብራንድ ስም
- **የፕሮግራም መድሀኒቶች** ቁጥጥር የሚደረግባቸው ንጥረነገሮች ይባላሉ፡፡ እነዚህ መድሀኒቶች አደገኛ ለመሆን ወይም አለአግባብ ለመጠቀም እና ለሱስ ለማጋለጥ ከፍተኛ አቅም አላቸው፡፡ ናርኮቲክ፣ የድብርት መድሀኒቶች፣ አነቃቂ መድሀኒቶች እና ሳይኮትፒክ መድሀኒቶች ምሳሌዎች ናቸው፡፡

መድሀኒት ምን ያደርጋል?

መድሀኒት ሶስተ ዋና-ዋና ነገሮችን ደርጋሉ፤

1. ህመም ማከም፣ ማዳን ወይም መቆጣጠር፡፡
2. የህመም ምልክቶችን ማስታገስ፡፡
3. በሽታ መከላከል፡፡

መድሀኒት ሲወሰድ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ መንስኤዎች

ስድስት የግል ባህሪይዎች የመድሀኒት ስራ ላይ ተጽዕኖ ያመጣሉ፤

1. እድሜ
2. ክብደት
3. ጾታ
4. የዘር ሀረግ
5. አካላዊ ሁኔታ
6. ስሜታዊ ሁኔታ

ለመድሀኒት የሚሰጥ ምላሽ ላይ ተጽዕኖ ሚያሳድሩ ሌሎች ምክነያቶች፤

- የመድሀኒት አሰጣጥ መንገድ
- መድሀኒቱ የሚሰጥበት ሰአት
- የሚወሰደው የመድሀኒት ቁጥር እና የመጠኑ ልኬት
- አካባቢያዊ ሁኔታ

የመድሀኒት የጎንዮሽ ችግሮች

የመድሀኒት የጎንዮሽ ችግሮች የመድሀኒት የህክምናው አላማ አካል ያልሆነ ሰውነት ላይ ያልታሰበ የመድሀኒት ውጤት ነው፡፡ መጫጫን፣ ራስ ምታት፣ እንቅለፍ ማጣት፣ ማቅለሽለሽ እና የሆድ መታወክ ምሳሌዎች ናቸው፡፡

የመድሀኒት መቀላቀል

የመድሀኒት መቀላቀል ማለት ቀደም ብሎ፣ በተመሳሳይ ሰአት ወይም ሌላ መድሀኒት ከተሰጠ በኋላ የተሰጠ መድሀኒት የአንዱን ወይም የሁለቱንም መድሀኒት ውጤት/ተጽዕኖ ሲቀይረው ነው፡፡ የአንዱን ወይም የሁለቱንም መድሀኒት ውጤት/ተጽዕኖ ሊጨምር ወይም ሊቀንስ ይችላል፡፡

አለርጂ

በአለርጂ የሚፈጠረው የሰውነት በሽታ የመከላከል ስርአት ማሳከክ፣ ማበጥ፣ የጡንቻ መኮማተር የሚያስከትሉ እና ጉሮሮ እና አየር መተላለፊያ የሚያጠቡ ኬሚካሎችን ሰውነት እንዲያመርት በማድረግ ለመድሀኒት ምላሽ ሲሰጥ ነው፡፡ ምላሹ ከመካከለኛ እስከ ህይወትን አደጋ ላይ እስከመጣል ይደርሳል፡፡

ሰባት መነገዶች

ሰባት የመድሀኒት አሰጣጥ መንገዶች ናቸው፤

በአፍ	በአፍ በመውሰድ መዋጥ
በምላስ	ከምላስ ስር በማስቀመጥ
ወቅታዊ	በቀጥታ ቆዳ ላይ ወይም የሙከስ ሜምብራን ላይ መስጠት
በፊንጢጣ	ፊንጢጣ ውስጥ በማስገባት
በማህጸን	ማህጸን ውስጥ በማስገባት
በትንፋሽ	በአፍነጫ ወይም ጉሮሮ በትንፋሽ ወደውስጥ የሚወሰድ ወይም የሚረጭ
መርፌ	መርፌ በመውጋት መድሀኒት ጡንቻ ውስጥ፣ ቆዳ ስር ወይም ደም-ስር**ማስገባት**

የመድሀኒት ማሸጊያ

በጣም የተለመዱት መድሀኒት ማሸጊያ አይነቶች፡

- ብልቃጥ ወይም ጠርሙስ
- የበብል እሽግ
- የመድሀኒት ማደራጂያ
- አንድ የመድሀኒት መጠን ማሸጊያ

የትምህርት ማጠቃለያ

የመድሀኒት ስም

ሁሉም የመድሀኒት ላይ ጽሁፍ የሚከተለውን መረጃ መያዝ አለበት፤

- የባለጉዳይ ስም
- የመድሀኒት ስም
- መጠን
- መንገድ
- ፕሮግራም
- አገልግሎት ማብቂያ ጊዜ

በነርስ ተልዕኮ ስር የመድሀኒት ረዳት እና አሰጣጥ

በነርስ ተልዕኮ ውስጥ የመድሀኒት እገዛ እና መድሀኒት አሰጣጥ መካከል የህግ ልዩነት አለ፡፡

የመድሀኒት ረዳት ማለት ባለጉዳዩ የራሱን መድሀኒት እራሱ እንዲወስድ እገዛ እስካስፈለገው ድረስ ያግዙታል፡፡ ባለጉዳዩ መድሀኒት እየወሰዱ እንደሆነ ያውቃሉ፡፡

በነርስ ተልዕኮ ስር በመድሀኒት አሰጣጥ ስራ ላይ እርስዎ ሀላፊነት በሰጠው RN እንደታዘዘው መድሀኒት ይሰጣሉ፡፡ በተልዕኮ ስር መድሀኒት መስጠት ሚችሉት HCA, NAC እና NAR ብቻ ናቸው፡፡

ባለጉዳዩ መድሀኒቱን አፉ ውስጥ ማስገባት ወይም ሰውነቱ ላይ ማድረግ ካልቻለ ወይም መድሀኒት እየወሰደ እንደሆነ ካላወቀ የመድሀኒት አሰጣጥ ስራው መተላለፍ አለበት፡፡

አምስቱ ትክክል ሁኔታዎች

መድሀኒት የሚሰጠው አምስቱን የመድሀኒት አሰጣጥ ትክክለኛ ሁኔታዎች በመጠቀም ነው፡፡

- ትክክለኛ ደንበኛ
- ትክለኛ መድሀኒት
- ትክክለኛ መጠን
- ትክክለኛ መንገድ
- ትክክለኛ ሰአት

የመድሀኒት አሰጣጥ ሂደት

የመድሀኒት አሰጣጥ ሂደቶች አምስት ቅደም-ተከተሎች አሉት፤

ቅድመ-ተከተል 1 ባለጉዳዩን መገምገም፡፡

ቅድመ-ተከተል 2 መድሀኒቱን ማዘጋጀት፡፡

ቅድመ-ተከተል 3 መድሀኒት መስጠት፡፡

ቅድመ-ተከተል 4 የመድሀኒት አሰጣጡን መመዝገብ፡፡

ቅድመ-ተከተል 5 ባለጉዳዩ የጎንዮሽ ችግሮች እንዳሉት መከታተል፡፡

የባለጉዳይ መብት

ሰዎች መድሀኒት ወይም ህክመና ያለመውሰድ መብት አላቸው፡፡

ሰዎች መድሀኒት ሲሰጣቸው የብቸኝነት መብት አላቸው፡፡ ሰውን የብቸኝነት መብት ለመጠበቅ ጥንቃቄ ያድርጉ፡፡ ይህ የመድሀኒት መሀደር እና የጤና መረጃ ብቻነትን ያካትታልን፡፡

ልዩ ሁኔታዎች

የሚከተሉትን ልዩ ሁኔታዎች ለማስተናገድ ዝግጁ እንዲሆኑ ሀላፊነት ከሚሰጠው RN ጋር ይወያዩበት፤

- ባለጉዳዩ መድሀኒት አልወስድም ሲል፡፡
- የመድሀኒት ስህተት ሲፈጽሙ ወይም መፈጸሙን ሲያውቁ፡፡

የመድሀኒት አቀማመጥ

- መድሀኒት በዋናው መያዣ፣ ዋናው መድሀኒት ላይ ጽሁፍ በሚነበብ መልኩ መቀመጥ አለበት፡፡
- ፍሪጅ ውስጥ የማይቀመጡ መድሀኒቶች ደረቅ ቦታ መቀመት አለባቸው ከ85°ፋራናይት ያልበለጠ፡፡
- ፍሪጅ ውስጥ የሚቀመጡ መድሀኒቶች ከ35 - 50°ፋራናይት ውስጥ መቀመጥ አለባቸው፡፡ ፍሪጅ ውስጥ የሚቀመጡ መድሀኒቶችን መዝጊያ ባለው የላስቲክ ቦርሳ ወይም ሌላ ማያፈስ መያዣ ውስጥ መቀመጥ አለባቸው፡፡
- የመድሀኒት ማስቀመጫን ከምግብ ማስቀመጫ ጋር ይለዩ፡፡
- የአዋቂ ቤተሰብ ቤት ወይም እገዛ የሚደረግለት መኖሪያ ቦታ የሚሰሩ ከሆነ የመድሀኒት አቀማመጥን በተመለከተ የቦታውን ፖሊሲ ይመልከቱ፡፡

አወጋገድ

መድሀኒት መወሰድ ሲቆም መድሀኒቱ መወገድ አለበት፡፡

- መድሀኒቱ እንዴት እንዲወገድ እነደሚፈልጉ ባለጉዳዩን ወይም ተወካዩን ይጠይቁ፡፡
- በህዝብ አገልግሎት መስጫ ውስጥ የሚሰሩ ከሆነ መድሀኒት ሲያስወግዱ ውጤቱን ሁሌ ይመዝግቡ፡፡ እርስዎ እና ምስክር የመድሀኒት አወጋገድ ቅጹ ላይ መፈረም አለብዎት፡፡

የተግባር ልምምድ

መመሪያዎች፤ በማስታወስ የቻሉትን ያህል ጥያቄ ይመልሱ። በመቀጠል ለቀሪዎቹ ጥያቄዎች በመጽሀፉ ላይ ያሉትን መልሶች ይመልከቱ። ጥያቄዎቹን ከጨረሱ በኋላ በቢህ መጽሀፍ ገጽ 84-85 ላይ የሚገኘው የመልስ ቁልፍ ላይ በመሄድ የሰጡትን መልስ ያረጋግጡ።

ሁለት አይነት መድሀኒቶች ምንድን ናቸው እንዲሁም የሁለቱ ማብራሪያ ምንድን ነው?

1. _____

2. _____

የመድሀኒት ጎንዮሽ ችግር ምንድን ነው? አራት ምሳሌ ይስጡ።

የመድሀኒት ጎንዮሽ ችግር፤ _____

1. _____

2. _____

3. _____

4. _____

የመድሀኒት መቀላቀል ምንድን ነው?

_____

_____

የመድሀኒት አሰጣጥ አምስቱ ትክክለኛ ሁኔታዎች ምንድን ናቸው?

1. _____

2. _____

3. _____

4. _____

5. _____

ሶስት የመድሀኒት አሰጣጥ መንገዶችን ይግለጹ።

1. _____

2. _____

3. _____

በመድሀኒት አሰጣጥ ስራ ላይ መከተል ያለብዎት አምስት ቅደም-ተከተሎች ምንድን ናቸው?

1. _____

2. _____

3. _____

4. _____

5. _____

Carl Green እርስዎ ባሉበት ህዝብ አገልግሎት መስጫ ቦታ ባለጉዳይ ነው። ለ Carl የአይን ጠብታ የማድረግ ስራ ተሰጥቶዎታል።

Carl መድሀኒቱን እና ቪታሚኑን ለመውሰድ በጣም ተቸግሯል። ሚስቱ ብዙግዜ መድሀኒቱን እና ቪታሚኑን ፈጭታ ምግቡ ውስጥ እንደምትጨምር በስልክ ነገረችዎት። መድሀኒቱን በተከታታይ እንዲወስድ ይህ በጣም ቀላሉ መንገድ ነው።

መድኒቱን ፈጭተው ምግቡ ውስጥ እዲጨምሩት ሚስቱ ጠየቀችዎት። Carl እርስዎን እንደሚያምንዎት እና ለአይን ጠብታው በሚያደርጉለት እገዛ ባጣም ደስተኛ እንደሆን ለሚስቱ ብዙ ጊዜ ነግሯታል። ምነ ማድረግ አለብዎት?

_____

_____

_____

_____

_____

Cynthia Brown ባለጉዳይ ናት። የጨጓራ -አንጀት አልሰር መድሀኒቷን እዲሰጧት ሀላፊነት ተሰጥቶዎወታል።

ዛሬ መድሀኒቱ ሆዷን እንደሚያሳምማት ቅሬታ አቀረበችልዎት እና መድሀኒቱን አልወስድም አለች። ምነ ማድረግ አለብዎት?

_____

_____

_____

_____

_____

የተግባር ልምምድ የመልስ ቁልፍ

የትያቄዎቹ መልሶች ከስር ተገልጸዋል። መረጃውን ማግኘት የሚችሉበት የገጽ ቁጥር በቅንፍ ተቀምጧል።

1. ሁለት አይነት መድሀኒቶች ምንድን ናቸው እንዲሁም የእያንዳዱ ማብራሪያ ምንድን ነው? (**ገጽ 64**)

   የጽሁፍ መድሀኒቶች - እነዚህ መድሀኒቶች መሸጥ የሚችሉት በማዘዣ እንደሆነ በህግ ተደንግጓል።

   የጽሁፍ ያልሆኑ መድሀኒቶች - እነዚህ ከመሸጫ መደርደሪየ (OTC) ላይ ወይም ያለማዘዣ የሚገዙ መድሀኒቶች ናቸው። የጀርባ ህመም፣ የሚቆጠቁጥ ጉሮሮ፣ የሆድ ህመም፣ ሳል፣ ጉንፋን፣ ድርቀት እና አጠቃለይ የሆኑ ህመሞችን የመሳሰሉ ሁኔታዎችን የሚያሽሉ ናቸው።

2. የመድሃኒት የጎንዮሽ ችግር ምንድን ነው? አራት ምሳሌ ይስጡ። (**ገጽ66-67**)

   የመድሀኒት የጎንዮሽ ችግር ማለት መድሀኒቱ ከተሰጠበት አላማ ሌላ ሰውነት ላይ የሚከሰት ውጤት ነው። ለምሳሌ ለማቅለሽለሽ የተሰጠ መድሀኒት ሰውን እንቅልፋም ሊያደርግ ይችላል። እንቅልፋምነቱ የጎንዮሽ ችግር ነው።

3. የመድሀኒት መቀላቀል ምንድን ነው? (**ገጽ 67**)

   የመድሀኒት መቀላለቀል ማለት ሁለት ወይም ከዛ በላይ መድሀኒቶች የአንዱን ወይም የሌላኛውን መድሀኒት ውጤት ሲቀይሩ ነው። የከፍተኛ የደም ግፊት መድሀኒት ከጉንፋን መድሀኒት ጋር መቀላቀል ጥሩ ምሳሌ ነው።

4. የመድሀኒት አሰጣጥ አምስት ትክክለኛ ሁኔታዎች ምንድን ናቸው? (**ገጽ 72**)

   ትክክለኛ ደንበኛ

   ትክክለኛ መድሀኒት

   ትክክለኛ መጠን

   ትክክለኛ መንገድ

   ትክክለኛ ሰአት

5. ሶስተ የመድሀኒት አሰጣጥ መንገዶችን ግለጹ (**ገጽ 70**)

   ማንኛውም ሶስቱ ትክክለኛ መልስ ናቸው፤

   በአፍ፣ በምላስ፣ ወቅታዊ፣ በፊንጢጣ፣ በማህጸን፣ በትንፋሽ ወይም በመርፌ

6. በመድሀኒት አሰጣጥ ወቅት መከተል ያለብዎት አምስት ቅደም-ተከተሎች ምንድን ናቸው? (**ገጽ 73**)

   ባለጉዳዩን መገምገም

   መድሀኒቱን ማዘጋጀት

   መድሀኒት መስጠት

   የመድሀኒት አሰጣጡን መመዝገብ

   ባለጉዳዩ የጎንዮሽ ችግሮች እንዳሉት መከታተል

7. Carl Green እርስዎ ባሉበት ህዝብ አገልግሎት መስጫ ቦታ ባለጉዳይ ነው። ለ Carl የአይን ጠብታ የማድረግ ስራ ተሰጥቶዎታል።

   Carl መድሀኒቱን እና ቪታሚኑን ለመውሰድ በጣም ተቸግሯል። ሚስቱ ብዙግዜ መድሀኒቱን እና ቪታሚኑን ፈጭታ ምግቡ ውስጥ እንደምትጨምር በስልክ ነገረችዎት። መድሀኒቱን በተከታታይ እንዲወስድ ይህ በጣም ቀላሉ መንገድ ነው። መድኒቱን ፈጭተው ምግቡ ውስጥ እዲጨምሩት ሚስቱ ጠየቀችዎት።

   Carl እርስዎን እንደሚያምንዎት እና ለአይን ጠብታው በሚያደርጉለት እገዛ ባጣም ደስተኛ እንደሆነ ለሚስቱ ብዙ ጊዜ ነግሯታል። ምነ ማድረግ አለብዎት? መልሱን በነርስ ተልዕኮ እና የህግ ትምህርተ ስር **ገጽ 10 ላይ ያገኙታል።**

   መልስ፤ የአይን ጠብታውን በታዘዙት መሰረት መስጠት መቀጠል አለብዎት። ሀላፊነት የሚሰጠው RN ካላዘዘ በስተቀር ሌላ የ Carlን መድሀኒት መስጠት እንደማይችሉ ለሚስቱ ይንገሯት። ስለ Carl ሚስት ስጋቶች ከተቆጣጣሪወት እና/ወይም ሀላፊነት የሚሰጠው RN ጋር መነጋገር አለብዎት።

8. Cynthia Brown ባለጉዳይ ናት። የጨጓራ -አንጀት አልሰር መድሀኒቷን እዲሰጧት ሀላፊነት ተሰጥቶዎወታል።

   ዛሬ መድሀኒቱ ሆን እንደሚያሳምማት ቅሬታ አቀረበችልዎት እና መድሀኒቱን አልወስድም አለች። ምን ማድረግ አለብዎት? (**ገጽ 76**)

   መልስ፤ Cynthia ለምን መድሀኒቱን መውሰድ እንዳልፈለገች ተጨማሪ መረጃ ማግኘት የሚችሉ ከሆነ ይሞክሩ። ሆዷን የሚያማት በመድሀኒቱ ነው ወይስ ሌላ ጊዜም ሆዷን ያማታል? መድኒቱን ለምን እንደምትወስደው ከ Cynthia ጋር ይነጋገሩበት።

   Cynthia ሆዷን እደሚያማት እና አልሰር መድሀኒቱን መውሰድ እነደማትፈልግ ሀላፊነት ለሰጠው RN ማሳወቅ አለብዎት።

   Cynthia መድሀኒቱን እንዳልወሰደች መመዝገብ አለብዎት።

   ዋናው ቁም-ነገር ባለጉዳይ መድሀኒት አልወስድም የማለት መብት አለው።

እዚህ ጋር መጽሀፉን ማንበብ ያቁሙ ።

የህክምና ስርአት የሚለውን የቪድዮውን ክፍልይመልከቱ ለመጀመር።

ወደ ድህረ-ገጽ የሚወስደውን መገናኛ ይከተሉ። በትምህርት መደዳ ስር የነርስ ተልዕኮ ወደሚለው ያውርዱ። በመረጡት ቋንቋ ላይ ይጫኑ። ማየት የሚፈልጉትን ቪድዮ ይምረጡ። www.dshs.wa.gov/altsa/training/dshs-curriculum-available**።**

ህክምናዎች

አጭር መግለጫ እና ቅድመ-እይታ

በዚህ ትምህርት እርስዎ እንዲሰሩ የሚሰጥዎት አንዳንድ በጣም የተለመዱ ህክመናዎች የሚከናወኑበትን ተመራጭ መንገድ ይማራሉ (ከስር ተዘርዝሯል)።

ከተለያዩ በሽታዎች ሊመጣ የሚችል ውስብስብነትን በመለየት እና የባለጉዳይዎትን ሁኔታ ሀላፊነት ለሚያስተላልፉት RN በማሳወቅ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ።

የትምህርት አላማዎች

ይህን ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ ለሚከተሉት ህክመናዎች ጥሩ ተግባር መግለጽ ይችለሉ፤

- የጆሮ ጠብታ
- አይን ጠብታ ወይም ቅባት
- የአፍንጫ ጠብታ ወይም የሚረጭ
- በአፍ በመተንፈስ ሚወሰድ ህክመና
- የፊንጢጣ ሰፖሲቶሪ ወይም ክሬም
- የማህጸን ሰፖሲቶሪ ወይም ክሬም
- ከጀርም ነጻ ያልሆነ የቁስል መሸፈኛ መቀየር
- የግሉኮሜትር ምርመራ
- ጋስትሮስቶሚ አመጋገብ
- ኦስቶሚ እንክብካቤ
- ቀጥ-ያለ ንጹህ የሽንት ቱቦ አጠቃቀም

የጆሮ ጠብታ

መግቢያ

ይህ ክፍል የጆሮ ጠብታ አሰጣጥ መሰረታዊ አሰራሩን ይሸፍናል።

ይህ አጠቃለይ መረጃ ብቻ ነው። ለእያንዳዱ ባለጉዳዩ ሀላፊነት በሚሰጠው RN የተገለጸውን የተለየ መመሪያ ሁልጊዜ ይከተሉ።

አሰራር፤ የጆሮ ጠብታ

ቅደም ተከተል 1፤ ባለጉዳዩን ይገምግሙ

- ስለአሰራሩ ከባለጉዳዩ ጋር ያውሩ
- ባለጉዳዩ እንዴት እንደሆነ ይጠይቁ፣ ማንኛውም አይነት ለውጥ የሚሰማው ከሆነ ይወቁ፤ የመስማት ለውጥ፣ የጆሮ ፍሳሽ ወይም ህመም ለምሳሌ። ማንኛውንም ቅሬታ ይመዝገቡ፡

ቅደም ተከተል 2፤ ለአሰራሩ መዘጋጀት

- የተልዕኮውን መመሪያ እና መድሀኒት መሀደሩን ይገምግሙ።
- የመድሀኒቱን መሀደር ከጆሮ ጠብታው ጽሁፍ ጋር ያስተያዩ
- እጅዎትን በሳሙና እና በውሀ ይታጠቡ እና በሙሉ ያድርቁ
- ጓንት ያድርጉ
- አስፈላጊውን መሳሪያ ያዘጋጁ።
- የመድሀኒት ውህዱን ከመጨመርዎት በፊት የሰውነት ሙቀት ላይ እስኪሆን ድረስ በመዳፍዎት በመያዝ ያሙቁት።
- ጠርሙሱን እነዲበጠብጡ የሚያዝ ከሆነ ይበጥብጡት።
- የጆሮ ጠብታ ማንጠባጠቢያውን በመድሀኒት በግማሽ ይሙሉት።
- ባለጉዳዩ ህክምና የሚደረግለትን ጆሮውን ወደላይ አድርጎ በጎኑ እንዲሆን ያግዙት። ወይም ባለጉዳዩ ከፈለገ ህክምና የሚደረግለትን ጆሮውን ወደላይ አድርጎ ጭንቅላቱን ወደጎን በማጠፍ መቀመጥ ይችላል።

ቅደም ተከተል 3፤ አሰራሩን መጨረስ

- ውህዱ በጆሮው ካናል (ቱቦ) በሙሉ መፍሰስ እንዲችል የጆሮ ውጭኛውን ክፍል በቀስታ ወደ ላይ እና ወደታች በመሳብ ቀጥ ማድረግ።
- ትክክለኛውን የጠብታ ቁጥር በጆሮው ካናል (ቱቦ) መጨመር። መድሀኒቱን ወደውስጥ ማለትም በጆሮው ካናል (ቱቦ) መካከል ላይ ማድረግ መድሀኒቱ በቀጥታ የጆሮ ታንቡር ላይ እዲያርፍ ያደርጋል፤ ይህ ደግሞ ጆሮው ውስጥ ጩኸት እና ህመም ይፈጥራል። ማንጠባጠቢያው የጆሮውን ወይም የካናሉን ማንኛውንም አካል እንዳይነካ ያድርጉ።
- መድሀኒቱን ከመጨመሩ በኋላ ባለጉዳዩ በጎኑ እንደሆነ ወይም ራሱን ወደጎን አጥፎ እንደተቀመጠ ለ5 ደቂቃ አካባቢ እንዲቆይ ያድርጉ።
- ማዘዣ የተሰጠው ባለሙያ ካዘዘ ጠብታው መግባቱን ለማረጋገጥ የተጠቀለለ ጥጥ ላላ አድርገው ጆሮ ላይ ያስገቡ።
- ጓንት ያስወግዱ።
- እጅዎትን በሳሙና እና በውሀ ይታጠቡ እና በሙሉ ያድርቁ

ቅደም ተከተል 4፤ መድሀኒት አሰጣጡን ይመዝግቡ

ቅደም ተከተል 5፤ ባለጉዳዩ ለመድሀኒቱ ያለውን ምላሽ እና የጎንዮሽ ችግሮችን ይከታተሉ

የአይን ጠብታ ወይም ቅባት

መግቢያ

ይህ ክፍል የአይን ጠብታ ወይም ቅባት አሰጣጥ መሰረታዊ አሰራሩን ይሸፍናል።

ይህ አጠቃለይ መረጃ ብቻ ነው። ለእያንዳዱ ባለጉዳዩ ሀላፊነት በሚሰጠው RN የተገለጸውን የተለየ መመሪያ ሁልጊዜ ይከተሉ።

አሰራር፤ የጆሮ ጠብታ ወይም ቅባት

ቅደም ተከተል 1፤ ባለጉዳዩን ይገምግሙ

- ባለጉዳዩ እንዴት እንደሆነ ይጠይቁ፣ ማንኛውም አይነት ለውጥ የሚሰማው ከሆነ ይወቁ፤ ለምሳሌ የማየት ለውጥ፣ የአይን መቅላት፣ ማበጥ፣ ፍሳሽ ወይም ህመም። ማንኛውንም ቅሬታ ይመዝገቡ፡
- ስለአሰራሩ ከባለጉዳዩ ጋር ያውሩ የአይን መድሀኒት አሰጣጥ ብዙጊዜ ህመም የለውም። ብዙ ጊዜ ቅባቶች አይንን ያለሰልሳሉ ግን አንዳንድ ፈሳሾች መጀመሪያ ላይ ይቆጠቁጣሉ።
- ባለጉዳዩ ከአንድ በላይ የአይን መድሀኒት ካለው ሁለት ወይም ከዛ በላይ የአይን መድሀኒቶች ቢያንስ በየአምስት ደቂቃ ልዩነት እንደሚሰጠው ለባለጉዳዩ ያብራሩ። ባለጉዳዩ የሚወስደው የአይን ጠብታ እና ቅባት ካለው የአይን ቅባቱ የአይን ጠብታውን ከመግባት ስለሚከለክለው ጠብታው መጀመሪያ እንደሚሰጥ ያብራሩ።

ቅደም ተከተል 2፤ ለአሰራሩ መዘጋጀት

- የተልዕኮውን መመሪያ እና መድሀኒት መሀደሩን ይገምግሙ።
- የመድሀኒቱን መሀደር ከጆሮ ጠብታው/ቅባት ጽሁፍ ጋር ያስተያዩ።
- እጅዎትን በሳሙና እና በውሀ ይታጠቡ እና በሙሉ ያድርቁ
- ጓንት ያድርጉ
- አስፈላጊውን መሳሪያ ያዘጋጁ።
- ባለጉዳዩ ምቹ አኳኋን ላይ እዲሆን ማለተም እንዲቀመጥ ወይም እንዲንጋለል ያግዙት። ባለጉዳዩ ቆሞ መድሀኒቱን እንዳይሰጡ።
- የአይን ጠብታ ወይም ቅባት ከመስጠትዎ በፊት ቅንድብ እና ሽፋሽፍቱን ያጽዱ። አይን ለማጽዳት ንጹህ እና ሞቅ ያለ ቸርቅ ይጠቀሙ። ለእያንዳዱ አይን የጨርቁን የተለያየ ክፍለ ይጠቀሙ።
- አይን ሲየጸዱ ከውስጠኛው አይን ስር (ለአፍነጫ ከሚቀርበው) ወደውጭኛው የአይን መጨረሻ (ከአፍንጫ ለሚርቀው) ይጥረጉ።
- ቅባት ከሆነ መጀመሪያ ላይ የሚወጣውን ያስወግዱ። ከእቃው የሚወጣው የመጀመሪያው ቅባት የተበከለ ነው ተብሎ ይገመታል።

ቅደም ተከተል 3፤ አሰራሩን መጨረስ

- ለባለጉዳዩ ደረቅ የሚመጥ ጨርቅ ይስጡት፡፡ ባለጉዳዩ ወዳጣሪያ እንዲመለከት ያድርጉ፡፡ ባለጉዳዩ ወዳጣሪያ የሚያይ ከሆነ አይኑን አያርገበግብም፡፡
- ስራ-ማይሰራው እጅወዎት አውራ ጣት ወይም ጣትን ከአይን ስር ባለው የባለጉዳዩ የጉንጭ አጥንት ላይ በማድረግ የስረኛውን የኮንጀክቲቫ ከረጢት ይያዙት እና በቀስታ ቆዳውን ጉንጭ ላይ ዝቅ-ዝቅ ያድርጉት፡፡
- ባለጉዳዩ ማድረግ ከቻለ እንዲያደርግ ፍቀዱለት፤ የታችኛውን የአይን ሽፋን ወደታች ዝቅ-ዝቅ እንዲያደርጉ ያግዙ፡፡ የታችኛውን የአይን ሽፋን ካበጠ ወይም ከጠጠረ እንዳይጎዳ በጣም በጥንቃቄ ያድርጉት፡፡
- ጣትን የጉንጭ አጥንት ላይ ማድረግ ኮርኒያን የመንካት እድልን ይቀንሳል፣ አይን ኳስ ላይ ጫና ማሳደርን ያስወግዳል እንዲሁም አይንነ ከማርገብገብ ይከላከላል፡፡
- ከአይን ውስጥ በመጀመር ትክክለኛውን የጠብታ ቁጥር የታችኛው የኮንጀክቲቫ ከረጢት ሶስተኛው የውጪ ክፍል ላይ ያድርጉ፡፡ ማንጠባጠቢያውን ከከረጢቱ ከ1 እስከ 2 ሴሜ በላ ይያዙ፡፡ በጎን በኩል ከተደረገ ባለጉዳዩ አይኑን የማርገብገብ እድሉ ይቀንሳል፡፡ የኮንጀክቲቫ ከረጢት ላይ ሲደረግ ጠብታው ኮርኒያውን አይቆጠቁጠውም፡፡ ማንጠባጠቢያው ከረጢቱን ወይም ኮርኒያውን መንካት የለበትም፡፡
- ቅባት የሚጠቀሙ ከሆነ ቱዩቡን ከታችኛው የኮንጀክቲቫ ከረጢት በላይ ይያዙ እና የቅባቱን 3/4 ኢንች ከቱዩቡ ወደ ታችኛው የኮንጀክቲቫ ከረጢት ከውስጠኛው ካንተስ ወደውጪ ይጫኑት፡፡
- ባለጉዳዩ አይኑን እንዲጨፍን ያድርጉ፤ ጭምቅ ማድረግ ግነ አይደለም፡፡ አይን መዝጋት መድሀኒቱ በአይን ኳስ ዙሪያ ለማሰራጨት ይረዳል፡፡ አይንነ መጭመቅ አይንነ ሊጎዳ እና መድሀኒቱን ሊያስወጣው ይችለል፡፡
- ለፈሳሽ መድሀኒቶች እርስዎ ወይም ባለጉዳዩ ቢያንስ ለ30 ሰከንድ የእንባ ደክት ላይ በጣም ይጫኑ፡፡ ደክቱን መጫን መድሀኒቱ ከአይን እዳይወጣ እና እንዳይፈስ ይከላከላል፡፡
- እነደአስፈላጊነቱ ቅነድብን ያጽዱ፡፡ ትርፍ መድሀኒት ለመሰብሰብ ቅንድብን ከውስጠኛው ወደውጪኛው ካንተስ ይጥረጉ፡፡
- መድሀኒቱን ካደረጉ በኋላ ወዲያው እና መድሀኒቱ ከሰራ በኋላ በድጋሚ የባለጉዳዩን ምላሽ ይገምግሙ፡፡
- ጓንት ያስወግዱ እና እጅዎትን ይታጠቡ፡፡

ቅደም ተከተል 4፤ መድሀኒት አሰጣጡን ይመዝግቡ

ቅደም ተከተል 5፤ ባለጉዳዩን ይከታተሉ

- የአይን መቅላት፣ ፍሳሽ፣ ህመም፣ ማሳከክ፣ ማበጥ ወይም ሌላ ስሜት ወይም የዕይታ ችገር ካለ ይከታሉ እና ያሳውቁ፡፡
- ሀላፊነት በተሰጠው RN በታዘዘው መሰረት የጎንዮሽ ችግር ይከታተሉ፡፡

የአፍንጫ ጠብታ ወይም የሚረጭ

መግቢያ

ይህ ክፍል **የአፍንጫ ጠብታ ወይም የሚረጭ** አሰጣጥ መሰረታዊ አሰራሩን ይሸፍናል። ይህ አጠቃለይ መረጃ ብቻ ነው። ለእያንዳዱ ባለጉዳዩ ሀላፊነት በሚሰጠው RN የተገለጸውን የተለየ መመሪያ ሁልጊዜ ይከተሉ።

አሰራር፤ የአፍንጫ ጠብታ ወይም የሚረጭ

ቅደም ተከተል 1፤ ባለጉዳዩን ይገምግሙ

- ባለጉዳዩ እንዴት እንደሆነ ይጠይቁ፣ ማንኛውም አይነት ለውጥ የሚሰማው ከሆነ ይወቁ፤ ለምሳሌ የአፍንጫ መታፈን፣ የአፍንጫ ፍሳሽ፣ አተነፋስ። ማንኛውንም ቅሬታ ይመዝገቡ፡
- ስለአሰራሩ ከባለጉዳዩ ጋር ያውሩ

ቅደም ተከተል 2፤ ለአሰራሩ መዘጋጀት

- የተልዕኮውን መመሪያ እና መድሀኒት መሀደሩን ይገምግሙ።
- የመድሀኒቱን መሀደር ከአፍንጫ ጠብታ ወይም ምርጫው ጽሁፍ ጋር ያስተያዩ።
- እጅዎትን በሳሙና እና በውሀ ይታጠቡ እና በሙሉ ያድርቁ
- ጓንት ያድርጉ
- አስፈላጊውን መሳሪያ ያዘጋጁ።
- ባለጉዳዩ የአፍንጫ መተላለፊያውን ለማጽዳት አፍነጫቸውን በቀስታ እዲናፈጡ ያድርጉ።
- የአፍነጫ ጠብታ ለማድረግ ባለጉዳዩ ጭንቅላቱን ወደኋላ ዘመም በማድረግ መንጋለል ወይም መቀመጥ አለበት።
- ባለጉዳዩ ከተንጋለለ ትከሻቸው ስር ትራስ በማድረግ ጭንቅላታቸው ከትራሱ መጨረሻ ላይ እንዲያርፍ ያድርጉ። አንዳንድ የሚረጩ መድሀኒቶች ባለጉዳዩ ጭንቅላቱን ቀጥ እንዲያደርግ ይመከራሉ።

ቅደም ተከተል 3፤ አሰራሩን መጨረስ

- አውራጣትን አፍነጫ ጫፍ ላይ በመጫን የአፍነጫ ቀዳዳዎችን በቀስታ መግፋት።
- ማንጠባጠቢያውን ወይም የሚረጨውን ከባለጉዳዩ አፍንጫ ቀዳዳ በላይ በመያዝ መድሀኒቱን በአፍንጫ ቀዳዳ መካከል ማነጣጠር። መድሀኒቱ በአፍንጫ ቀዳዳ ስር አቅጠጫ ከተነጣጠረ በኢዩስታቺያን ቱቦው ይወርዳል።
- መያዣው እንዳይበከል የማንጠባጠቢያው ወይም የመርጫውን ጠርሙስ ጫፍ ከሙከስ ሜምብሬን ጋር እንዳያገናኙት።
- ባለጉዳዩን የሚከተሉትን ይጠይቁ፡
  - በአፍንጫ በኩል በቀስታ እና በጥልቀት ወደ ውስጥ እንዲተነፍሱ
  - ለበርካታ ሰከንዶች ትንፍሻቸውን እንዲይዙ
  - አየር ወደውጪ በቀስታ እንዲያስገቡ
  - ውሀዱ አጠቃላይ አፍንጫውን ገጽ እንዲያገኘው በጀርባቸው ተንጋለው ለ1 ደቂቃ እንዲቆዩ።
- ማንጠባጠቢያውን ወደ ጠርሙሱ ከመመለስዎት በፊት ማንጠባጠቢያው ውስጥ የቀረ መድሀኒት ማስወገድ።
- የማንጠባጠቢያውን ጫፍ በሙቅ ውሀ ማለቅለቅ፣ በጨርቅ ማድረቅ እና ወዲያው ድጋሚ መዝጋት።
- ጓንት ያስወግዱ።
- እጅዎትን በሳሙና እና በውሀ ይታጠቡ እና በሙሉ ያድርቁ

ቅደም ተከተል 4፤ መድሀኒት አሰጣጡን መመዝገብ።

ቅደም ተከተል 5፤ ባለጉዳዩ ለመድሀኒቱ ያለውን ምላሽ እና የጎንዮሽ ችግር ይከታተሉ።

በአፍ የሚወሰድ የትንፋሽ ህክመና

መግቢያ

ይህ ክፍል **በአፍ የሚወሰድ የትንፋሽ ህክምና አሰጣጥ መሰረታዊ አሰራሩን ይሸፍናል።**

ይህ አጠቃለይ መረጃ ብቻ ነው። ለእያንዳዱ ባለጉዳዩ ሀላፊነት በሚሰጠው RN የተገለጸውን የተለየ መመሪያ ሁልጊዜ ይከተሉ።

አሰራር፤ የአፍ መተንፈሻ ህክመና

ቅደም ተከተል 1፤ ባለጉዳዩን ይገምግሙ።

- ባለጉዳዩ እንዴት እንደሆነ ይጠይቁ፣ ማንኛውም አይነት ለውጥ የሚሰማው ከሆነ ይወቁ፤ ለምሳሌ አተነፋስ። ማንኛውንም ቅሬታ ይመዝገቡ፡
- ስለአሰራሩ ከባለጉዳዩ ጋር ያውሩ

ቅደም ተከተል 2፤ ለአሰራሩ መዘጋጀት።

- የተልዕኮውን መመሪያ እና መድሀኒት መሀደሩን ይገምግሙ።
- የመድሀኒቱን መሀደር በትንፋሽ ወይም በመርጨት ከሚወሰደው መድሀኒት ጽሁፍ ጋር ያስተያዩ።
- እጅዎትን በሳሙና እና በውሀ ይታጠቡ እና በሙሉ ያድርቁ
- ጓንት ያድርጉ
- አስፈላጊውን መሳሪያ ያዘጋጁ።

ቅደም ተከተል 3፤ አሰራሩን መጨረስ።

- መድሀኒት መንፊያውን (መንፊያ) ከመጠቀምዎት በፊት ይበጥብጡት። ወደ አፍ ከሚገባው ላይ ክዳኑን ያንሱ።
- ባለጉዳዩ ጎሮሮውን እንዲያጸዳ ይጠይቁ።
- ባለጉዳዩ ሳንባ ውስጥ ያለውን አየር በሙሉ በቀስታ ወደውጪ ይተንፍሱ እና ትንፈሻቸውን ይያዙ።
- ወደአፍ የሚገባውን አፍ ውስጥ በማስገባት መሳቢያውን ቀጥ አድርጎ ወደላይ መያዝ። ባለጉዳይ ወደአፍ በሚገባው ዙሪያ ከንፈሩን አጥብቆ እንዲዘጋ ያድርጉ።
- ባለጉዳይ በአፉ በጥልቀት ወደ ውስጥ ሲስብ መሳቢያውን ይጭመቁ። ይህ ብዙጊዜ ከባድ ነው።
- ባለጉዳዩ ለ 5 ሰከንድ ትንፋሹን እንዲይዝ ይንገሩ።
- ባለጉዳዩ ወደ ውጪ ከመተንፈሱ በፊት መሳቢያውን ከአፉ ያውጡት። ሌላ መመሪያ ከሌለ በስተቀር ድጋሚ መሳቢያውን ከመጠቀምዎት በፊት ቢያንስ 2 ደቂቃ ይጠብቁ።
- የታዘዘው 2 ጊዜ መሳብ ከሆነ ሂደቱን ይድገሙት።
- ሁለት ወይም ከዛ በላይ መሳቢያ ካለዎት የስቴሮይድ መድሀኒቱን ሁሌ መጨረሻ ይጠቀሙ። ከዛ የባለጉዳዩን አፍ በውሀ ያጉመጥምጡ እና እንዲተፉ ያድርጉ።
- የመሳቢያውን አፍ ላይ የሚደረገውን በቶሎ-ቶሎ ያጽዱ እና በሙሉ ያድርቁት።
- ጓንት ያስወግዱ።
- እጅዎትን በሳሙና እና በውሀ ይታጠቡ እና በሙሉ ያድርቁ

ቅደም ተከተል 4፤ መድሀኒት አሰጣጡን መመዝገብ።

ቅደም ተከተል 5፤ ባለጉዳዩ ለመድሀኒቱ ያለውን ምላሽ እና የጎንዮሽ ችግር ይከታተሉ።

የፊንጢጣ ሰፖሲቶሪ ወይም ክሬም

መግቢያ

ይህ ክፍል **የፊንጢጣ ሰፖሲቶሪ ወይም ክሬም** መድሀኒት አሰጣጥ መሰረታዊ አሰራሩን ይሸፍናል፡፡

ይህ አጠቃለይ መረጃ ብቻ ነው፡፡ ለእያንዳዱ ባለጉዳዩ ሀላፊነት በሚሰጠው RN የተገለጸውን የተለየ መመሪያ ሁልጊዜ ይከተሉ፡፡

አሰራር፤ የፊንጢጣ ሰፖሲቶሪ ወይም ክሬም

ቅደም ተከተል 1፤ ባለጉዳዩን ይገምግሙ፡፡

- ባለጉዳዩ እንዴት እንደሆኑ ይጠይቁ፣ ማንኛውም አይነት ለውጥ የሚሰማው ከሆነ ይወቁ፤ ለምሳሌ ህመም፣ ማሳከክ፣ ማቃጠል ወይም ድርቀት፡፡ ማንኛውንም ቅሬታ ይመዝገቡ፡
- ስለአሰራሩ ከባለጉዳዩ ጋር ያውሩ

ቅደም ተከተል 2፤ ለአሰራሩ መዘጋጀት፡፡

- የተልዕኮውን መመሪያ እና መድሀኒት መሀደሩን ይገምግሙ፡፡
- የመድሀኒቱን መሀደር ከሰፖሲቶሪ ወይም ክሬም ጽሁፍ ጋር ያስተያዩ፡፡
- እጅዎትን በሳሙና እና በውሀ ይታጠቡ እና በሙሉ ያድርቁ
- ጓንት ያድርጉ
- አስፈላጊውን መሳሪያ ያዘጋጁ እና ብቸኝነትን ይስጡ፡፡
- ማሸጊያውን ያንሱ እና ለስላሳ እና ዱልዱም የሆነውን ጫፍ ያርጥቡት ወይም የአምራቹን መመሪያ ይመልከቱ፡ ፡ ዱልዱሙ ጫፍ ብዙጊዜ መጀመሪያ ይገባል፡፡ ማርጠብ የፊንጢጣ ጫፍ እነዳይቆጣ ያደርጋል፡፡ ሰፖሲቶሪው በጣም ለስላሳ ከሆነ ማሸጊያውን ከማንሳትዎ በፊት ፍሪጅ ውስጥ ያስቀምጡት፡፡
- ለግመሽ ሰፖሲቶሪ፤ ሰፖሲቶሪውን በቁመቱ ይቁረጡት፡፡
- ባለጉዳይ በአፉ አንዲተነፍስ በማድረግ ዘና እንዲሉ ያበረታቱ፡፡
- ባለጉዳይ የሚመቸውን ቦታ/ሁኔታ እንዲያገኝ ያድርጉ፡፡ ባለጉዳዩ በግራ ጎኑ ተኝቶ ሰፖሲቶሪ ማስገባት በጣም ውጤታማ ነው፡፡ ሆኖም ሰፖሲቶሪ በማንኛውም የመተኛት እነ የመቀመጥ አኳኋን ማስገባት ይቻላል፡፡

ቅደም ተከተል 3፤ አሰራሩን መጨረስ፡፡

- ስራ-የሚሰሩበት እጅዎት አመልካች-ጣት ጓንተ ላይ ያርጥቡት፡፡
- ሰፖሲቶሪውን ዱልዱም በሆነው ጫፍ መጀመሪያ ወይም በአምራቹ መመሪያ መሰረት ጓንት የተደረገበትን የአመልካች ጣት በመጠቀም በቀስታ በፊንጢጣ ግርግዳ በኩል ወደፊንጢጣ ያስገቡ፡፡
- ሰፖሲቶሪውን በአማካይ 4 ኢንች ወደ ፊንጢጣው ያስገቡ፡፡
- ሰፖሲቶሪውነ ወደሰገራ መጨመር ያስወግዱ፡፡
- የባለጉዳዩን መቀመጫ ለጥቂት ደቂቃዎች አጣምረው ይያዙ፡፡
- ሰፖሲቶሪው እንዲቆይ ባለጉዳዩ ቢያንስ ለ5 ደቂቃ በነበረበት እንዲንጋለል ያድርጉ፡፡
- ሰፖሲቶሪው ቢያንስ ከ 30 እስከ 40 ደቂቃ ወይም በአምራቹ መመሪያ መሰረት መያዝ አለበት፡፡
- የፊንጢጣ ክሬም፤ የማስገቢያውን ጫፍ ወደ ፊንጢጣው ያስገቡ እና ክሬሙን ለመቀባት ቲዩቡን ይጭመቁት፡፡
- ማስገቢያውን ያውጡ፡፡ በሙቅ የሳሙና ውሀ ይጠቡት እና ከማስቀመጥዎት በፊት በደንብ ያድርቁት፡፡
- ጓንት ያስወግዱ፡፡
- እጅዎትን በሳሙና እና በውሀ ይታጠቡ እና በሙሉ ያድርቁ

ቅደም ተከተል 4፤ መድሀኒት አሰጣጡን መመዝገብ፡፡

ቅደም ተከተል 5፤ ባለጉዳዩ ለመድሀኒቱ ያለውን ምላሽ እና የጎንዮሽ ችግር ይከታተሉ፡፡

የማህጸን ሰፖሲቶሪ ወይም ክሬም

መግቢያ

ይህ ክፍል**የማህጸን ሰፖሲቶሪ ወይም ክሬም መድሀኒት አሰጣጥ መሰረታዊ አሰራሩን ይሸፍናል፡፡**

ይህ አጠቃለይ መረጃ ብቻ ነው፡፡ ለእያንዳዱ ባለጉዳዩ ሀላፊነት በሚሰጠው RN የተገለጸውን የተለየ መመሪያ ሁልጊዜ ይከተሉ፡፡

አሰራር፤ የማህጸን ሰፖሲቶሪ ወይም ክሬም

ቅደም ተከተል 1፤ ባለጉዳዩን ይገምግሙ፡፡

- ባለጉዳዩ እንዴት እንደሆነ ይጠይቁ፣ ማንኛውም አይነት ለውጥ የሚሰማው ከሆነ ይወቁ፤ ለምሳሌ ማሳከክ፣ ማቃጠል ወይም ፍሳሽ፡፡ ማንኛውንም ቅሬታ ይመዝገቡ፡
- ስለአሰራሩ ከባለጉዳዩ ጋር ይነጋገሩ፡፡

(ወደሚቀጥለው ገጽ የቀጠለ)

ቅደም ተከተል 2፤ ለአሰራሩ መዘጋጀት፡፡

- የተልዕኮውን መመሪያ እና መድሀኒት መሀደሩን ይገምግሙ፡፡
- የመድሀኒቱን መሀደር ከሰፖሲቶሪ ወይም ከሬም ጽሁፍ ጋር ያስተያዩ፡፡
- እጅዎትን በሳሙና እና በውሀ ይታጠቡ እና በሙሉ ያድርቁ
- ጓንት ያድርጉ
- አስፈላጊውን መሳሪያ ያዘጋጁ፡፡
- ሰፖሲቶሪውን ይፍቱት እና በተከፈተው ማሸጊያው ላይ ያስቀምጡት ወይም ማስገቢያው ውስጥ የታዘዘውን ክሬም፣ ጄል ወይም አረፋ ያስገቡ፡፡ በአምራቹ ማስገቢያ ላይ መመሪያ ተሰጥቷል፡፡
- የብቸኝነት ሁኔታ ይስጡ እንዲሁም ከስራው በፊት ባለጉዳዩዋ ፊኛዋን ባዶ እንድታደርግ ያድርጉ፡፡ ፊኛ ባዶ ከሆነ በህክመናው ወቅት ባለጉዳዩዋ የሚሰማት አነስተኛ ጫና ነው እንዲሁም የማህጸን ተደራቢን የመጉዳት እድል ይቀንሳል፡፡
- ባለጉዳዩዋ ጉልበቷን አጥፋ እና ዳሌዋን ወደ ውስጥ አዙራ በጀርባዋ እንድትንጋለል ያግዙ፡፡
- የብልት ቦታው ብቻ እንዲታይ አድርገው ባለጉዳዩዋን በአግባቡ ይሸፍኑ፡፡
- ባለጉዳይ በአፉ አንዲተነፍስ በማድረግ ዘና እንዲሉ ያበረታቱ፡፡

ቅደም ተከተል 3፤ አሰራሩን መጨረስ

- መጀመሪያ የሚገባውን የሰፖሲቶሪውን ዱልዱሙን (ለስላሳውን) ጫፍ ያርጥቡ፡፡
- ስራ ሚሰሩበተን እጅ ጓንት ያለበትን አመልካች ጣት ያርጥቡት፡፡
- የማህጸንን ከንፈር ስራ በማይሰራው እጅዎት በመክፈት የማህጸንን ቀዳዳ ግለጽ ያድርጉት፡፡
- ሰፖሲቶሪውን ከ3-4 ኢንች ወደ ማህጸን የጀርባ ግርግዳ ያስገቡ፡፡
- ክሬም ለማስገባት፤ ማስገቢያውን 2 ኢንች አካባቢ በቀስታ ያስገቡ፡፡ የማስገቢያውን መግፊያ ማስገቢያው ባዶ እስኪሆን ድረስ በቀስታ ይደግፉት፡፡ ማስገቢያውን ያውጡት እና ፎጣ ላይ ያስቀምጡት፡፡ ለአንድ-ጊዘ አገልግሎት የሚውል ማስገቢያ ከሆነ ይጣሉት ወይም በአምራቹ መመሪያ መሰረት ያጽዱት፡፡
- ጓንቱን ከውስጥ ወደውጪ በመገልበጥ ያስወግዱ፡፡ በአግባቡ ይጣሉት፡፡
- እጅዎትን በሳሙና እና በውሀ ይታጠቡ እና በሙሉ ያድርቁ፡፡
- ካስገቡ በኋላ ባለጉዳዩ አልጋ ላይ ከ5 እስከ 10 ደቂቃ እንዲንጋለል ያድርጉ፡፡
- የብልት አካባቢውን በጨርቅ ያድርቁት፡፡ አልጋ ላይ ሚነጠፍ ከተጠቀሙ ያንሱት፡፡
- የእርጥበት መከላከያ ሞዴስ እና መሸፈኛውን ያስወግዱ፡፡ የበዛ ፍሳሽ ካለ ንጹህ ሞዴስ ያድርጉ፡፡

ቅደም ተከተል 4፤ መድሀኒት አሰጣጡን መመዝገብ፡፡

ቅደም ተከተል 5፤ ባለጉዳዩ ለመድሀኒቱ ያለውን ምላሽ እና የጎንዮሽ ችግር ይከታተሉ፡፡

ከጀርም ነጻ የሆነ የቁስል መሸፈኛ መለወጥ

መግቢያ

ይህ ክፍል **ከጀርም ነጻ የሆነ የቁስል መሸፈኛ የመለወጥ** ስራ መሰረታዊ አሰራሩን ይሸፍናል፡፡

ይህ አጠቃለይ መረጃ ብቻ ነው፡፡ እያንዳዱ ባለጉዳይ የተለያየ ስለሆነ ማድረግ ያለብዎት የተለዩ ቅድመ-ተከተሎች ይለያያሉ፡፡ ለእያንዳዱ ባለጉዳዩ ሀላፊነት በሚሰጠው RN የተገለጸውን የተለየ መመሪያ ሁልጊዜ ይከተሉ፡፡

አሰራር፤ ከጀርም ነጻ ያልሆነ የቁስል ሽፋን መቀየር

ቅደም ተከተል 1፤ ባለጉዳዩን ይገምግሙ፡፡

- ስለአሰራሩ ከባለጉዳዩ ጋር ያውሩ
- ባለጉዳዩ እንዴት እንደሆነ ይጠይቁ፣ ማንኛውም አይነት ለውጥ የሚሰማው ከሆነ ይወቁ፡፡ ማንኛውንም ቅሬታ ይመዝገቡ፡ ባለጉዳዩ በአግባቡ እየተመገበ እና በቂ ፈሳሽ እየወሰደ እንደሆነ ይከታተሉ፤ ይህ ለቁስል መዳን ጠቃሚ ነው፡፡

ቅደም ተከተል 2፤ ለአሰራሩ መዘጋጀት፡፡

- የተልዕኮውን መመሪያ ይገምግሙ፡፡
- እጅዎትን በሳሙና እና በውሀ ይታጠቡ እና በሙሉ ያድርቁ
- አስፈላጊውን መሳሪያ ያዘጋጁ፡፡
- ጓንት ያድርጉ

ቅደም ተከተል 3፤ አሰራሩን መጨረስ፡፡

- የነበረውን የቁስል ማሸጊያ ያስወግዱ እና በተገቢው መያዣ ይጣሉት፡፡
- ጓንተ ያውልቁ፣ እጅ ይታጠቡ እና አዲስ ጓንተ ያድርጉ፡፡
- ሀላፊነት በሰጠው RN በታዘዘው መሰረት ቁስሉን ያጽዱት፡፡
- ሀላፊነት በሰጠው RN በታዘዘው መሰረት ቁስሉን ይከታተሉ፡፡
- ሀላፊነት በሰጠው RN በታዘዘው መሰረት ማንኛውንም ቅባት ወይም መድሀኒት ማድረግ፡፡
- ሀላፊነት በሰጠው RN በታዘዘው መሰረት አዲስ ቁስል ማሸጊያ ያድርጉ፡፡
- ጓንት ያስወግዱ፡፡
- እጅዎትን በሳሙና እና በውሀ ይታጠቡ እና በሙሉ ያድርቁ

ቅደም ተከተል 4፤ ሀላፊነት በሰጠው RN በታዘዘው መሰረት ቁስሉን ይከታተሉ እነዲሁም መሸፈኛውን ይቀይሩ እና ይመዝግቡ፡፡

ቅደም ተከተል 5፤ ባለጉዳዩ ለውጥ ወይም ውስብስብነት ካለው ይከታተሉ፡፡

ቁስሉን ይከታተሉ

ቁስል መከታተል

- ቁስል መሸፈኛ ሲነሳ ፍሳሽ እንዳለው ይመልከቱ፡፡
- **ቁስሉ ከጸዳ በኋላ፤** የሚከተለውን ይመልከቱ
  - ቀለም
  - ቁስሉ ከተጸዳ በኋላ የሚቆይ ሽታ (አንዳንድ የቁስል መሸፈኛዎች ሽታ ይኖራዋል)
  - የፈሳሽ መጠን
  - የፈሳሽ ቀጣይነት

- ቁስሉ ከተጸዳ በኋላ የቁስሉን ጫፍ እና የቁስሉን ስር ይግለጹ፡፡ የሚከተሉትን ይመልቱ፤
  - የቁስል መጠን

    "ስሙኒ" ወይም "የብር ሳንቲም" በሚል መጠን ይግለጹት፡፡ ትክክለኛ መሆን የለበትም ግን በተከታታይ ተመሳሳይ መለኪያ መጠቀም አለብዎት (እንደ ኢንች ወይም የ“___” መጠን)
  - የቁስል ቀለም፡ ቀይ፣ ቢጫ ወይም ጥቁር?
  - የቁስል ፈሳሽ

    ካለ፤ እንደ ድሮ ነው ወይም ጠንካራ ሽፋን አለው?
  - የቁስል ጫፍ - ክብ ወይስ ቅርጽ አልባ?
  - ክፍተት አለው (ቆዳ ስር የጎረጎደ)? (የጎረጎዱ ቦታዎችን ጥልቀት እንክብካቤ ሰጪ አይለካም፡፡)

የቁስል ሽፋን መቀየር

- ሀላፊነት የሰጠው RN እንዲጠቀሙ ባሳየዎት መሸፈኛ ቁስሉን ይሸፍኑ፡፡ የተለያዩ አይነቶች መሸፈኛዎች አሉ፡፡ እያንዳዱ የተለያየ አላማ አለው እንዲሁም መጠቀም ያለብዎት ሀላፊነት የሰጠው RN ባሳይዎት መሰረት ብቻ ነው፡፡
- ሀላፊነት የሰጠው RN በጠየቀው ቁጥር ልክ ቁስል ክትትሉን ይመዝግቡ፡፡ ቁስሉ ላይ ያልተለመደ ነገር ካለ ሀላፊነት ለሰጠው RN ያሳውቁ፡፡

.የግሉኮሜትር ምርመራ

መግቢያ



ይህ ክፍል **የግሉኮሜትር ምርመራ** መሰራታዊ አሰራሮችን ይሸፍናል። ግሉኮሜትር የሰጠውን የደም ስኳር የምንለካበት ማሽን ነው። የስኳር በሽታ ላለባቸው ባለጉዳዮች እንክብካቤ ለመስጠት ለበለጠ መረጃ ገጽ 46 ላይ የስኳር በሽታ ክፍልን ይገምግሙ።

ይህ የግሉኮሜትር ምርመራ አሰራር አጠቃላይ መረጃ ነው። ለእያንዳዱ ባለጉዳዩ ሀላፊነት በሚሰጠው RN የተገለጸውን የተለየ መመሪያ ሁልጊዜ ይከተሉ።

አሰራር፤ የግሉኮሜትር ምርመራ

ቅደም ተከተል 1፤ ባለጉዳዩን ይገምግሙ

- ስለግሉኮሜትር ምርመራው ከባለጉዳዩ ጋር ይነጋገሩ።
- ባለጉዳዩ እንዴት እንደ ሆነ ይጠይቁ፣ ማንኛውም አይነት ለውጥ የሚሰማው ከሆነ ይወቁ።
- ደም ከየት መውሰድ እንዳለብዎት ባለጉዳዩን ይጠይቁ። ብዙ ጊዜ ደም የሚወሰደው ከጣት ላይ ነው። ያበጠ ወይም የተጎዳ ቦታ አይጠቀሙ። ቦታው ሞቃት ቢሆን ጥሩ ነው።

ቅደም ተከተል 2፤ ለአሰራሩ መዘጋጀት።

- የተልዕኮውን መመሪያ ይገምግሙ።
- እጅዎትን በሳሙና እና በውሀ ይታጠቡ እና በሙሉ ያድርቁ።
- አስፈላጊውን መሳሪያ ያዘጋጁ።
- ጓንት ያድርጉ

ቅደም ተከተል 3፤ አሰራሩን መጨረስ።

- ሀላፊነት በሰጠው RN በታዘዘው መሰረት የሰውነቱን ክፍል መውጋት። ለእያንዳንዱ ምርመራ የሚወጉበትን ቦታ ቢቀይሩ ጥሩ ነው።

  ምክር፡ የጣት ጫፍ፣ በጣቱ ጎን በኩል የተሻለ ነው።
- በመሳሪያው አምራች እና ሀላፊነት በሰጠው RN መመሪያ መሰረት ምርመራ ያድርጉ።
- መድማቱን ለማቆም ካስፈለገ በቀጥታ ይጫኑት
- ጓንት ያስወግዱ።
- እጅዎትን ታጥበው ያድርቁ።

ቅደም ተከተል 4፤ ውጤቱን ከቀን እና ሰአት ጋር እንዲሁም ሀላፊነት በሰጠው RN የተጠየቀ ሌላ መረጃ ይመዝግቡ።

- ሀላፊነት በሰጠው RN መመሪያ መሰረት ለውጤቱ ምላሽ ይስጡ።

ቅደም ተከተል 5፤ የተወጋው ቦታ እንዳይቆጣ ክትትል ያድርጉ።

የጋስትሮስቶሚ አመጋገብ

ይህ ክፍል **የጋስትሮስቶሚ** አመጋገብ መሰራታዊ አሰራሮችን እንዲሁም ስለ**አስቶሚ** እንክብካቤ (የጨጓራ-አንጀት ስርአትን በተመለከተ) የበለጠ መረጃ ይሸፍናል።

መግቢያ

አስቶሚ ብዙጊዜ ከአንጀት ወይም ከሽንት ፊኛ ወደ ውጪ የሚወጣ የሆድ ግርግዳ ላይ ያለ ክፍተት ነው። የሚደረገው የአንጀት ወይም የሽንት ስርአቱ ላይ ችግር ሲኖር ነው።

ጋስትሮስቶሚ ከሆድ ግርግዳ በኩል ወደውጪ የሚወጣ ክፍተት ነው። ሰው የመዋጥ ችግር ሲኖርበት በቱቦ ምግብ፣ ፈሳሽ ወይም መድሀኒት እንዲገባ ያደርጋል።

ለእያንዳዱ ባለጉዳዩ ሀላፊነት በሚሰጠው RN የተገለጸውን የተለየ መመሪያ ሁልጊዜ ይከተሉ።

አሰራር፤ የጋስትኖሚ አመጋገብ

ቅደም ተከተል 1፤ ባለጉዳዩን ይገምግሙ።

- ባለጉዳዩ እንዴት እንደሆነ ይጠይቁ፣ ማንኛውም አይነት ለውጥ የሚሰማው ከሆነ ይወቁ።
- ምን እንደሚያደርጉ ለባለጉዳዩ ይንገሩ። ባለጉዳዩ ካልተመቸው እንዲነግርዎት ያድርጉ።

ቅደም ተከተል 2፤ ለአሰራሩ መዘጋጀት።

- የተልዕኮውን መመሪያ ይገምግሙ።
- እጅዎትን በሳሙና እና በውሀ ይታጠቡ እና በሙሉ ያድርቁ
- አስፈላጊውን መሳሪያ ያዘጋጁ።
- ጓንት ያድርጉ

ቅደም ተከተል 3፤ አሰራሩን መጨረስ።

- የቁስል ማሸጊያውን ያስወግዱ - ለመቁረጥ መቀስ በፍጹም እንዳይጠቀሙ።
- ሀላፊነት በሰጠው RN በታዘዘው መሰረት ቱቦውን ማገናኘት።
- ባለጉዳዩ ይቀመጥ ወይም ተንጋሎ ቀና ይበል።
- ጓንት በማድረግ የጋስትሪክ ይዘት ያላቸውን ነገሮች መኖራቸውን እንዲያጣሩ እና በትልቅ ሲሪንጅ እንዲያወጡት ሀላፊነት የሰጠው RN ሊተይቅዎት ይችላል።
- ሀላፊነት በሰጠው RN መመሪያ መሰረት ውሀዱን ወይም መድሀኒቱን ይስጡ።
- ከእያንዳንዱ ምግብ እና መድሀኒት አሰጣጥ **በፊት እና በኋላ** የመመገቢያ ቱቦው ላይ ከ30-60 ሚሊ ውሀ ያፍሱበት።
- ጓንት ያስወግዱ።
- እጅዎትን ይታጠቡ።

ቅደም ተከተል 4፤ ሀላፊነት በሰጠው RN መመሪያ መሰረት አመጋገቡን ይመዝግቡ።

ቅደም ተከተል 5፤ ሀላፊነት በሰጠው RN መመሪያ መሰረት ባለጉዳዩ ላይ ማንኛውም ውስብስብነትን ይከታተሉ።

የምግብ ቱቦ

የምግብ ቱቦ ያለትንታ በራሱ መመገብ ወይም መጠጣት ለማይችል ባለጉዳይ ሆድ ውስጥ የሚገባ ቱቦ ነው፡፡ መመገብ አለመቻል የሚከሰተው በስትሮክ፣ ካንሰር፣ MS ወይም ኮማ ውስጥ በመግባት ነው፡፡

ሁለት አይነት የምግብ ቱቦዎች አሉ፤

- ናሶጋስትሪክ(NG) ቱቦ በአፍንጫ ገብቶ በጉሮሮ አድርጎ ወደ ሆድ የሚገባ ነው፡፡ ይህ ከስትሮክ ወይም ሌላ ድንገተኛ አጋጣሚ በኋላ ሚደረግ ስለሆነ ብዙጊዜ ጊዜያዊ ነው፡፡
- ጋስትሮስቶሚ ቱቦ በሆድ ግርግዳ በኩል በቀጥታ ወደቸጓራ በቀዶጥገና የሚገባ ቱቦ ነው፡፡ አንዳንዶቹ የተለያየ ስም አላቸው፡፡ አንድ የጋስትሮስቶሚ ቱቦ አይነት የ PEG ቱቦ ይባላል፡፡
- ቀስበቀስ ቱቦው በ"ፎሊ አይነት" ቱቦ ወይም ቁልፍ ይቀየራል፡፡ ባለጉዳዩ ያለውን የቱቦ አይነት እና ሰውነት ውስጥ እንዴት እንደተቀመጠ ማወቅ ይረዳዎታል፡፡

ለፈሳሽ ምግብ ምርጥ አሰጣጥ

በምግብ ቱቦ አልሚ ምግብ ሲሰጡ የሚከተሉትን መረጃ ያስታውሱ፡፡

- ባለጉዳዩን በተቻለ መጠን ተሳተፊ ያድርጉት፡፡ የምግብ ሰአት ለብዙ ሰዎች የማህበራዊ ኑሮ አካል የሆኑ ሰአታት ናቸው፡፡ ባለጉዳዩ ምግብ ሲወስድ ከሌሎች ሰዎች ጋር መሆን ወይስ ብቻውን መሆን እንደሚፈልግ ማወቅ አለብዎት፡፡
- የአመጋብ ሂደቱን፣ የምግቡን መጠን፣ የውሀውን መጠን፣ የማስገባት ፍጥነቱን እና ባለጉዳዩ ፈሳሽ ምግቦች ሲሰጠው በምን አይነት አቀማመጥ መሆን እንዳለበት ሀላፊነት ከሚሰጠው RN ጋር በጽሁፍ ማረጋገጥ፡፡
- ባለጉዳዩን ሲያንቀሳቅሱ፣ ሲያጥቡ እና ሲያለብሱ ቱቦውን እንዳይስቡት ጥንቃቄ ያድርጉ፡፡
- ማንኛውንም አለመመቸት ያሳውቁ፡፡
- መቆጥቆጥ፣ መቅላት፣ ማበጥ ወይም ቱቦው በገባበት አካባቢ ፍሳሽ ካለ ይከታተሉ፡፡
- አንዳንዴ ባለጉዳይ የምግብን ጣዕም ለማጣጠም ምግብ አፋ ውስጥ ሊይዙ ይችላሉ ግን መዋጥ አይችሉም፡፡ ይህ ከተፈቀደ ባለጉዳዩ ምን አይነት ምግብ ማጣጣም እንደሚፈልጉ ይጠይቁ፡፡
- ትውከት ወይም ግሳት ካለ ለነርስ ያሳውቁ፡፡
- ባለጉዳዩ የቱቦ ምግብ ሲሰጠው ቀጥ ብሎ ወይም በ30-45 ዲግሪ እንዲቀመጥ እና ምግቡን ከወሰደ በኋላ ለአንድ ሰአት ቀጥ ብሎ እንዲቆይ ያድርጉ፡፡
- የባለጉዳዩ አፍ መድረቁን ወይም ቆዳ መሰነጣጠቅ እንዳለው ይከታተሉ፡፡
- ባለጉዳዩ ጥርሱን እንዲቦርሽ እና የአፍ ማጠቢያ ወይም ሌላ አፍ ማጽጃ ምርቶን ለምሳሌ ሳሊን ስዋብስ እንዲጠቀም ያበረታቱ፡፡ ባለጉዳዩ ጥርሱን ሲቦርሽ ትን ሊለው ስለሚችል ውሀውን እንዳይውጥ ይንገሩት፡፡
- ባለጉዳዩ ጥርሱን ሲቦርሽ ወይም የአፍ ማጠቢያ ሲጠቀም ድነገተኛ መዋጥን ለመከላከል በ90 ዲግሪ አንግል መቀመጥ አለበት፡፡
- "በማስወገድ ሁኔታ" (ጨጓራ ውስጥ የሚገኙ ይዘቶችን በፍጥነት ወደ ትንሹ አንጀት ማውጣት) ምክንያት ብዙ ጊዜ ተቅማጥ ይከሰታል፡፡ ይህ ሲሆን ሀላፊነት የሰጠውን RN ወይም የሚከታተለውን ሀኪም ያነጋሩ፡፡
- በመመሪያው መሰረት መሳሪያውን ያጽዱ፡፡

ውስብስብነት

የሚከተለው ሊከሰት የሚችል ውስብስብነት ዝርዝር ነው፡፡ ከእነዚህ ውስብስብነቶች አንዱ ከተከሰተ ማን መጠራት እንዳበት እርስዎ እና ሀላፊነት የሰጠው RN መወሰን አለባችሁ፡፡

- ቱቦው ከወጣ፡፡
- ቱቦው በገባበት አካባቢ የጋስትሪክ ክምችት ሊፈስ እና ቆዳውን ሊያስቆጣ ስለሚችል የቆዳ መቆጣት ሊከሰት ይችላል፡፡
- ቱቦው በመድሀኒት ወይም በደንብ ስላልተለቀለቀ ሊደፈን ይችላል፡፡
- ሀላፊነት የሚሰጠው RN በተለየ የሚነግርዎት ሌላ ውጤት፡፡

የኦስቶሚ እንክብካቤ

መግቢያ

ይህ ክፍለ **የኦስቶሚ እንክብካቤ** መሰራታዊ አሰራሮችን ይሸፍናል።

ይህ አጠቃለይ መረጃ ብቻ ነው። እያንዳዱ ባጉዳይ ስለሚለያይ የሚሰጠው እንቅስቃሴ ከሰው ሰው ይለያያል። ለእያንዳዱ ባለጉዳዩ ሀላፊነት በሚሰጠው RN የተገለጸውን የተለየ መመሪያ ሁልጊዜ ይከተሉ።

ከግንዛቤ መግባት ያለባቸው

ኦስቶሚ ከአንደኛው የውስጥ አካላችን ጋር የሚገናኝ በሆድ ግርግዳ ላይ የሚገኝ የሰው-ሰራሽ ክፍተት ነው። ይህ የሚደረገው የሰውነት ስርአት አካል ላይ ችግር ሲኖር ነው። ለምሳሌ ሰው በእጢ ምክንያት አንጀቱ ከተደፈነ የቀዶ-ጥገና ሀኪም የሰገራውን መጓጓዣ አካል በሆድ ግርግዳ ላይ ከሚገኝ ክፍተት ጋር ያገናኘዋል። ይህ **ኮሎስቶሚ** ይባላል።

ሰው የመዋጥ ችግር ሲኖርበት ጋስትሮስቶሚ የሚባል ክፍተት ሆድ ላይ መፍጠር ይቻላል ወይም **ዩሮስቶሚ**. የሚባል ክፍተት የሽንት ፊኛ ላይ መፍጠር ይቻላል። ኦስቶሚው ጊዜያዊ ወይም ቋሚ ሊሆን ይችላል።

ክፍተቱ የሚደረግበት ቦታ "**ስቶማ**" ይባላል። የሰገራ ወይም የሽንት ቆሻሻዎች በስቶማው በኩል ወደ ከረጢት ይወጣሉ። ለባጉዳይ በክፍል ወይም ሙሉ የኦስቶሚ እንክብካቤ እነዲሰጡ ሀላፊት ሊሰጥዎት ይችላል።



ባለጉዳዩ ስለኦስቴቶሚው ቁጡ ሊሆን ወይም ሊያፍር ይችላል በተለይ አዲስ ከሆነ። እንክብካቤ ሰጪው አስተያየት ባይሰጥ ወይም ኦስቶሚ እንክብካቤ በማድረጉ ደስተኛ እንዳልሆነ ባለጉዳዩ እንዲሰማው ባያደርግ ጥሩ ነው።

ይህ ክፍል የኮሎስኮሚ እንክብካቤ ላይ በተልዕኮ ስለሚሰራው ስራ እና ያለተልዕኮ ስለሚሰራ ስራ ይገልጻል። ባለጉዳዩ የኮሎስቶሚ ከረጢቱን ለመድፋት፣ ቆሻሻ ለማስወገድ ወይም ከረጢቱን ለማስወገድ እገዛ የሚያስፈልገው ከሆነ እንደ የግል እንክብካቤ ስለሚቆጠር ተልዕኮ አያስፈልገውም።

አንዳንድ ባጉዳዮች የኮሎስቶሚ ከረጢታቸው ቶሎ-ቶሎ እንዲደፋላቸው ይፈልጋሉ ግን መደፋት ያለበት ከረጢቱ ስቶማው ያለበት አካባቢ ያለውን ቆዳ እንዳይስበወ የከረጢቱ ግማሽ ወይም አንድ ሶስተኛ ሲሞላ ነው።

ስቶማው ያለበት አካባቢ ያለውን ቆዳ መንከባከብ ወይም ዋፈር ወይም ስቶማው ያለበት አካባቢ ያለው ቆዳ ጋር የተያያዘ ሌላ ክፍል ከመቀየር ጋር የተያያዘ ማንኛውም ስራ መተላለፍ አለበት።

ዋፈር ወይም ሌላ መሳሪያ ወደ ውጪ በማፍሰስ መዝጊያው በደንብ መዘጋት ሲያቆም ወይም በሀኪሙ ትዕዛዝ መሰረት ለምሳሌ በየሶስት ቀን ይለወጣል። ሀላፊነት የሚሰጠው ነርስ እነዚህን ስራዎች በተመለከተ መመሪያ ይሰጣል።

ቅደም ተከተል 1፤ ባለጉዳዩን ይገምግሙ፡፡

- ስለአሰራሩ ከባለጉዳዩ ጋር ያውሩ ባለጉዳዩ የኦስቶሚ እንክብካቤው የት እንዲደረግ እንደሚፈልግ ያረጋግጡ፡፡ ብዙ ጊዜ መታጠቢያ ቤት ቢደረግ ጥሩ ነው፡፡
- የትም ቢደረግ የባለጉዳዩ የብቸኝነት መብት መከበሩን ያረጋግጡ፡፡
- ባለጉዳዩ እንዴት እደሆነ ይጠይቁ እና ማንኛውም ለውጥ ካለ ይመዝግቡ፡፡

ቅደም ተከተል 2፤ ለአሰራሩ መዘጋጀት፡፡

ተልዕኮ ካስፈለገ የተልዕኮውን መመሪያ ይከተሉ፡፡



- አስፈላጊውን መሳሪያ ያዘጋጁ፡፡
- እጅዎትን በሳሙና እና በውሀ ይታጠቡ እና በሙሉ ያድርቁ፡፡
- ጓንት ያድርጉ

ቅደም ተከተል 3፤ አሰራሩን መጨረስ፡፡

- የነበረውን የኦስቶሚ ከረጢት እና ዋፈር ወይም ሌላ መሳሪያ ከስቶማው ያስወግዱ፡፡
- ሀላፊነት በሰጠው RN ወይም ፈሳሽ መያዣ ከረጢት ላይ ባለው መመሪያ መሰረት ከረጢቱን ያስወግሳ፡፡
- ስቶማው አካባቢ የሚገኝ ማንኛውንም ሰገራ በሶፍት በቀስታ ያስወግዱ፡፡ በመቀጠል ስቶማው አካባቢ ያለውን ቆዳ በሳሙና እና በውሀ ያጽዱት፡፡ በቀስታ በመጫን ያድርቁት፡፡
- ስቶማው ወይም በአካባቢው ያለ ቆዳ ከፍተት፣ መቆጥቆጥ፣ ሽፋታ ወይም ሌላ አይነት ሁኔታ ካለው ሀላፊነት በሰጠው RN መመሪያ መሰረት ይከታተሉ፡፡
- በመመሪያው መሰረት ማነኛውንም ቅባት ያድርጉ፡፡
- ሀላፊነት በሰጠው RN መመሪያ መሰረት አዲስ ከረጢት ያድርጉ፡፡ በርካታ አይነት ያላቸው ከረጢቶች አሉ፡፡ ባለጉዳዩ ስለሚጠቀመው ከረጢት ሀላፊነት የሚሰጠው RN የተለየ መመሪያ ይሰጥዎታል፡፡
- ጓንት ያስወግዱ፡፡
- እጅዎትን በሳሙና እና በውሀ ይታጠቡ እና በሙሉ ያድርቁ

ቅደም ተከተል 4፤ ሀላፊነት በሰጠው RN መመሪያ መሰረት ኦስቶሚ እንክብካቤውን ይመዝግቡ፡፡

ቅደም ተከተል 5፤ ባለጉዳዩ ለውጥ ወይም ውስብስብነት ካለው ይከታተሉ፡፡

ቀጥ-ያለ ንጹህ የሽንት ቱቦ

መግቢያ

ይህ ክፍል ቀጥ-ያለ ንጹህ የሽንት ቱቦ መሰረታዊ አሰራርን ይሸፍናል።

ቀጥ-ያለ ንጹህ የሽንት ቱቦ ሽንት ለማውጣት የሽንት ፊኛ ውስጥ የሚገባ ቱቦ ሲሆን ከዛ በኋላ ይወጣል። ይህ የሚደረገው ሰው የሽንት ፊኛውን ያለቱቦ ባዶ ማድረግ ካልቻለ ነው።

ለእያንዳዱ ባለጉዳዩ ሀላፊነት በሚሰጠው RN የተገለጸውን የተለየ መመሪያ ሁልጊዜ ይከተሉ።

አሰራር፤ ቀጥ-ያለ ንጹህ የሽንት ቱቦ

ቅደም ተከተል 1፤ ባለጉዳዩን ይገምግሙ።

ባለጉዳዩ እንዴት እንደሆነ እና የሚሰማው ለውጥ ካለ ይጠይቁ።

ምን እንደሚያደርጉ ለባለጉዳዩ ያብራሩ። ባለጉዳዩ ምቾት የነሳው ነገር ካለ ወይም ስራውን እንዴት እንደሚሰሩት ምርጫ ካላቸው ይጠይቁ።

ቅደም ተከተል 2፤ ለአሰራሩ መዘጋጀት።

- የባለጉዳዩን የብቸኝነት መብት ይጠብቁ።
- የተልዕኮውን መመሪያ ይገምግሙ።
- እጅዎትን በሳሙና እና በውሀ ይታጠቡ እና በሙሉ ያድርቁ።
- አስፈላጊውን መሳሪያ ያዘጋጁ።
- ጓንት ያድርጉ

ቅደም ተከተል 3፤ አሰራሩን መጨረስ፡፡

- ባለጉዳዩ ምቹ የመቀመጥ ወይም የመንጋለል ቦታ እንዲይዙ ያግዙ፡፡
- ሀላፊነት በሰጠው ነርስ መመሪያ መሰረት የብልት ቦታን ወይም የወንድ ብልቱን ጫፍ ያጽዱ፡፡
- የዩሬትራውን መክፈቻ ፈልገው ያግኙት፡፡
- ቱቦውን ውሀ ውስጥ በሚሟሟ ማለስለሻ ለምሳሌ KY ጄሊ ያርጥቡት፡፡
- ቱቦውን የዩሬትራ ክፍተት ውስጥ በማስገባት ወደፊኛው ያስገቡት፡፡ ይህ ለወንዶች በአማካይ 9 ኢንች ሲሆን ለሴቶች ደግሞ 2½ እስከ 3ኢንች ይሆናል፡፡ ቱቦው ፊኛ ውስጥ መግባቱን የሚያውቁት በቱቦው ጫፍ ሽንት መምጠት ሲጀምር ነው፡፡
- ባለጉዳዩ በቀስታ እና በጥልቀት እንዲተነፍስ ያድርጉ፡፡ ይህ የፊኛው መከፈቻ ዘና እንዲል ይረዳል፡፡ ቱቦውን ሲከቱ ቀስ ያለ ሆኖም ጠንከር ያለ ሀይል ይጠቀሙ፡፡
- ሽንት መውጣት እስኪያቆም ድረስ ቱቦውን ይያዙት፡፡
- ቱቦውን ያውጡት
- የብልት ቦታን ያጽዱ እና ያድርቁ፡፡

ቅደም ተከተል 4፤ ሀላፊነት በሰጠው RN መመሪያ መሰረት የሽንት ቱቦ ስራውን ይመዝግቡ፡፡

ቅደም ተከተል 5፤ ሀላፊነት በሰጠው ነርስ መመሪያ መሰረት ባለጉዳዩ ውስብስብነት ካለው ይከታተሉ፡፡

እዚህ ጋር መጽሀፉን ማንበብያቁሙ፡፡

ህክምና የሚለውን የቪድዮውን ክፍልይመልከቱ፡፡

ወደ ድህረ-ገጽ የሚወስደውን መገናኛ ይከተሉ፡፡ በትምህርት መደዳ ስር የነርስ ተልዕኮ ወደሚለው ያውርዱ፡፡ በመረጡት ቋንቋ ላይ ይጫኑ፡፡ ማየት የሚፈልጉትን ቪድዮ ይምረጡ፡፡ www.dshs.wa.gov/altsa/training/dshs-curriculum-available**፡፡**

የልምምድ ትምህርት አጭር መግለጫ

ማጠቃለያ

በዚህ ክፍል የልምምድ ፈተና በመውሰድ በመጽሀፉ የተሸፈኑትን መረጃዎች ይገመግማሉ።

ይህን ፈተና እንደማጥኛ መማሪያ ይውሰዱት። የፈተና ጥያቄዎች እንዴት እንደሚጻፉ እና መገምገም ያለብዎት ቦታን እዲያውቁ ይረዳዎታል።

የልምምድ ፈተና ከመጨረሻው ፈተና ረዥም ጊዜ ይወስዳል እንዲሁም ከበድ ይላል። ስለዚህ አንዴ የልምምድ ፈተና ከጨረሱ በኋላ የመጨረሻ ፈተናውን በስኬታማነት ለመጨረስ ዝግጁ ይሆናሉ።

ትምህርት መጨረስ

ይህን የልምምድ የትምህርት ፈተና ከጨረሱ በኋላ ስልጠናውን ለማጠናቀቅ እና የምስክር ወረቀትዎን ለማግኘት የሚያስፈልገውን የመጨረሻ ቅደም-ተከተል ለመውሰድ ዝግጁ ነዎት።

ትምህርቱን ለመጨረስ የሚከተሉትን ማድረግ አለብዎት፤

- መጽሀፉን የሰጥዎት አስተማሪ ፈተናዎትን እንዲያስቀጥርልዎት ማነጋገር።
- ፈተናውን በ80% ወይም በተሸለ ማለፍ።
- የተማሪ ግምገማዎትን ለአስተማሪው መስጠት።
- መጽሀፍዎትን ለግምገማ በጊዜያዊነት መስጠት (ይህ ሚደረገው የተግባር ልምምድ ላይ የሰሩትን ለመገምገም ነው)።

የመጨረሻው ፈተና እንዴት ነው?

የመጨረሻው ፈተና ላይ 20 ጥያቄዎች አሉ። እውነት ወይም ውሸት፣ ምርጫ፣ ማዛመድ እና ባዶ ቦታ መሙላት አለው።

ለፈተና መዘጋጀት

ለመጨረሻ ፈተና ለመዘጋጀት፤

- መጽሀፉ ላይ ያለውን ትምህርት ይገምግሙ።
- በእያንዳንዱ ትምህርት መጨረሻ ላይ የሚገኘው የትምህርት ማጠቃለያውን ያጥኑ። ማስታወስ ያለብዎት መረጃ በትምህርት ማጠቃለያው ላይ ያለው ነው።
- ለእያንዳንዱ ትምህርት ቪድዮውን ይገምግሙ።
- የትምህርቱን የልምምድ ፈተና ይውሰዱ።
- በመጽሀፉ የመልስ ቁልፍ ክፍል የሚገኘውን መልስ ይገምግሙ።
- ከብዶዎት የነበረውን ቦታ በድጋሚ ይመልከቱ።

እነዚህን ቅደም-ተከተሎች ካደረጉ በኋላ ለመጨረሻው ፈተና በደንበ ዝግጁ ይሆናሉ።

መጽሀፉን ማንበብ እዚህ ጋር ያቁሙ።

ዝግጁ ሲሆኑ፤ በሚቀጥለው ገጽ ላይ የሚገኘውን የልምምድ ትምህርት ፈተና ይስሩ። የልምምድ ትምህርት ፈተናውን መጽሀፍዎትን ሳያዩ ይስሩ።

የተግባር ፈተና

1. ለነርስ ተልዕኮ መሟላት ያለባቸው አምስት ሁኔታዎች ምንድን ናቸው?

   1. _____
   2. _____
   3. _____
   4. _____
   5. _____

2. ለእርስዎ የማይሰጡ አራት የተለዩ ስራዎችን ይግለጹ፡፡

   1. _____
   2. _____
   3. _____
   4. _____

3. የተልዕኮ ስራ ለመቀበል ብቁ ለመሆን አራቱ መስፈርቶች ምንድን ናቸው?

   1. _____
   2. _____
   3. _____
   4. _____

4. ተልዕኮ የሚሰጥበት አራት ሁኔታዎች አሉ፡፡ ምንድን ናቸው?

   1. _____
   2. _____
   3. _____
   4. _____

5. የማዕከላዊ መስመር መደስ ስራ ለነርስ ረዳት ወይም ለቤት ውስጥ እንክብካቤ ሰጪ ረዳት ሊሰጥ ይችላል፡፡

   ☐ እውነት ☐ ሀሰት

6. ፈቃድ ያለው የተግባር ነርስ ለነርስ ረዳት ወይም ለቤት ውስጥ እንክብካቤ ሰጪ ረዳት ስራ መስጠት ይችላል፡፡

   ☐ እውነት ☐ ሀሰት

7. በተልዕኮ ሂደት ውስጥ ሀላፊነት የሚሰጥው RN ሀላፊነት የሆነ ስራ ይግለጹ፡፡

1. _____

8. ተልዕኮ ሲየገኙ የእርስዎ ሀላፊነት የሆኑ ሁለት ነገሮች ምንድን ናቸው?

1. _____

2. _____

9. የባለጉዳዩ ሁኔታ ላይ ለውጥ ካለ የነርስ ረዳት ወይም የቤት ውስጥ እንክብካቤ ሰጪ ረዳት ወዲያው ሀላፊነት ለሰጠው RN ማሳወቅ አለበት፡፡

☐ እውነት ☐ ሀሰት

10. በማንኛውም ምክነያት የተልዕኮ ስራ መስራት ካልቻሉ ምን ማድረግ አለብዎት?

_____

_____

11. የእድገት ውስንነት ሁለት ምሳሌዎች ምንድን ናቸው?

1. _____

2. _____

12. መጽሀፉ ላይ ከተገለጹት ዘጠኝ የሰውነት ስርቶች አራቱን ይግለጹ፡፡

1. _____

2. _____

3. _____

4. _____

13. ከላይ ለተገለጹት አራት የሰውነት ስርአቶች አንድ የጋራ ችግር ይግለጹ፡፡

1. _____

2. _____

3. _____

4. _____

14. የስኳር በሽታ ሜሊተስ የትኛውን የሰውት ስርአት ያጠቃል?

_____

15. መድሀኒት ምንድን ነው?

_____

16. ሁለቱ የመድሀኒት አይነቶች ምንድን ናቸው? ለእያዳንዱ ማብራሪያ ይስጡ፡፡

1. _____

_____

2. _____

_____

17. የፕሮግራም መድሀኒቶች ቁጥጥር የሚደረግባቸው ንጥረ ነገሮች ይባላሉ፡፡ አደገኛ ሊሆኑ ይችላሉ እዲሁም አለአግበብ ጥቅም ላይ ለመዋል እድላቸው ሰፊ ነው፡፡ የዚህ አይነት መድሀኒት አንድ ምሳሌ፤

_____

18. የመድሀኒት ስራ ላይ ተጽዕኖ ያላቸው ሶስት ምክንያቶች ምንድን ናቸው?

1. _____

2. _____

3. _____

19. _____ የመድኒት ህክመና አላማ አካል ያልሆኑ፣ ያላታሰቡ ውጤቶች ናቸው፡፡

20. _____ ቀደም ብሎ፣ በተመሳሳይ ሰአት ወይም ሌላ መድሀኒት ከተሰጠ በኋላ የተሰጠ መድሀኒት የአንዱን ወይም የሁለቱንም መድሀኒት ውጤት/ተጽዕኖ ሲቀይረው ነው፡፡ የአንዱን ወይም የሁለቱንም መድሀኒት ውጤት/ተጽዕኖ ሊጨምር ወይም ሊቀንስ ይችለል፡፡

21. በአፍ መድሀኒት የመስጠት ስራ ሲሰጥዎት ኪኒኑን ባለጉዳዩ አፍ ውስጥ ማስቀመጥ ይችላሉ፡፡

☐ እውነት ☐ ሀሰት

22. የመድሀኒት አሰጣጥ መንገድ መድሀኒቱ ሚሰጥበት መንገድ ነው፡፡

☐ እውነት ☐ ሀሰት

23. ከስር የሚገኙትን እያንዳንዱን መንገዶች ከትክክለኛው ማብራሪያው ጋር መስመር በመሳል ያዛምዱ

መንገድ	**ማብራሪያ**
ፊንጢጣ	በአፍ ተወስዶ የሚዋጥ
ምላስ	ቆዳን በመርፌ በመውጋት መድሀኒት ወደ ጡንቻ፣ ቆዳ ስር ወይም ወደደም ስር ማስገባት
መርፌ	በአፍንጫ፣ ጉሮሮ እና ሳንባ የሚረጭ ወይም በትንፋሽ ሚወሰድ
አፍ	በፊንጢጣ የሚገባ
በትንፋሽ የሚወሰድ	ምላስ ስር የሚቀመጥ
የማህጸን	ቆዳ ወይም ሙኮስ ሜምብሬን ላይ በቀጥታ ሚደረግ
ወቅታዊ	በማህጸን የሚገባ

24. በመድሀኒት መያዣ ጽሁፍ ላይ ሁልግዜ መገለጽ ያለበት ሁለት ነገር ግለጽ፡፡

1. _____

2. _____

25. የመድሀኒት አሰጣጥ አምስት ትክክለኛ ሁኔታዎች ግለጹ፡፡

1. _____

2. _____

3. _____

4. _____

5. _____

26. ከስር ቁጥር በተሰጠው ቦታ ላይ በመድሀኒት አሰጣጥ ሂደት ውስጥ እነዚህን አምስት ቅድመ-ተከተሎች እነደቀዳሚነታቸው ግለጹ። (#1 የመጀመሪያው ቅደም-ተከተል ነው፣ #2 ሁለተኛው ቅደም-ተከተል ነው ወዘተ።)

የመድሀኒት አሰጣጥ መመዝገብ

መድሀኒት መስጠት

ባለጉዳይ መገምገም

የመድሀኒቱን ውጤቶች ለማየት ባለጉዳይን መከታተል

መድሀኒት ማዘጋጀት

1. _____

2. _____

3. _____

4. _____

5. _____

27. የመድሀኒት አሰጣጥን በተመለከተ ባለጉዳዮች ያሏቸው ሁለት አስፈላጊ መብቶች አሉ።

ባለጉዳይ መድሀኒት ወይም ህክምና _____ አለው።

መድሀኒት _____ ሲሰጥ ባለጉዳይ አለው።

28. ፍሪጅ ውስጥ የመድሀኒት ማስቀመጫ ከ _____ መለየት አለበት።

29. ግሉኮሜትር መመርመሪያ በሰው ደም ውስጥ _____ ይለካል።

የመልስ ቁልፉ በሚቀጥለው ገጽ ላይ ነው። መልስዎትን ለመገምገም ይጠቀሙት እና ማወቅ ያለብዎትን ቦታ ያጥኑ።

ጀርባዎትን መታ-መታ ያድርጉ። በርትተው ሲሰሩ ነበር!

የልምምድ ትምህርት ፈተናመልስ ቁልፍ

ይህን የመልስ ቁልፍ መልስዎትን ለማረም ይጠቀሙበት። ከጥያቄው ቀጥሎ የሚያገኙት የገጽ ቁጥር መጽሀፉ ላይ መረጃ ሚያገኙበት ቦታ ነው።

1. ለነርስ ተልዕኮ መሟላት ያለባቸው አምስት ሁኔታዎች ምንድን ናቸው? **ገጽ 9**

1. ፈቃድ ያለው የተመዘገበ ነርስ ስራን ያስተላልፋል።

2. የማይተላለፉ ሶስት የተለዩ ስራዎች አሉ።

3. ተልዕኮ ለአንድ ባለጉዳይ የተለየ ስራን ይሸፍናል።

4. ብቁ የነርስ ረዳት ወይም የቤት ውስጥ እንክብካቤ ሰጪ ረዳት ብቻ የተልዕኮ ስራን መቀበል ይችላል

5. ተልዕኮ መሰጠት የሚችለው በአራት የማህበረሰብ ሁኔታዎች ውስጥ ነው።

2. ለእርስዎ የማይሰጥዎ አራት የተለዩ ስራዎችን ይግለጹ። **ገጽ 9**

1. መርፌ ፣ ከኢንሱሊን ሌላ

2. ከጀርም ነጻ የሆነ አሰራር

3. ማዕከላዊ መስመር መያዝ

4. የነርስ ውሳኔ የሚፈልግ ስራ

3. የተልዕኮ ስራ ለመቀበል ብቁ ለመሆን አራቱ መስፈርቶች ምንድን ናቸው? **ገጽ 10**

1. በዋሽንግተን ግዛት ውስጥ HCA፣ NA-R ወይም NA-C መሆን።

2. ለተልዕኮ የሚያስፈልገውን የትምህርተ መስፈርት ማሟላት።

3. የሚሰጠውን የተለየ ስራ ለመስራት ፈቃደኛ መሆን።

4. የሚ ሰጠውን ስራ በትክክል እና ሀላፊነት ከሚሰጠው RN ቀጥተኛ ቁጥጥር ሳይኖር ለመስራት ብቃትዎን ያሳዩ።

4. ተልዕኮ የሚሰጥበት አራት ሁኔታዎች አሉ። ምንድን ናቸው? **ገጽ 14**

1. የምስክር ወረቀት ያላቸው የማህበረሰብ መኖሪያ መርሀግብሮች የእድገት ውስንነት ላለባቸው።

2. ፈቃድ ያለው የአዋቂ ቤተሰብ ቤት።

3. ፈቃድ ያለው እገዛ የሚደረግለት መኖሪያ ቦታ።

4. ቤት ውስጥ።

5. ማዕከላዊ መስመር የመያዝ ስራ ለነርስ ረዳት/የቤት ውስጥ እንክብካቤ ሰጪ ረዳት መሰጠት ይችላል (**ገጽ 9**)

ሀሰት

6. ፈቃድ ያለው የተግባር ነርስ ስራ ለነርስ ረዳት/የቤት ውስጥ እንክብካቤ ሰጪ ረዳት መሰጠት ይችላል። **ገጽ 9**

ሀሰት

7. በተልዕኮ ሂደት ውስጥ ሀላፊነት የሚሰጠው RN ሀላፊነት የሆነ አንድ ነገር ይግለጹ። (**ገጽ 15**)

ከእነዚህ መካከል አንዱ ትክክል ነው፤

ለተልዕኮው ከባለጉዳዩ ወይም ፈቃድ ያለው ተወካይ የጽሁፍ ስምምነት ማግኘት።

ስራውን መስጠት።

ተልዕኮውን መቆጣጠር።

ተልዕኮውን መተው ወይም መሰረዝ።

8. ተልዕኮ ሲሰጥዎት ያለብዎት ሁለት ሀላፊነቶች ምንድን ናቸው? (**ገጽ 17**)

ከሚከተሉት አንዱ ትክክል ነው፤

የተሰጠውን ስራ በመመሪያ መሰረት መስራት።

ባለጉዳዩ ሊኖረው የሚችለውን የመድሀኒት የጎንዮሽ ችግር፣ የህክመና ምላሽ ወይም ከበሽታ ሚመጣ ውስብስብነት መከታተል።

የባለጉዳዩን ለውጦች በፍጥነት ማሳወቅ።

በተልዕኮው መመሪያ ላይ ለውጥ ሊያስከትል የሚችል ስለአዲስ ወይም የተለወጡ መድሀኒቶች ወይም ህክመናዎች ሀላፊነት ለሰጠው RN ወይም ተቆጣሪዎት ማሳወቅ።

9. የነርስ ረዳት ወይም የቤት ውስጥ እንክብካቤ ሰጪ ረዳት የባለጉዳዩ ሁኔታ ላይ ስላሉ ለውጦች ሀላፊነት ለሰጠው RN ወዲያው ማሳወቅ አለበት። (**ገጽ 17**)

እውነት

10. በማንኛውም ምክንያት የተልዕኮ ስራ መስራት ካልቻሉ ምን ማድረግ አለብዎት? (**ገጽ 18**)

የተልዕኮ ስራ መስራት ካልቻሉ ሀላፊነት ለሰጠው RN እና ለቀጣሪዎት ወዲያው ማሳወቅ።

11. የእድገት ውስንነት ሁለት ምሳሌዎች ምንድን ናቸው? (**ገጽ 30**)

    ከሚከተሉት ሁለቱ ትክክለኛ መልስ ናቸው፤

    የአእምሮ ጉዳት

    የሰረብራል ዝለት

    የሚጥል ህመም

    ኦቲዝም

    አዕምሮ ዝግመት

12. *መጽሀፉ ላይ ከተገለጹት ዘጠኝ የሰውነት ስርአቶች አራቱን ይግለጹ።* (**ገጽ 32**)

    ከሚከተሉት አራቱ ትክክለኛ መልስ ናቸው፤

    ልብ

    አተነፋፈስ

    ቆዳ

    ሽንት ወይም ብልት-ሽት መሽናት

    ዝግ እጢ

    ነርቭ

    ጡንቻ-አጥንት

    የስሜት ህዋሳት

13. ከላይ ለተገለጹት አራት የሰውነት ስርአቶች አንድ የጋራ ችግር ይግለጹ።

    *መልስዎትን ለማስተያየት የትምህርት መገምገሚያ ሰንጠረዥ ከ**ገጽ 53-55** ይጠቀሙ።* ለመረጡት የሰውነት ስርአት የተገለጸው ማንኛውም ችግሮች ትክክል ነው።

14. የስኳር በሽታ ሜሊተስ የትኛውን የሰውት ስርአት ያጠቃል? (**ገጽ 46**)

    ዝግ እጢ

15. *መድሀኒት ምንድን ነው?* (**ገጽ 64**)

    በሰው ሰውነት ውስጥ የኬሚካል ስራን የሚቀይር ማንኛውም ውህድ ነው።

16. ሁለቱ የመድሀኒት አይነቶች ምንድን ናቸው? ለእያዳንዱ ማብራሪያ ይስጡ፡፡ (ገጽ 64)

የጽሁፍ መድሀኒቶች መሸጥ ወይም መሰጠት የሚችሉት በማዘዣ ብቻ ነው፡፡
የጽሁፍ ያልሆኑ መድሀኒቶች ያለማዘዣ የሚገዙ መድሀኖቶች ናቸው፡፡

17. የፕሮግራም መድሀኒቶች ቁጥጥር የሚደረግባቸው ንጥረ ነገሮች ይባላሉ፡፡ አደገኛ ሊሆኑ ይችላሉ እዲሁም አለአግበብ ጥቅም ላይ የመዋል እድላቸው ሰፊ ነው፡፡ የዚህ አይነት መድሀኒት ምሳሌዎች፤ (ገጽ 64)

የሚከተሉት በሙሉ ትክክል ናቸው፡ ናርኮቲክ፣ የድብርት፣ አነቃቂ ወይም የሳይኮቴራፒክ መድሀኒቶች፡፡

18. የመድሀኒት ስራ ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ሶስት ምክንያቶች? (ገጽ 66)

ከሚከተሉት ሶስቱ ትክክል ነው፡ እድሜ፣ ጾታ፣ ኪሎ፣ ዘር፣ አካላዊ ሁኔታ እና ስሜታዊ ሁኔታ፡፡

19. **Side effects** የመድሀኒት የጎንዮሽ ችግሮች የመድሀኒት የህክምናው አላማ አካል ያልሆነ ሰውነት ላይ ያልታሰበ የመድሀኒት ውጤት ነው፡፡ (ገጽ 66)

20. **የመድሀኒት መቀላቀል** ማለት ቀደም ብሎ፣ በተመሳሳይ ሰአት ወይም ሌላ መድሀኒት ከተሰጠ በኋላ የተሰጠ መድሀኒት የአንዱን ወይም የሁለቱንም መድሀኒት ውጤት/ተጽዕኖ ሲቀይረው ነው፡፡ የአንዱን ወይም የሁለቱንም መድሀኒት ውጤት/ተጽዕኖ ሊጨምር ወይም ሊቀንስ ይችለል፡፡ (ገጽ 67)

21. የአፍ መድሀኒት አሰጣጥ ስራ ሲሰጥዎት ኪኒኑን ባለጉዳዩ አፍ ውስጥ ማስቀመጥ ይችላሉ፡፡ (ገጽ 71)

እውነት

22. የመድሀኒት አሰጣጥ መንገድ መድሀኒቱ ሚሰጥበት መንገድ ነው፡፡
(ገጽ 68 እና 69)

እውነት

23. ከስር ለሚገኙት እያንዳንዱ ማብራሪያዎችከአሰጣጡ መንገድ ትክክለኛ ስም ጋር ያዛምዱት፡፡ **(ገጽ 68)**

መንገድ	**ማብራሪያ)**
ፊንጢጣ	በአፍ ተወስዶ የሚዋጥ
ምላስ	ቆዳን በመርፌ በመውጋት መድሀኒት ወደጡንቻ፣ ቆዳ ስር ወይም ወደደም ስር ማስገባት
መርፌ	በአፍንጫ፣ ጉሮሮ እና ሳንባ የሚረጭ ወይም በትንፋሽ ሚወሰድ
አፍ	በፊንጢጣ የሚገባ
በትንፋሽ የሚወሰድ	ምላስ ስር የሚቀመጥ
የማህጸን	ቆዳ ወይም ሙኮስ ሜምብሬን ላይ በቀጥታ ሚደረግ
ወቅታዊ	በማህጸን የሚገባ

24. በመድሀኒት መያዣ ጽሁፍ ላይ ሁልግዜ መገለጽ ያለበት ሁለት ነገር ግለጽ፡፡ **(ገጽ 70)**

ከሚከተሉት ሁለቱ ትክክል ናቸው፤

የባለጉዳይ ስም፣ የመድሀኒት ስም፣ መጠን፣ መንገድ፣ ፕሮግራም እና የአገልግሎት ማብቂያ ጊዜ፡፡

25. የመድሀኒት አሰጣጥ አምስት ትክክለኛ ሁኔታዎች ግለጹ፡፡ **(ገጽ 72)**

1. ትክክለኛ ባለጉዳይ

2. ትክክለኛ መድሀኒት

3. ትክክለኛ መጠን

4. ትክክለኛ መንገድ

5. ትክክለኛ ሰአት

26. ከስር ቁጥር በተሰጠው ቦታ ላይ በመድሀኒት አሰጣጥ ሂደት ውስጥ እነዚህን አምስት ቅደም-ተከተሎች እነደ ቀዳሚነታቸው ግለጹ፡፡ **(ገጽ 73)**

1. ባለጉዳይ መገምገም

2. መድሀኒት ማዘጋጀት

3. መድኒት መስጠት

4. የመድሀኒት አሰጣጥን መመዝገብ

5. መድሀኒቱ ባለጉዳዩ ላይ መስራቱን መከታተል፡፡

27. የመድሀኒት አሰጣጥን በተመለከተ ሁለት አስፈላጊ የባለጉዳይ መብቶች አሉ፡፡ (ገጽ 75)

    ባለጉዳይ መድሀኒት ወይም ህክመና ያለመውሰድ መብት አለው፡፡

    መድሀኒት ሲሰጥ ባለጉዳይ የብቸኝነት መብት አለው

28. ፍሪጅ ውስጥ መድሀኒት ማስቀመጫ **ከምግብ ማስቀመጫ**መለየት አለበት፡፡ (ገጽ 77)

29. ግሉኮሜትር መመርመሪያ በሰው ደም ውስጥ ያለውን **ስኳር**ይለካል፡፡ (ገጽ 98)

መጽሀፉን ማንበብ እዚህ ጋር ያቁሙ፡፡

አሁን መልስዎትን ከልምምድ ፈተናው የመልስ ቁልፍ ጋር አስተያይተዋል፤ የተሳሳቱትን ቦታ እና ጥያቄ ያለበትን መንኛውንም ቦታ ያጥኑ፡፡

ባገኙት እውቀት አንዴ ከተማሙኑ የመጨረሻ ፈተናዎትን ለማስቀጠር ዝግጁ ነዎት፡፡

ለሰሩት ከባድ ስራ እንኳንደስ አለዎት!

የቃላት መፍቻ

የቃላት	ማብራሪያ
አለርጂ	ሰውነት ለመድሀኒት፣ አቧራ፣ ሻጋታ፣ የአበባ ብናኝ ወይም በአካባቢው ላሉ ሌሎች ነገሮች የሚሰጠው ምላሽ ነው። ምላሹ ማሳከክ፣ ማስነጠስ፣ የአፍንጫ መታፈን፣ ሽፍታ እንዲሁም ማቃተት እና ሌሎች ምልክቶችን ያካትታል።
የአልዛይመር በሽታ	መርሳት እና የአዕምሮ ችሎታ ማነስን የሚያስከትል እየባሰ ሚሄድ በሽታ ነው። የመጀመሪያው ምልክት መርሳት ነው።
አምቡሌት	መራመድ።
አነስ	ሰገራ የሚያልፍነት የፊንጢጣ መከፈቻ።
አርተሪያል አልሰር (የስኳር በሽታ አልሰር)	ከአርተሪ ወደ እግር የደም ፍሰት ባለመኖሩ የእግር መርገጫ እና የታችኛው እግር ላይ የሚታይ ህመም።
አርተሪ	ኦክሲጂን ያለው ደም ከልብ ወደ ሰውነት ህዋሶች የሚያስተላልፍ የደም ስር።
አርትራይተስ	የመገጣጠሚያዎች ህመም። የአርትራይተስ ዋና አይነቶች ኦስቲዮአርትረይተስ፣ ሪሁማቶይድ አርትራይተስ እና ጎውት ናቸው።
አስም	የመተንፈሻ ስርአት በአካባቢው ላሉ ነገሮች ለምሳሌ ብክለት፣ የአበባ ብናኝ ወይም አቧራ ምላሽ የሚሰጥበት ችግር ነው። ምልክቶቹ የመተንፈስ ችግር፣ ማቃተት እና ሳልን ያካትታሉ።
ቤድሶር	በክብደት ምክነያት የደም ዝውውር ባለመኖሩ ከስር ያለው ቆዳ እና ህዋስ የሚሞትበት ቦታ ነው። በተጨማሪ **የክብደት ህመም** ወይም **ዲኩቢተስ አልሰር ይባላል**።
ደም	ኦክሲጂን፣ ካርቦን ዳይኦክሳይድ፣ አልሚ ምግብ፣ በሽታ መከላከያ እና ቆሻሻ ከ እና ወደ ህዋስ የሚያስተላልፍ የሰውነት ፈሳሽ ነው። ደም ቀይ የደም ሴል፣ ነጭ የደም ሴል፣ ፕሌትሌት እና በሽታ መከላከያን ይይዛል።
የደም ስር	በሁሉም የሰውነተ አካል የሚገኝ፣ የተለያየ መጠን ያላቸው ለስላሳ እና ተጣጣፊ ቱቦዎች ስብስብ ነው።
የበብል እሽግ	በተጨማሪ የቢንጎ ካርድ ይባላል ፣ ይህ የካርድቦርድ ካርድ የቢንጎ ካርድ ይመስላል እንዲሁመ ለእያንዳንዱ የመድሀኒት መጠን የላስቲክ በብሎች መደዳ አለው።
ቃጠሎ	በእሳት፣ ጸሀይ፣ ኬሚካል፣ ትኩስ ነገር፣ ትኩስ ፈሳሽ ወይም በኤሌክትሪክ የሚከሰት የቆዳ ላይ ጉዳት ነው። ቆዳው በተቃጠለበት ጥልቀት መሰረት ቃጠሎ በምድብ ይገለጻል።
ካፒላሪስ	አርተሪ እነ ቬይን የሚያገናኙ ትናንሽ የደም ስሮች።
ካርድዮፑልመናሪ (CPR) ሪሱሳይቴሽን	ልብ የመምታት ስራውን ድጋሚ እንዲጀምር ማድረጊያ መንገድ፤ ልዩ ስልጠና ያስፈልጋል CPR መስራት።
የልብ ስርአት	ልብ፣ ደም ስር እና ደምን ይይዛል። ዋና አላማው ለተለያዩ የሰውነት አካሎች ኦክሲጂን ለማድረስ እና ካርቦን ዳይኦክሳይድ ለማስወገድ ደም ማዘዋወር ነው።
ካርቲሌጅ	ምቹ እንቅስቃሴን የሚያስችል አጥንት መጨረሻ ላይ የሚገኝ መጋጠሚያ ላይ የሚገኝ ጠንካራ ህዋስ።

የቃላት መፍቻ

ሰረብራል ቫስኩላር አደጋ (CVA)	አዕምሮ ውስጥ የደም ስር ሲፈነዳ ወይም ሲደፈን እና የአዕምሮ አካል ደም እንዳይደርሰው ሲከለከል ነው። እነዲሁም ስትሮክ በመባል ይታወቃል።
ስርየሰደደ ኦብስትራክቲቭ የፐልሞናሪ በሽታ (COPD)	እየባሰ የሚሄድ እና የማይድን የሳንባ በአግባቡ ስራ አለመስራት። ከሚከተሉት በሽታዎች አንዱ ሊመጣ ይችላል፡ ስርየሰደደ ብሮንካይተስ፣ ፐልሞናሪ ኢምፋይሴማ እና አስም። በጣም የተለመደው ምክንያት ማጨስ ነው።
ኮሎን	ትለቁ አንጀት።
ኮላይተስ (የሚቆጠቁጥ የሰገራ እንቅስቃሴ)	የትልቁ አንጀት መቆጣት።
ኮሎስሚ	ከኮሎን ወደውጪ በሆድ ግርግዳ የሚወጣ ሰው-ሰራሽ ክፍተት።
የታፈነ ልብ ድካም (CHF)	ልብ ለሙሉው ሰውነት ደም ለመርጨት ጠንካራ ሳይሆን ሲቀር። የልብ ልብ በጣም በዝግታ ደም በመርጨቱ ምክንያት ደም ወደቬይን እና ሰውነት አካል ይመለሳል።
ስር-የሰደደ	ረዥም ጊዜ የሚቆይ።
የኮንጀክቲቫ ከረጢት	ከታችኛው የቅንድን ስር የሚገኝ የአይን ቦታ።
ድርቀት	መደበኛ የሰገራ እንቅስቃሴ አለመኖር።
ተላላፊ	በመመረዝ ከሰው ወደ ሌላ ሰው ሚተላለፍበት ሁኔታ።
ቁጥጥር የሚደረግበት ንጥረ-ነገር	ሱስ ወይም በቀላሉ አለአግባብ አተቃቀምን ሊያስከትሉ ስለሚችሉ ልዩ ህገ ያላቸው መድሀኒቶች። ናርኮቲክ እና አንዳድ የእንቅልፍ መድሀኒቶች ምሳሌዎች ናቸው።
ኮርኒያ	ግለጽ የሆነ የአይን ኳስ የውጪው መሸፈኛ።
ማስወገድ	ከቁስል ላይ የሞቱ ህዋሶችን ማንሳት ።
ዲኩቢተስ አልሰር	በክብደት ምክንየት የደም ዝውውር ባለመኖሩ ከስር ያለው ቆዳ እና ህዋስ የሞተበት ቦታ። ከክብደት ህመም ወይም አልጋ ላይ ረዥም ጊዜ በመተኛት ከሚመጣ የቆዳ መቆጣት ጋር ተመሳሳይ ነው።
የመረቀዘ ቁስል	በቀዶ-ጥገና የሚመጣ፣ በትክክል ያልዳነ እና የተከፈተ ቁስል ነው። ይህ ከውስጥ ወደውጪ ቀስብሎ ይድናል።
ድርቀት	ሰውነት በቂ ውሀ ያላገኘበት ሁኔታ። ይህ በርካታ ውሀ በላብ ከማውጣት፣ ተቅማጥ ወይም ማስታወክ ወይም በቂ ፈሳሽ ካለመውሰድ የሚመጣ ነው።
ማስተላለፍ	ለአንድ ባለጉዳይ አንድ ስራ በተለየ ቦታ እንዲሰራ RN ብቁ ለሆነ የነርስ ረዳት ወይም የቤት ውስጥ እንክብካቤ ሰጪ ረዳት ሀላፊነት ያዘዋውራል።
የመርሳት በሽታ	በአዕምሮ ህዋሶች መረበሽ እየባሰ የሚሄድ በሽታ ነው። መደበኛው የመረዳት፣ የማስታወስ ወይም የማሰብ መንገድ ይጠፋል። የአልዛይመር በሽታ የተለመደው የመርሳት በሽታ መንስኤ ነው።
ደርሚስ	ከኢፒደርሚስ ተደራቢ ስር የሚገኘው የቆዳ የስረኛው ተደራቢ ነው። ጥቃቅን የደም ስሮች እና የነርቭ መጨረሻዎች ካላቸው አገናኝ ህዋሶች የተሰራ ነው። የጸጉር ቀዳዳ፣ የቅባት እጢ፣ የላብ እጢ እና የስሜት ህዋሳት መልዕክት ተቀባዮችን ይይዛል።
እድገት ውስንነት	ከ18 አመት በፊት የሚጀምር፣ ላልተወሰነ ጊዜ የሚቀጥል እና ትልቅ አካል ጉዳተኝነት የሚያመጣ ሁኔታ ነው። የእውቀት ውስንነት፣ ሰረብራል ዝለት፣ አውቲዝም እና የአዕምሮ ዝግመትን ያካትታል።
የስኳር በሽታ	ሜሊተስ ጣፊያ ምንም ወይም በቂ የሆነ ኢንሱሊን ማምረት አለመቻል ነው። ያለኢንሱሊን ሰውነት ለህዋሶቹ ሀይል ለመስጠት ስኳሩን መጠቀም አይችልም።

መመዝገባ	የሰራውን ስራ መጽሁፍ መመዝገብ።
ስራ-የሚሰራበት እጅ	ለመጻፍ፣ ለመመገብ ወይም ብዙ ነገር ለማድረግ የሚጠቀሙበት እጅ።
መጠን	የሚወሰደው የመድሀኒት መጠን።
ፈሳሽ	ከቁስል፣ ከተመረዘ ቦታ ወይም ከተጎዳ ሰውነት አካል ሚወጣ ነገር።
የዝግ እጢ	ስርአት የሰውነት ስራዎችን ለመቆጣጠር ሆርሞን የሚያከማቹ እጢዎችን ያካትታል። እነዚህ እጢዎች የጣፊያ፣ ፒቲታሪ፣ ታይሮይድ እና ፓራታይሮይድ፣ እሬናል እጢ፣ የሴት እንቁላል እና ቴስቴስን ያካትታል።
ኢንዛይም ምግብ የሚፈጭ ኢንዛይም	የምግብ አፈጫጨት ስርአት ምግብን ወደ አልሚ ምግቦች ለመፍጨት የሚያመርተው ኬሚካል።
የሚጥል በሽታ	ሲዝር ያለበት ሰር-የሰደደ ችግር።
ኢፒደርሚስ	የቆዳ የውጨኛው ተደራቢ።
የሚጥል በሽታ	አዕምሮ ውስጥ የሚገኙ ህዋሶች ያላስፈላጊ መልዕክት ሲልኩ እና ሲዝር ሲያስከትሉ።
ኢፒተሊያላይዜሽን	ቆዳ ድጋሚ ማደግ የሚጀምርበት የቁስል መዳን ደረጃ ነው።
ጉሮሮ	ምግብ ሲውጡ የሚጓዝበት ጉሮሮ።
ኤክሱዴት	ከቁስል ወይም መመረዝ የሚወጣ ፈሳሽ ለምሳሌ ከአይን።
የሰገራ ጫና	ፊንጢጣ ላይ የተያዘ እና በእንቅስቃሴ መውጣት ያልቻለ ሰገራ። ይህ የሚሆነው ሰው ለረዥም ጊዜ ድርቀት ሲይዘው ነው።
ስብራት	የአጥንት ስብራት።
የሀሞት ከረጢት	ጉበት የሚያመርተውን ቢል የሚይዝ ከጉበት አጠገብ የሚገኝ ትንሽ ከረጢት።
የሀሞት ከረጢት በሽታ	ቢል እንዳይወጣ የሚያደርግ የሀሞት ከረጢት መከፈቻ መቆጣት ወይም መደፈን።
የጨጓራ-አንጀት (GI) የስርአት	አፍ፣ ጉሮሮ፣ ጨጓራ፣ አንጀት፣ ጉበት፣ የሀሞት ከረጢት እና ጣፊያ። እነዚህ አካሎች የምንመገበውን ምግብ ወደአልሚ ምግብነት በመለወጥ ቆሻሻ ነገሮችን በሰገራ መልክ ያስወግዳሉ።
የጨጓራ-አንጀት አልሰር	በ GI መስመር ላይ የተቆጣ ወይም ህመም ያለው ቦታ።
ጋስትሮስቶሚ	የሆድ ግርግዳ ላይ ከሆድ ወደውጪ የሚወጣ ክፍተት። ሰው የመዋጥ ችግር ሲኖርበት ምግብ፣ ፈሳሽ ወይም መድሀኒት በቱቦ እንዲወስድ ያስችላል።
አጠቃላይ ስም	ስለመድሀኒት ኬሚካላዊ አሰራር የሚገልጽ የመድሀኒት ስም። ለምሳሌ አሴታሚኖፌን፣ ኢቡፕሮፌን እና ፉሮሴማይድ።
የብልት-ሽንት መሸናት ስርአት	ኩላሊት፣ ዩሬተር፣ የሽንት ፊኛ፣ ዩሬትራ እና የመራቢያ አካሎችን ይይዛል። እነዚህ አካሎች ቆሻሻ ከደም አጣርተው ያወጣሉ፣ ሰውነት ውስጥ ያለውን ውሀ ይቆጣጠራሉ፣ ደም ውስጥ ያለውን የኬሚካል መመጣጠን ይቆጣጠራል እንዲሁም የወንድ እና ሴት ባህሪይ ይሰጣል፤ መራባትን ጨምሮ።
GERD	የጋስትሮ-ኤሶፋጊያል ሪፍሌክስ ችግር "ቃር"። ይህ የሚፈጠረው የጨጓራ ይዘት ወደታችኛው የጉሮሮ ክፍል ሲገባ ነው።

የቃላት መፍቻ

ግሉኮሜትር	ደም ውስጥ ያለውን ስኳር መለኪያ ማሽን ነው።
ግሉኮስ	ደም ውስጥ የሚገኝ የስኳር አይነት።
የቁስል መዳን	አዳዲስ ህዋሶች የሚያድጉበት የቁስል መዳን ደረጃ።
ልብ	ሰውነት ውስጥ ደም የሚረጭ። አራት ክፍሎች ያሉት እንዲሁም ከ ወይም ወደ ቻምበሩ የሚጓዙ ትላልቅ ደም ስሮች ያሉት ጡንቻ ነው።
የልብ አርትሚያ	መደበኛ ያልሆነ የልብ ምት።
የልብ ድካም (ማዮካርዲያል ነው) Infarct ወይም MI ሲሆን	የሚከሰተው በልብ ጡንቻ ውስጥ የሚገኝ የደም ስር ሲዘጋ ወይም ሲደፈን እና የልብ ጡንቻ እራሱ በቂ ኦክሲጂን አያገኝም።
ሄሞራይደስ	ፊንጢጣ ላይ የሚገኝ ቫሪኮስቬይን ነው። አንዳንዴ ፊንጢጣ አካባቢ አበጥ-አበጥ ብለው ይታያሉ።
ሆርሞን	የሰውነት እንቅስቃሴ እና እድገት የሚቆጣጠር ኬሚካል ነው።
ሀይፐርግሊሴሚያ (ከፍተኛ የደም ስኳር)	ደም ውስጥ በርካታ ግሉኮስ
ሀይፐርቴንሽን (ከፍተኛ የደም ግፊት)	የአርተሪ ግርግዳ ላይ ከፍተኛ የደም ግፊት።
ሀይፖግሊሴሚያ (ዝቅተኛ የደም ስኳር)	የደም ውስጥ አነስተኛ ግሉኮስ
ሀይፖቴንሽ (ዝቅተኛ የደም ግፊት)	የደም ግፊት ለመደበኛ የደም ፍሰት እና ለሰውነት ህዋሶች በቂ ኦክሲጂን ለማድረስ በቂ አይደለም።
ሀይፖታይሮይዲዝም	የታይሮይድ እጢ በቂ ሆርሞን የማይሰራበት ሁኔታ። ምልክቶቹ ድካም፣ ቆዳ እና ጸጉር መድረቅ፣ የሚሰበር ጥፍርን የካትታሉ።
ሽንት አለመቆጣጠር	ሽንት ወይም የሰገራን እንቅስቃሴ መቆጣጠር አለመቻል።
መመረዝ	ባክቴሪያ፣ ቫይረስ ወይም ፈንገስ ሰውነት ላይ የሚሰፍሩበት ሁኔታ ነው።
መቆጣት/ህመም	ለአደጋ ሰውነት የሚሰጠው ምላሽ ነው። ጉዳቱን ለማከም ሰውነት መከላከያውን ይልካል።
ወደውስጥ መተንፈስ	መድሀኒት ወደውስጥ በመተንፈስ በአፍንጫ፣ ጉሮሮ እና ሳንባ ማስገባት።
መወጋት	በመርፌ ቆዳን በመውጋት መድሀኒት ሲሰጥ።
ኢንሱሊን	ሰውነት ያለውን ስኳር እንዲጠቀም የሚያደርገው በጣፊያ የሚሰራ ሆርሞን። በርካታ ምግቦች ወደስኳር የሚለወጡት በመፈጨት እና ኢንሱሊን ለሰውነት ባለው አስፈላጊነት ነው።
የቆዳ ስርአት	ቆዳ፣ ጸጉር፣ ጥፍር እና ቆዳ ላይ የሚገኙ እጢዎችን ያካትታል። ለሰውነት ጥበቃ ይሰጣል።
አንጀት	ሰገራ። ትንሹ አንጀት እና ትልቁ አንጀትን (ኮሎን) ያካትታል።
መገጣጠሚያዎች	አጥንቶች የሚገጣጠሙበት ቦታ። ለምሳሌ ጉልበት፣ ዳሌ እና የእጅ አንጓ።
ኩላሊት	ደም በማጣራት ሽንት የሚያመርት አካል።
የማህጸን ከንፈር	የማህጸን መከፈቻ ላይ የሚገኘው መሸፈኛ ህዋስ።

የጽሁፍ መድሀኒት	የማዘዣ መድሀኒት፡፡
ጅማት	መገጣጠሚያዎችን አጣምሮ የሚይዝ ጠንካራ ማሰሪያ፡፡
ጉበት	ከጨጓራ አጠገብ የሚገኝ በርካታ ነገሮችን የሚሰራ ለምሳሌ ለስብ መፈጨት የሚጠቅመውን ቢል ማምረት እና ከደም ውስጥ ቆሻሻን ማጣራት ነው፡፡
መድሀኒት	የሰውነትን የኬሚካል ስራ የሚቀይር ማንኛውም ውህድ ነው፡፡
የመድሀኒት መሀደር	ሰው የሚወስደውን መድሀኒት፣ መጠኑን፣ ፕሮግራሙን እና የአሰጣጥ መንገዱን የሚያሳይ ወረቀት ነው፡፡ እንዲሁም የመድሀኒት አሰጣጡን ማን እንደሰራ ወይም እንዳገዘ ያሳያል፡፡
የመድሀኒት መቀላቀል	ሁለት ወይም ከዛ በላይ መድሀኒቶች አንዱን ወይም የሁለቱንም መድሀኒቶች ውጤት ሲቀይር ነው፡፡
የመድሀኒት ማደራጃ	መድሀኒት ማስቀመጫ ወይም የሳምንታዊ ኪኒን ማስቀመጫ ሳጥን፡፡
የመድሀኒት አሰጣጥ መንገድ	መድሀኒት የሚሰጥበት መንገድ፡፡ በአፍ፣ በመርፌ፣ ወቅታዊ (ቆዳ ላይ መቀባት)፣ በትንፋሽ (ወደውስጥ በመተንፈስ)፣ በማህጸን፣ በፊንጢጣ እና በምላስ (ከምላስ ስር በማድረግ) መስጠትን ያካትታል፡፡
የመድሀኒት የጎንዮሽ ችግሮች	ያልታሰቡ የመድሀኒት ውጤቶች፡፡
ጡንቻ	እንቅስቃሴን የሚያስችል የሰውነት ህዋስ፡፡ ሁለት አይነቶች አሉ፡ 1) በፈቃደኛ፡ ሰው መቆጣጠር የሚችለው ለምሳሌ እጅ እና እግር ላይ እንዲሁም 2) ከፈቃደኝነት ውጪ፡ በራሳቸው የሚንቀሳቀሱ ለምሳሌ ልብ እና አንጀት፡፡
የጡንቻ-አጥንት ስርአት	አጥንት፣ ጡንቻ፣ ጅማት፣ ቴንዶን እና ካርቲሌጅን ይይዛል፡፡ ይህ ስርአት የሰውነት ውስጣዊ አካሎችን ከጉዳት ይከላከላል፣ ለሰውነት ቅርጽ ይሰጣል፣ አቋምን ያስተካክላል እንዲሁም የሰውነት እንቅስቃሴን ያከናውናል፡፡
ነርቭ	የነርቭ ስርአት አካል፡፡ ከአዕምሮ ወደሰውነት ከዛ መልሶ ወደ አዕምሮ የኤሌክትሪክ መልዕክቶች የሚልክ ቀጭን ረዥም ሽቦ መሰል ነው፡፡
የነርቭ ስርአት	አዕምሮ፣ አከርካሪ አጥንት እና ነርቭ፡፡ የሰውነት ስራን ያስተባብራል፣ ሰውነት እና አካባቢው ላይ ያሉትን ለውጦች ይቆጣጠራል፡፡ ስርአቱ ሰውነት እንዲያይ፣ እንዲሰማ፣ እንዲያሸት፣ እንዲያጣጥም እና እንዲዳስስ ደርጋል፡፡
የጽሁፍ ያልሆኑ መድሀኒቶች	ከመደርደሪያ ላይ የሚገዙ ወይም ያለማዘዣ የሚገዙ መድሀኒቶች፡፡
አፍንጫ ቀዳዳ	የአፍንጫ ቀዳዳ/ክፍተት፤ ሌላ ስሙ ናርስ ነው፡፡
አልሚ ምግብ	ሰውነት ምግብን እንዲጠቀመው ወደአልሚ ምግቦች (ፕሮቲን፣ ስብ፣ ካርቦሀይድሬት፣ ቪታሚን፣ ሚነራል እና ውሀ) እንዲቀየሩ ይፈጫል፡፡
ቅባት	ቆዳ፣ አይን ወይም ጆሮ ላይ የሚቀባ የመድሀኒት አይነት ነው፡፡
የአፍ መድሀኒት	አፍ ላይ ተደርገው በውሀ ወይም ከውሀ ጋር የሚዋጡ ኪኒን ወይም ፈሳሽ መድሀኒቶች፡፡
ኦስቲዮፖሮሲስ	ቀስ-በቀስ አጥንት እየደከመ የሚሄድበት እና በቀላሉ ለምሳሌ በማስነጠስ ሊሰበር የሚችልበት በሽታ ነው፡፡ የጀርባ ህመም፣ የትከሻ መጉበጥ እና ከፍተኛ የቁመት መቀነስን ሊያስከትል ይችላል፡፡ ኦስቲዮፖሮሲስ ወንዶችን የሚያጠቃ ቢሆንም ባብዛኛው ከማረጥ በኋላ የሚገኙ ሴቶችን ያጠቃል፡፡

የቃላት መፍቻ

አስቶሚ	ከአንጀት ወይም የሽንት ፊኛ ወደውጪ የሚወጣ የሆድ ግርግዳ ላይ የሚገኝ ክፍተት ነው። የአንጀት ወይም ሽንት ስርአትን ከመጠቀም ለመከላከል የሚደረግ ነው።
ጣፊያ	ምግብ ለመፍጨት ኢንዛይም የሚሰራ እና ስኳርን ለማድቀቅ ኢንሱሊን የሚሰራ ከጨጓራ አጠገብ የሚገኝ አካል ነው።
የፓርኪንሰን በሽታ	ሰው ላይ መንቀጥቀጥ፣ ሰውነት መገተር እና የእንቅስቃሴ መቀነስን የሚያስከትል ቀስ-በቀስ እየባሰ የሚሄድ የማዕከላዊ ነርቭ ስርአት በሽታ ነው።
ብልት	የሴት ሰውነት ማህጸን አካባቢ።
እንቅስቃሴ	ምግብን ከአፍ ወደ ፊንጢጣ የሚያንቀሳቅስ እና እንደሞገድ በራሱ የሚንቀሳቀስ የምግብ መፍጨት ስርአት የጡንቻ ስራ።
ኒሞኒያ	በባክቴሪያ፣ ቫይረስ እና ፈንገስ ምክነያት የሳንባ ህመም/መቆጣት። ምልክቶቹ ትኩሳት፣ ብርድ-ብርድ ማለት እና ሳል ናቸው።
ማዘዣ	በሀኪም፣ ነርስ፣ የሀኪም ረዳት፣ የጥርስ ሀኪም እና ሌላ የጤና ባለሙያ የሚሰጥ የመድሀኒት ወይም ህክምና ትእዛዝ ነው።
የክብደት ጉዳት	የደም ፍሰት እጦት ህዋሱ እንዲሞት ያደረገው የቆዳ ቦታ ነው። እንዲሁም ዲኩቢተስ አልሰር ወይም አልጋ ላይ ረዥም ጊዜ በመተኛት የሚመጣ የቆዳ መቆጣት።
PRN	PRN መድሀኒት (በላቲንኛ ፕሮ ሪ ናታ) "ሲያስፈልግ" የሚወሰድ ነው።
የምርት ስም	የመድሀኒቱ ምልክት/ብራንድ ነው ለምሳሌ ታሌኖል፣ ሞትሪን እና ላሲክስ።
ፕሮስቴት	እጢ የወንድ ብልት ጋር የሚገኝ እጢ። ሲተልቅ ከሽንት ፊኛው የሽንት ፍሰትን ሊከለክል ይችላል።
ሳይኮትሮፒክ	አዕምሮ ላይ ውጤት የሚያስከትል መድሀኒት ነው።
ሽፍታ	ብዙጊዜ ኩፍታ፣ መቅላት እና አበጥ ያሉ እና ማሳከክን የሚያስከትል የቆዳ ሁኔታ ነው።
ፊንጢጣ	ፊንጢጣ እስኪወጣ ድረስ ሰገራ የሚቀመጥበት የትልቁ አንጀት የመጨረሻው አካል ነው።
የፊንጢጣ መድሀኒት የመድሀኒቱ አሰጣጥ	የሰፖሲቶሪ ወይም ኢነማ አይነት መድሀኒቶችን በፊንጢጣ ማስገባት።
የአተነፋፈስ ስርአት	አፍንጫ፣ ጉሮሮ (ፋሪኔክስ)፣ የድምጽ ሳጥን (ላሪኔክስ)፣ የአየር ቱቦ (ትራኪያ)፣ መተንፈሻ እና ሳንባን ይይዛል። እነዚህ አካሎች ከአየር ወደደም አክሲጂን ያደርሳሉ እንዲሁም ከደም ወደ አየር ካርቦንዳይአክሳይ ያስወግዳሉ።
ሲዝር	አዕምሮ ውስጥ ያልተፈለጉ የነርቭ መልዕክቶች መላክ ነው። ሲዝሩ ከቀላል ራስ-መሳት ወይም መንቀጥቀጥ እስከ ድንገተኛ እና ቁጥጥር የማይደረግበት መላሰውነትን የሚያካትት የጡንቻ እንቅስቃሴ ድረስ ያካትታል።
የስሜት ህዋስ	ስርአት ጆር፣ አይን፣ አፍንጫ፣ ምላስ እና መንካት። እንድናይ፣ እንድንሰማ፣ እድናሸት፣ እንድናጣጥም እና እንድነካ ከሚያደርገን የነርቭ ስርአት ጋር ይሰራል።
ስፊኒክተር	የፊንጢጣ እና የሽንት ፊኛ መከፈቻ ላይ የሚገኝ የሰገራ፣ አየር እና ሽንት ፍሰትን የሚቆጣጠር የቀለበት ቅርጽ ያለው ጡንቻ ነው።
ስታቲስ ወይም ቬነስ አልሰር	ብዙጊዜ በታችኛው እግር እና እግር መርገጫ የሚገኝ በቬን የደከመ የደም ዝውውር የሚከሰት ክፍት ህመም ነው።

ስቶማ	ሰው-ሰራሽ ክፍተት የሚሰራበት ቦታ ነው። የሰገራ ወይም የሽንት ቆሻሻዎች በስቶማው በኩል ወደ ከረጢት ይወጣሉ።
ስትሮክ	የህክመና ቃሉ **ሰረብራል ቫስኩላር አክሲደንት** (CVA)ነው። አዕምሮ ውስጥ ያለ የደም ስር ሲፈነዳ ወይም ሲደፈን እና የአዕምሮ አካላትን ደም ሲያሳጣ።
ስብኩታነስ ተደራቢ	የፋይበር እና የስብ አገናኝ ህዋስ ውህድ የሆነ ቆዳ ስር የሚገኝ ተደራቢ።
በምላስ መድሀኒት መውሰድ መድሀኒት አሰጣጥ	ምላስ ስር መድሀኒት ይቀመጥ እና ምራቅ ውስጥ ይሟሟላል። መድሀኒት የሚመጠጠው አፍ ላይ ባለው በሙከስ ሜምብራን ነው።
ሰፖሲቶሪ	ወደፊንጢጣ ወይም ማህጸን የሚገባ መድሀኒት። ሙቀት ሲያገኝ ከሚሟሟ ጠጣር ነገር የተሰራ ነው።
ምልክት	የበሽታ ወይም ሁኔታ ምልክት።
ቴንዶን	ጡንቻን ከአጥንት ጋር የሚያያዝ ጠንካራ እና ተሳቢ ማሰሪያ።
ወቅታዊ (መድሀኒት ለአሰጣጥ)	በቀጥታ ቆዳ ላይ ወይም ሙከስ ሜምብራን ላይ ማድረግ ብዙጊዜ ለአካባቢው ውጤት የሚያመጣ።
በአደጋ የአዕምሮ ጉዳት	በመውደቅ፣ በአደጋ፣ ድብደባ ወይም ሌላ ሁኔታ የሚከሰት የአዕምሮ ጉዳት።
መንቀጥቀጥ	ሰው መቆጣጠር የማይችለው የመንቀጥቀጥ እንቅስቃሴ በተለይ እጅ ላይ።
አንድ-ጊዜ የሚወሰድ እሽግ	እያንዳንዱ የመድሀኒት መጠን ለብቻው ታሽጓል።
የላይኛው አተነፋፈስ መመረዝ (URI)	ጉንፋን፣ ሳይነስ ችግር፣ ስርየሰደደ ሳል፣ የጉሮሮ መቆጣት፣ ንፍጥ ፣ የሳይነስ መመረዝ እና ቶንሲልን ያካትታል። ባክቴሪያ ወይም ቫይረስ ይህን መመረዝ ያመጣል።
ዩሬተር	ከኩላሊት ወዴሽንት ፊኛ ሽንት የሚያስተላልፍ ቱቦ።
ዩሬትራ	ከሽንት ፊኛ ወደውጪ የሚወስድ ቱቦ።
ሽንት	በኩላሊት የሚሰራ ፈሳሽ። ሽንት ከሰውነት የተረፈ ውሀን እና አንዳንድ ቆሻሻ እንዲወጣ ያደርጋል።
የሽንት ፊኛ	ሽንት እስኪወጣ ድረስ ይይዛል።
የሽንት መስመር መመረዝ (UTI)	አንድ ወይም ከዛ በላይ የሽንት መስመር አካል መመረዝ። ሁኔታው ሴት ላይ የበለጠ የተለመደ ሲሆን ምልክት ላይኖረው ይችላል።
ዩሮስቶሚ	ከሽንት ፊኛ ወደውጪ የሚወጣ በሆድ ግርግዳ ላይ የሚገኝ ሰው-ሰራሽ ክፍተት ነው።
በማህጸን መድሀኒት መስጠት	በክሬም፣ አረፋ፣ ኪኒን ወይም ሰፖሲቶሪ መልክ ያሚገኝን መድኒት በማህጸን ማስገባት።
ቬይን	ካርቦንዳይኦክሳይድ የያዘ ደም ወደልብ የሚያጓጉዝ ደም ስር።
እይታ	ከእይታ ጋር የሚገናኝ።

የነርስ ተልዕኮ መግባቢያ ዝርዝር

መመሪያዎች

ይህ ቅጽ በተለየ ሁኔታ ላይ ማነጋገር ያለብዎትን ሰው በተመለከተ ስለፖሊሲዎች እና የሚጠበቁ ነገሮች እነዲወያዩ እና እንዲያስቀምጡ ይረዳዎታል፡፡

ትምህርቱን ከጨረሱ በኋላ ሀላፊነት ከሚሰጠው RN፣ ተቆጣጣሪዎት፣ የቦታው አስተዳደር ወይም የጉዳይ ሀላፊ ጋር ከስር ያሉትን ነገሮች ለመወያየት ይገናኙ፡፡ ፖሊሲዎቹን ያዙ እና በተሰጠው ቦታ ላይ መገኛ አድራሻ፡፡

የሚከተለው ሲሆን የምደውለው ማን ጋር ነው፤

አደጋ _____

_____

የእቃ አቅርቦት ካስፈለገ _____

_____

የሀኪም ትዕዛዝ ላይ ለውጥ ካለ _____

_____

የነርስ ተልዕኮ ስራ በሚሰራበት ቀን ወደስራ መሄድ ባልችል _____

_____

_____

ባለጉዳዩ የሚከተሉትን ከሆነ የማነጋግረው ማንን ነው፤

መታመም ከጀመረ _____

_____

በሁኔታው ላይ ለውጥ ካሳየ _____

_____

መድሀኒት ወይም ህክምና መውሰድ ካልፈለገ _____

_____

አጠቃላይ መረጃ፡ _____

_____

_____

ለመድሀኒት በተለምዶ የሚያገለግሉ ምህጻረ-ቃላት

ለመድሀኒት በተለምዶ የሚያገለግሉ ምህጻረ-ቃላት			
a	በፊት	mg	ሚሊግራም
ac	ከምግብ በፊት	ml	ሚሊ ሊትር
@	በ	mm	ሚሊሜትር
bid	በቀን ሁለቴ	noc, noct	ኖክቶራል
BM	የሰገራ እንቅስቃሴ	NPO	በአፍ ምንም አይገባም
BP	የደም ግፊት	OD	የቀኝ አይን
C	ሴንቲግሬድ	OS	የግራ አይን
c	ከ	OU	ሁለቱም አይን
cc	ኩዩብ ሴንቲ ሜትር	P	በኋላ
cm	ሴንቲ ሜትር	pc	ከምግብ በኋላ
dc	ማቋረጥ	po	በአፍ
elix	ኢሊክሲር	prn	እንደአስፈላጊነቱ
F	ፋራናይት	q	ሁሌ
gm	ግራም	qd	ሁል ቀን
gtt	ጠብታ	qid	በቀን አራቴ
gtts	ጠብታዎች	qod	አንድ ቀን እያለፉ
hs	የእንቅልፍ ሰአት	q4h	በየ 4 ሰአቱ
IM	በጡንቻ ውስጥ	qhs	ሁሌ የእንቅልፍ ሰአት ላይ
IU	አለማቀፋዊ መለኪያ	s	ያለ
IV	በደምስር የሚሰጥ	subcu	በሰብኩታነስ
Kg	ኪሎግራም	2	በቀን ሶስቴ
L	ሊትር	TPR	ሙቀት፣ ምት እና ላብ
Mcg	ማይክሮግራም		
mEg	ሚሊኢኩቫለንት	VS	አስፈላጊ ምልክቶች፣ እንደ TPR

የጆር ጠብታ አሰጣጥ

ይህ አጠቃለይ መረጃ ብቻ ነው። ለእያንዳዱ ባለጉዳዩ ሀላፊነት በሚሰጠው RN የተገለጸውን የተለየ መመሪያ ሁልጊዜ ይከተሉ።

መግቢያ

አሰራር፤ የጆሮ ጠብታ አሰጣጥ

ቅደም ተከተል 1፤ ባለጉዳዩን ይገምግሙ።

- ስለአሰራሩ ከባለጉዳዩ ጋር ያውሩ
- ባለጉዳዩ እንዴት እንደሆነ ይጠይቁ፣ ማንኛውም አይነት ለውጥ የሚሰማው ከሆነ ይወቁ፤ የመስማት ለውጥ፣ የጆሮ ፍሳሽ ወይም ህመም ለምሳሌ። ማንኛውንም ቅሬታ ይመዝገቡ።

ቅደም ተከተል 2፤ ለአሰራሩ መዘጋጀት።

- የተልዕኮውን መመሪያ እና መድሀኒት መሀደሩን ይገምግሙ።
- የመድሀኒቱን መሀደር ከጆሮ ጠብታው ጽሁፍ ጋር ያስተያዩ
- እጅዎትን በሳሙና እና በውሀ ይታጠቡ እና በሙሉ ያድርቁ
- ጓንት ያድርጉ
- አስፈላጊውን መሳሪያ ያዘጋጁ።
- የመድሀኒት ውህዱን ከመጨመርዎት በፊት የሰውነት ሙቀት ላይ እስኪሆን ድረስ በመዳፍዎት በመያዝ ያሙቁት።
- ጠርሙሱን እነዲበጠብጡ የሚያዝ ከሆነ ይበጥብጡት።
- የጆሮ ጠብታ ማንጠባጠቢያውን በመድሀኒት በግማሽ ይሙሉት።
- ባለጉዳዩ ህክምና የሚደረግለትን ጆሮውን ወደላይ አድርጎ በጎኑ እንዲሆን ያግዙት። ወይም ባለጉዳዩ ከፈለገ ህክምና የሚደረግለትን ጆሮውን ወደላይ አድርጎ ጭንቅላቱን ወደጎን በማጠፍ መቀመጥ ይችላል።

ቅደም ተከተል 3፤ አሰራሩን መጨረስ።

- ውህዱ በጆሮው ካናል (ቱቦ) በሙሉ መፍሰስ እንዲችል የጆሮ ውጭኛውን ክፍል በቀስታ ወደ ላይ እና ወደታች በመሳብ ቀጥ ማድረግ።
- ትክክለኛውን የጠብታ ቁጥር በጆሮው ካናል (ቱቦ) መጨመር። መድሀኒቱን ወደውስጥ ማለትም በጆሮው ካናል (ቱቦ) መካከል ላይ ማድረግ መድሀኒቱ በቀጥታ የጆሮ ታንቡር ላይ እዲያርፍ ያደርጋል፤ ይህ ደግሞ ጆሮው ውስጥ ጩኸት እና ህመም ይፈጥራል። ማንጠባጠቢያው የጆሮውን ወይም የካናሉን ማንኛውንም አካል እንዳይነካ ያድርጉ።
- መድሀኒቱን ከመጨመሩ በኋላ ባለጉዳዩ በጎኑ እንደሆነ ወይም ራሱን ወደጎን አጥፎ እንደተቀመጠ ለ5 ደቂቃ አካባቢ እንዲቆይ ያድርጉ።
- ማዘዣ የተሰጠው ባለሙያ ካዘዘ ጠብታው መግባቱን ለማረጋገጥ የተጠቀለለ ጥጥ ላላ አድርገው ጆሮ ላይ ያስገቡ።
- ጓንት ያስወግዱ።
- እጅዎትን በሳሙና እና በውሀ ይታጠቡ እና በሙሉ ያድርቁ

ቅደም ተከተል 4፤ መድሀኒት አሰጣጡን መመዝገብ።

ቅደም ተከተል 5፤ ባለጉዳዩ ለመድሀኒቱ ያለውን ምላሽ እና የጎንዮሽ ችግር ይከታተሉ።

የአይን ጠብታ ወይም ቅባት አሰጣጥ

መግቢያ

ይህ አጠቃለይ መረጃ ብቻ ነው። ለእያንዳዱ ባለጉዳዩ ሀላፊነት በሚሰጠው RN የተገለጸውን የተለየ መመሪያ ሁልጊዜ ይከተሉ።

አሰራር፤ የጆሮ ጠብታ ወይም ቅባት

ቅደም ተከተል 1፤ ባለጉዳዩን ይገምግሙ።

- ባለጉዳዩ እንዴት እንደሆነ ይጠይቁ፣ ማንኛውም አይነት ለውጥ የሚሰማው ከሆነ ይወቁ፤ ለምሳሌ የማየት ለውጥ፣ የአይን መቅላት፣ ማበጥ፣ ፍሳሽ ወይም ህመም። ማንኛውንም ቅሬታ ይመዝገቡ።
- ስለአሰራሩ ከባለጉዳዩ ጋር ያውሩ የአይን መድሀኒት አሰጣጥ ብዙጊዜ ህመም የለውም። ብዙ ጊዜ ቅባቶች አይንን ያለሰልሳሉ ግን አንዳንድ ፈሳሾች መጀመሪያ ላይ ይቆጠቁጣሉ።
- ባለጉዳዩ ከአንድ በላይ የአይን መድሀኒት ካለው ሁለት ወይም ከዛ በላይ የአይን መድሀኒቶች ቢያንስ በየአምስት ደቂቃ ልዩነት እንደሚሰጠው ለባለጉዳዩ ያብራሩ። ባለጉዳዩ የሚወስደው የአይን ጠብታ እና ቅባት ካለው የአይን ቅባቱ የአይን ጠብታውን ከመግባት ስለሚከለክለው ጠብታው መጀመሪያ እንደሚሰጥ ያብራሩ።

ቅደም ተከተል 2፤ ለአሰራሩ መዘጋጀት።

- የተልዕኮውን መመሪያ እና መድሀኒት መሀደሩን ይገምግሙ።
- የመድሀኒቱን መሀደር ከጆሮ ጠብታው/ቅባት ጽሁፍ ጋር ያስተያዩ።
- እጅዎትን በሳሙና እና በውሀ ይታጠቡ እና በሙሉ ያድርቁ
- ጓንት ያድርጉ
- አስፈላጊውን መሳሪያ ያዘጋጁ።
- ባለጉዳዩ ምቹ አኳኋን ላይ እዲሆን ማለተም እንዲቀመጥ ወይም እንዲንጋለል ያግዙት። ባለጉዳዩ ቆሞ መድሀኒቱን እንዳይሰጡ።
- የአይን ጠብታ ወይም ቅባት ከመስጠትዎ በፊት ቅንድብ እና ሽፋሽፍቱን ያጽዱ። አይን ለማጽዳት ንጹህ እና ሞቅ ያለ ቸርቅ ይጠቀሙ። ለእያንዳዱ አይን የጨርቁን የተለያየ ክፍለ ይጠቀሙ።
- አይን ሲየጸዱ ከውስጠኛው አይን ስር (ለአፍነጫ ከሚቀርበው) ወደውጭኛው የአይን መጨረሻ (ከአፍንጫ ለሚርቀው) ይጥረጉ።
- ቅባት ከሆነ መጀመሪያ ላይ የሚወጣውን ያስወግዱ። ከእቃው የሚወጣው የመጀመሪያው ቅባት የተበከለ ነው ተብሎ ይገመታል።

ቅደም ተከተል 3፤ አሰራሩን መጨረስ

- ባለጉዳዩ ወዳጣሪያ እንዲመለከት ያድርጉ። ለባለጉዳዩ ደረቅ የሚመጥ ጨርቅ ይስጡት። ባለጉዳዩ ወዳጣሪያ የሚያይ ከሆነ አይኑን አያርገበግብም።
- ስራ-ማይሰራው እጅወዎት አውራ ጣት ወይም ጣትን ከአይን ስር ባለው የባለጉዳዩ የጉንጭ አጥንት ላይ በማድረግ የስረኛውን የኮንጀክቲቫ ከረጢት ይያዙት እና በቀስታ ቆዳውን ጉንጭ ላይ ዝቅ-ዝቅ ያድርጉት።
- ባለጉዳዩ ማድረግ ከቻለ እንዲያደርግ ፍቀዱለት፤ የታችኛውን የአይን ሽፋን ወደታች ዝቅ-ዝቅ እንዲያደርጉ ያግዙ። የታችኛውን የአይን ሽፋን ካበጠ ወይም ከጠጠረ እንዳይጎዳ በጣም በጥንቃቄ ያድርጉት።
- ጣትን የጉንጭ አጥንት ላይ ማድረግ ኮርኒያን የመንካት እድልን ይቀንሳል፣ አይን ኳስ ላይ ጫና ማሳደርን ያስወግዳል እንዲሁም አይንነ ከማርገብገብ ይከላከላል።
- ከአይን ውስጥ በመጀመር ትክክለኛውን የጠብታ ቁጥር የታችኛው የኮንጀክቲቫ ከረጢት ሶስተኛው የውጪ ክፍል ላይ ያድርጉ። ማንጠባጠቢያውን ከከረጢቱ ከ1 እስከ 2 ሴሜ በላ ይያዙ። በጎን በኩል ከተደረገ ባለጉዳዩ አይኑን የማርገብገብ እድሉ ይቀንሳል። የኮንጀክቲቫ ከረጢት ላይ ሲደረግ ጠብታው ኮርኒያውን አይቆጠቁጠውም። ማንጠባጠቢያው ከረጢቱን ወይም ኮርኒያውን መንካት የለበትም።
- ቅባት የሚጠቀሙ ከሆነ ቱዩቡን ከታችኛው የኮንጀክቲቫ ከረጢት በላይ ይያዙ እና የቅባቱን 3/4 ኢንች ከቱዩቡ ወደ ታችኛው የኮንጀክቲቫ ከረጢት ከውስጠኛው ካንተስ ወደውጪ ይጫኑት።
- ባለጉዳዩ አይኑን እንዲጨፍን ያድርጉ፤ ጭምቅ ማድረግ ግነ አይደለም። አይን መዝጋት መድሀኒቱ በአይን ኳስ ዙሪያ ለማሰራጨት ይረዳል። አይንነ መጭመቅ አይንነ ሊጎዳ እና መድሀኒቱን ሊያስወጣው ይችለል።
- ለፈሳሽ መድሀኒቶች እርስዎ ወይም ባለጉዳዩ ቢያንስ ለ30 ሰከንድ የእንባ ደክት ላይ በጣም ይጫኑ። ደክቱን መጫን መድሀኒቱ ከአይን እዳይወጣ እና እንዳይፈስ ይከላከላል።
- እነደአስፈላጊነቱ ቅነድብን ያጽዱ። ትርፍ መድሀኒት ለመሰብሰብ ቅንድብን ከውስጠኛው ወደውጪኛው ካንተስ ይጥረጉ።
- መድሀኒቱን ካደረጉ በኋላ ወዲያው እና መድሀኒቱ ከሰራ በኋላ በድጋሚ የባለጉዳዩን ምላሽ ይገምግሙ።
- ጓንት ያስወግዱ እና እጅዎትን ይታጠቡ።

ቅደም ተከተል 4፤ መድሀኒት አሰጣጡን መመዝገብ።

ቅደም ተከተል 5፤ ባለጉዳዩን ይከታተሉ

- የአይን መቅላት፣ ፍሳሽ፣ ህመም፣ ማሳከክ፣ ማበጥ ወይም ሌላ ስሜት ወይም የዕይታ ችገር ካለ ይከታሉ እና ያሳውቁ።
- ሀላፊነት በተሰጠው RN በታዘዘው መሰረት የጎንዮሽ ችግር ይከታተሉ።

የአፍንጫ ጠብታ ወይም መርጫ አሰጣጥ

መግቢያ

ይህ አጠቃለይ መረጃ ብቻ ነው። ለእያንዳዱ ባለጉዳዩ ሀላፊነት በሚሰጠው RN የተገለጸውን የተለየ መመሪያ ሁልጊዜ ይከተሉ።

አሰራር፤ የአፍንጫ ጠብታ ወይም የሚረጭ

ቅደም ተከተል 1፤ ባለጉዳዩን ይገምግሙ።

- ባለጉዳዩ እንዴት እንደሆነ ይጠይቁ፣ ማንኛውም አይነት ለውጥ የሚሰማው ከሆነ ይወቁ፤ ለምሳሌ የአፍንጫ መታፈን፣ የአፍንጫ ፍሳሽ፣ አተነፋስ። ማንኛውንም ቅሬታ ይመዝገቡ።
- ስለአሰራሩ ከባለጉዳዩ ጋር ያውሩ

ቅደም ተከተል 2፤ ለአሰራሩ መዘጋጀት።

- የተልዕኮውን መመሪያ እና መድሀኒት መሀደሩን ይገምግሙ።
- የመድሀኒቱን መሀደር ከአፍንጫ ጠብታ ወይም ምርጫው ጽሁፍ ጋር ያስተያዩ።
- እጅዎትን በሳሙና እና በውሀ ይታጠቡ እና በሙሉ ያድርቁ
- ጓንት ያድርጉ
- አስፈላጊውን መሳሪያ ያዘጋጁ።
- ባለጉዳዩ የአፍንጫ መተላለፊያውን ለማጽዳት አፍነጫቸውን በቀስታ እዲናፈጡ ያድርጉ።
- የአፍነጫ ጠብታ ለማድረግ ባለጉዳዩ ጭንቅላቱን ወደኋላ ዘመም በማድረግ መንጋለል ወይም መቀመጥ አለበት።
- ባለጉዳዩ ከተንጋለለ ትከሻቸው ስር ትራስ በማድረግ ጭንቅላታቸው ከትራሱ መጨረሻ ላይ እንዲያርፍ ያድርጉ። አንዳንድ የሚረጩ መድሀኒቶች ባለጉዳዩ ጭንቅላቱን ቀጥ እንዲያደርግ ይመከራሉ።

ቅደም ተከተል 3፤ አሰራሩን መጨረስ።

- አውራጣትን አፍነጫ ጫፍ ላይ በመጫን የአፍነጫ ቀዳዳዎችን በቀስታ መግፋት።
- ማንጠባጠቢያውን ወይም የሚረጨውን ከባለጉዳዩ አፍንጫ ቀዳዳ በላይ በመያዝ መድሀኒቱን በአፍንጫ ቀዳዳ መካከል ማነጣጠር። መድሀኒቱ በአፍንጫ ቀዳዳ ስር አቅጠጫ ከተነጣጠረ በኢዩስታቺያን ቱቦው ይወርዳል።
- መያዣው እንዳይበከል የማንጠባጠቢያው ወይም የመርጫውን ጠርሙስ ጫፍ ከሙከስ ሜምብሬን ጋር እንዳያገናኙት።
- ባለጉዳዩ በአፍንጫ በኩል በቀስታ እና በጥልቀት ወደ ውስጥ እንዲተነፍሱ፣ ለበርካታ ሰከንዶች ትንፍሻቸውን እንዲይዙ፣ አየር ወደውጪ በቀስታ እንዲያስገቡ እና ውህዱ አጠቃላይ አፍንጫውን ገጽ እንዲያገኘው በጀርባቸው ተንጋለው ለ1 ደቂቃ እንዲቆዩ ይጠይቁ።
- ማንጠባጠቢያውን ወደ ጠርሙሱ ከመመለስዎት በፊት ማንጠባጠቢያው ውስጥ የቀረ መድሀኒት ማስወገድ።
- የማንጠባጠቢያውን ጫፍ በሙቅ ውሀ ማለቅለቅ፣ በጨርቅ ማድረቅ እና ወዲያው ድጋሚ መዝጋት።
- ጓንት ያስወግዱ።
- እጅዎትን በሳሙና እና በውሀ ይታጠቡ እና በሙሉ ያድርቁ

ቅደም ተከተል 4፤ መድሀኒት አሰጣጡን መመዝገብ።

ቅደም ተከተል 5፤ ባለጉዳዩ ለመድሀኒቱ ያለውን ምላሽ እና የጎንዮሽ ችግር ይከታተሉ።

በአፍ የሚወሰድ የትንፋሽ ህክመና

ይህ አጠቃለይ መረጃ ብቻ ነው። ለእያንዳዱ ባለጉዳዩ ሀላፊነት በሚሰጠው RN የተገለጸውን የተለየ መመሪያ ሁልጊዜ ይከተሉ።

መግቢያ

አሰራር፤ በአፍ የሚወሰድ የትንፋሽ ህክምና

ቅደም ተከተል 1፤ ባለጉዳዩን ይገምግሙ።

- ባለጉዳዩ እንዴት እንደሆነ ይጠይቁ፣ ማንኛውም አይነት ለውጥ የሚሰማው ከሆነ ይወቁ፤ ለምሳሌ አተነፋስ። ማንኛውንም ቅሬታ ይመዝገቡ።
- ስለአሰራሩ ከባለጉዳዩ ጋር ያውሩ

ቅደም ተከተል 2፤ ለአሰራሩ መዘጋጀት።

- የተልዕኮውን መመሪያ እና መድሀኒት መሀደሩን ይገምግሙ።
- የመድሀኒቱን መሀደር በትንፋሽ ወይም በመርጨት ከሚወሰደው መድሀኒት ጽሁፍ ጋር ያስተያዩ።
- እጅዎትን በሳሙና እና በውሀ ይታጠቡ እና በሙሉ ያድርቁ
- ጓንት ያድርጉ
- አስፈላጊውን መሳሪያ ያዘጋጁ።

ቅደም ተከተል 3፤ አሰራሩን መጨረስ።

- መድሀኒት መንፊያውን (መንፊያ) ከመጠቀምዎት በፊት ይበጥብጡት። ወደ አፍ ከሚገባው ላይ ክዳኑን ያንሱ።
- ባለጉዳዩ ጎሮሮውን እንዲያጸዳ ይጠይቁ።
- ባለጉዳዩ ሳንባ ውስጥ ያለውን አየር በሙሉ በቀስታ ወደውጪ ይተንፍሱ እና ትንፈሻቸውን ይያዙ።
- ወደአፍ የሚገባውን አፍ ውስጥ በማስገባት መሳቢያውን ቀጥ አድርጎ ወደላይ መያዝ። ባለጉዳይ ወደአፍ በሚገባው ዙሪያ ከንፈሩን አጥብቆ እንዲዘጋ ያድርጉ።
- ባለጉዳይ በአፉ በጥልቀት ወደ ውስጥ ሲስብ መሳቢያውን ይጭመቁ። ይህ ብዙጊዜ ከባድ ነው።
- ባለጉዳዩ ለ 5 ሰከንድ ትንፋሹን እንዲይዝ ይንገሩ።
- ባለጉዳዩ ወደ ውጪ ከመተንፈሱ በፊት መሳቢያውን ከአፉ ያውጡት። ሌላ መመሪያ ከሌለ በስተቀር ድጋሚ መሳቢያውን ከመጠቀምዎት በፊት ቢያንስ 2 ደቂቃ ይጠብቁ።
- የታዘዘው 2 ጊዜ መሳብ ከሆነ ሂደቱን ይድገሙት።

ቅደም ተከተል 3፤ አሰራሩን መጨረስ (የቀጠለ)

- ሁለት ወይም ከዛ በላይ መሳቢያ ካለዎት የስቴሮይድ መድሀኒቱን ሁሌ መጨረሻ ይጠቀሙ። ከዛ የባለጉዳዩን አፍ በውሀ ያጉመጥምጡ እና እንዲተፉ ያድርጉ።
- የመሳቢያውን አፍ ላይ የሚደረገውን በቶሎ-ቶሎ ያጽዱ እና በሙሉ ያድርቁት።
- ጓንት ያስወግዱ።
- እጅዎትን በሳሙና እና በውሀ ይታጠቡ እና በሙሉ ያድርቁ

ቅደም ተከተል 4፤ መድሀኒት አሰጣጡን መመዝገብ።

ቅደም ተከተል 5፤ ባለጉዳዩ ለመድሀኒቱ ያለውን ምላሽ እና የጎንዮሽ ችግር ይከታተሉ።

የፊንጢጣ ሰፖሲቶሪ ወይም ክሬም አደራረግ

መግቢያ

ይህ አጠቃለይ መረጃ ብቻ ነው፡፡ ለእያንዳዱ ባለጉዳዩ ሀላፊነት በሚሰጠው RN የተገለጸውን የተለየ መመሪያ ሁልጊዜ ይከተሉ፡፡

አሰራር፤ የፊንጢጣ ሰፖሲቶሪ ወይም ክሬም

ቅደም ተከተል 1፤ ባለጉዳዩን ይገምግሙ፡፡

- ባለጉዳዩ እንዴት እንደሆኑ ይጠይቁ፣ ማንኛውም አይነት ለውጥ የሚሰማው ከሆነ ይወቁ፤ ለምሳሌ ህመም፣ ማሳከክ፣ ማቃጠል ወይም ድርቀት፡፡ ማንኛውንም ቅሬታ ይመዝገቡ፡፡
- ስለአሰራሩ ከባለጉዳዩ ጋር ያውሩ

ቅደም ተከተል 2፤ ለአሰራሩ መዘጋጀት፡፡

- የተልዕኮውን መመሪያ እና መድሀኒት መሀደሩን ይገምግሙ፡፡
- የመድሀኒቱን መሀደር ከሰፖሲቶሪ ወይም ክሬም ጽሁፍ ጋር ያስተያዩ፡፡
- እጅዎትን በሳሙና እና በውሀ ይታጠቡ እና በሙሉ ያድርቁ
- ጓንት ያድርጉ
- አስፈላጊውን መሳሪያ ያዘጋጁ እና ብቸኝነትን ይስጡ፡፡
- ማሸጊያውን ያንሱ እና ለስላሳ እና ዱልዱም የሆነውን ጫፍ ያርጥቡት ወይም የአምራቹን መመሪያ ይመልከቱ፡፡ ዱልዱሙ ጫፍ ብዙጊዜ መጀመሪያ ይገባል፤ ማለስለስ የፊንጢጣ ጫፍ እንዳይቆጣ ያደርጋል፡፡ ሰፖሲቶሪው በጣም ለስላሳ ከሆነ ማሸጊያውን ከማንሳትዎ በፊት ፍሪጅ ውስጥ ያስቀምጡት፡፡
- ለግመሽ ሰፖሲቶሪ፤ ሰፖሲቶሪውን በቁመቱ ይቁረጡት፡፡
- ባለጉዳይ በአፉ እንዲተነፍስ በማድረግ ዘና እንዲሉ ያበረታቱ፡፡
- ባለጉዳይ የሚመቸውን ቦታ/ሁኔታ እንዲያገኝ ያድርጉ፡፡ ባለጉዳዩ በግራ ጎኑ ተኝቶ ሰፖሲቶሪ ማስገባት በጣም ውጤታማ ነው፡፡ ሆኖም ሰፖሲቶሪ በማንኛውም የመተኛት እነ የመቀመጥ አኳኋን ማስገባት ይቻላል፡፡

ቅደም ተከተል 3፤ አሰራሩን መጨረስ፡፡

- ስራ-የሚሰሩበት እጅዎት አመልካች-ጣት ጓንተ ላይ ያርጥቡት፡፡
- ሰፖሲቶሪውን ዱልዱም በሆነው ጫፍ መጀመሪያ ወይም በአምራቹ መመሪያ መሰረት ጓንት የተደረገበትን የአመልካች ጣት በመጠቀም በቀስታ በፊንጢጣ ግርግዳ በኩል ወደፊንጢጣ ያስገቡ፡፡
- ሰፖሲቶሪውን በአማካይ 4 ኢንች ወደ ፊንጢጣው ያስገቡ፡፡
- ሰፖሲቶሪውነ ወደሰገራ መጨመር ያስወግዱ፡፡
- የባለጉዳዩን መቀመጫ ለጥቂት ደቂቃዎች አጣምረው ይያዙ፡፡
- ሰፖሲቶሪው እንዲቆይ ባለጉዳዩ ቢያንስ ለ5 ደቂቃ በነበረበት እንዲንጋለል ያድርጉ፡፡
- ሰፖሲቶሪው ቢያንስ ከ 30 እስከ 40 ደቂቃ ወይም በአምራቹ መመሪያ መሰረት መያዝ አለበት፡፡
- የፊንጢጣ ክሬም፤ የማስገቢያውን ጫፍ ወደ ፊንጢጣው ያስገቡ እና ክሬሙን ለመቀባት ቲዩቡን ይጭመቁት፡፡
- ማስገቢያውን ያውጡ እና በሙቅ የሳሙና ውሀ ይጠቡት እና ከማስቀመጥዎት በፊት በደንብ ያድርቁት፡፡
- ጓንት ያስወግዱ፡፡
- እጅዎትን በሳሙና እና በውሀ ይታጠቡ እና በሙሉ ያድርቁ

ቅደም ተከተል 4፤ መድሀኒት አሰጣጡን መመዝገብ፡፡

ቅደም ተከተል 5፤ ለመድሀኒቱ እና የጎንዮሽ ችግር የባለጉዳዩን ምላሽ ይከታተሉ፡፡

የማህጸን ሰፖሲቶሪ እና ክሮም አሰጣጥ

ይህ አጠቃለይ መረጃ ብቻ ነው፡፡ ለእያንዳዱ ባለጉዳዩ ሀላፊነት በሚሰጠው RN የተገለጸውን የተለየ መመሪያ ሁልጊዜ ይከተሉ፡፡

መግቢያ

አሰራር፤ የማህጸን ሰፖሲቶሪ ወይም ክሬም

ቅደም ተከተል 1፤ ባለጉዳዩን ይገምግሙ፡፡

- ባለጉዳዩ እንዴት እንደሆነ ይጠይቁ፣ ማንኛውም አይነት ለውጥ የሚሰማው ከሆነ ይወቁ፤ ለምሳሌ ማሳከክ፣ ማቃጠል ወይም ፍሳሽ፡፡ ማንኛውንም ቅሬታ ይመዝገቡ፡፡
- ስለአሰራሩ ከባለጉዳዩ ጋር ይነጋገሩ፡፡

ቅደም ተከተል 2፤ ለአሰራሩ መዘጋጀት፡፡

- የተልዕኮውን መመሪያ እና መድሀኒት መሀደሩን ይገምግሙ፡፡
- የመድሀኒቱን መሀደር ከሰፖሲቶሪ ወይም ክሬም ጽሁፍ ጋር ያስተያዩ፡፡
- እጅዎትን በሳሙና እና በውሀ ይታጠቡ እና በሙሉ ያድርቁ
- ጓንት ያድርጉ
- አስፈላጊውን መሳሪያ ያዘጋጁ፡፡
- ሰፖሲቶሪውን ይፍቱት እና በተከፈተው ማሸጊያው ላይ ያስቀምጡት ወይም
- ማስገቢያው ውስጥ የታዘዘውን ክሬም፣ ጄል ወይም አረፋ ያስገቡ፡፡ በአምራቹ ማስገቢያ ላይ መመሪያ ተሰጥቷል፡፡
- የብቸኝነት ሁኔታ ይስጡ እንዲሁም ከስራው በፊት ባለጉዳዩዋ ፊኛዋን ባዶ እንድታደርግ ያድርጉ፡፡ ፊኛ ባዶ ከሆነ በህክመናው ወቅት ባለጉዳዩዋ የሚሰማት አነስተኛ ጫና ነው እንዲሁም የማህጸን ተደራቢን የመጉዳት እድል ይቀንሳል፡፡
- ባለጉዳዩዋ ጉልበቷን አጥፋ እና ዳሌዋን ወደ ውስጥ አዙራ በጀርባዋ እንድትንጋለል ያግዙ፡፡
- የብልት ቦታው ብቻ እንዲታይ አድርገው ባለጉዳዩዋን በአግባቡ ይሸፍኑ፡፡
- ባለጉዳይ በአፉ አንዲተነፍስ በማድረግ ዘና እንዲሉ ያበረታቱ፡፡

ቅደም ተከተል 3፤ አሰራሩን መጨረስ

- መጀመሪያ የሚገባውን የሰፖሲቶሪውን ዱልዱሙን (ለስላሳውን) ጫፍ ያርጥቡ፡፡
- ስራ ሚሰሩበተን እጅ ጓንት ያለበትን አመልካች ጣት ያርጥቡት፡፡
- የማህጸንን ከንፈር ስራ በማይሰራው እጅዎት በመከፈት የማህጸንን ቀዳዳ ግለጽ ያድርጉት፡፡
- ሰፖሲቶሪውን ከ3-4 ኢንች ወደ ማህጸን የጀርባ ግርግዳ ያስገቡ፡፡
- ክሬም ለማስገባት፤ ማስገቢያውን 2 ኢንች አካባቢ በቀስታ ያስገቡ፡፡ የማስገቢያውን መግፊያ ማስገቢያው ባዶ እስኪሆን ድረስ በቀስታ ይደግፉት፡፡ ማስገቢያውን ያውጡት እና ፎጣ ላይ ያስቀምጡት፡፡ ለአንድ-ጊዘ አገልግሎት የሚውል ማስገቢያ ከሆነ ይጣሉት ወይም በአምራቹ መመሪያ መሰረት ያጽዱት፡፡
- ጓንቱን ከውስጥ ወደውጪ በመገልበጥ ያስወግዱ፡፡ በአግባቡ ይጣሉት፡፡
- እጅዎትን በሳሙና እና በውሀ ይታጠቡ እና በሙሉ ያድርቁ፡፡
- ካስገቡ በኋላ ባለጉዳዩ አልጋ ላይ ከ5 እስከ 10 ደቂቃ እንዲንጋለል ያድርጉ፡፡
- የብልት አካባቢውን በጨርቅ ያድርቁት፡፡ አልጋ ላይ ሚነጠፍ ከተጠቀሙ ያንሱት፡፡
- የእርጥበት መከላከያ ሞዴስ እና መሸፈኛውን ያስወግዱ፡፡ የበዛ ፍሳሽ ካለ ንጹህ ሞዴስ ያድርጉ፡፡

ቅደም ተከተል 4፤ መድሀኒት አሰጣጡን መመዝገብ፡፡

ቅደም ተከተል 5፤ ባለጉዳዩ ለመድሀኒቱ ያለውን ምላሽ እና የጎንዮሽ ችግር ይከታተሉ፡፡

ከጀርም ነጻ የሆነ የቁስል መሸፈኛ መለወጥ

መግቢያ

ይህ አጠቃለይ መረጃ ብቻ ነው፡፡ እያንዳዱ ባለጉዳይ የተለያየ ስለሆነ ማድረግ ያለብዎት የተለዩ ቅድመ-ተከተሎች ይለያያሉ፡፡ ለእያንዳዱ ባለጉዳዩ ሀላፊነት በሚሰጠው RN የተገለጸውን የተለየ መመሪያ ሁልጊዜ ይከተሉ፡፡

አሰራር፤ ከጀርም ነጻ የሆነ የቁስል መሸፈኛ መለወጥ

ቅደም ተከተል 1፤ ባለጉዳዩን ይገምግሙ፡፡

- ስለአሰራሩ ከባለጉዳዩ ጋር ያውሩ
- ባለጉዳዩ እንዴት እንደሆነ ይጠይቁ፣ ማንኛውም አይነት ለውጥ የሚሰማው ከሆነ ይወቁ፡፡ ማንኛውንም ቅሬታ ይመዝገቡ፡፡ ባለጉዳዩ በአግባቡ እየተመገበ እና በቂ ፈሳሽ እየወሰደ እንደሆነ ይከታተሉ፤ ይህ ለቁስል መዳን ጠቃሚ ነው፡፡

ቅደም ተከተል 2፤ ለአሰራሩ መዘጋጀት፡፡

- የተልዕኮውን መመሪያ ይገምግሙ፡፡
- እጅዎትን በሳሙና እና በውሀ ይታጠቡ እና በሙሉ ያድርቁ
- አስፈላጊውን መሳሪያ ያዘጋጁ፡፡
- ጓንት ያድርጉ

ቅደም ተከተል 3፤ አሰራሩን መጨረስ፡፡

- የነበረውን የቁስል ማሸጊያ ያስወግዱ እና በተገቢው መያዣ ይጣሉት፡፡
- ጓንተ ያውልቁ፣ እጅ ይታጠቡ እና አዲስ ጓንተ ያድርጉ፡፡
- ሀላፊነት በሰጠው RN በታዘዘው መሰረት ቁስሉን ያጽዱት፡፡
- ሀላፊነት በሰጠው RN በታዘዘው መሰረት ቁስሉን ይከታተሉ፡፡
- ሀላፊነት በሰጠው RN በታዘዘው መሰረት ማንኛውንም ቅባት ወይም መድሀኒት ማድረግ፡፡
- ሀላፊነት በሰጠው RN በታዘዘው መሰረት አዲስ ቁስል ማሸጊያ ያድርጉ፡፡
- ጓንት ያስወግዱ፡፡
- እጅዎትን በሳሙና እና በውሀ ይታጠቡ እና በሙሉ ያድርቁ

ቅደም ተከተል 4፤ ሀላፊነት በሰጠው RN በታዘዘው መሰረት ቁስሉን ይከታተሉ እንዲሁም መሸፈኛውን ይቀይሩ እና ይመዝግቡ፡፡

ቅደም ተከተል 5፤ ባለጉዳዩ ለውጥ ወይም ውስብስብነት ካለው ይከታተሉ፡፡

(ወደሚቀጥለው ገጽ የቀጠለ)

ቁስሉን ይከታተሉ

- ቁስል መሸፈኛ ሲነሳ ፍሳሽ እንዳለው ይመልከቱ፡፡
- **ቁስሉ ከጸዳ በኋላ** የሚከተለውን ይመልከቱ፤
  - ቀለም፡፡
  - ቁስሉ ከተጸዳ በኋላ የሚቆይ ሽታ (አንዳንድ የቁስል መሸፈኛዎች ሽታ ይኖራዋል)፡፡
  - የፈሳሽ መጠን፡፡
  - የፈሳሽ ቀጣይነት፡፡

- ቁስሉ ከተጸዳ በኋላ የቁስሉን ጫፍ እና የቁስሉን ስር ይግለጹ፡፡ የሚከተሉትን ይመልቱ፤
  - የቁስል መጠን
  - "ስሙኒ" ወይም "የብር ሳንቲም" በሚል መጠን ይግለጹት፡፡ ትክክለኛ መሆን የለበትም ግን በተከታታይ ተመሳሳይ መለኪያ መጠቀም አለብዎት (እንደ ኢንች ወይም የ“___” መጠን)፡፡
  - የቁስል ቀለም፡ ቀይ፣ ቢጫ ወይም ጥቁር?
  - የቁስል ፈሳሽ
  - ካለ፤ እንደ ድሮ ነው ወይም ጠንካራ ሽፋን አለው?
  - የቁስል ጫፍ - ክብ ወይስ ቅርጽ አልባ?
  - ክፍተት አለው (ቆዳ ስር የጎረጎደ)? (የጎረጎዱ ቦታዎችን ጥልቀት እንክብካቤ ሰጪ አይለካም፡፡)

አሰራር፤ በአፍ የሚወሰድ የትንፋሽ ህክምና

- ሀላፊነት የሰጠው RN እንዲጠቀሙ ባሳየዎት መሸፈኛ ቁስሉን ይሸፍኑ፡፡ የተለያዩ አይነቶች መሸፈኛዎች አሉ፡፡ እያንዳዱ የተለያየ አላማ አለው እንዲሁም መጠቀም ያለብዎወት ሀላፊነት የሰጠው RN ባሳይዎት መሰረት ብቻ ነው፡፡
- ሀላፊነት የሰጠው RN በጠየቀው ቁጥር ልክ ቁስል ክትትሉን ይመዝግቡ፡፡ ቁስሉ ላይ ያልተለመደ ነገር ካለ ሀላፊነት ለሰጠው RN ያሳውቁ፡፡

የቁስል ሽፋን መቀየር

የግሉኮሜትር ምርመራ

መግቢያ

ግሉኮሜትር የሰጠውን የደም ስኳር የምንለካበት ማሽን ነው፡፡ የስኳር በሽታ ላለባቸው ባለጉዳዮች እንክብካቤ ለመስጠት ለበለጠ መረጃ ገጽ 48 ላይ የስኳር በሽታ ክፍልን ይገምግሙ፡፡



ይህ የግሉኮሜትር ምርመራ አሰራር አጠቃላይ መረጃ ነው፡፡ ለእያንዳዱ ባለጉዳዩ ሀላፊነት በሚሰጠው RN የተገለጸውን የተለየ መመሪያ ሁልጊዜ ይከተሉ፡፡

አሰራር፤ የግሉኮሜትር ምርመራ

ቅደም ተከተል 1፤ ባለጉዳዩን ይገምግሙ

- ስለግሉኮሜትር ምርመራው ከባለጉዳዩ ጋር ይነጋገሩ፡፡
- ባለጉዳዩ እንዴት እንደ ሆነ ይጠይቁ፣ ማንኛውም አይነት ለውጥ የሚሰማው ከሆነ ይወቁ፡፡
- ደም ከየት መውሰድ እንዳለብዎት ባለጉዳዩን ይጠይቁ፡፡ ብዙ ጊዜ ደም የሚወሰደው ከጣት ላይ ነው፡፡ ያበጠ ወይም የተጎዳ ቦታ አይጠቀሙ፡፡ ቦታው ሞቃት ቢሆን ጥሩ ነው፡፡

ቅደም ተከተል 2፤ ለአሰራሩ መዘጋጀት፡፡

- የተልዕኮውን መመሪያ ይገምግሙ፡፡
- እጅዎትን በሳሙና እና በውሀ ይታጠቡ እና በሙሉ ያድርቁ
- አስፈላጊውን መሳሪያ ያዘጋጁ፡፡
- ጓንት ያድርጉ

ቅደም ተከተል 3፤ አሰራሩን መጨረስ፡፡



- ሀላፊነት በሰጠው RN በታዘዘው መሰረት የሰውነቱን ክፍል መውጋት፡፡ ለእያንዳንዱ ምርመራ የሚወጉበትን ቦታ ቢቀይሩ ጥሩ ነው፡፡

  ምክር፡ የጣት ጫፍ፣ በጣቱ ጎን በኩል የተሻለ ነው፡፡
- በመሳሪያው አምራች እና ሀላፊነት በሰጠው RN መመሪያ መሰረት ምርመራ ያድርጉ፡፡
- መድማቱን ለማቆም ካስፈለገ በቀጥታ ይጫኑት
- ጓንት ያስወግዱ፡፡
- እጅዎትን ታጥበው ያድርቁ፡፡

ቅደም ተከተል 4፤ ውጤቱን ከቀን እና ሰአት ጋር እንዲሁም ሀላፊነት በሰጠው RN የተጠየቀ ሌላ መረጃ ይመዝግቡ፡፡

- ሀላፊነት በሰጠው RN መመሪያ መሰረት ለውጤቱ ምላሽ ይስጡ፡፡

ቅደም ተከተል 5፤ የተወጋው ቦታ እንዳይቆጣ ክትትል ያድርጉ፡፡

የጋስትሮስቶሚ አመጋገብ

መግቢያ

ጋስትሮስቶሚ ከሆድ ግርግዳ በኩል ወደውጪ የሚወጣ ክፍተት ነው፡፡ ሰው የመዋጥ ችግር ሲኖርበት በቱቦ ምግብ፣ ፈሳሽ ወይም መድሀኒት እንዲገባ ያደርጋል፡፡

ለእያንዳዱ ባለጉዳዩ ሀላፊነት በሚሰጠው RN የተገለጸውን የተለየ መመሪያ ሁልጊዜ ይከተሉ፡፡

ቅደም ተከተል 1፤ ባለጉዳዩን ይገምግሙ፡፡

- ባለጉዳዩ እንዴት እንደሆነ ይጠይቁ፣ ማንኛውም አይነት ለውጥ የሚሰማው ከሆነ ይወቁ፡፡
- ምን እንደሚያደርጉ ለባለጉዳዩ ይንገሩ፡፡ ባለጉዳዩ ካልተመቸው እንዲነግርዎት ያድርጉ፡፡

አሰራር፤ የጋስትሮስቶሚ አመጋገብ

ቅደም ተከተል 2፤ ለአሰራሩ መዘጋጀት፡፡

- የተልዕኮውን መመሪያ ይገምግሙ፡፡
- እጅዎትን በሳሙና እና በውሀ ይታጠቡ እና በሙሉ ያድርቁ
- አስፈላጊውን መሳሪያ ያዘጋጁ፡፡
- ጓንት ያድርጉ

ቅደም ተከተል 3፤ አሰራሩን መጨረስ፡፡

- የቁስል ማሸጊያውን ያስወግዱ - ለመቁረጥ መቀስ በፍጹም እንዳይጠቀሙ፡፡
- ሀላፊነት በሰጠው RN በታዘዘው መሰረት ቱቦውን ማገናኘት፡፡
- ባለጉዳዩ ይቀመጥ ወይም ተንጋሎ ቀና ይበል፡፡
- ጓንት በማድረግ የጋስትሪክ ይዘት ያላቸውን ነገሮች መኖራቸውን እንዲያጣሩ እና በትልቅ ሲሪንጅ እንዲያወጡት ሀላፊነት የሰጠው RN ሊተይቅዎት ይችላል፡፡
- ሀላፊነት በሰጠው RN መመሪያ መሰረት ውህዱን ወይም መድሀኒቱን ይስጡ፡፡
- ከእያንዳዱ ምግብ እና መድሀኒት አሰጣጥ በፊት እና በኋላ የመመገቢያ ቱቦው ላይ ከ30-60 ሚሊ ውሀ ያፍሱበት፡፡
- ጓንት ያስወግዱ፡፡
- እጅዎትን ይታጠቡ፡፡

ቅደም ተከተል 4፤ ሀላፊነት በሰጠው RN መመሪያ መሰረት አመጋገቡን ይመዝግቡ፡፡

ቅደም ተከተል 5፤ ሀላፊነት በሰጠው RN መመሪያ መሰረት ባለጉዳዩ ላይ ማንኛውም ውስብስብነትን ይከታተሉ፡፡

ለፈሳሽ ምግብ ተመራጭ አሰራር



በምግብ ቱቦ አልሚ ምግብ ሲሰጡ የሚከተሉትን መረጃ ያስታውሱ፡፡

- ባለጉዳዩን በተቻለ መጠን ተሳተፊ ያድርጉት፡፡ የምግብ ሰአት ለብዙ ሰዎች የማህበራዊ ኑሮ አካል የሆኑ ሰአታት ስሆኑ ባለጉዳዩ ምግብ ሲወስድ ከሌሎች ሰዎች ጋር መሆን ወይስ ብቻውን መሆን እንደሚፈልግ ማወቅ አለብዎት፡፡
- የአመጋብ ሂደቱን፣ የምግቡን መጠን፣ የውሀውን መጠን፣ የማስገባት ፍጥነቱን እና ባለጉዳዩ ፈሳሽ ምግቦች ሲሰጠው በምን አይነት አቀማመጥ መሆን እንዳለበት ሀላፊነት ከሚሰጠው RN ጋር በጽሁፍ ማረጋገጥ፡፡
- ባለጉዳዩን ሲያንቀሳቅሱ፣ ሲያጥቡ እና ሲያለብሱ ቱቦውን እንዳይስቡት ጥንቃቄ ያድርጉ፡፡
- ማንኛውንም አለመመቸት ያሳውቁ፡፡
- መቆጥቆጥ፣ መቅላት፣ ማበጥ ወይም ቱቦው በገባበት አካባቢ ፍሳሽ ካለ ይከታተሉ፡፡
- አንዳንዴ ባለጉዳይ የምግብን ጣዕም ለማጣጠም ምግብ አፋ ውስጥ ሊይዙ ይችላሉ ግን መዋጥ አይችሉም፡፡ ይህ ከተፈቀደ ባለጉዳዩ ምን አይነት ምግብ ማጣጣም እንደሚፈልጉ ይጠይቁ፡፡
- ትውከት ወይም ግሳት ካለ ለነርስ ያሳውቁ፡፡
- ባለጉዳዩ የቱቦ ምግብ ሲሰጠው ቀጥ ብሎ ወይም በ30-45 ዲግሪ እንዲቀመጥ እና ምግቡን ከወሰደ በኋላ ለአንድ ሰአት ቀጥ ብሎ እንዲቆይ ያድርጉ፡፡
- የባለጉዳዩ አፍ መድረቁን ወይም ቆዳ መሰነጣጠቅ እንዳለው ይከታተሉ፡፡
- ባለጉዳዩ ጥርሱን እንዲቦርሽ እና የአፍ ማጠቢያ ወይም ሌላ አፍ ማጽጃ ምርቶን ለምሳሌ ሳሊን ስዋብስ እንዲጠቀም ያበረታቱ፡፡ ባለጉዳዩ ጥርሱን ሲቦርሽ ትን ሊለው ስለሚችል ውሀውን እንዳይውጥ ይንገሩት፡፡
- ባለጉዳዩ ጥርሱን ሲቦርሽ ወይም የአፍ ማጠቢያ ሲጠቀም ድነገተኛ መዋጥን ለመከላከል በ90 ዲግሪ አንግል መቀመጥ አለበት፡፡
- "በማስወገድ ሁኔታ" (ጨጓራ ውስጥ የሚገኙ ይዘቶችን በፍጥነት ወደ ትንሹ አንጀት ማውጣት) ምክንያት ብዙ ጊዜ ተቅማጥ ይከሰታል፡፡ ይህ ሲሆን ሀላፊነት የሰጠውን RN ወይም የሚከታተለውን ሀኪም ያነጋሩ፡፡
- በመመሪያው መሰረት መሳሪያውን ያጽዱ፡፡

የኦስቶሚ እንክብካቤ

መግቢያ

ይህ ክፍለ የኦስቶሚ እንክብካቤ መሰራታዊ አሰራሮችን ይሸፍናል። ይህ አጠቃለይ መረጃ ብቻ ነው። እያንዳዱ ባጉዳይ ስለሚለያይ የሚሰጠው እንቅስቃሴ ከሰው ሰው ይለያያል። ለእያንዳዱ ባለጉዳዩ ሀላፊነት በሚሰጠው ነርስ የተገለጸውን የተለየ መመሪያ ሁልጊዜ ይከተሉ።

ከግንዛቤ መግባት

ኦስቶሚ ከአንደኛው የውስጥ አካላችን ጋር የሚገናኝ በሆድ ግርግዳ ላይ የሚገኝ የሰው-ሰራሽ ክፍተት ነው። ይህ የሚደረገው የሰውነት ስርአት አካል ላይ ችግር ሲኖር ነው። ለምሳሌ ሰው በእጢ ምክንያት አንጀቱ ከተደፈነ የቀዶ-ጥገና ሀኪም የሰገራውን መጓጓዣ አካል በሆድ ግርግዳ ላይ ከሚገኝ ክፍተት ጋር ያገናኘዋል። ይህ ኮሎስቶሚ ይባላል።



የኦስቶሚ ከረጢት

ሰው የመዋጥ ችግር ሲኖርበት ጋስትሮስቶሚ የሚባል ክፍተት ሆድ ላይ መፍጠር ይቻላል ወይም ዩሮስቶሚ የሚባል ክፍተት የሽንት ፊኛ ላይ መፍጠር ይቻላል። ኦስቶሚው ጊዜያዊ ወይም ቋሚ ሊሆን ይችላል።

ክፍተቱ የሚደረግበት ቦታ "ስቶማ" ይባላል። የሰገራ ወይም የሽንት ቆሻሻዎች በስቶማው በኩል ወደ ከረጢት ይወጣሉ። ለባጉዳይ በክፍል ወይም ሙሉ የኦስቶሚ እንክብካቤ እነዲሰጡ ሀላፊት ሊሰጥዎት ይችላል።

ባለጉዳዩ ስለኦስቴቶሚው ቁጡ ሊሆን ወይም ሊያፍር ይችላል በተለይ አዲስ ከሆነ። እንክብካቤ ሰጪው አስተያየት ባይሰጥ ወይም ኦስቶሚ እንክብካቤ በማድረጉ ደስተኛ እንዳልሆነ ባለጉዳዩ እንዲሰማው ባያደርግ ጥሩ ነው።

ይህ ክፍል ስለኮሎስቶሚ ከረጢት አቀያየር ይገልጻል። ስቶማው ዙሪያ ያለውን ቆዳ ከመሳብ ለመከላከል ከረጢቱ መቀየር ያለበት አንድ ሶስተኛው ወይም ግምሹ ሲሞላ ነው።

አሰራር፤ የጋስትሮስቶሚ አመጋገብ

ቅደም ተከተል 1፤ ባለጉዳዩን ይገምግሙ።

- ስለአሰራሩ ከባለጉዳዩ ጋር ያውሩ ባለጉዳዩ የኦስቶሚ እንክብካቤው የት እንዲደረግ እንደሚፈልግ ያረጋግጡ። ብዙ ጊዜ መታጠቢያ ቤት ቢደረግ ጥሩ ነው።
- የትም ቢደረግ የባለጉዳዩ የብቸኝነት መብት መከበሩን ያረጋግጡ።
- ባለጉዳዩ እንዴት እንደሆነ ይጠይቁ፣ ማንኛውም አይነት ለውጥ የሚሰማው ከሆነ ይወቁ።

ቅደም ተከተል 2፤ ለአሰራሩ መዘጋጀት።

- ተልዕኮ ካስፈለገ የተልዕኮውን መመሪያ ይከተሉ።
- አስፈላጊውን መሳሪያ ያዘጋጁ።
- እጅዎትን በሳሙና እና በውሀ ይታጠቡ እና በሙሉ ያድርቁ።
- ጓንት ያድርጉ



(ወደሚቀጥለው ገጽ የቀጠለ)

ቅደም ተከተል 3፤ አሰራሩን መጨረስ፡፡

- የነበረውን የኦስቶሚ ከረጢት እና ዋፈር ወይም ሌላ መሳሪያ ከስቶማው ያስወግዱ፡፡
- ሀላፊነት በሰጠው RN ወይም ፈሳሽ መያዣ ከረጢት ላይ ባለው መመሪያ መሰረት ከረጢቱን ያስወግሳ፡፡
- ስቶማው አካባቢ የሚገኝ ማንኛውንም ሰገራ በሶፍት በቀስታ ያስወግዱ፡፡ በመቀጠል ስቶማው አካባቢ ያለውን ቆዳ በሳሙና እና በውሀ ያጽዱት፡፡ በቀስታ በመጫን ያድርቁት፡፡
- ስቶማው ወይም በአካባቢው ያለ ቆዳ ክፍተት፣ መቆጥቆጥ፣ ሽፋታ ወይም ሌላ አይነት ሁኔታ ካለው ሀላፊነት በሰጠው RN መመሪያ መሰረት ይከታተሉ፡፡
- በመመሪያው መሰረት ማነኛውንም ቅባት ያድርጉ፡፡
- ሀላፊነት በሰጠው RN መመሪያ መሰረት አዲስ ከረጢት ያድርጉ፡፡ በርካታ አይነት ያላቸው ከረጢቶች አሉ፤ ባለጉዳዩ ስለሚጠቀመው ከረጢት ሀላፊነት የሚሰጠው RN የተለየ መመሪያ ይሰጥዎታል፡፡
- ጓንት ያስወግዱ፡፡
- እጅዎትን በሳሙና እና በውሀ ይታጠቡ እና በሙሉ ያድርቁ

ቅደም ተከተል 4፤ ሀላፊነት በሰጠው RN መመሪያ መሰረት ኦስቶሚ እንክብካቤውን ይመዝግቡ፡፡

ቅደም ተከተል 5፤ ባለጉዳዩ ለውጥ ወይም ውስብስብነት ካለው ይከታተሉ፡፡

ቀጥያለ ንጹህ የሽንት ማስወገጃ ቱቦ ማስገባት

መግቢያ

ቀጥ-ያለ ንጹህ የሽንት ቱቦ ሽንት ለማውጣት የሽንት ፊኛ ውስጥ የሚገባ ቱቦ ሲሆን ከዛ በኋላ ይወጣል። ይህ የሚደረገው ሰው የሽንት ፊኛውን ያለቱቦ ባዶ ማድረግ ካልቻለ ነው።

ለእያንዳዱ ባለጉዳዩ ሀላፊነት በሚሰጠው RN የተገለጸውን የተለየ መመሪያ ሁልጊዜ ይከተሉ።

አሰራር፤ ቀጥ-ያለ ንጹህ የሽንት ቱቦ

ቅደም ተከተል 1፤ ባለጉዳዩን ይገምግሙ።

- ባለጉዳዩ እንዴት እንደሆነ ይጠይቁ፣ ማንኛውም አይነት ለውጥ የሚሰማው ከሆነ ይወቁ።
- ምን እንደሚያደርጉ ለባለጉዳዩ ያብራሩ። ባለጉዳዩ ምቾት የነሳው ነገር ካለ ወይም ስራውን እንዴት እንደሚሰሩት ምርጫ ካላቸው ይጠይቁ።

ቅደም ተከተል 2፤ ለአሰራሩ መዘጋጀት።

- የባለጉዳዩን የብቸኝነት መብት ይጠብቁ።
- የተልዕኮውን መመሪያ ይገምግሙ።
- እጅዎትን በሳሙና እና በውሀ ይታጠቡ እና በሙሉ ያድርቁ።
- አስፈላጊውን መሳሪያ ያዘጋጁ።
- ጓንት ያድርጉ

ቅደም ተከተል 3፤ አሰራሩን መጨረስ።

- ባለጉዳዩ ምቹ የመቀመጥ ወይም የመንጋለል ቦታ እንዲይዙ ያግዙ።
- ሀላፊነት በሰጠው ነርስ መመሪያ መሰረት የብልት ቦታን ወይም የወንድ ብልቱን ጫፍ ያጽዱ።
- የዩሬትራውን መክፈቻ ፈልገው ያግኙት።
- ቱቦውን ውሀ ውስጥ በሚሟሟ ማለስለሻ ለምሳሌ KY ጄሊ ያርጥቡት።
- ቱቦውን የዩሬትራ ክፍተት ውስጥ በማስገባት ወደፊኛው ያስገቡት። ይህ ለወንዶች በአማካይ 9 ኢንች ሲሆን ለሴቶች ደግሞ 2½ እስከ 3ኢንች ይሆናል። ቱቦው ፊኛ ውስጥ መግባቱን የሚያውቁት በቱቦው ጫፍ ሽንት መምጠት ሲጀምር ነው።
- ባለጉዳዩ በቀስታ እና በጥልቀት እንዲተነፍስ ያድርጉ። ይህ የፊኛው መክፈቻ ዘና እንዲል ይረዳል። ቱቦውን ሲከቱ ቀስ ያለ ሆኖም ጠንከር ያለ ሀይል ይጠቀሙ።
- ሽንት መውጣት እስኪያቆም ድረስ ቱቦውን ይያዙት።
- ቱቦውን ያውጡት
- የብልት ቦታን ያጽዱ እና ያድርቁ።

ቅደም ተከተል 4፤ ሀላፊነት በሰጠው RN መመሪያ መሰረት የሽንት ቱቦ ስራውን ይመዝግቡ።

ቅደም ተከተል 5፤ ሀላፊነት በሰጠው ነርስ መመሪያ መሰረት ባለጉዳዩ ውስብስብነት ካለው ይከታተሉ።